
## የከምባታና ሀዲያ አውራጃ




# አብዮታዊ የምርትና የባህል ዕድገት ዘመቻ በከምባታና ሀዲያ አውራጃ ከ1971 እስከ 1975

*For the Brad Lapsleys with my best wishes and kindest regards— Lapiso G. Dilebo April 18, 1984*

*Revolutionary Economic and Cultural Development Campaign in the Province of Kombata and Hadiya, 1978-1983*

ከዶክተር ላጲሶ ጌ. ድሌቦ
ረዳት ፕሮፌሰርና በባህልና ስፖርት ሚኒስቴር
የኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ክፍል ኃላፊ

1975
አዲስ አበባ




ጓድ ሊቀመንበር መንግሥቱ ኃይለማርያም
የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግና
የኢሠፓአኮ ሊቀመንበር የአብዮታዊ ጦር ኃይሎች ጠቅላይ አዛዥ



ጓድ አዲስ ተድላ

የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ የቋሚ ኮሚቴ አባል፣ የብሔራዊ አብዮታዊ የምርት ዘመቻና የማዕከላዊ ፕላን ጠቅላይ መምሪያ ምክትል ሊቀመንበርና የኢሠፓአኮ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባል በታኅሣሥ 24—25 ቀን 1974 ዓ. ም. የምርት ዘመቻና የማዕከላዊ ፕላን ጠቅላይ መምሪያና የመንግሥት ከፍተኛ ባለሥልጣኖች አስከትለው የከምባታና ሀዲያ አውራጃ የኢኮኖሚና የባህል ዘመቻ ሂደትና ይዘት ለሦስት ቀናት በጉብኙበት ወቅት


(የጉብኝቱ ዝርዝር ታሪክ በዚህ መጽሐፍ በገጽ 155 --161 ይገኛል)።



ጓድ አዲስ ተድላ

የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ የቋሚ ኮሚቴ አባል ፣ የብሔራዊ አብዮታዊ የምርት ዘመቻና የማዕከላዊ ፕላን ጠቅላይ መምሪያ ምክትል ሊቀመንበርና የኢሠፓአኮ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባል በታኅሣሥ 24—25 ቀን 1974 ዓ. ም. የምርት ዘመቻና የማዕከላዊ ፕላን ጠቅላይ መምሪያና የመንግሥት ከፍተኛ ባለሥልጣኖች አስከትለው የከምባታና ሀዲያ አውራጃ የኢኮኖሚና የባህል ዘመቻ ሂደትና ይዘት ለሦስት ቀናት በጐበኙበት ወቅት

(የጉብኝቱ ዝርዝር ታሪክ በዚህ መጽሐፍ በገጽ 155--161 ይገኛል) ።



ጓድ ጴጥሮስ ገብሬ
የከምባታና ሀዲያ አውራጃ የኢሠፓአኮ ተጠሪ



ደራሲው ላጽሶ ጌ. ድሌቦ

# ማ ው ጫ


ገጽ

መቅድምና መግቢያ ........................................ 19

ክፍል አንድ

የኢትዮጵያና የኢትዮጵያውያን አጭር ሐተታ ..................... 25

1. የኢትዮጵያና የኢትዮጵያውያን ታሪካዊ አመጣጥና ዕድገት ከጥንት እስከ 1850 ........................................ 25

1. ሀ. የኢትዮጵያ ምድር፣ ብሔረሰቦችና ቋንቋዎች .............. 25

ለ. ለኢትዮጵያ ምድርና ሕዝብ ብሔራዊ ቅርጽና ይዘት የሰጡ አራት ዋና ታሪካዊ ኃይላት ..................... 29

1. ሐ. በጦር አበጋዞች ዘመን የተነሱ ሦስት ዋና ፖለቲካዊ ማዕከላትና ኃይላት ........................................ 30

2. የኢትዮጵያ የማዕከላዊ መንግሥት ግምባታ ከ1850 እስከ 1966 ..... 31

2. ሀ. የማዕከላዊው መንግሥትና ብሔራዊ ሥርዓት ምሥረታ. 31

2. ለ. የጉልተኛና የገባር መደቦች ዕድገት፣ ልዩነትና ትግል..... 34

2. ለ. 1. የጉልተኛው መደብ ኃይልና ድል .................. 34

2. ለ. 2. የጉልተኛው መደብ ሕግና ሥርዓት .............. 36

2. ለ. 3. የገባርና የጢሰኛ መደብ ........................ 38

2. ለ. 3. 1. የገባር ሕግና ሥርዓት ..................... 38

2. ለ. 3. 2. የጢሰኛ ሕግና ሥርዓት .................... 41

2. ሐ. የዘመነ ገባር ፍጻሜና የፊውዶ ቡርዧ ሥርዓት ግምባታ 43

2. መ. የፊውዶ ቡርዧ ሥርዓት ውድቀትና የአብዮቱ ፍንዳታ ... 45

ክፍል ሁለት

የኢትዮጵያ አብዮትና የሶሻሊዝም ግምባታ ዘመን ........... 51

1. የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮት ፍንዳታ ............................ 51

1. ሀ. የአብዮቱ ወታደራዊ አመራር .......................... 51

1. ለ. የወታደሩ አብዮታዊ ፖሊሲና ፕሮግራም ................ 54

1. ሐ. ፀረ አብዮት ኃይላት ...................................... 59

1 ሐ. 1. የአብዮቱ የውስጥ ቀልባሽ ጠላቶች .............. 59

1. ሐ. 2. የሱማሊያ ወራሪ መንግሥት ...................... 61

1. ሐ. 3. የኤርትራ ተገንጣዮች ............................ 65

1. ሐ. 4. የኢኮኖሚ አሻጥረኞች .......................... 67

1. ሐ. 5. የተፈጥሮ አደጋ ................................... 69

1. ሐ. 6. ስውር የፖለቲካ ድርጅቶች ሚና .................. 70

2. የኢትዮጵያ አብዮት ድል አድራጊነትና የሶሻሊዝም ግምባታ ትግል.. 71

2. ሀ. መግቢያ፣ የሶሻሊዝም ግምባታ መንገድና መሣሪያዎች.. 71

2. ለ. ያገር መከላከያ ግምባታ ትግል ........................ 71
2. ሐ. የኢትዮጵያ ሠርቶ አደሮች ፓርቲ (ኢሠፓ) ምሥረታ ትግል ........................ 73
2. ሐ. 1. የፓርቲ ጥያቄ በኢትዮጵያ አብዮት ........ 73
2. ሐ. 2. የኢሠፓአኮ ምሥረታና ተግባራት ........ 75
2. መ. የሶሻሊስት ኢኮኖሚ ግምባታ ትግል ........................ 80
2. መ. 1. የኢኮኖሚና የባህል ዘመቻ ጥሪ ........ 80
2. መ. 2. የወዛደር ርዕዮተ ዓለምና የምርት ኃይል ዕድገት ጥያቄ. . . . . . . . . . . 81
2. መ. 3. የኢኮኖሚና የባህል ዘመቻ ........................ 85
2. መ. 3. 1. የኢኮኖሚና የባህል ዘመቻ ዓላማዎች ........................ 85
2. መ. 3. 2. የኢሠፓአኮ የኢኮኖሚና የባህል ዕድገት መመሪያ ............ 87

## ክፍል ሦስት

የጉልተኛው ሥርዓት በከምባታና ሀዲያ አውራጃ ከ1884—1966 .... 93
1. የሥርዓቱ ምሥረታና ጠባይ ........................ 93
2. የገባርና የጉልተኛ መደባዊ ትግል ........................ 97
3. የመሬት ዘረፋና የሕዝብ ስደት ከ1933 እስከ 1966 ........................ 98
4. የተማሪዎችና የገበሬዎች አመጽ በአብዮቱ ዋዜማ ........................ 103
5. የከምባታና ሀዲያ አውራጃ ጉባኤ የፖለቲካ ውሳኔ 1965 . . . 105

## ክፍል አራት

አብዮቱና የኢኮኖሚው ዘመቻ በከምባታና ሀዲያ አውራጃ 1966-1975. 117
1. የአብዮቱ ፍንዳታና የመደብ ትግል ከ1966 እስከ 1971 ........................ 117
2. የኢኮኖሚና የባህል ዘመቻ ዝግጅትና ድርጅት በከምባታና ሀዲያ አውራጃ ከ1971 እስከ 1975 ........................ 120
2. 1. ሀ. የአውራጃውን የልማት ደረጃ የሚያሬጥኑና የሚወስኑ መሠረታዊ የአካባቢው ሁኔታዎች ........................ 120
2. ለ. የድርጅት ፣ የርዕዮተ ዓለምና የምርት ግንኙነት ........ 123
3. የኢኮኖሚና የባህል ዘመቻ ሥምሪትና ውጤት ........................ 125
3. ሀ. የኢኮኖሚና የባህል ዘመቻ በሆሣዕና ከተማ ........................ 125
3. ለ. የኢኮኖሚና የባህል ዘመቻ በትምህርት ዘርፍ ........................ 137
3. ለ. 1. የመሠረተ ትምህርት ዘመቻ ሥምሪትና ውጤት ..... 137
3. ለ. 2. የመደበኛ ትምህርት ዕድገት ........................ 139
3. ሐ. የምርትና የመንግሥት ገንዘብ ገቢ ዕድገት ........................ 144
3. ሐ. 1. የምርት ዕድገትና ስርጭት ........................ 144
3. ሐ. 2. የመንግሥት ገንዘብ ገቢ ዕድገት ........................ 144
4. የሆሣዕና ሆስፒታል ፣ የሕዝብና የአብዮታዊ መንግሥት ትብብር ውጤትና ምሳሌ ........................ 148
ሀ. የሕዝብ ጅምር ........................ 148
ለ. የአብዮታዊ መንግሥት ሚና ........................ 156
5. የሆሣዕና ሆስፒታል አቀማመጥና ክፍሎች ........................ 161
የጥናቱ ጽሑፋዊ ምንጮች ........................ 167



# ሠንጠረዦች

ገጽ

1. በድህረ አብዮት የምርትና የባህል ለውጥና ልማት ሁኔታዎች በከምባታና ሀዲያ አውራጃ እስከ 1975 ........................ 22
2. የኢትዮጵያ ብሔረሰቦችና ቋንቋዎች ........................ 27
3. የተፈጥሮ አካባቢዎችና ሁኔታዎች ሚና በኢትዮጵያ ብሔረሰቦች ፣ ቋንቋዎች ፣ ባህሎችና ዕደ ጥበባት ዕድገት ብዛትና አንድነት ..... 28
4. ከ1865 እስከ 1900 ድረስ የኢትዮጵያ ንዑስ መንግሥታት ፣ አገሮች ፣ ብሔረሰቦችና ክፍለ ሀገራት በምኒልካዊ ማዕከላዊ መንግሥት ሥር የሆኑበት ጊዜ (ጊዜው እንደ አውሮፓውያን ዘመን) ........................ 33
5. የኢትዮጵያ ሕዝብ ከ1820 እስከ 1952 ከወራሪዎችና ከኢምፔሪያሊስቶች ጋር ያካሄዳቸው ጦርነቶች ........................ 44
6. የኢትዮጵያ የመሬት ይዞታና ግብር ከ1933 እስከ 1966 በጋሻና በብር ........................ 47
7. የኢትዮጵያ የውጭ ምንዛሬ ሁኔታ ከ1946 እስከ 1974 እንደ አውሮፓውያን ዘመን በሚሊዮን ብር ........................ 48
8. መንግሥታዊ የገንዘብ ፣ የንግድ ፣ የእርሻ ፣ የምርትና የማከፋፈያ ድርጅቶች ከነካፒታላቸው ከ1967 እስከ 1973 ........................ 55
9. ከገበሬና ከተማ ማህበራት በተገኘው ማስረጃ መሠረት ፣ በ1966 በአብዮቱ ፍንዳታ ወቅት የኢትዮጵያ ሕዝብ ብዛት ግምት ....... 58
10. የኢጣልያ ፋሽስቶች የኤርትራ ተገንጣዮችና የሱማሊያ መንግሥት በኢትዮጵያ ላይ በጦርነት ያደረሱት ጥፋት በንጽጽር ........................ 67
11. ከ1966 እስከ 1972 ድረስ በኢኮኖሚ አሻጥረኞች የተዘረፈና የተበዘበዘ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሀብት መጠን ........................ 68
12. በ1972 በተለያዩ ክፍለ ሀገራት በድርቅና በረሀብ የተጐዱ ሰዎች ብዛት ........................ 69
13. የኢትዮጵያ መንግሥታዊና ሕዝባዊ መሥሪያ ቤቶች ፣ ድርጅቶችና ማህበራት በ1975 ........................ 77
14. ለትምህርት ፣ ለርዕዮተ ዓለም ፣ ለቅስቀሳና ለድርጅት ተቋሞችና ሥራዎች በአብዮታዊ መንግሥት የተመደበው በጀት በሚሊዮን ብር ከ1967—1974 ........................ 88
15. በኢትዮጵያ የትምህርት ቤቶች የተማሪዎችና የአስተማሪዎች ብዛት ከ1966 እስከ 1972 ........................ 83
16. ከ1971 እስከ 1972 በመጀመሪያዎቹ ሦስት የመሠረተ ምህርት ዘመቻ ዙሮች በኢትዮጵያ ማንበብና መጻፍ የቻሉ ጉልማሶች ብዛት ........................ 84
17. እስከ 1975 ከሶሻሊስት አገሮች ለኢትዮጵያ በልዩ ልዩ መንገዶችና መስኮች ከተሰጡ ከገንዘብ ፣ ከምርት መሣሪያ ፣ ከቴክኒክና ከምህርት እርዳታዎች በከፊል ........................ 90

18. በሸዋና በሲዳሞ ክፍለ ሀገራት ከከምባታና ሀዲያ ብሔረሰቦች ጋር የቋንቋ ግንኙነት ያላቸው ብሔረሰቦች ........................ 93
19. የጉራጌ ፣ የማረቆ ፣ የስልጤ ፣ የሀዲያ ፣ የከምባታና የአላባ ጦርነቶች ከ1867 እስከ 1884 ........................................ 96
20. የገባር ብዛትና አገልግሎት በከምባታና ሀዲያ አውራጃ በ1907 ..... 97
21. በከምባታና ሀዲያ አውራጃ ወረዳዎች በየቀኑ የሚውሉ ገበያዎች ብዛት ...... ...... ................................................ 107
22. የከምባታና ሀዲያ አውራጃ አስገባሪዎች ፣ ገዢዎችና አስተዳዳሪዎች ከ1878 እስከ 1970 ................................................ 119
23. የመሬት ፣ የሰውና የእንስሳት ሚዛን በከምባታና ሀዲያ አውራጃ .... 121
24. የዓለምገና-ወላይታና የወልቅጤ-ሆሣዕና የመኪና መንገዶች ሥራና አገልግሎት .......................................................... 122
25. የከምባታና ሀዲያ አውራጃ ሕዝባዊ ድርጅቶችና ማህበራት በ1975.... 124
26. በሆሣዕና ከተማ በዓመት ውስጥ የሚዘንበው የዝናብ መጠን በሚሊ. ሜትር .................................................................. 125
27. በኢኮኖሚና በባህል ዘመቻ ከ1971 እስከ 1975 በሆሣዕና ከተማ ለግል ፣ ለሕዝባዊና ለመንግሥታዊ አገልግሎት የተሰጠ መሬት በካሬ ሜትር .............................................................. 127
28. በኢኮኖሚና በባህል ዘመቻ በአውራጃው ለልዩ ልዩ የልማት ሥራ ዎችና ጉዳዮች የከምባታና ሀዲያ አውራጃ ሕዝብ ያዋጣው ገንዘብ በከፊል እስከ 1975 .................................................. 134
29. የሆሣዕና ከተማ ሕዝብ ብዛት በ1955 ፣ በ1958 ፣ በ1973 ፣ በ1975 ........................................................................ 135
30. የሆሣዕና ማዘጋጃ ቤት የዓመት ገቢ መጠን ከ1965 እስከ 1974 በብር .......................................................................... 136
31. በከምባታና ሀዲያ አውራጃ ወረዳዎችና መንገዶች ላይ በየቀኑ ሰውና ዕቃ ጭነው የሚንቀሳቀሱ የድርጅት ፣ የመንግሥትና የግል መኪ ናዎች ብዛት በ1975 .................................................. 137
32. ከአንደኛው እስከ ስምንተኛው ዙር የመሠረተ ትምህርት ዘመቻ ከ1971 እስከ 1975 .................................................. 138
33. የትምህርት ቤቶች ፣ የተማሪዎችና የአስተማሪዎች ዕድገት ከ1965 እስከ 1975 .............................................................. 141
34. በ1975 በሸዋ አውራጃዎች የ6ኛና የ8ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና የሚፈተኑ ተማሪዎች ብዛት ........................................ 142
35. በ1975 የከምባታና ሀዲያ አውራጃ ወረዳዎች የትምህርት ቤት ቀጠናዎችና ዞኖች ...................................................... 143



36. ከከምባታና ሀዲያ አውራጃ የእርሻ ሰብል ገበያ ኮርፖሬሽን ከ1972 እስከ 1975 መጀመሪያ የገዛው እህል መጠን በኩንታል .......... 145
37. ከከምባታና ሀዲያ አውራጃ ከ1968 እስከ 1975 መጀመሪያ ድረስ ለማዕከላዊ ቡና ገበያ የቀረበ ቡና በቶንና በኩንታል ............. 146
38. በከምታና ሀዲያ አውራጃ የመሬት ግብር ገቢ መጠን በ1965 እና በ1974 በብር ................................................ 147
39. በ1970 በኢትዮጵያ ክፍለ ሀገራትና በከምባታ-ሀዲያ አውራጃ የሕዝብ ብዛት የጤና ተቋሞችና አገልግሎት ....................... 149
40. በ1971 ለሆሣዕና ሆስፒታል ሕንፃ ማሠሪያ ገንዘብ ለማዋጣት የከምባታና ሀዲያ አውራጃ ያካሄደው ዘመቻ ....................... 150
41. በግንቦት 1972 ሦስት የሕንፃ ተቋራጮች በጨረታ የቀረቡት የሆሣዕና ሆስፒታል ሕንፃ ዋጋ .......................................... 152
42. የነርስ ት/ቤትና የሐኪሞች መኖሪያ ቤት ዋጋ ጭምር የሆሣዕና ሆስፒታል የጠቅላላ ወጭ ግምት በብር ............................. 160
43. የሆሣዕና ሆስፒታል መጠንና ይዘት .................................. 164

# መታሰቢያ

ይህ መጽሐፍ ፥—

1. በገዛ መሬታቸው ፣ ጉልበታቸውና በምርት መሣሪያቸው የዘመኑንና የሥርዓቱን ቀምበር ተሸክመው በአለፈው ምዕተ ዓመት ክውጭ ወራሪዎችና ከኢምፔሪያሊስቶች ጋር እየተዋደቁ አዱሱን የኢትዮጵያ ማዕከላዊ መንግሥትና ብሔራዊ ግዛት በምርትና በጦር ለገነቡት የኢትዮጵያ ገባሮች ፣
2. ከመሬታቸው በሥርዓታዊ በደልና ግፍ ተነቅለው በጉልበታቸውና በምርት መሣሪያቸው ሕብረተሰቡን እያገለገሉ በቅድመ አብዮት ለኢትዮጵያ ከተሜ ወዛደር ፣ ወታደርና ተማሪ ወላጅና ምንጭ ለሆኑ የኢትዮጵያ ጢሰኞች ፣
3. ራሱ ሳይማር ላስተማረው ውለታውና ፍቅሩ በምንም ሥፍራና ጊዜ ለማይለየው የኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝብ ፣
4. በገባርነት ፣ በባርነትና በጢሰኝነት ለዘመናት ሲበዘበዝ የኖረውን የኢትዮጵያን ጭቁን ሕዝብ ከሥርዓት ሰንሰለት ነፃ ላወጣው ለታላቁ ለየካቲት 25 ቀን 1967 የመሬት ማለትም ለአርነት አዋጅ ፣
5. ከ1966 ጀምረው በየግምባሩ ለሰው ልጅ ክብርና ነፃነት ከውስጥና ከውጭ አድሃሪ ኃይላት ጋር በክብር እየተዋደቁ አብዮታዊ ሰማዕታት ለሆኑ ኢትዮጵያውያን ፣
6. ወራሪዎቹንና ተገንጣዮቹን በመደምሰስ አብዮቱንና እናት አገሩን ከጥፋት ላዳነው የኢትዮጵያ አብዮታዊ ጦር ፣
7. የ1971 ብሔራዊ የኢኮኖሚና የባህል ዘመቻ አካል ፣ ውጤት መግለጫና ምልክት ለሆነው የሆማዕና ሆስፒታል ፣

የደራሲው መታሰቢያ ነው ።

# መቅድምና መግቢያ

በየካቲት 1966 እንደ አሳተገሞራ የፈነዳውን የኢትዮጵያን ሕዝባዊ አብዮት ለመቀልበስ ብሎም የአገሩን ብሔራዊ ህልውና፣ነፃነትና አንድነት ከምድረ ገጽ ለማጥፋት በአገርና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተደራጅተው የተነሱ የውስጥና የውጭ አድሃሪ ኃይላትና ድርጅቶች በኢትዮጵያ አብዮታዊ ሕዝብ ፣ መንግሥትና ጦር እንደያመጣጣቸው አንድ በአንድ ከተደመሰሱ በኋላ ፣ በጥቅምት 1971 የኢትዮጵያ አብዮታዊ መንግሥት ለአገር ግምባታ የኢኮኖሚና የባህል ዘመቻ አወጀ ። እንዲሁም ለኢትዮጵያ ሕዝብ ኋላ ቀርነት ዋናው ባህላዊ መሠረትና መሣሪያ የሆነውን መሃይምነትን ከአገሩ ለማጥፋት በሐምሌ 1971 በአገር አቀፍ ደረጃ የመሠረተ ትምህርት ዘመቻ ተጀመረ ። በተጨማሪም አብዮታዊ መንግሥት ለኢትዮጵያ ሠርቶ አደሮች ፓርቲ (ኢሠፓ) ምሥረታ በታህሣሥ 1972 የኢትዮጵያ የሠርቶ አደሮች ፓርቲ አደራጅ ኮሚሽንን (ኢሠፓአኮ) በአዋጅ መሥርቶ መዋቅሩንና ተግባሩን በአገር አቀፍ ደረጃ ዘረጋ ።

በዚህ አንፃርና ተግባር ከሁሉ በፊት የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮትና ተግባሮቹ ማለትም የኢትዮጵያ አብዮታዊ አዋጆች ፣ ድርጅቶች ፣ ዘመቻዎች ፣ ፖሊሲዎችና የተግባር ፕሮግራሞች በሙሉ ለኢትዮጵያ ጭቁኑ ሰፊ ሕዝብ ራሱንና አካባቢውን ለመለወጥ ብሎም አዲስና ተራማጅ ሕብረተሰብ ፣ ኢኮኖሚ ፣ ባህልና ሥርዓት ለመገንባት የሚያስችሉ መሠረታዊ የኢኮኖሚ ፣ የፖለቲካና የርዕዮተ ዓለም መሣሪያዎች ናቸው ። በዚህ አኳያ በአጭሩ የአብዮት ፀሐይና ብርሃን ለዘመናት በሥርዓት ጨለማና ሰንሰለት ታሥረው ለኖሩ ኢትዮጵያውያን በሙሉ ወጥቶላቸዋል ። የአብዮቱ ዝናብ ለጭቁኑና ለምዝብሩ የኢትዮጵያ ሕዝብ በሙሉ ዘንቦለታል ።

ነገሩን በዝርዝርና በግልጽ ለማስቀመጥ የኢትዮጵያ አብዮታዊ ፣ ሕዝባዊና ብሔራዊ አዋጆች ፣ ሕጐችና ድርጅቶች ማለትም የሠራተኛ ፣ የገበሬ ፣ የከተማ የወጣትና የሴት ማህበራት ለኢትዮጵያ ወዛደሮች ፣ አርሶ አደሮች ፣ ከተማ ነዋሪዎች ፣ ወጣቶች፣ሴቶች ፣ ብሔረሰቦች ፣ ከተሞች ፣ መንደሮች ፣ ቀበሌዎች ፣ ወረዳዎች ፣ አውራጃዎች ና ክፍለ ሀገራት በሙሉ በቀድሞው ዘመንና ሥርዓት ይደረግ እንደነበር በመከከላቸው የጐሣ ፣ የቋንቋ ፣ የሃይማኖት ፣ የጾታና የዕድሜ ወይም የስፍራ ልዩነትና ምርጫ ሳይደረግ ለሁሉም ዲሞክራሲያዊና ብሔራዊ እኩልነት መብትንና ክብርን አስገኝቶላቸዋል ።

በእነዚህ በኢትዮጵያ አብዮታዊ ፣ ሕዝባዊና ብሔራዊ አዋጆች ፣ ሕጐች ፣ ድርጅቶች ፣ ዘመቻዎች ፣ ፕሮግራሞችና ፖሊሲዎች መሠረት እያንዳንዱ አብዮቱ የመጣለት ኢትዮጵያዊ ግለሰብ ፣ ድርጅት ፣ ቀበሌ ፣ ከተማ ፣ መንደር ፣ ወረዳ ፣ አውራጃና ክፍለ ሀገር ጠንክሮ ራሱንና አካባቢውን ሲያጸዳ ፣ ሲያደራጅ ፣ ሲለውጥና ሲገነባ ያንኑ ያህል በአጠቃላይ ለአገሩ ግምባታና ዕድገት የራሱን አብዮታዊና ብሔራዊ አስተዋጽኦ ያደርጋል ። በዚህ አንፃርና ተግባር ሕዝባዊ አብዮት የመጣላቸው የኢትዮጵያ የተለያዩ አካባቢዎችና አካላት ከአብዮቱ ፍንዳታ እስከ ዛሬ ድረስ በልዩ ልዩ መስኮችና ዘርፎች ለእናት አገር ብሔራዊ ህልውና ነፃነት ፣ አንድነትና ዕድገት የጊዜውና የአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታዎች በፈቀዱት መንገድና መጠን የየራሳቸውን አካባቢያዊና ብሔራዊ አስተዋጽኦ አድርገዋል ፣ በማድረግም ላይ ናቸው ።

እነዚህ በየአካባቢው የተካሄዱና የሚካሄዱ የኢትዮጵያ አብዮታዊና ሕዝባዊ የአገር ግምባታ ትግሎችና ሥራዎች በአንድነት ሲደመሩና በሳይንሳዊ ምርምር ሲጸፉ የታላቁ አብዮታችን ሙሉ ገጾች ፣ ምዕራፎችና ገጽታዎች ይሆናሉ ። እነዚህ ብሔራዊ ትግሎችና ድሎች ታላቁ ሕዝባዊ አብዮታችን በአገራችን በየመስኩና በየአካባቢው ያስከተለውን ፖለቲካዊ ፣ ኢኮኖሚያዊና ፣ ባህላዊ ለውጥና ልማት ለጠላቶችም ለወዳጆችም በትክክል በማሳየት የአብዮቱን ኃያልነትና ድል አድራጊነት ለዓለምና ለመጪው ትውልድ ያሳያሉ ።

ስለዚህ ዛሬ በአገራችን በየመስኩና በየአካባቢው ማለትም በፖለቲካዊ ፣ በወታደራዊ ፣ በርዕዮተ ዓለማዊ ፣ በኢኮኖሚያዊ ፣ በባህላዊና በድርጅታዊ መስኮችና ግምባሮች በገጠርና በከተማ የተገኙትንና የሚገኙትን የአብዮቱን ድሎች በሳይንሳዊ ጥናትና ምርምር በዝርዝርና በጥልቀት መጻፍና ማሳወቅ ለአገሩ ምሁራን አብዮታዊና ወቅታዊ ተግባር ነው ።

በዚህ አንፃርና ተግባር ይህ አጭር ታሪካዊ ጽሑፍ የሚገልጸው በተለይ በከምባታና ሀዲያ አውራጃ በመካሄድ ላይ ያለውን አብዮታዊ ለውጥና ልማት ነው ። በሌላ አካባቢዎች በአገር አቀፍ ደረጃ እንደተደረገው ሁሉ በአውራጃውም ውስጥ በኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮትና በብሔራዊ አንድነት ላይ የተነሱ የውስጥና የውጭ አድሃሪ ኃይላትና ድርጅቶች በአብዮቱ ወገኖችና ደጋፊዎች ኃይል በቁጥጥር ሥር ከዋሉ በኋላ የከምባታና ሀዲያ አውራጃ ሕዝብ በኢትዮጵያ ብሔራዊ አብዮታዊ የኢኮኖሚና የባህል ዘመቻ መሠረት በ1971 በኢኮኖሚ፣ በትምህርት ፣ በባህልና በጤና ዘርፎችና መስኮች የራሱን መለስተኛ የሆነ የአውራጃ ልማት እቅድና ዘመቻ ቀየሰ ።

የከምባታና ሀዲያ አውራጃን የኢኮኖሚና የባህል ዘመቻ ዓይነተኛ ከሚያደርጉት አያሌ ገጽታዎችና ሥራዎች አንዱ በሆሣዕና ከተማ በብዙ ሚሊዮን ብር ወጭ ከምድር ቤት በላይ ሦስት ፎቆች ያሉበት ባለ 250 አልጋ ሆስፒታል ለመሥራት የአውራጃው ሕዝብ የወሰደው ታሪካዊ እቅድና እርምጃ ነው ። በጥር 1971 የአውራጃው ሕዝብና አስተዳደር የሆስፒታሉን ሥራ እቅድ ለአገሩ ሕዝብና መንግሥት ባስታወቀ ጊዜ ለብዙ ሰዎች እቅዱ ተግባራዊ ሊሆን የሚችል ነገር ሆኖ አልታየም ነበር ።

ይህ ደራሲ የአውራጃውን ይህንን ዓይነት የልማት እንቅስቃሴና ራስን በራስ የመርዳት ጥረት በመደገፍ በ1972 "የኢትዮጵያ አብዮት ታሪካዊ መነሻና ሂደት በከምባታና ሀዲያ አውራጃ" በሚል እርዕስት አንድ አጭር ጥናታዊ ጽሑፍ አዘጋጅቶ ነበር ። የሆሣዕና ሆስፒታል እቅድ በሚመለከት ደራሲው ጥናቱን ከዚህ በሚከተሉት ሁለት አረፍተ ነገሮች ሲደመድም የሆስፒታሉን እቅድ ተግባራዊ የሚያደርግ የገንዘብ እርዳታ ከአውራጃዎ ውጭ ከየትና እንዴት እንደሚገኝ በወቅቱ እርግጠኛ አልነበረም ። በ1972 በጥናቱ መደምደሚያ ላይ ደራሲው እንደአስቀመጠው ፣

"በአጭርና በአጠቃላይ አድሃሪ ኃይላትና የአብዮት ቀልባሾች በሰፊው ጭቁን ሕዝብና በአብዮታዊ መንግሥት ትብብር በሚያዝያ 1971 ከተደመሰሱ ወዲህ በከምባታና ሀዲያ አውራጃ የታየው ከፍተኛ የምርት ፣ የትምህርት ፣ የባህል ፣ የስፖርትና የኪነት እንቅስቃሴ የአብዮታዊ ሕዝብና መንግሥት ሕብረት ውጤት ሲሆን የዚህ አብዮታዊ ትብብር ከፍተኛ ምልክትና መግለጫ ደግሞ አሁን በመሥራት ላይ ያለው የሆሣዕና ሆስፒታል ነው ። ሆስፒታሉን በተቻለ ፍጥነት



ለሕብረተሰቡ አገልግሎት እንዲውል ማድረግ ለአብዮቱና ለአብዮቱ ሠፊር ዕድገትና ጥንካሬ የበለጠውን ተግባራዊ አስተዋጽኦ እንደሚያደርግ እሙን ነው ።

"ስለሆነም በ1971 የታወጀው የምርትና የባህል ዕድገት ዘመቻ ውጤት የሆነው የሆሣዕና ሆስፒታል ሥራው በፍጥነት አልቆ እንደታሰበው ለሕብረተሰቡ አገልግሎት እንዲውል ማድረግ ለኢትዮጵያ አብዮታዊ ሕዝብና መንግሥት ብሔራዊ ሃላፊነትና ተግባር ነው ።"

ይህ ቃል በ1972 ከተጻፈ በኋላ በሚቀጥሉት ሦስት ዓመታት ውስጥ በከምባታና ሀዲያ አውራጃ ከኢኮኖሚና ከባህል ዘመቻ አንፃርና ተግባር ብዙ የልማትና የዕድገት ውጤቶች ተገኝተዋል ። አንደኛ ፣ በኢኮኖሚና ባህል ዘመቻ መስኮችና ዘርፎች የሚከተለው ሠንጠረዥ እንደሚያሳየው ፣ በአውራጃ አቀፍ ደረጃ ብዙ የለውጥና የልማት ሥራዎች ተከናውነዋል ።

ለእነዚህ የልማት እቅዶችና ሥራዎች የአውራጃው ሕዝብ የጉልበቱ ዋጋ ሳይገመት በድምር እስከ 1975 ድረስ በ16.000.000 የሚቆጠር ብር ማውጣቱን በዚህ ጥናት ይዘትና ሂደት ከዚህ በታች ይታያል[1] ።

ሁለተኛ ፣ ከአውራጃው ሕዝብ የጉደለውን የገንዘብ ወጭ አሟልቶ ለሕብረተሰቡ አገልግሎት እንዲውል ለማድረግ አብዮታዊ መንግሥት የሆሣዕናን ሆስፒታል በ1974 መጨረሻ ተረክቦታል ። በእቅዱ መሠረት ከሆስፒታሉ ጋር አብረው የሚሄዱ አንድ የነርሶች ማሠልጠኛ ትምህርት ቤትና የሕክምና ባለሙያዎች የመኖሪያ ቤቶች ዋጋ ሲጨመር የሆሣዕና ሆስፒታል ዋጋ ማለትም ጠቅላላ የሕንፃው ሥራና የውስጥ መሣሪያዎች ዋጋ በድምር ወደ 13.000.000 ብር ወጭ እንደሚፈጅ ተገምቷል ። በዝርዝር ሲታይ ከዚህ ጠቅላላ ወጭ 5.146.505 ብር የሚሆን የሆስፒታሉ የሕንፃ ሥራ ዋጋ ፣ 4.000.000 ብር የሚሆን የውስጥ መሣሪያዎች ዋጋ 3.000.000 ብር የሚሆን የነርሶች ማሠልጠኛ ትምህርት ቤት ማሠሪያ ዋጋ ፣ 600.000 ብር የሚሆን ደግሞ የሕክምና ባለሙያዎች መኖሪያ ቤቶች ማሠሪያ ዋጋ እንደሚሆን ተገልጸዋል ።

ከዚህ ከሆስፒታሉ ጠቅላላ ወጭ እስከ 1975 ድረስ የከምባታና ሀዲያ አውራጃ ሕዝብ 2.933.777 ብር ፣ የኢትዮጵያ አብዮታዊ መንግሥት ደግሞ 2.779.000 ብር ከፍለዋል ። የሆስፒታሉ የውስጥ መሣሪያዎች ደግሞ ከሁለት ልዩ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች በሥጦታ ተገኝተዋል ። ከዚህ በላይ እንደተባለው ከነሐሴ 1974 ጀምሮ የሆስፒታሉ ሥራና ኃላፊነት ከአውራጃው ሕዝብ እጅ ወደ አብዮታዊ መንግሥት እጅ ተላልፎዋል ። ከዚያ በኋላ የሆስፒታሉ ሥራ በሕዝቡ ዓላማና እቅድ መሠረት በአብዮታዊ መንግሥት ወጭና ሃላፊነት በፍጥነት ስለአለቀ ከ1975 መጨረሻ ጀምሮ የሆሣዕና ሆስፒታል አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል ።

1 በተጨማሪም የከምባታና ሀዲያ አውራጃ ሕዝብ በ20.000 የሚቆጠሩ ሚሊሺያዎች አሰልጥኖ ከእነዚህ መካከል ከግማሽ በላይ አዝምቷል ።

ሰንጠረዥ 1

በድህረ አብዮት የምርትና የባህል ለውጥና ልማት ሁኔታዎች በከምባታና ሀዲያ አውራጃ እስከ 1975

| ተራ ቁ. | የምርትና የባህል መስኮችና ዘርፎች | የለውጥ ዓመታት | የለውጥ እንቅስቃሴ ብዛትና መጠን በመጀመሪያ | የለውጥ እንቅስቃሴ ብዛትና መጠን በ1975 | የዕድገት ደረጃ በቁጥርና በፐርሰንት በቁጥር | የዕድገት ደረጃ በቁጥርና በፐርሰንት በፐርሰንት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | በትምህርት ዘርፍ | | | | | |
| | ሀ. የተማሪዎች ብዛት በቁጥጥርና በፐርሰንት | 1965—1975 | 23,664 | 151,095 | 127,431 | 539% |
| | ለ. የት/ቤቶች ብዛት በቁጥርና በፐርሰንት | 1965—1975 | 85 | 277 | 192 | 226% |
| | ሐ. የአስተማሪዎች ብዛት በቁጥርና በፐርሰንት | 1965—1975 | 530 | 2,050 | 1,520 | 287% |
| | መ. ከ1ኛ እስከ 4ኛ ዙር በመሠረተ ትምህርት ዘመቻ ፈተና ያለፉ ጉልማሶች ብዛት | 1971—1973 | | 520,842 | | |
| 2 | የሆማዕና ከተማ ሕዝብ በቁጥርና በፐርሰንት | 1972—1975 | 18,049 | 25,215 | 7,166 | 39% |
| 3 | የሆማዕና ማዘጋጃ ቤት ገቢ በብር | 1965—1974 | 32,870.43 | 152,865.99 | 119,995.56 | 363% |
| 4 | የአውራጃው የመሬት ግብር ገቢ በብር | 1965—1974 | 767,832.74 | 4,052,699.00 | 3,283,866.26 | 426% |
| 5 | የአውራጃው ጠቅላላ የግብር ገቢ በብር | 1965—1974 | 1,129'222.41 | 5,190,646.62 | 4,061,424.21 | 360% |
| 6 | ከአውራጃው ለመንግሥት የተሸጠ እህል በኩንታል | 1972—1974 | 55,885.56 | 108,774.10 | 52,888.44 | 95% |
| 7 | ከአውራጃው ለመንግሥት የተሸጠ ቡና በኩንታል | 1968—1975 | 15,590 | 29,350 | 13,760 | 88% |

የተገኘበት ፤ በዚህ ጥናት ከዚህ በታች ሠንጠረዦች ቁጥር 28 ፤ 29 ፤ 31 ፤ 32 ፤ 35 ፤ 36 ፤ 37 በትንተና ።



ከታሪክ አንፃር በ1972 የኢሠፓአኮ አንደኛው ጉባኤ ከመደረጉ በፊት በአውራጃው ባካሄደው አጭር ጥናት ለዚህ ደራሲ የከምባታና ሀዲያ አውራጃ የኢኮኖሚና የባህል ዘመቻ ሥምሪት በዓይነትም ፣ በመጠንም ፣ በጥራትም እንደዚህ በከፍተኛ ፍጥነት ይካሄዳል ወይም በአውራጃው ሕዝብና በአብዮታዊ መንግሥት መካከል ያለው የዓላማና የተግባር አንድነትና ትብብር እንደዚህ በስፋትና በጥልቀት በአጭር ጊዜ ውስጥ ተግባራዊ ይሆናል ብሎ ግልጽ ምሁራዊ ግምገማና አስተያየት ለመሰንዘር የሚያስችሉ ብዙ ተጨባጭ ማስረጃዎችና ምልክቶች ገና አልነበሩትም ። ይህም በትክክል የሚያሳየው መሠረታዊ ነገር ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮት እንዴት ፈጣን ብሔራዊ ኃይልና ሂደት እንደሆነ ነው።

በአጭርና በአጠቃላይ ከዚህ በላይ በቀረቡት ተገቢና ትምህርታዊ ምክንያቶች በከምባታና ሀዲያ አውራጃ ውስጥ በመካሄድ ላይ ያለው የልማት እንቅስቃሴ በስፋትና በዝርዝር እንደገና ተጠንቶ "አብዮታዊ የምርትና የባህል ዘመቻ በከምባታና ሀዲያ አውራጃ" በሚል አርዕስት ከዚህ በታች ቀርቦዋል ። ጥናቱም የተዘጋጀው በአራት ክፍሎች ሲሆን በመጀመሪያዎቹ ሁለት ዋና ክፍሎች የሕዝባዊ አብዮቱን ፍንዳታና ሂደት ጭምር የኢትዮጵያ ታሪክ አጠቃላይ ይዘትና ሂደት እስከ 1975 ድረስ ከሥፍራና ከጊዜ አንፃር በአጭርና በጥልቅ ተገልጾዋል ። በሁለቱ መጨረሻ ክፍሎች ደግሞ በከምባታና ሀዲያ አውራጃ ብቻ የሕዝባዊ አብዮቱ መነሻ ፣ ይዘት ፣ ሂደትና ውጤት በተለይ በዝርዝር ተገልጾዋል ።

በመጨረሻም የዚህ አጭር ጥናት ንጥረ ነገር ማለትም ከ1971 እስከ 1975 ድረስ በአራት ዓመታት ውስጥ በከምባታና ሀዲያ አውራጃ የተካሄደው ከፍተኛ የልማት እንቅስቃሴና ሥራ የሆማዕና ሆስፒታል ጭምር በተግባራዊ ልምድና ትምህርት በተጨባጭ እንደአሳየን ፣ ዛሬ በአገራችን አዲስ የሶሻሊስት ኢኮኖሚ ባህል ፣ ሥርዓትና ሕብረተሰብ ለመገንባት በምናካሂደው ወሳኝ ብሔራዊ ትግል በአብዮታዊ መሪያችን በጓድ መንግሥቱ ኃይለ ማርያም እንደበት "አብዮታችንን ከቅልበሳ ፣ ሀገራችንን ከመከፋፈል ያዳነ የሀገሪቱ ኢኮኖሚ የጀርባ አጥንትና ወሳኝ ኃይላችን ገበሬው ነው" በመባል በትክክል የተመሰከረለት የኢትዮጵያ አርሶ አደር ከድርጅት ፣ ከርዕዮተ ዓለም ፣ ከትምህርት ፣ ከአስተዳደርና ከፍትሕ አንፃር አብዮታዊ ፣ ማዕከላዊና ሚዛናዊ የሆነ አመራር ከተሰጠው በመሬቱ ፣ በጉልበቱና በጊዜው ከሚታሰበው በላይ ያገር ግምባታ ሚና ሊጫወት ይችላል ።

በአጭሩ የኢትዮጵያ ገበሬና መሬት እንደዚህ በትምህርትና በወዛደራዊነት ርዕዮተ ዓለም ከተደራጀና ምርታማ ከሆነ በእርግጥ በአገራችን ሶሻሊስት ኢኮኖሚ ፣ ባህል ፣ ሥርዓትና ሕብረተሰብ በብሔራዊ ትግላችን ይገነባል ። ሳይንስ ፣ ቴክኖሎጂና ምርት ያድጋል ። ሶሻሊዝም ይገነባል ። የኢትዮጵያ አብዮት ዓላማም ፣ ተግባርም ፣ ተልዕኮም ፣ ግብም ሁሉ በአንድነት ሶሻሊዝም ነው ።

ላ. ጌ. ድ.
ሚያዝያ 1975
አዲስ አበባ

ክፍል አንድ

# የኢትዮጵያና የኢትዮጵያውያን አጭር ሐተታ

## 1. የኢትዮጵያና የኢትዮጵያውያን ታሪካዊ አመጣጥና ዕድገት ከጥንት እስከ 1850

### 1. ሀ. የኢትዮጵያ ምድር፣ ብሔረሰቦችና ቋንቋዎች

ለጥናታዊ ትችትና ትንተና፣ ከሥፍራና ከጊዜ አንፃር፣ የኢትዮጵያን ረጅምና ውስብስብ ታሪክ 1/ ከጥንት እስከ 1850 ድረስ በምሥራቅ አፍሪካ መለስተኛ አህጉር እያሉ የኢትዮጵያ ጕሣዎች፣ ነገዶች፣ ብሔረሰቦች፣ ቋንቋዎች፣ ንዑስ መንግሥታት፣ አዳጊ ስልተ ምርቶች፣ ባህሎች፣ ዕደ ጥበባትና ሃይማኖቶች አመጣጥና ዕድገት ዘመን፣ 2/ ከ1850 እስከ 1966 ድረስ በዘመነ ኢምፔሪያሊዝም የኢትዮጵያ ምድርና ሕዝብ ከአያሌ ወራሪዎችና ኢምፔሪያሊስቶች ጋር ለብሔራዊ ህልውና፣ ነፃነትና አንድነት እየተዋጋ ከፍተኛ የሕይወትና የንብረት መስዋዕት ከፍሎ በአንድ ጠንካራ ማዕከላዊ መንግሥትና ብሔራዊ ሥርዓት ሥር የተደራጀበት ታሪካዊ የአገር ግምባታ ትግልና ዘመን፣ 3/ ከ1966 ጀምሮ ደግሞ የኢትዮጵያ የሕዝባዊ አብዮትና የሶሻሊዝም ግምባታ ዘመን በማለት የአገሩን አጠቃላይ ታሪክ ከጥንት እስከ ዛሬ በሦስት ተከታታይ ክፍለ ዘመናት መድቦ በሳይንሳዊ ምርምርና ሚዛን ማቅረብና መግለጽ ይቻላል።

ከሥፍራ አኳያ ለኢትዮጵያ ሕዝብና ታሪክ ከጥንት ጀምሮ ህልውናዊ መሠረት፣ መነሻና ምክንያት የሆነው ተጨባጭ መሠረታዊ ነገር በሦስቱ በተፈጥሮ ጠረፎችና አካባቢዎች ማለትም በአባይ ሸለቆ፣ በቀይ ባህርና በሕንድ ውቅያኖስ የተከለለ የምሥራቅ አፍሪካ መለስተኛ አህጉር ነው። ይህ ደራሲ በጥር 1974 በምዕዋ ሲምፖዚዮም ተንትና በዝርዝር እንደአስቀመጠው፣[1]

"ይህ የኢትዮጵያ ምድር ከጥንት ጀምሮ በየጊዜው በዓለም ላይ በተፈራረቁ ባዕዳን ሕዝቦችና መንግሥታት ማለትም በጥንታዊ ግብጻውያን፣ በኑቢያውያን በባቢሎናውያን፣ በግሪኮች፣ በሮማውያን፣ በፋርሶች፣ በአረቦችና በቱርኮች ስላልተያዘ በምድረ ኢትዮጵያ የነበሩና የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን በሥፍራ፣ በጊዜና በታሪክ አንድ የሆኑ አፍሪካውያን ናቸው።

"ከጊዜ አንጻር ሲታይ ደግሞ፣ ከዛሬ 3500 ዓመታት በፊት ማለትም ከክርስቶስ ልደት በፊት በ1500 አካባቢ ፐረሁ በተባለ ንጉሥና አጢ በተባለች ንግሥት የሚገዙ፣ በከተማና በገጠር የሚኖሩ በእርሻና በንግድ ሥራ የሰለጠኑና የተስማሩ፣ በሃይማኖት የተፈጥሮ አማልክት፣ መቅደስና ካህናት የነበሩ

1 ላጵሶ ድሌቦ፣ "የቀይ ባህርና የአባይ ሸለቆ ሚና"፣ የምዕዋ ሲምፖዚዮም (ጥር 1974)፣ ገጽ 19—21።

አቸው በዓለም ታሪክ ፑንታውያን ተብለው የሚጠሩ ጥንታዊ ሰዎች በቀይ ባህር ጠረፍ በዛሬው ኤርትራ ክፍለ ሀገርና በጅቡቲ አካባቢ እንደነበሩ ፣ አን ዱት የግብጽ ንግሥት በ1480 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት አምስት የንግድ መርከቦች ወደ ምድረ ፑንት በላከችበት ጊዜ በአንድ መርከበኛ ተስሎ አሁን በምድረ ግብጽ በአንድ ጥንታዊ ቤተ መቅደስ ውስጥ በሚገኘው ሥዕላዊ ማስ ረጃ በትክክል ተረጋግጠዋል ።

"ከታሪካዊ ዕድገትና ሂደት አንፃር ሲታይ ደግሞ ፣ ከፑንታውያን ዘመን እስከ ዛሬ ድረስ ለኢትዮጵያ ምድርና ሕዝብ የዛሬውን ብሔራዊ ይዘትና ቅርጽ የሰጡ የውስጥና የውጭ ሁኔታዎችና ኃይላት እጅግ ብዙ ሲሆኑ ከእነርሱ ዋና ዋናዎቹን ከዚህ እንደሚከተለው በሦስት ክፍል ዘመናት ከፍሎ የአገሩን አጠ ቃላይ ታሪክ በሳይንሳዊ ጥናትና ምርምር ማስተማርና መግለጽ ይቻላል ።

"ከጥንት እስከ 1850 ድረስ በኢትዮጵያ ምድር አያሌ ነገዶች ፣ ጐሣዎች ፣ ብሔረሰቦችና መንግሥታት በሥፍራ ፣ በጊዜ ፣ በንግድ ፣ በጋብቻ ፣ በጦርነት ፣ በሃይማኖት ፣ በቋንቋና በባህል በመገናኘትና በመፈራረቅ ፣ በመቀላቀልና በመ ወራረስ የብሔረሰቦችን ብዛትና አንድነት የኢትዮጵያ ሕዝብና ታሪክ መሠረት አድገውታል ። በዚህ ረገድ ከጥንት እስከ 1850 ድረስ በሥፍራና በጊዜ ፣ በታ ሪክና በባህል በመቀላቀልና በመወራረስ ለኢትዮጵያ ብሔረሰቦች ብዛትና አን ድነት መሠረት ፣ መነሻና ምክንያት የሆኑ ኢትዮጵያውያን ከዚህ የሚከተሉ ናቸው ።

"አክሱማውያን ፣ ቤጃ ፣ ባርያ ፣ ኩናማ ፣ አገው ፣ ፈላሻ ፣ ትግራይ ፣ ትግሬ፣ አማራ ፣ ሸዋ ፣ ማለትም ከ890 እስከ 1285 ድረስ በደቡብ ምሥራቅ የነበረው የኢትዮጵያ ሱልጣኔት (ማለትም እስላማዊ አገርና መንግሥት) ፣ ዳሞት ፣ ሀዲያ ጉራጌ ፣ ይፋት ፣ ዳዋሮ ፣ አራብቢኒ ፣ ሻርካ (ሳርካ) ፣ ደራ ፣ ባሊ ፣ አዳል ፣ ፈጠ ጋር ፣ ወጅ ፣ ጋፋት ፣ አርጎባ ፣ ከምባታ ፣ ወላይታ ፣ ሱማሌ ፣ አፋር ፣ እናርያ ፣ በሻ ፣ ጀማ ፣ አደሬ ፣ አጀንጂራ (ጃንጀሮ) ፣ኦሮሞ ፣ ከፋቾ ፣ ጊሚራ ፣ ሸናሻ ፣ ኑር ፣ አኑአክ ፣ ጋሞ ፣ ጐፋ ፣ ኩሎ ፣ ኮንታ ፣ በርታ ፣ ማለትም በዛሬው ወለጋ ክፍለ ሀገር በአሶሳ አውራጃ የነበረው የቤንሻንጉል ሱልጣኔት ፣ ጉሙዝ ፣ አላባ፣ ሲዳሞ ፣ ጌዴኦ ፣ (ደራሳ) ፣ ቡርጂ ፣ ኮንሶ ወዘተ... ናቸው ።[2]

2 "The Adulis Inscription" in Cosmas, *The Christian Topography of Cosmas*, tr. and ed. by J. McCrindle (1897), pp. 59-66; D. Muller, "On the Inscriptions from Yeha and Aksum" in J. T. Bent, *The Sacred City of the Ethiopians* (1896), pp. 231-281; A. J. Drewes, *Inscriptions de L'Ethiopie* (1962); R. Schneider, "Les Debuts de L'Histoire Ethiopienne" *Documents Histoire Civilisation Ethiopienne*, RCP 230, CNRS, FASC. 7(1976), p. 47-54; G. W. B. Huntingford, "Arabic Inscriptions in Southern Ethiopia", *Antiquity*, Vol. 29 (1955), pp. 230-233; M. Schneider, "Steles Funeraire Muslmanes de la Province du Choa", *Annales d'Ethiopie*, Vol. 8 (1970); G. W. B. Huntingford, tr. and ed., *The Glorious Victories of Amda Seyon King of Ethiopia* (1965); O. G. S. Crawford, ed., *Ethiopian Itineraries Ca.* 1400-15204 (1958); Ibn Fadl A. Omari, *Masalik el Absar Fi Mamalik el Masar*, tr. and



ሠንጠረዥ 2

የኢትዮጵያ ብሔረሰቦችና ቋንቋዎች

| "ሴማዊ" ቋንቋዎች | "ኩሻዊ" ቋንቋዎች | | | "ናይል—ሰሓራ ቋንቋዎች" |
|---|---|---|---|---|
| | የሰሜንና የመሀል | የምሥራቅ | የምዕራብ | |
| ግዕዝ ፤ ትግሬ ፤ ትግርኛ ፤ አማርኛ ፤ አርጎብኛ ፤ አደርኛ ፤ ጋፋትኛ ፤ <br> የጉራጌ ቋንቋዎች <br> ስልጢኛ ፤ ሶዶኛ ፤ ሙሀርኛ ፤ መስቃንኛ ፤ እነሞርኛ ፤ ቸሀኛ ፤ እንደጋኛ ጌቶኛ ፤ እዣኛ ፤ ጉመርኛ ፤ ጐጐትኛ ፤ ወለንኛ ፤ (ከስልጢኛ እስከ ወለንኛ የጉራጌ ቋንቋዎች ናቸው) | ቢጃና ፤ ቢለንኛ ፤ ቅማንትኛ ፤ ሀምታንኛ ፤ አገውኛ | ሱማሊኛ ፤ ሬንዴልኛ ፤ ባይሶኛ ፤ አርቦሬኛ ፤ ኮንሶኛ ፤ ገደአኛ ፤ ገዋዳኛ ፤ አርቦርኛ ፤ ማሎ ጉደኛ ፤ ወረዛኛ ፤ ገለብኛ ፤ አፋርኛ ፤ ሳሆኛ ፤ ሲዳምኛ ፤ ከምባትኛ ፤ ተምባርኛ ፤ ሀዲይኛ ፤ አላባኛ ፤ ቀቢናኛ ፤ ሊባዲኛ (ማረቆኛ) ጌዴኦኛ (ደራሳኛ) ፤ ቡርጂኛ፤ | አሪኛ ፤ ዲሜኛ ፤ በዴኛ ፤ ማጂኛ ፤ ናኦኛ ፤ ሼኮኛ ፤ የምኛ ፤ ከፋኛ ፤ ሸናሻኛ ፤ ጊሚርኛ ፤ ጃንጀሮኛ ፤ ዳውሮኛ ፤ ዶርዜኛ ፤ ኩሎኛ ፤ ኮንትኛ ፤ ወይዴኛ ፤ ወላይትኛ ፤ ጊዲቾኛ ፤ ቀጫምኛ ፤ ኮይሬኛ ፤ ዘይሴኛ ፤ ባስኬቶኛ ፤ ማሌኛ ፤ ዶኮኛ ፤ ኦዮሎኛ ፤ ጋሞኛ ፤ | ኩናማኛ ፤ መኢኒኛ ፤ መዠንጉኛ ፤ ቲርማኛ ፤ ሙርሲኛ ፤ ዚልማሞኛ ፤ ናራኛ (የባርያ) ፤ ቱርካኛ ፤ ማባንኛ ፤ መጣመትኛ ፤ ጉባኛ - (ምስት የበርታ ቋንቋዎች) አኝዋክኛ ፤ ኑዌርኛ ፤ ኩናምኛ ፤ ጉሙዝኛ ፤ ሲአኛ ፤ ኮሞኛ ፤ ትሽናኛ ፤ ሱሪኛ ፤ ባሌኛ ፤ ሙርሌኛ ፤ ኒያንጋቶም ፤ |
| ድምር 21 ቋንቋዎች | 5 ቋንቋዎች | 23 ቋንቋዎች | 26 ቋንቋዎች | 23 ቋንቋዎች |

Source: H. C. Fleming, "West Cushitic Within Hamitio-Semitic" in D.F. McCall, *East African History* (1969); M. L. Bender, ed., *Non-Semitic Languages of Ethiopia* (1976); H. S. Lewis, ,,Origins of the Galla and Somali", *Journal of African History*, Vol. 7, No. 1 (1966); M. L. Bender, *The Ethiopian Nilo-Saharans* (1975); W. Leslau, "Is There A Proto-Gurace *Proceedings of the International Conference on Semitic Studies* (Jerusalam 1965); G. P. Murdock, *Africa: Its Peoples and Culture History* (1959).

ed., by G. Demombynes (1927), Maqrizi, *The Book of the Ttrue Knowledge of the Moslem Kings in Abyssinia*, tr. by G. W. B. Huntingford (Typescript, 1955); J. Perruchon, tr. and ed., Les *Chroniques de Zara Yaeqob et de Baeda Maryam* (1893); Arab-Faqih, *Histoire de la Conquete de L'Abyssinie*, tr. and ed. by R. Basset (1897); U. Braukamper, *Geschichte des Hadiya Sud-Athiopiens* (1980); R. Basset, tr. and ed., *Etudes Sur L'Histoire de L'Ethiopie* (1881); H. S. Lewis, "Origins of the Galla and Somali", *Journal of African History*, Vol. 7, No. 1 (1966); Bahrey, *History of the Galla* in C. F. Beckingham and G.B.W. Huntingford, trs, and eds., *Some Records of Ethiopia* 1593-1646 (1954); J. Bruce, *Travells to Discover the Source of the Nile*, 5 Vols (1790); H. W. Blundell, tr, and ed., The Royal Chronicle of Abyssiniq (1922); ተክለሥላሴ (ጢኖ ተስማ) አዘ/ ፤ የአጼ ሱስንዮስ ታሪክ (ያልታተመ ዜና መዋዕል) ።

ሠንጠረዥ 3

የተፈጥሮ አካባቢዎችና ሁኔታዎች ሚና በኢትዮጵያ ብሔረሰቦች ፤ ቋንቋዎች ፤ ባህሎችና ዕደ ጥበባት ብዛትና አንድነት

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| የቀይ ባህር ፤ የመረብ ፤ የጋሽ ፤ የተከዜ ፤ የጣና ፤ የአባይ ፤ የበሽሎ አካባቢ ጉማዎች ፤ ነገዶች ፤ ቋንቋዎች ፤ ብሔረሰቦች ፤ ባህሎች ፤ ዕደ ጥበባት ፤ አገሮችና መንግሥታት በሰሜን ኢትዮጵያ | የአባይ ፤ የሙገር ፤ የጊቤ ፤ የዴዴሳ ፤ የጉጀብ ፤ የባሮ አካባቢ ጉማዎች ፤ ነገዶች ፤ ቋንቋዎች ፤ ብሔረሰቦች ፤ ባህሎች ፤ ዕደ ጥበባት ፤ አገሮችና መንግሥታት በምዕራብ ኢትዮጵያ | የአዋሽ ፤ የዋቤሸበሌ ፤ የዙዋይ ፤ የላንጋኖ ፤ የሻላ ፤ የአባያታ ፤ የአዋሳ ፤ የብሌቴ የጊቤ ፤ አካባቢ ጉማዎች ፤ ነገዶች ፤ ቋንቋዎች ፤ ብሔረሰቦች ፤ ባህሎች ፤ ዕደ ጥበባት ፤ አገሮችና መንግሥታት በደቡብ ምሥራቅ ኢትዮጵያ | የኦሞ ፤ የአባያ ፤ የጫሞ ፤ የጨው ባህር ፤ የሩዶልፍ አካባቢ ጉማዎች ፤ ነገዶች ፤ ቋንቋዎች ፤ ብሔረሰቦች ፤ ባህሎች ፤ ዕደ ጥበባት አገሮችና መንግሥታት በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ | የዳዋ ፤ የጋናሌ ፤ የጁባ ፤ የዋቢሸበሌ አካባቢ ጉማዎች ፤ ነገዶች ፤ ቋንቋዎች ፤ ብሔረሰቦች ፤ ባህሎች ፤ ዕደ ጥበባት ፤ አገሮች በደቡብ ኢትዮጵያ |
| አክሱማውያን ፤ ኩናማ ፤ ቤጃ ፤ ባርያ ፤ ወይም ናራ ትግረ ፤ ትግራይ ፤ አገው ፈላሻ ፤ አማራ ፤ ዶባ ፤ ወዘተ... | ዳሞት ፤ ጋፋት ፤ እናርያ ፤ ቦሻ ፤ አጀንጂራ ፤ ጂማ ፤ ከፋ ፤ ጉንጋ ፤ ሸናሻ ፤ አንፍሎ ፤ ጊሚራ ፤ ማጂ ፤ አኑዋክ ፤ ኑር ፤ ማጃንግር ፤ በርታ ፤ ክዋማ ፤ ጉሙዝ ፤ ጉማ ፤ ጉማ ፤ ሊሙ ፤ ጌራ ፤ ወዘተ... | ሀርላ ፤ ሸዋ ፤ ይፋት ፤ ሀዲያ ፤ ዳዋሮ ፤ አራባቢኒ ፤ ሻርካ ፤ ባሊ ፤ ደራ ፤ ወጅ ፤ ፈጠጋር ፤ ማያ ፤ አዳል ፤ ጉራጌ ፤ ከምባታ ፤ አላባ ፤ ሲዳማ ፤ ጌዴኦ ፤ ቡርጂ ፤ ኮንሶ ፤ ወዘተ... | ወላይታ ፤ ኩሎ ፣ ኮንታ ፤ ጋሞ ፣ ጎፋ ፤ ካመር ፤ ካርስ ፤ ባና ፤ ማሌ ፤ ዶርዜ ፤ ማሎ ፤ አርቦር ፤ ኒያንጋቶም ፤ ገለብ ፤ ወዘተ... | ሳሆ ፤ አፋር ፤ ሱማሌ ፤ ኦሮሞ ፤ ከ16ኛው ምዕተ ዓመት በፊት ። |



## 1. ለ. ለኢትዮጵያ ምድርና ሕዝብ ብሔራዊ ቅርጽና ይዘት የሰጡ አራት ዋና ታሪካዊ ኃይላት

ከጥንት እስከ 1850 ድረስ ባለው ረጅምና ውስብስብ ዘመን እንደዚሁ የኢትዮጵያ አያሌ ጉማዎች ፣ ነገዶች ፣ ብሔረሰቦች ፣ ቋንቋዎች ፣ ንጉስ መንግሥታት ፣ አዳጊ ስልተ ምርቶችና ሃይማኖቶች በሥፍራና በጊዜ እንዲቀላቀሉና እንዲወራረሱ ወሳኝ ታሪካዊና ባህላዊ መሠረቶች ፣ መነሻዎች ፣ መንገዶችና መሣሪያዎች የሆኑ አራት የኢትዮጵያ ልዩ ማህበራዊና ብሔራዊ ኃይላት ፣ ሁኔታዎች ፣ ሂደቶችና ሥርዓቶች 1/ የአክሱማውያን ባህልና ሥልጣኔ ፣ 2/ የክርስትና ባህልና ሥርዓት 3/ የእስልምና ባህልና ሥርዓት 4/ የገዳ ባህልና ሥርዓት እንደሆኑ ሳይንሳዊ ጥናትና ምርምር በትክክል በሥፍራና በጊዜ ያሳያል ።

በዚህ ረገድ ፣ የአክሱማውያን ባህልና ሥልጣኔ ከሞላው ጎደል ከ500 ዓመተ ዓለም እስከ 1000 ዓመተ ምሕረት ድረስ ለ1500 ዓመታት በሰሜን ኢትዮጵያ ፣ በአረቢያ ና በአባይ ሸለቆ የተስፋፋ ዓለም አቀፍ ባህልና ሥልጣኔ ሲሆን ፣ ይህ የኢትዮጵያ ጥንታዊ ሥልጣኔ ለኢትዮጵያ ምድርና ሕዝብ በሙሉ ሥርዓተ መንግሥትን ፣ ፊደልን ጽሕፈትንና ሥነ ጽሑፍን ፣ የእርሻ ፣ የንግድ ፣ የአስተዳደርና የሕንፃ ጥበባትና ተግባራትን እንደ ብሔራዊ ቅርሶችና ውርሶች አውርሶዋል ። ቀጥሎ ከ330 ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ለአሥራ ሰባት ምዕተ ዓመታት የክርስትና ባህልና ሥርዓት ለኢትዮጵያ ምድርና ሕዝብ ብሔራዊ ይዘትና ቅርጽ ከሰጡ ታሪካዊ ኃይላት አንዱ ሆኖዋል ። በዚህ አኳያ ፣ በመካከለኛው ዘመን ዘውዳዊ የክርስቲያን መንግሥትና ንጉሠ የጉማ ፣ የቋንቋ ፣ የባህልና የሃይማኖት ልዩነት ሳያደርግ መላውን የኢትዮጵያ ምድርና ሕዝብ ለአያሌ ምዕተ ዓመታት በአንድ ማዕከላዊ ብሔራዊ ሥርዓት ሥር ያስተዳድር እንደነበር ይታወሳል ።

እንዲሁም ከሰባተኛው ምዕተ ዓመት እስከ ዛሬ ድረስ ለረጅም ዘመን የእስልምና ባህልና ሥርዓት የኢትዮጵያን ምድር ፣ ሕዝብና ታሪክ በዓለም ዓይነተኛ ከአደረጉ ታሪካዊና ባህላዊ ኃይላትና ሁኔታዎች አንዱ ሆኖዋል ። በዚህ አንጻር ፣ ከአሥራ ስድስተኛው ምዕተ ዓመት በፊት በምሥራቅና በደቡብ ኢትዮጵያ የነበሩ አያሌ የኢትዮጵያ ሱልጣኔቶች ማለትም እስላማዊ ሕዝቦችና መንግሥታት የአገሩ የክርስቲያን ዘውድና ንጉሠ ነገሥት ገባሮችና ዜጎች እንደነበሩ የዘመኑ ታሪክ የመዘገበው ነገር ነው ። በአሥራ ስድስተኛው ምዕተ ዓመት በአያሌ ውስጣዊና ውጫዊ ምክንያቶች የአገሩ ማዕከላዊ የንጉሠ ነገሥት ኃይልና ዘውዳዊ ሥርዓት ከኢትዮጵያ ንጉስ እስላማዊ መንግሥታት ጋር ከተደመሰሱ ወይም እየደከሙ ከሄዱ በኋላ የእስልምና ባህልና ሥርዓት በተለይ በምሥራቅና በደቡብ ክፍለ ሀገራት በሥፍራና በጊዜ እየተስፋፋ በመሄድ በአገሩ አንድ ታሪካዊና ባህላዊ ኃይል ለመሆን በቃ ።

የገዳ ሥርዓት በአሥራ ስድስተኛው ምዕተ ዓመት በደቡብ ከዛሬው ቦረና አውራጃ በአገር አቀፍ ፍለሳ ተነስተው በደቡብ ፣ በምሥራቅ ፣ በመሀል ፣ በሰሜንና በምዕራብ ኢትዮጵያ በተስፋፉበት ታሪካዊ ዘመን የኦሮሞ ዘላኖች የነበራቸው በአገሩ ታሪክ አዲስና ልዩ የሆነ ማህበራዊ ሥርዓት ነው ። በዘመኑ በገዳ ሕግ ፣ ባህልና ሥርዓት የኦሮሞ ወንድ የሕብረተሰቡ አባሎች ከሕፃንነት ጀምረው ሙጫ ፣ ኢልማ ፣ ጉርባ ፣ ቁንዳለ ፣ ሉባና ገዳ ማለትም ሕፃን ልጅ ፣

ወጣት፣ ጉልማሳ፣ ዕጮ ተሞጊና ተሞጊ አዝማች ተብለው በስድስት ተከታታይ በመደብ ሳይሆን በጾታ ፣ በዕድሜና በትውልድ ክልሎች ወይም ዘመናት ተመድበው በተግባራዊ ልምድ ለ48 ዓመታት ጦርነት ዘመቻና ወረራ ይግሩ ነበር ። በዚህ ጉግዊ ባህልና ሥርዓት መሠረት ከ40 እስከ 48 ዕድሜ ክልል የሚገኙ የኦሮሞ ወንዶች ለስምንት ዓመት ጊዜ የሕብረተሰቡን የአመራር ሥልጣንና ተግባር በመያዝ ያለፈው ትውልድ ያልደረሰበትን አገርና አካባቢ በወረራ ሄዶ መያዝ የሥርዓቱ ባህላዊ ሕግና ግዴታ ነበር ። በዚህ በገዳ ሕግና ሥርዓት እየተመሩ የኦሮሞ ዘለኖች ከ1520 እስከ 1600 ድረስ በ80 ዓመታት ጊዜ ውስጥ ብቻ በደቡብ፣ በምሥራቅ፣ በመሀል በሰሜንና በምዕራብ ኢትዮጵያ ዘውዳዊ የንጉሥ ነገሥቱን ማዕከላዊ መንግሥትና ሥልጣን ጭምር በከፍተኛ ዕድገት ደረጃ የተደራጁ አያሌ አገሮችን ሕዝቦችንና ንዑስ መንግሥታትን በጦርነት በማሸነፍ በመላው አገሩ በፍለሳና በሰፈራ ተስፋፉ ።

በሌላ በኩል በዚያን ዘመን የኦሮሞ ዘላኖች ባዕዳን ግለሰቦችንና ጉግዎችን በልዩ ጉግዊና ባህላዊ ሥነ ሥርዓት የራሳቸው አካሎችና አባሎች አድርገው የሚቀበሉአቸው ጉዲፈቻና ሞጋሳ የተባሉ ሁለት ማህበራዊ ሕጐችና ሥርዓቶች ነበሩአቸው ። በአጭሩ በአሥራ ስድስተኛውና በአሥራሰባተኛው ምዕተዓመታት የኦሮሞ ዘላኖች በጉዲፈቻና በሞጋሳ ሕጐችና ሥርዓቶች በብዙ አካባቢዎች ኢየሌ ነዋሪ ሕዝቦችን እንደ ራሳቸው ሰዎች በመቀበልና በማዋሀድ በአጭር ታሪካዊ ዘመን በአገሩ የራሳቸውን የጉግ ቁጥር አበዙ ። በሌላ በኩል በሰፈሩበት አካባቢ ሁሉ የነዋሪ ሕዝቦች ባህልና የግብርና ተግባር በመማር እንዲሁም የእስልምናና የክርስትና ሃይማኖቶችንና ሥርዓቶች በመቀበል በዘመኑ በታሪካዊ ዕድገት በዝቅተኛ ደረጃ የነበሩ የኦሮሞ ሰዎች ራሳቸው በባህላዊ ለውጥና ዕድገት ከአካባቢ ሕዝቦች ጋር እየተዋሀዱ ሄዱ ።

ከዚህም የተነሣ ዛሬ ምንም አንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይ ቋንቋ ቢናገሩ በልዩ ልዩ ክፍለ ሀገራት የሚኖሩ የኦሮሞ ብሔረሰብ አባሎች በባህል፣ በመልክና በጠባዩ ከአካባቢ ሰዎች ለምሳሌ በወሎ፣ በጐንደር ፣ በጐጃምና በሸዋ ከአማሮች በባሌ፣ በሐረርጌና በምሥራቃዊ ወሎ ከሱማሌና ከአፋር ሰዎች በደቡብ ሸዋ በአርሲና በምዕራባዊ ባሌ ከሀዲዎች በወለጋ፣ በከፋና በኢሉባቡር ደግሞ ከአካባቢው ነዋሪዎች ልዩነት አይታይባቸውም ።

በዚህ ታሪካዊና ባህላዊ ምክንያት "ገዳ" የተባለው የኦሮሞዎች ጥንታዊና ማህበራዊ ሥርዓት በአገሩ ረጅምና ውስብስብ ታሪክ ከአክሱማውያን ሥልጣኔ፣ ከክርስትናና ከእስልምና ጋር ለኢትዮጵያ ብሔረሰቦች ብዛትና አንድነት ታሪካዊና ባህላዊ ሁኔታዎች ከፈጠሩ ኃይላት አንዱ ነው ለማለት ይቻላል ።

## 1.ሐ. በጦር አበጋዞች ዘመን የተነሱ የአገሩ ሦስት ዋና ፖለቲካዊ ማዕከላትትና ኃይላት

ከአገሩ ታሪካዊ ዕድገትና ሂደት አንፃር ሲታይ፣ በአሥራ ስድስተኛው ምዕተ ዓመት በደቡብ፣ በምሥራቅ፣ በመሀልና በምዕራብ ኢትዮጵያ የገባር አገሮች፣ መንግሥታትና ክፍለ ሀገራት ጦርነትና የኦሮሞዎች አገር አቀፍ ፍለሳ የንጉሥ ነገሥቱን ማዕከላዊ የዘውድ ሥርዓትና ሥልጣን ከደመሰሱት ወይም ካዳከሙት በኋላ እስከ 1850 ድረስ በሚቀጥሉት ሦስት ምዕተ ዓመታት ውስጥ



በአገሩ በየአካባቢው አያሌ የባላባቶችና የጦር አበጋዞች ሥርዓቶችና ማዕከላት ተፈጠሩ ። ከእነዚህ ንዑስ ባላባታዊ መንግሥታትና ግዛቶች ሦስቱ ማለትም ጐንደር በሰሜናዊ ምዕራብ፣ ትግራይ በሰሜን ሸዋ በደቡብ በተለይ እያንዳንዳቸው የባላባቶችንና የጦር አበጋዞችን ዘመንና ሥርዓት ደምስሰው መላውን የኢትዮጵያ ምድርና ሕዝብ በአንድ ማዕከላዊ መንግሥትና ሥርዓት ለማደራጀትና ለመምራት የሚችሉ ፖለቲካዊ ኃይላትና ማዕከላት ሆነ አደጉ ።

ነገር ግን ከሦስቱ ከ1696 ጀምሮ በአገሩ ስትራቴጂያዊ እምብርት በሆነ ሥፍራና አካባቢ የተነሳው የሸዋ ንዑስና ተራራማ መንግሥት ከሌሎች የበለጠ ጠንካራ የሆነ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የጦር ድርጅቶችና መሣሪያዎች ነበሩት ። ይህም በሦስቱም ማዕከላትና ኃይላት መካከል የነበረው ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ወታደራዊ የዕድገት ደረጃ ልዩነት በኋላ በዘመነ ኢምፔሪያሊዝም የኢትዮጵያ ምድርና ሕዝብ እንደገና በአንድ ማዕከላዊ መንግሥት ሥር በሚደራጅበት ጊዜ ግልጽና ገሃድ ሆኖ እንደሚታይ ከዚህ በታች ግጤን ነው ።

## 2. የኢትዮጵያ የማዕከላዊ መንግሥት ግምባታ ከ1850 እስከ 1966

### 2. ሀ. የማዕከላዊው መንግሥትና የብሔራዊ ሥርዓት ምሥረታ

ከዚህ በላይ እንደተገለጸው፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድ ማዕከላዊ የፖሊቲካ ሥርዓትና አመራር ሳይኖረው በአያሌ ባላባቶችና በጦር አበጋዞች እጅና ግዛቶች ተከፋፍሎ ሲኖር በአሥራ ዘጠነኛው ምዕተ ዓመት ከቀይ ባህርና ከአባይ ሸለቆ ጠረፎች የወራሪዎችና የኢምፔሪያሊስቶች አደጋ በብሔራዊ ህልውና ነፃነትና አንድነት ላይ ተሰነዘረበት ። በዚህ ወሳኝ ዘመን የኢትዮጵያን ምድርና ሕዝብ ከወራሪዎችና ኢምፔሪያሊስቶች ጥፋት የሚያድነው ብቸኛ መንገድና መሣሪያ የአገሩ ብሔራዊና ፖለቲካዊ አንድነት ሆነ ። ስለዚህ የኢትዮጵያ ባላባታዊ መሪዎችና ሕዝብ በየአካባቢው አንደኛ፣ አገሩን በአንድ ማዕከላዊ መንግሥትና ብሔራዊ ግዛት ሥር ለማደራጀት፣ ሁለተኛ፣ የአገሩን ብሔራዊ ጠረፍ፣ ህልውና፣ ነፃነትና አንድነት ከወራሪዎችና ከኢምፔሪያሊስቶች ለማዳን ወሳኝ የሆነ ብሔራዊና ታሪካዊ ትግል ጀመሩ ።

በዚህ ታሪካዊ ዘመንና ተግባር ከ1845 እስከ 1868 ድረስ በ23 ዓመታት የአዲሱ የኢትዮጵያ ማዕከላዊ መንግሥት መሠረቱ በዳግማዊ ቴዎድሮስ ተጀመረ ። ቀጥሎ ከ1871 እስከ 1889 ድረስ በ18 ዓመታት አጼ ዮሐንስ የግብጽና የደርቡሽ ወራሪዎችን በጉንዳት፣ በጉራዕና በመተማ ጦር ሜዳዎች አሸንፈው በመመለስ በቴዎድሮስ የተጀመረውን የኢትዮጵያን ማዕከላዊ መንግሥት ብሎም ብሔራዊ ነፃነትና አንድነት ከፍተኛ ሕይወትና ንብረት በመሰዋት ከውጭ አደጋ አዳኑት

ይህ ሁሉ ሲሆንና ሲባል፣ አጼ ቴዎድሮስ ከጐንደር አጼ ዮሐንስ ደግሞ ከትግራይ ከ1845 እስከ 1889 ድረስ በተከታታይ ለ44 ዓመታት ያካሄዱትን ታሪካዊ የአገር ግምባታ ትግል ከመቅደላናከመተማጦርሜዳዎችባሻገር ከግቡ ለማድረስ የማያስችሉ ድርብርብ አካባቢያዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና ወታደራዊ ችግሮች አጋጠሙአቸው ።

በዚህ አኳያ ፥ አንደኛ ፥ ከ1531 ጀምሮ ለምዕተ ዓመታት በአካባቢው የተካሄዱ የሃይማኖት ፥ የፍለሳ ፥ የጐሣ ፥ የነገሥታት ፥ የመሳፍንቶች ፥ የእርስ በርስ የግዛትና የሥልጣን ጦርነቶች በሰሜን ኢትዮጵያ ቋሚ የሆነ የኢኮኖሚና የፀጥታ ችግር አስከትለው ነበር ። በዚህ ምክንያት አጼ ቴዎድሮስና አጼ ዮሐንስ በሰሜን ኢትዮጵያ በተከታታይ የጀመሩትን የአገር ግምባታ ትግል ከግቡ እንዳያደርሱ ከፍተኛ የሆነ የኢኮኖሚችግርነበራቸው ።ሁለተኛ ፥ የጠረፍወራሪ ዎችና የኢምፔሪያሊዝም ወኪሎች ለአጼ ቴዎድሮስና ለአጼ ዮሐንስ ውድቀት የየራሳቸውን አስተዋጽኦ አደረጉ ።

አጼ ቴዎድሮስና አጼ ዮሐንስ በዘመነ ኢምፔሪያሊዝም የኢትዮጵያን ማዕከላዊ መንግሥትና ብሔራዊ ሥርዓት ለመገንባት የነበሩአቸው ብሔራዊ የአገር ግምባታ ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች ከዚህ በላይ በተጠቀሱት ውስጣዊና ውጫዊ ምክንያቶች ከራሳቸው ጋር በቀደም ተከተል በመቅደላና በመተማ ጦር ሜዳ ዎች በ1868 እና በ1889 ከፈረሱ በኋላ ከ1889 እስከ 1909 ድረስ ባለው ፥ የ20 ዓመታት ጊዜ ውስጥ ዳግማዊ ምኒልክ በአገር አቀፍ ደረጃ አዳዲስ የመሬት ፥ የሥራ የግብር ፥ የጦር ፥ የንግድ ፥ የመገናኛ ፥ የፖለቲካ ፥ የአስተዳደርና የከተማ ድርጅቶችን ፥ ሥሪቶችንና ሥርዓቶችን በሥፍራና በጊዜ በማስፋፋት ለአዲሱ ማዕከላዊ መንግሥትና ሥርዓት ጥንካሬና ዕድገት ወሳኝ ድርጅታዊ መዋቅርና አስተዳደራዊ አመራር ሰጡ ።

በአገሩ ታሪክ የምኒልክን ፖሊሲና ዘመን እንደዚህ ወሳኝና ዘላቂ ያደረጉ ታሪካዊ ፥ ኢኮኖሚያዊ ፥ ፖለቲካዊ ፥ ወታደራዊና ፥ ዲፕሎማሲያዊ ሁኔታዎች ምክንያቶችና መሣሪያዎች ብዙና መሠረታዊ ናቸው ። አንደኛ አጼ ምኒልክ በ1696 ነጋሢ ክርስቶስ በተባለው በአንድ ሸዋ ባላባት የተፈጠረ በኢትዮጵያ ታሪክ በዓይነት አዲስ የሆነ "የጋሻ መሬት" ወይም "የመንግሥት መሬት" የሚባል የመሬት ይዞታ ሕግና ሥሪት ነበራቸው ። በአጭሩ በዚህ በነጋሢ ክርስቶስ ሕግና ሥርዓት መሠረት ፥ የሸዋ ባላባታዊ መንግሥት ከአካባቢው ሕዝብ በመግሪያ ኃይል የሚይዘው መሬት የመንግሥት ሀብትና ንብረት ሲሆን ነዋሪዎቹ ደግሞ ከሥፍራ የመንቀሳቀስ ምርጫና ፈቃድ የሌላቸው የመንግሥት ገባሮችና አገልጋዮች ናቸው ። እንደ አውሮፓውያን ዘመን ከ1865 እስከ 1909 ድረስ ይህ የነጋሢ ክርስቶስ የመሬትና የገባር ሕግ በአጼ ምኒልክ መንግሥትና በዘመኑ ሻለቆች ተብለው በሚጠሩ የጦር መሪዎችና አገረ ገዥዎች አማካይነት በዛሬ ወሎ ሸዋ ፥ ሐረርጌ ፥ አርሲ ፥ ባሌ ፥ ሲዳሞ ፥ ጋሞጐፋ ፥ከፋ ፥ ኢሉባቡርናወለጋ ክፍለ ሀገራት ዋናው የመሬት ሥሪት ሆኖ ተስፋፋ ። ብሎም የዘመኑና የሥርዓቱ ወሳኝ የኢኮኖሚ መሠረትና መሣሪያ ሆነ ።

ሁለተኛ ፥ ከነጋሢ ክርስቶስ ጊዜ ጀምሮ በሸዋ አገርና መንግሥት "ገንደ በል" የሚባል መንግሥታዊ ሰፋሪ ጦር ወይም ወታደር ነበር ። እንደ ጋሻ መሬትም ደግሞ የገንደበልጦር "ነፍጠኛ" በሚል አዲስ ስምና ድርጅት በምኒልክ መሪነትና ዘመን ከዚህ በላይ በተጠቀሱት አሥር ክፍለ ሀገራት በነዋሪነት ሰፍሮ አገሩንና መንግሥቱን ማገልገል ጀመረ ። ሦስተኛ ፥ አጼ ምኒልክና የጦር አለቆቻቸው ከዚህ በላይ በተጠቀሱት አሥር ክፍለ ሀገራት ብዙ ከተሞች በመመሥረት በአስተዳደር ፥ በመንገድና በንግድ ከአዲስ አበባ መዲና ጋር አገናኙ አቸው ። አራተኛ ፥ በተጨማሪም ዳግማዊ ምኒልክ በዘመነ መንግሥታቸው መጨረሻ ከአውሮፓ የሚኒስቴሮች ሹመትና ምክር ቤት ወደ ኢትዮጵያ በማስገባት በአገሩ ታሪክ አዲስ የሆነ መንግሥታዊ የአስተዳደር ሕግና ሥርዓት ጀመሩ ።



መንጠረዥ 4

ከ1865 እስከ 1900 ድረስ የኢትዮጵያ ንዑስ መንግሥታት ፤ ብሔረሰቦችና ክፍለ ሀገራት በምኒልካዊ ማዕከላዊ መንግሥት የሆኑበት ጊዜ (ጊዜው እንደአውሮፓ ዘመን)

| ተራ ቁ. | የአገሮችና የብሔረሰቦች ስም | ጊዜ በዓመት | ተራ ቁ. | የአገሮችና የብሔረሰቦች ስም | ጊዜ በዓመት |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የሸዋ አገር | 1865 | 27 | ጉሊሷ | 1897 |
| 2 | ወሎ | 1867—1876 | 28 | የዛራ አገር | 1890—1894 |
| 3 | ቱላማ | 1879—1882 | 29 | የኩሉ አገር | 1890—1894 |
| 4 | ሜጫ | 1882—1886 | 30 | የኮንታ አገር | 1890—1894 |
| 5 | ወለጋ | 1882—1886 | 31 | የወላይታ አገር | 1890—1894 |
| 6 | የጉማ አገር | 1879—1882 | 32 | የኩሻ አገር | 1894 |
| 7 | የጐማ አገር | 1879—1887 | 33 | የቦርዳ አገር | 1894 |
| 8 | የሊሙ — እናርያ አገር | 1879—1887 | 34 | የጐፋ አገር | 1894—1895 |
| 9 | የጌራ አገር | 1879—1887 | 35 | ባኮ ፤ ገለብ | 1898 |
| 10 | የጅማ አገር | 1882 | 36 | ማጂ | 1898 |
| 11 | አርሲ | 1882—1886 | 37 | የጋሞ አገር | 1894—1895 |
| 12 | ኢቱና የሐረር ከተማ | 1885—1887 | 38 | ኮንሶ | 1897 |
| 13 | ባሌ | 1890—1891 | 39 | ቡርጂ | 1897 |
| 14 | ቦረና | 1897 | 40 | ሲዳማ ፤ ጌዴኦ (ደራሳ) | 1890—1891 |
| 15 | ጉራጌ | 1875—1889 | 41 | ጉጂም | 1889 |
| 16 | ሊቢዶ (ማረቆ) | 1891 | 42 | ቤጌምድር ፤ ላስታ ፤ ሰሜን | 1889 |
| 17 | አባባ | 1890 | 43 | ትግራይ | 1889—1899 |
| 18 | ሀዲያ | 1875—1890 | 44 | አጋዴን | 1890—1897 |
| 19 | ከምባታ | 1891 | 45 | ኢማ | 1890—1897 |
| 20 | የአጃንጂራ (የጀንጀሮራ) አገር | 1894 | 46 | የአውሳ (የአፋር) አገር | 1896 |
| 21 | ቦሻ (ጋሮ) | 1890—1894 | 47 | ሳሆ | 1896 |
| 22 | የከፋ አገር | 1879—1897 | 48 | ጉባ | 1898 |
| 23 | ቤንሶ | 1897 | 49 | ጉንዛ | 1898 |
| 24 | ጋራ ፋርዳ | 1897 | 50 | በርታ | 1898 |
| 25 | ጊሚራ | 1897 | 51 | ኑር ፤ አኘዋክ ፤ ማጀንገር | 1897 |
| 26 | የኮሻ አገር | 1897 | 52 | ማስታወቂ፤ኤርትራ ከቀይ ባህር ጋር | 1952 |

በአጭርና በአጠቃላይ ፣ ከዚህ በላይ በተገለፁ ኢኮኖሚያዊ ፣ ፖለቲካዊ፣ ወታደራዊና አስተዳደራዊ ድርጅቶችና መሣሪያዎች ፣ ምንም በሰሜንና በምሥራቅ የኢትዮጵያ አራት የጠረፍ ግዛቶች ከአያሌ ብሔረሰቦች ጋር "ኤርትራ" ፣ "የፈረንሳይ ሱማሌ" "የእንግሊዝ ሱማሌ" ፣ እና "የኢጣሊያን ሱማሌ" ተብለው በቀጥታ በኢምፔሪያሊስቶች እጅ ቢወድቁ ከዚህ በላይ ሠንጠረዥ 4 በሥፍራና በጊዜ እንደሚያሳየን ፣ አጼ ምኒልክ መላውን የኢትዮጵያ ምድርና ሕዝብ በአንድ ጠንካራ ማዕከላዊ መንግሥትና ብሔራዊ ሥርዓት ሥር ለማደራጀት ቻሉ።

## 2.ለ. የጉልተኛና የገባር መደቦች ዕድገት ፣ ልዩነትና ትግል

### 2.ለ.1. የጉልተኛው መደብ ኃይልና ድል

በዘመነ ኢምፔሪያሊዝም በከፍተኛ ሕይወትና ንብረት መስዋዕት የተገነባው የኢትዮጵያ ማዕከላዊ መንግሥትና ሥርዓት ለሁለት ተጻራሪ ማለትም ለጉልተኛና ለገባር መደቦች ዕድገት ፣ ልዩነትና ትግል ታሪካዊ ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ መሠረት ፣ መነሻና መድረክ ሆነ ። በዚህ አንፃር ፣ በምኒልክ ፖሊሲና ዘመን ለአገርና ለመንግሥት አገልግሎት በመንግሥት ስምና ሥር የተያዘው የሕብረተሰቡ መሬት ከገባር ጉልበት ጋር ለጉልተኞች ማለትም ለመንግሥትና ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች ፣ ሠራተኞች ፣ ባለሥልጣኖችና አገልጋዮች በባለቤቱ ግል ፍላጐትና ፈቃድ የሚሸጥ የሚለወጥና የሚወረስ የግል ሀብትና ንብረት ገና አልነበረም ።

ነገሩን በአጭርና በጥቅል ለማስቀመጥ በምኒልክ ፖሊሲና ዘመን ከዚህ በላይ የተገለፀው የነጋሚ ክርስቶስ የመሬትና የገባር ሥርዓት በተስፋፋባቸው በአሥሩ በወሎ ፣ በሸዋ ፣ በሐረርጌ ፣ በአርሲ ፣ በባሌ ፣ በሲዳሞ ፣ በጋሞ ጐፋ ፣ በከፋ ፣ በኢሉባቡርና በወለጋ ክፍለ ሀገራት የሕብረተሰቡ መሬት በሦስት ዋና ክፍሎች ተከፈለ ። አንደኛ ፣ ከመሬቱ የተወሰነ ክፍልና መጠን "የገባር መሬት" ተብሎ ለአራሹና ለአምራቹ ገበሬ በግል ይዞታ ተሰጠ ። የዘመኑና የሕብረተሰቡ ዋናው አምራቹ ገበሬ ማለትም ገባር በግል ይዞታ የተሰጠውን "የገባር መሬት" እንደግል ሀብቱ ለመያዝ ፣ ለመጠቀም ፣ ለመሸጥ ፣ ለመለወጥና ብሎም ለልጆቹ ለማውረስ በመንግሥቱ ወይም በንጉሡ ትእዛዝ ፣ ሕግና መመሪያ መሠረት ለአገሩ ማለትም ለመንግሥት ፣ ለጦርና ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች ፣ ሠራተኞች ፣ አላፊዎች ፣ ሹማምንቶችና አገልጋዮች በዓመት በተወሰነ ጊዜ አረምንም ክፍያና ውለታ የጉልበት ፣ የምግብ ፣ የምርት ፣ የአሥራት ፣ የቀረጥና የግብር አገልግሎት ይሰጣል ።

ገባሩ "የገባር መሬት"ባለቤትና ተጠቃሚ ሆኖ ጉዳዩ ለሚመለከተው ክፍል የሚፈለግበትን የጉልበትና የገንዘብ አገልግሎት ባይሰጥ ግን ይታሠራል ይገረፋል ። በሆነው ሁሉ ምክንያት የሚፈለግበትን አገልግሎት ለመስጠት ባይችል መሬቱ "ግብረጠል" መሬት ተብሎ በመንግሥት ተወርሶ ግብርና አገልግሎት ለመስጠት ለሚችል ገባር ይሰጣል ። መሬቱ የተወሰደበት ገባር ለመንግሥት ምንም የግብርና የአገልግሎት ግዴታ ሳይኖርበት በሌላ ሰው መሬት



በጢሰኝነት ሰፍሮ የጉልበቱን ምርትና ፍሬ በውላዊ ስምምነት ለባለመሬቱ እየሰጠ "በነፃነት" ይኖራል ። ባለመሬቱ ጢሰኛውን ቢፈልግ ከመሬቱ ይነቅለዋል እንጂ ሊያስረውና በግድ ሊያሰራው አይችልም ። በአጭሩ በምኒልክ ፖሊሲና ዘመን ገባር ባለመሬት ሲሆን ጢሰኛው ግን በውላዊ ስምምነት የሰውን መሬት እያረሰ የሚኖር የግል መሬት የሌለው አርሶ አደር ነበር ።

ሁለተኛ ፣ ከዚህ በላይ በተጠቀሱ ክፍለ ሀገራት ከሕብረተሰቡ መሬት የተወሰነ ክፍልና መጠን "የባላባት መሬት" ተብሎ ለጐሣና ለሀገር መሪዎችና ተጠሪዎች በግል ይዞታ ተሰጠ ። የጐሣ መሪዎችና የሀገር ሽማግሌዎች "የባላባት መሬትን" በግል ይዞታ ለመያዝ ፣ ለመጠቀም ፣ ለመሸጥ ፣ ለመለወጥና ለልጆቻቸውና ለዘመዶቻቸው እንደፈለጉ ለማውረስ የአካባቢው ተጠሪዎችና ተወካዮች በመሆን የመንግሥቱን ትእዛዝ ፣ ሕግና ደምብ በገባሮች ላይ ተፈጻሚና ተግባራዊ ማድረግ አለባቸው ። ነገር ግን ይህን ማድረግ ባይችሉ ወይም ለማድረግ ፈቃደኞች ባይሆኑ "የባላባት መሬታቸው" በመንግሥት ተወርሶ ለሌላ ባላባቶች ይሰጣል ።

ሦስተኛ ፣ የነጋሚ ክርስቶስ የመሬትና የገባር ሥርዓት በተመሠረተባቸው በወሎ ፣ በሸዋ ፣ በሐረርጌ ፣ በባሌ ፣ በአርሲ ፣ በሲዳሞ ፣ በጋሞ ጐፋ ፣ በከፋ ፣ በኢሉባቡርና በወለጋ ክፍለ ሀገራት ለገባሮችና ለባላባቶች በግል ይዞታ ያልተሰጠ የሕብረተሰቡ መሬት "የመንግሥት መሬት" ተብሎ በቀጥታ በመንግሥት ተያዘ ። ከዚህ ከመንግሥት መሬት "የማደሪያ መሬት" ፣ "የግንደበል መሬት" እና "የሰሞን መሬት" ተብሎ ከገባር ጉልበትና አገልግሎት ጋር ለተወሰነ አገልግሎት ዘመን የመሬቱን ፍሬና አበል ብቻ እንዲጠቀሙ ለመንግሥት ፣ ለጦርና ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሠራተኞች ፣ ባለሥልጣኖች ፣ ሹማምንቶችና አገልጋዮች ታደለ ። በአጭሩ በምኒልክ ፖሊሲና ዘመን "የማደሪያ መሬት" "የግድበል መሬት" እና "የሰሞን መሬት" ለአገርና ለመንግሥት አገልግሎት እንዲሆን በመንግሥት ስምና ሥር የተያዘ የሕብረተሰብ ብሔራዊ ሀብትና ንብረት ሲሆን ለመንግሥት ፣ ለጦርና ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች ፣ ሠራተኞች ፣ ባለሥልጣኖችና አገልጋዮች የሚሸጥ የሚለወጥና የሚወረስ የግል ሀብትና ንብረት ፈጽሞ አልነበረም ።

ነገር ግን ከምኒልክ ዘመነ መንግሥት በኋላ የኢትዮጵያ ጉልተኛ ሚኒስቴሮች ፣ የመንግሥት ባለሥልጣኖች ፣ የጦር መሪዎች ፣ ያገር ገዥዎችና የቤተ ክርስቲያን ባለሥልጣኖች በመደባዊ አንድነትና ስምምነት የአገሩን በትረ መንግሥት በወል ይዘው በፊት በምኒልክ ፖሊሲና ዘመን በመንግሥት ስምና ሥር የተያዘውን የሕብረተሰቡን መሬት የግል ይዞታና ንብረት ብሎም የአምራቹን የገባር መደብ ለጉልተኛው መደብና መንግሥት ሕጋዊ ተገዥና አገልጋይ የሚያደርግ ሕግና ሥርዓት መፍጠር ጀመሩ ።

በዚህ ረገድ ፣ አንደኛ ፣ አጼ ምኒልክ እንደ አውሮፓውያን ዘመን በጥቅምት 26 ቀን 1907 የኢትዮጵያን የመጀመሪያ የሚኒስትሮች ጉባኤ ተቋም ማቋቋማቸውን በታሪካዊ መግለጫ ለአገሩ ሕዝብና በአዲስ አበባ ለሚኖሩ ለውጭ አገር መንግሥታት ተወካዮችና ዜጎች በይፋ አስታወቁ ። ከዚያ በኋላ በአራተኛው ቀን ማለትም በጥቅምት 30 ቀን አጼ ምኒልክ በአገሩ ታሪክ ለመጀመሪያው ጊዜ በአዲስ አበባ ከተማ መሬት የግል ሀብትና ንብረት በመሆን በአገሩ ተወላጆችና በውጭ አገር ዜጎችም እንዲሁም በመንግሥት እንደ ሸቀጥና የንግድ

ዕቃ የሚሸጥበትንና የሚገዛበትን አዲስ ሕግ በአገሩ ጉልተኞችና በውጭ አገር ዜጐች ግፊትና ተጽዕኖ በአዋጅ ማውጣታቸው ይታወሳል ።[1]

ሁለተኛ ፣ የኢትዮጵያ የጉልተኛ ሚኒስቴሮች ጉባኤ በሐምሌ 8 ቀን 1908 ባካሄደው በመጀመሪያው ስብሰባ ላይ በአገሩ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ አዲስ የፍርድ ፣ የዳኝነት ፣ የፍትሐ ብሔር ፣ የወንጀል ፣ የግል መሬት ይዞታ ፣ የመንግሥት ሀብት ፣ የግል ሀብትና ውርስ ሕጐችና ደምቦች ደነገገ ። የጉልተኛው መደብና መንግሥት አዲሱ የ1908 የመሬት ይዞታና የውርስ ሕግ በግልጽ እንደ አስቀመጠው ፣

"በወንጀል እየተያዘ መሬቱን የሚነቅል ሰው ሁሉ ወንጀልም ቢገኝበት በከብቱና በሰውነቱ ይቀጣ እንጂ መሬቱን አይነቀል ። ነገር ግን ነፍስ ገድሎ በመንግሥቱ ክፉ ሥራ የሠራ ይነቀል ። ርስትም ማለት ያባት ፣ የናት መሬት ደግሞ በወርቁ የገዛው መሬት ነው እንጂ የመንግሥት መትከያ የሆነ አይደለም ደግሞ የመትከያም መሬት ቢሆን መንግሥት ርስት ያደረገለት ይረጋል ።

"መካንም የሞተ እንደሆን አባቱ እናቱ ገንዘቡንም ርስቱንም ይውሰዱ እንጂ ሹም አይወርስም ። እናት አባት እህት ወንድም የሌለው እንደሆነ ግን እስከ አራት ትውልድ ላለ ለቅርብ ዘመዱ ይሁን ። ደግሞም ከዘመዱ ለይቶ ለእገሌ ይሁን ብሎ የተናዘዘ እንደሆነ የተናዘዘለት ይውሰድ ። ከአራት ትውልድ ወዲያ የሆነ ግን ውርሱ ለሹም ይሁን ብለው ሥራት ሠሩ ። ይኸውም ምክር በመኳንንቱም በሠራዊቱም የተወደደ ሆነ ። በጃንሆይ ፈቃድ በነጋሪት በአደባባይ አዋጅ ተነገረ ።"[2]

ሦስተኛ ፣ በ1931 ሕገ መንግሥት የኢትዮጵያ የጉልተኛው መደብና መንግሥት መሪዎችና አባሎች ማለትም 23 ከፍተኛ መሳፍንቶች ፣ ካህናቶች ፣ መኳንንቶችና ሹማምንቶች በአጼ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መሪነት የኢትዮጵያን ምድርና ሕዝብ ከመንግሥት ሥልጣን ጋር ፍጹም የጉልተኛው መደብ ሀብትና ንብረት የሚያደርግ ሕግና ሥርዓት ደነገጉ ።

## 2. ለ. 2. የጉልተኛው መደብ ሕግና ሥርዓት

የጉልተኛው መደብ የሕገ መንግሥቱ የመጀመሪያ አንቀጾች የአገሩን ዙፋንና ዘውድ የቀዳማዊ ኃይሌ ሥላሴ ዘር ውርስና ቅርስ ሲያደርጉ ፣ አንቀጾች 34 35 ፣ 36 ፣ 37 ፣ 39 ፣ 74 እና 75 ደግሞ ለሌሎቹ ለጉልተኛው መደብ መሪዎ

1 C. P. Rosenfeld, *A Chronology of Menelik II of Ethiopia* (1976), p. 232;

"በአዲስ አበባ ከተማ ርስት መግዛት" ፣ በማህተመ ሥላሴ ፣ ዘከረ ነገር (1942) ፣ ገጽ 167—172 ።

2 ገብረ ሥላሴ (ጸሐፊ ትእዛዝ) ፣ ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ፣ (1959) ፣ ገጽ 334—336 ።



ችና አባሎች ከዚህ እንደሚከተለው የመሬትና የገባር ሀብት በግል ይዞታ ይሰጣሉ ። የሕገ መንግሥቱ አንቀጾች በገሃድ እንደአስቀመጡት ፣

አንቀጽ 2፣ የኢትዮጵያ መሬትም ፣ ሕዝቡም ፣ ሕጉም በጠቅላላው የንጉሠ ነገሥት ነው ።

አንቀጽ 3፣ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ከኢየሩሳሌም ንጉሥ ከሰለሞንና ንግሥተ ሣባ ከተባለችው ከኢትዮጵያ ንግሥት ከተወለደው ከቀዳማዊ ምኒልክ ነገድ ተያይዞ ከመጣው ከንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ዘር ከተወለደው ከቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ትውልድ እንዳይወጣ በሕግ ተወስኖአል ።

አንቀጽ 5፣ ንጉሠ ነገሥቱ የነጋሢ ዘር በመሆኑና ቅብዐ መንግሥት በመቀባቱ ክብሩ የማይቀነስ ፣ ማዕረጉ የማይገሰስ ፣ ኃይሉ የማይደፈር ሆኖ በቆየው ልማድ ባዲሱም ሕግ በሚገባው ክብር ሁሉ ይከበራል ፣ ክብሩንም ለመንካት በድፍረት የተነሣ ሰው በሕግ እንዲቀጣ ተወስኗል ።

አንቀጽ 15፣ ንጉሠ ነገሥቱ የመስፍንነትና ሌላም የክብር ስም ለመስጠት ርስት ጉልትም ለመትከል አዲስ ኒሻንም ለማውጣት ይችላል

አንቀጽ 34፣ በቅኝነትም በሌላም ለኢትዮጵያ በሚጠቅም አገልግሎት ከንጉሠ ነገሥቱ የመሳፍንትነት ማዕረግ የተቀበሉት ወደ ፊትም የሚቀበሉት ይህ አቅኚነትና አገልግሎት ከመሳፍንትነት ያደረሳቸው ስለ ሆነ ንጉሠ ነገሥቱ በምክር ቤት አስመስክሮ ያቆመውን ሕግ ለሥራቸው ሁሉ ዋና መሪ እያደረጉ የመስፍንነታቸውን አገር እንዲገዙ ሆኖ በሕግ ተወስኗል ።

አንቀጽ 35፣ ማንኛውም መስፍንና አገረ ገዥም ቢሆን ከንጉሠ ነገሥቱ በተቀበለው ሥልጣንና መብት ለኢትዮጵያ መተዳደሪያ ለመሆን ከንጉሠ ነገሥቱ የወጣውን ሕግና ደንብ ዋና መሪ እያደረገ የተሾመበትን እንዲገዛ በሕግ ተወስኗል ።

አንቀጽ 36፣ በቅኝነትም በሌላም ለኢትዮጵያ በሚጠቅም ሥራ አባቶቻቸው ያገለገሉ መሳፍንቶች ያቅኝ ያገልጋይ ባለውለታና የባለውለታ ልጆች መሆናቸውን ንጉሠ ነገሥቱ እያስመረመረ አባቶቻቸው እያቀኑ ከያዙት ላይ ለትውልድ የሚያልፍ የመስፍንነት ርስተ ጉልት ሊተክላቸው ይችላል ።

አንቀጽ 37፣ ደግሞ እንደዚሁ ባቅኝነትም በሌላም ለኢትዮጵያ በሚጠቅም ሥራ አባቶቻቸው ያገለገሉ መኳንንቶች ባላባቶች ያቅኝና ያገልጋይ ልጆች ሆነው እነሱም ራሳቸው ያገለገሉ መሆናቸውን ወደ ፊትም ለሥራ የሚችሉትን ንጉሠ ነገሥቱ እያስመረመረ ለትውልድ የሚያልፍ ርስተ ጉልት ሊተክላቸው ይችላል ።

አንቀጽ 38፣ መሳፍንቶችና አገረ ገዥዎች የዙፋኑና የዘውዱ አወራረስ በሕግ እንደተወሰነው ሆኖ ጸንቶ እንዲኖር የኢትዮጵያም አንድነቷና ነፃነቷ እንዳይጠፋ ፣ የንጉሠ ነገሥቱ ማዕረግ እንደተከበረ እንዲኖር በትጋት እንዲጠብቁ በሕግ ተወስኗል ።

አንቀጽ 39፤ መሳፍንቶች ካልጋ ወራሹ ቀጥለው መስፍን ከሆኑት ከነጋሢ ዘሮች ጋራ በማዕረግና በክብር ከሌሎች ባለማዕረጐች ይልቅ እንዲከበሩና እንዲታፈሩ በሕግ ተወስኗል ።

አንቀጽ 74፤ ንጉሠ ነገሥቱና የንጉሠ ነገሥቱ ቤተ ዘመዶች እስካሁን በጃ ቸው የነበረው ርስትና ገንዘባቸው ወደ ፊትም እንደ ሕዝቡ በገንዘባቸው የሚገዙት ርስት ሁሉ ስለ ርስት የቆመው ደንብ እየተጠበቀ ለራሳቸውም የሚጸና ለትውልዳቸውም የሚያልፍ እንዲሆን በሕግ ተወስኗል ።

አንቀጽ 75፤ እንደዚሁ መሳፍንቶችና አገረ ገዥዎች ሌላውም የኢትዮጵያ ተወላጅ የሆነ ሁሉ ማናቸውም ዓይነት ወንጀል ከሠራ በሕግ እንደተጻፈው ይቀጣል እንጂ እስካሁን በጁ የነበረውን ወደ ፊትም በገንዘቡ የሚገዛውን ርስቱን እንዳይነቀል በሕግ ተወ ስኗል ።

## 2. ለ. 3. የገባርና የጢሰኛ መደብ[3]

### 2. ለ. 3. 1. የገባር ሕግና ሥርዓት

ቁጥር 5349፤ የሻለቃ በግዛት ከሚያስተዳድርበት ሀገር ውስጥ ገባር ተቆጥሮ ሁለት እጅ ለሻለቃ አንድ እጅ ለመንግሥት ማድቤት እንዲ ሆን ከተከለለ በኋላ ከመንግሥት አስፈቅዶ ማዘዣ ሳይቀበል እመንግሥት ማድቤት ውስጥ ገብቶ መቀጫና ግብር ሊቀበል አይችልም ። ቢቀበልም ተቀብሎ የነበረውን ገንዘብ በደረሰኙ ተሳስቦ ሊመለስ ይገባዋል ።

ቁጥር 5463፤ አንድ ባላባት በሀገሩ ገባር ሳያስቆጥር መንግሥት በፈቀደለት ልክ ከሀያ ወይም ከአሥር አንድ ገባር በምርጥ የተፈቀደለት እንደሆነ ያንኑ ባለሲሶ የተፈቀደለትን ገባር ያው ባለርስት የሆነው ባላባት ግብሩን ይቀበላል እንጂ አገረ ገዥው ሊወስድበት አይገባም ።

ቁጥር 1063፤ መልከኛና መልከኛ በገባር ተጣልተው ገባሩ የተከሳሹ ገባር ነኝ ብሎ ቃሉን ቢሰጥ አንደኛው መልከኛ ውስጥ ሌላ መሬት ካለው በመሬቱ ልክ ሊገብር ይገባዋል እንጂ ገባርህ አይደለ ሁም ብሎ ተከራክሮ ቢረታ አንድነት ግብረአበር ሆኖ የተረ ታው መልከኛ መልከኝነቱን ገባሩም ርስቱን ሊነቅሉ አይገባ ቸውም ።

---

3 ከዚህ በታች የተጻፈው የገባርና የጢሰኛ ሥርዓት የተወሰደው በኢትዮጵያ ከጥንታ ውያን የፍርድ መዛግብት የተገኘና የተዘጋጀ የፍትሐብሔር ሕጋዊ ድርጅት በሚል አር ዕስት በአራት መጻሕፍት በ1945 ከተደራጀው ሕግ መጽሐፍ ሲሆን በዚህ የተጠቀሱት ቁጥሮች ደግሞ የሕጉ ቁጥሮች ናቸው ። ሕጉ በጠቅላላው ከ1 እስከ 7276 ተራ ቁጥሮች አሉት ።





የኢትዮጵያ የገባር ዘመንና ሥርዓት
From Borelli, *Èthiopte Meridionale* (1980)

ቁጥር 5033፥ ለንጉሠ ነገሥቱ የሚገባውን ግብር መንግሥት ለሌላ ሰው ከሰጠው ለመንግሥት የሚገባውን ግብር ገባሮች ይሰጣሉ እንጂ እንቢ ማለት አይገባቸውም ።

ቁጥር 5435፥ የገባር መሬት ያለው ሰው ብዙ ጊዜ ለንጉሠ ነገሥቱ ሲገብር ቢኖርም ለመንግሥት የሚገባውን ግብር ለሻለቃም ሆነ ለሌላ ሰው ቢሰጥ ገባሩ ለታዘዘለት ሰው ግብሩን ይሰጣል እንጂ ለንጉሠ ነገሥቱ ግምጃ ቤት ካልሆነ በቀር አልገብርም ማለት አይገባም ።

ቁጥር 5363፥ የገባር መሬት ያለው ለባለ መሬቱ ሶስት ጊዜ ጭነት መጫን፥ አንድ ጊዜ አንድ ሸክም እንጨት አምጥቶ እከተማ መስጠት፥ አራተኛ በሰኔ ለንጉሥ ጭነት መጫን አንድ ሸክም እንጨት መስጠት ስለአለበት በታዘዘ ጊዜ እህሉን ተቀብሉ ወይም አልቀበልም ብሎ ሳይጭን እንጨቱንም ሳይከፍል የከረመ እንደሆነ ለባለጉልቱ ዳፈን ይሰጣል ። እንጨቱንም እህሉን ከነውዝፉ ይሰጣል እንጂ ሳይጭን መከረሙን ካመነ ወይም ከተመሰከረበት ዳፈን አልከፍልም ብሎ ሲከራከር አይገባውም ።

ቁጥር 5370፥ የገባር መሬት ያለው ሰው በዓመት ባመቱ ለተፈቀደለት የሻለቃ ወይም ለባለ ጉልት ግር ሲሠፍር ከአንድ ቁና የሩብ ግማሽ በአንድ ጉንዶ በአንድ ሩብ የደብዳቤ ጽሐፊ ሊሰጥ ይገባዋል እንጂ በአንድ መልከኛ አንድ ሩብ ብቻ መክፈል አይገባውም

ቁጥር 5320፥ በመሬቱ ጭቃ ሹም ሆኖ የመንግሥት ከብት እገባር ዘንድ እንዲመራ ከበላይ ታዞ ለገባሩ ከመራ በኋላ የተመራው ከብት ከገባሩ እጅ ቢጠፋ የጣለው ገባር ኃላፊ ሆኖ ይከፍላል እንጂ በጭቃ ሹምነቱ ከበላይ ባለሥልጣን ታዞ የመራ ጭቃ ሹሙ ሊከፍል አይገባውም ።

ቁጥር 5680፥ ገባር በገባርነቱ ዘብ እንዲጠብቅ ጭቃ ሹም አዞት አዛዥ ታዛዥ በተካካዱበት የትእዛዝ ነገር ጭቃሹም ለማዘዝ ሲሄድ ምስክር እየያዘ አይዞርም ራሱ ጭቃሹሙ ምስክርነት ብቻ በቂ ይሆናል እንጂ ሌላ ምስክር አያስፈልግም ።

ቁጥር 5477፥ ለቤተ ክህነት ሆነ ለሻለቃ ግብር የሚገብሩ ገባሮች እህሉን በሚያስረክቡበት ጊዜ መንግሥት ባወጣው ባሥራት ቁና ይሰጣሉ እንጂ ተቀባዮቹ በፈቀዱት ለመጠየቅ አይችልም ።

ቁጥር 5476፥ ለቤተ ክርስቲያን የሚገብሩ ገባሮች ገዳሙ ያለበት ዕርቀቱ በጣም የበዛ ካልሆነ በቀር እገዳሙ ድረስ ይጭናሉ እንጂ እፋፉ ከደረስን እገዳሙ አለበት ድረስ አንወስድም ለማለት አይችሉም ።

ቁጥር 5398፥ የገባር መሬት ያለው ሰው ግብር የሚከፍልበትን ጊዜ አሳልፎ ሲከፍል የዳፋን ጭምር መክፈል ይገባዋል ።

ቁጥር 5319፥ እየገበረ መሬት የሚበላ ሰው አቅም ወይም ገንዘብ ከማጣት የተነሣ ግብሩን ለመገበር አልችልም ለቅቄአለሁ ብሎ ለመልከኛው ሆነ ለባላባቱ መሬቱን የለቀቀ እንደሆነ እየገበረ የሚበላ ቢገኝ በፈቃዱ ይተከልበታል ቢታጣ ግን በጠፍነት በባለሥልጣን እጅ መሬቱ ይቆያል እንጂ ግብሩን አልችልም ብሎ መሬቱን ከለቀቀ በኋላ ያለውን ግብር ሊከፍል አይገደድም ።



ቁጥር 5385፥ ማናቸውም ሰው በገባር መሬቱ ግብር መገበር አቅቶት መሬቱን ለመንግሥት ለቆ መሬቱ በጠፍነት ሲኖር መንግሥት ለሌላ ሰው ከሸጠው ወይም ከሰጠው በኋላ ልዩ የሆነ የንጉሠ ነገሥቱ ትእዛዝ ከሌለበት በቀር መሬቱን በፈቃድ ለመውሰድ አይችልም ።

ቁጥር 5485፥ የገባር መሬት ያለው ሰው አልችል ብሎ የሚለቅ ሲሆን የመሬቱን ሰብል እስከ በላበት ዘመን ድረስ ያለውን ግብር ከፍሎ ይለቃል እንጂ ሰብሉን በልቶ ግብሩን ሳይከፍል ለቆ መሄድ አይችልም ።

ቁጥር 1778፥ ገባር መሬቱን ለቆ ሄዶ ሌላ ሰው በይርጋው ዘመን ልክ ከገበረበት ለገባሪው ሰው ይፀናለታል እንጂ ለቆ የሄደው ሰው በኋላ መጥቶ የኔ ከነበረ እወስዳለሁ ለማለት አይችልም ።

## 2. ለ. 3. 2. የጢሰኛ ሕግና ሥርዓት

ቁጥር 3273፥ እሰው መሬት ላይ በጢሰኝነት ቤት ሠርቶ የጢሰኝነት ግብር እየገበረ የሚኖር ሰው ባለመሬቱ ልቀቅልኝ ካለው በቀር የጢሰኝነት ግብሩን እየገበረ ይቀመጣል እንጂ የመሬት ግምት ወይም እሌላ ዘንድ ካለው መሬት ነጠሮ ልስጥ ብሎ ሊከራከር አይገባውም ።

ቁጥር 3272፥ ሌላ ሰው በተቀበለው ማደሪያ መሬት በጢሰኝነት ቤት ሠርቶ የተቀመጠ ሰው ከባለመሬቱ ሳይስማማ የቀረ እንደሆነ ባለመሬቱ ተነስተህ ሂድ ባለው ጊዜ መሄድ አለበት ።

ቁጥር 3275፥ የገባር መሬት ያለው ሰው ከመልከኛው መሬት ላይ ቤት ሠርቶ የተቀመጠ እንደሆነ መልከኛው እገባር መሬትህ ላይ ሄደህ ሥራ የእኔን የመልከኛ መሬትን ልቀቀልኝ ባለው ጊዜ እገባር መሬቱ ላይ ሄዶ ይሠራል እንጂ ከመልከኛው ሊከራከር አይችልም ።

ቁጥር 3225፥ ጢሰኛ ሆኖ በገዳም ውስጥ የሚቀመጥ ሰው ከገዳሙ ካህናት ጋር ተጣልተው ከጢሰኛው አንድ ሰው ሞቶ ገዳዩን በሞት ፍርድ ቤት ካስፈረደበት በኋላ ጢሰኞቹ ከገዳሙ ካህናትች ደመኛ ከሆንን እነሱ አያዙንም በሻለቃ እንታዘዛለን ማለት አይገባቸውም ። መታዘዝን ባይፈልጉ ግን ጢሰኝነታቸውን ለቀው ይሄዳሉ ።

ቁጥር 3368፣ በርስቱ ላይ ጢሰኛ ያስቀመጠ ሰው ተፋልመውኛልና ይነሱልኝ ብሎ ለፍርድ ቤት ካመለከተ ጢሰኞቹ ልዩ ውለታ ከሌላቸው ቤታቸውን አፍርሰው ሀብታቸውን ይዘው ሊለቁ ይገባቸዋል ።

ቁጥር 711፣ ባለመሬቱ ጢሰኛውን መሬቱን ልቀቅ ባለው ጊዜ በጢሰኝነት በያዘው መሬት ላይ የተከለው የአትክልት ግምት መሬቱ ከሚያወጣው ዋጋ በላይ ሆኖ ባለመሬቱ የአትክልቱን ግምት መስጠት የማይቻል በመሆኑ ጢሰኛው ለባለመሬቱ የመሬቱን ግምት ልስጥ ያለ እንደሆነ ባለመሬቱን አለስልሶ ለጢሰኛው የሰጠው ከሆነ ለሠራተኛና ላትክልቱ ዋጋ ለመሬት ግብር የከፈለውን ጢሰኛው ግምቱን ተቀብሎ መሬቱን ይለቃል ።

ቁጥር 3287፣ ባለርስቱ በፈቃዱ ካላኖራቸው በቀር በጢሰኝነት ገብተው ከሰው መሬት ላይ እርቦ እያፈሰሱ ማር እየገዙ የቆዩ ሰዎች በዘመን ብዛት አንነሣም ይረጋልናል ብለው በግዴታ ለመቀመጥ ወይም ለመከራከር አይችሉም ።

ቁጥር 3299፣ በሰው መሬት ላይ ጢሰኛ ሆኖ የሚኖር በጢሰኝነቱ መሬቱ ላይ ሌላ ጢሰኛ ተክሎ ለራሱ ግብር መቀበል አይችልም ።

ቁጥር 3295፣ በማናቸውም ምክንያት ቢሆን የተማማሉ ባለመሬትና ጢሰኛ አብረው ሊኖሩ የማይችሉ ስለሆነ ባለመሬቱ ጢሰኛውን ከመሬቱ ላይ ሊያስነሳው ይገባል ።

ቁጥር 3321፣ ጢሰኛ የሆነ ሰው ከሰው ቦታ ሲኖር የውሃ ጉድጓድ ምሶ አትክልት ተክሎ ብዙ ዘመን ቢቀመጥ ባለቦታው ልቀቅ ሲለው የውሃውንና ቢፈቅድ የአትክልቱን የቤቱን ግምት ተቀብሎ ይለቃል እንጂ የውሃ ጉድጓድ ምሼ አትክልት ተክዬ ብዙ ዘመን ከተቀመጥኩ አልለቅም ብሎ ሊከራከር አይችልም ።

ቁጥር 3418፣ ጢሰኛ የሆነ ከባለርስቱ ተስማምቶ ካልተቀመጠ በግዴታ እቀመጣለሁ ለማለት የተከራከረ እንደሆነ ቤቱን አፍርሶ መሄድ ይገባዋል ።

ቁጥር 4394፣ ጢሰኛ ወይም ተጠሪ ሆነው በሌላ ሰው መሬት ላይ የሚኖሩ ሰዎች ያሉበት መሬትም በሚሸጥበት ጊዜ ይኸው የሚሸጠው መሬት ተገባባሪ አለቃ ወይም ምንዝር ኖሮበት ልገዛ ይገባኛል ቢል ሊገዛ ይገባዋል እንጂ ጢሰኛው ወይም ተጠሪ ነበርኩ እኔ እገዛለሁ ብሎ ሊከራከር አይገባውም ።

ቁጥር 3425፣ በጢሰኝነት የተቀመጠ ሰው ለባለመሬት የሚገባውን ግብር መክፈል ካልቻለ ይለቃል እንጂ አልገብርም ወይም አለቅም ማለት አይገባውም ።

ቁጥር 3447፣ ሲሶ አራሹ በራሱ በሮች አርሶ ዘሩን ዘርቶ ባለመሬቱ አንድ እጅ አራሹ ሁለት እጅ ይካፈላል ።

ቁጥር 3454፣ በጢሰኝነት እሰው ቦታ ላይ የተቀመጠ ሰው ስለግብሩም ሆነ ስለቦታው አጠባበቅ ባለምድሩ ዋስ ጥራ ባለው ጊዜ መቀመጥ



ቢያስፈልገውም ዋስ ጠርቶ ይቀመጣል እንጂ ዋስ አልጠራም ማለት አይገባውም ።

ቁጥር 3372፣ የተወሰነ መሬት ከባለርስቱ ወስዶ በየዓመቱ እህል ወይም ገንዘብ ለምስጠት በቁጥር የተከናተረ ሰው አዝመራው ቢጠፋበትና አንበጣ ሆነ ሌላ ነገር ቢበላበት የተለየ ውል ከሌለው ለባለርስቱ ለመስጠት ግዴታ የገባበትን እበል ይከፍላል እንጂ በተዘረዘረው ምክንያት ጠፍቶብኛል አልከፍልም ለማለት አይችልም ።

## 2. ሐ. የዘመነ ገባር ፍጻሜና የፊውዶ ቡርዣ ሥርዓት ግምባታ

የኢትዮጵያ የጉልተኛው መደብ መሪዎችና አባሉች ከምኒልክ ዘመነ መንግሥት መጨረሻ እስከ የኢጣሊያኖች ወረራ ድረስ በሥልጣንና በእርስ በርስ ጦርነት ተጠምደው የአገር ግምባታውን ኃላፊነትና ተግባር ዘንጉት ። የወቅቱ ብሔራዊ ችግሮች ለነበሩ ለገባር፣ ለመሬት፣ ለባርያና ላገር መከላከያ ጥያቄዎች የመፍትሄ እርምጃዎች አልወሰዱም ። ከዚህም የተነሣ በመጨረሻ በ1928-1933 ኢጣልያኖች አገሩን በወረራ ጦርነት በማሸነፍ ለአምስት ዓመታት ያዙት ። ከአገሩ ታሪካዊ ዕድገትና ሂደት አንፃር ይህ የኢጣልያኖች ወረራ ያስከተላቸው ሁኔታዎች ብዙና ዘላቂ ናቸው ።

አንደኛ፣ ኢጣልያኖች በታንክ፣ በመትረየስ፣ በመድፍ፣ በቦምብ፣ በብረት ለበስ ተሽከርካሪ፣ በአይሮፕላንና በመርዛማ ጋዝ ባካሄዱት ወረራ ጦርነት በምኒልክ ዘመንና መሪነት የኢትዮጵያ ታላቅ የአገር ግምባታ ኃይልና መገልገያ የነበረውን የነፍጠኛን የጦር ድርጅትና ሥርዓት በ1928 በትግራይና በኦጋዴን ጦር ግንባሮች ደመሰሱት ። ሁለተኛ፣ የኢትዮጵያ የጉልተኛው መደብ መሪዎችና አባሉች በወራሪው ጠላት ተሸንፈው በሽሽት ከአገሩ ከወጡ በኋላ የገባርና የባርያ ሥርዓቶች ከኢትዮጵያ ምድርና ታሪክ ተደመሰሱ ። የቀድሞ ገባሮችና ባሮች የአገሩ ነፃ ዜጎች ሆኑ ። ሦስተኛው በወረራ ዘመን በአገር አቀፍ ደረጃ በጠላት የተሠሩ የመንገድ፣ የመገናኛ፣ የሕንፃ፣ የከተማ፣ የንግድ ፣ የእርሻና የኢንዱስትሪ ሥራዎችና ድርጅቶች በድህረ ጦርነት ለፊውዶ ቡርዧ ሥርዓትና ለወዛደር መደብ ዕድገት አመቺ ሁኔታዎች ሆኑ ።

አራተኛው፣ ከወራሪ ጠላት ጋር የኢትዮጵያ ሕዝብ ለብሔራዊ ሀልውና፣ ነፃነትና አንድነት ባካሄደው ብሔራዊ ትግል ወቅትና ሂደት በትግራይና በኦጋዴን ጦር ግንባሮች በፈረሰው በኢትዮጵያ ነፍጠኛ ጦር እግር የኢትዮጵያ የአርበኞች እንቅስቃሴ ብሎም ዘመናዊውና ብሔራዊው የጦር ድርጅት ተፈጠረ ። አምስተኛ፣ በጦርነቱ ወቅትና በኋላ የኢትዮጵያ ሕዝብ ባካሄደው ወታደራዊና ፖለቲካዊ ትግልና ድል የኤርትራ ክፍለ ሀገር ከቀይ ባህር ጋር ከኢምፔሪያሊስቶች እጅ ነፃ በመሆን በ1952 ከእናት አገር ኢትዮጵያ ጋር በብሔራዊ ነፃነትና አንድነት ተዋሀደ ።

ስድስተኛ፣ በድህረ ጦርነት የኢትዮጵያ የጉልተኛው መደብና መንግሥት በፊት በምኒልክ ዘመን በመንግሥት ስምና ሥር ሰደዱና ለመንግሥት አገልግሎት የተያዘውን የሕብረተሰቡን ብሔራዊ ሀብትና መሬት በንጉሣዊ ትእዛዝ፣

ሠንጠረዥ 5

የኢትዮጵያ ሕዝብ ከ1820 እስከ 1952 ከወራሪዎችና ከኢምፔሪያሊስቶች ጋር ያካሄዳቸው ጦርነቶች

| ተራ ቁ. | የጦርነቶች ወይም የውጊያዎች ስምና ሥፍራ | ጊዜ በዓመታት | ተራ ቁ. | የጦርነቶች ወይም የውጊያዎች ስምና ሥፍራ | ጊዜ በዓመታት |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የግብጽ ጦር የምፅዋን አካባቢ ያዘ | 1824 | 28 | የጉጃም ጦር በጎንደር አካባቢ በደርቡሾች ተሸነፈ | 1887 |
| 2 | ከገዳሪፍ የግብጽ የመጀመሪያ ወረራ በጎንደር አካባቢ | 1832 | 29 | የደርቡሽ ወራሪዎች ጎንደርን አቃጥለው ሄዱ | 1888 |
| 3 | ከገዳሪፍ የግብጾች 2ኛ ወረራ በጎንደር አካባቢ | 1834 | 30 | የራስ ጉበና ጦር በወለጋ 5000 የደርቡሽ ወራሪዎችን ገደለ | 1888 |
| 4 | ከገዳሪፍ የግብጽ 3ኛ ወረራ በመተማ | 1837 | 31 | አፄ ዮሐንስ ከደርቡሾች ጋር እየተዋጉ በመተማ ሞቱ | 1889 |
| 5 | ከገዳሪፍ የግብጽ 4ኛ ወረራ በከታልታቡ | 1838 | 32 | ደጃች አበራ ኃይሉ የኤርትራ ነፃነት ጦርነት በኢጣሊያኖች ላይ ጀመሩ | 1890 |
| 6 | በአርቂቆ የግብጽ ወረራ | 1847 | 33 | ደጃች ባህታ ሐጐስ በኢጣሊያኖች ላይ የነፃነት ጦርነት አወጁ | 1894 |
| 7 | የግብጽ ወረራ በመተማ አካባቢ | 1848 | 34 | የኮአቲት ጦርነት ከኢጣሊያኖች ጋር | 1895 |
| 8 | የደባርክ ጦርነት በግብጽና በኢትዮጵያ መካከል | 1848 | 35 | ከኢጣሊያኖች ጋር የሰናፌ ጦርነት | 1895 |
| 9 | የግብጽ ወረራ በከረን አካባቢ | 1854 | 36 | ከኢጣሊያኖች ጋር የአምባላጌ ጦርነት | 1895 |
| 10 | ከገዳሪፍ የግብጽ ወረራ በተከዜ አካባቢ | 1856 | 37 | ከኢጣሊያኖች ጋር የመቀሌ ጦርነት | 1896 |
| 11 | ከገዳሪፍ የግብጽ ወረራ በጎንደር አካባቢ | 1865 | 38 | ታላቁ የአድዋ ድል በኢጣሊያኖች ላይ | 1896 |
| 12 | የግብጽ ወረራ በምፅዋ ጠረፍ አካባቢ | 1866 | 39 | ከኢጣሊያኖች ጋር የወልወል ጦርነት | 1934 |
| 13 | የመቅደላ ጦርነት በኢትዮጵያና በእንግሊዝ መካከል | 1868 | 40 | ከኢጣሊያኖች ጋር የቆራሄ ጦርነት | 1935 |
| 14 | አንድ ኢጣሊያዊ ኩባንያ የአሰብን ወደብ ያዘ | 1869 | 41 | ከኢጣሊያኖች ጋር የአናሌ ጦርነት | 1935 |
| 15 | የግብጽ ጦር ከረንን ያዘ | 1974 | 42 | ከኢጣሊያኖች ጋር የገናሌ ጦርነት | 1936 |
| 16 | የግብጽ ጦር ሐረርን ያዘ | 1975 | 43 | ከኢጣሊያኖች ጋር የተንቤን ጦርነት (በጥር ወር) | 1936 |
| 17 | አንድ የግብጽ ወራሪ ኃይል በአውሳ ግዛትም በአፋር ተደመሰሰ | 1875 | 44 | ከኢጣሊያኖች ጋር የጎጌሌ ጦርነት | 1936 |
| 18 | አንድ የግብጽ ወራሪ ጦር በጉንደት ተደመሰሰ | 1875 | 45 | ከኢጣሊያኖች ጋር የአንደርታ ጦርነት | 1936 |
| 19 | አንድ ሌላ የግብጽ ጦር በጉራዕ ተደመሰሰ | 1876 | 46 | ከኢጣሊያኖች ጋር የተንቤን ጦርነት (በየካቲት ወር) | 1936 |
| 20 | የከረን ጦርነት በግብጽና በኢትዮጵያ ወታደሮች መካከል | 1876 | 47 | ከኢጣሊያኢኖች ጋር የሽሬ ጦርነት | 1936 |
| 21 | ኢጣሊያኖች አሰብን በጦር ያዙ | 1882 | 48 | ከኢጣሊያኖች ጋር የማይጨው ጦርነት | 1936 |
| 22 | የሰሐቲ ጦርነት በግብጽና በኢትዮጵያ ወታደሮች መካከል | 1883 | 49 | ኢጣሊያኖች የፈጸሙት የአሸንጌ እልቂት | 1936 |
| 23 | የኩፍት ጦርነት በደርቡሾና በኢትዮጵያ ወታደሮች መካከል | 1885 | 50 | ኢጣሊያኖች የፈጸሙት የአዲስ አበባ እልቂት | 1937 |
| 24 | ምጽዋ በኢጣሊያኖች ጦር ተያዘ | 1885 | 51 | ኢጣሊያኖች የፈጸሙት የደብረ ሊባኖስ እልቂት | 1937 |
| 25 | የደርቡሾች ወረራ በጎንደር አካባቢ | 1886 | 52 | በኤርትራ ኢጣሊያኖች የተሸነፉበት የከረን ጦርነት | 1941 |
| 26 | አንድ የኢጣሊያን የሰላ ቡድን በሐረር ተደመሰሰ | 1886 | 53 | በጉጃም ኢጣሊያኖች የተሸነፉበት የደብረ ማርቆስ ጦርነት | 1941 |
| 27 | የዶጋሊ ጦርነት በኢጣሊያኖችና በኢትዮጵያ ወታደሮች መካከል | 1887 | 54 | ኢጣሊያኖች የተሸነፉበት የጎንደር ጦርነት | 8941 |
| | | | 55 | የኤርትራ ነፃነት ትግል ከእንግሊዞች ጋር | 1941-1952 |

ከ1933 እስከ 1941 ከኢጣሊያኖች ጋር በተካሄደው ጦርነት የደረሰው የሕይወትና የንብረት ጥፋት (ሀ) የሞተው ሰው ብዛት 760 300 ፤ (ለ) የሞቱና የተዘረፉ እንስሳት ብዛት 1 370 000 ፤ (ሐ) ጠቅላላ የሕይወት ፣ የንብረትና የሀብት ጥፋት በገንዘብ ሲተመን 185 000 000 ፓውንድ ስተርሊንግ ማለትም 1 010 000 000 ብር ወይም 326 ብሊዮን ሊሬ ነበር ።

በሠንጠረዡ ውስጥ የሚገኘው የጊዜ አቆጣጠር እንደ አውሮፓውያ ዘመን ነው ።



ሲጦታና አዋጅ በወል ለመሳፍንቶች ፣ ለመኳንቶች ፣ ለመንግሥትና ለቤተ ክርስቲያን ባለሥልጣናች ፣ ለባለባቶችና ለከተማ ከበርቴዎች ለጦርና ለፖሊስ መኮንኖች የግልና የቤተሰብ ሀብትና ንብረት አድርጐ የሚሰጥ አዲስ የመሬት ይዞታ ሕግና ሥርዓት መሠረተ ። ከ1933 እስከ 1966 ይህ ኃይለ ሥላሴያዊ አዲስ የመሬት ይዞታ ሕግና ሥርዓት በአገሩ ላይ ያስከተላቸው የመደብ ፣ የኢኮኖሚ የፖለቲካ ፣ የብሔረሰብ ፣ የባህል ፣ የቋንቋና የሕብረተሰብ ችግሮች እጅግ በጣም ብዙና መሠረታዊ ናቸው ።

በዚህ አኳያ ፣ 1/ በገጠር የእርሻና የግጦሽ መሬት በመንግሥታዊ ትእዛዝና ሕግ በከተማ ለመኖሩ ብሎም መሬቱን አርሰው ለማይጠቀሙ መሳፍንታዊና ባላባታዊ ጉልተኞች በዘረፋ ስለተሰጠ የገጠሩ ሕዝብ በስደትና በፍልሳ ወደ ከተማ በመምጣት የቤት አሽከር ፣ የከተማ ቦዘኔ ፣ የፋብሪካ ሠራተኛ ፣ ተማሪ ፣ ወታደር ፣ ነጋዴ ፣ ዝሙት አዳሪ ፣ የከተማ ቀማኛና ሌባ መሆን ጀመረ። 2/ ከምጣድ ወደ እሳት እንደሚሉት ፣ በገጠር ከመሳፍንታዊና ከባላባታዊ ጉልተኞች በመሸሽ በከተማና በፋብሪካ የሚቀጠሩ የኢትዮጵያ ወዛደሮች በውጭና በብሔራዊ ካፒታሊስቶች ተበዘበዙ ። 3/ በገጠር ከአገሩ አርሶ አደሮች ና ዘላኖች በዘረፋ በተያዘ ምርጥ መሬት ንግዳዊና መንግሥታዊ ካፒታሊዝም ተስፋፋ

4/ በገጠር ለምና ሰፊ መሬት በከተማ እየኖሩ መሬቱን በራሳቸው ጥረትና ጉልበት አርሰውና አልምተው ለማይጠቀሙ መሳፍንታዊና ባላባታዊ ጉልተኞች በመሰጠቱና የገጠሩ አርሶ አደር በስደትና በፍለሳ ወደ ከተማ በመምጣቱ በአገሩ ለእርሻ ፣ ለንግድና ለኢንዱስትሪ ዕድገትና ልማት ቋሚና ወሳኝ እንቅፋት ሆነ ። በዚህ ረገድ ፣ እንድ ከአገር አስተዳደር ሚኒስቴር የተገኘው ሰነድ እንደሚያሳየው ፣ የኢትዮጵያ ጠቅላላ የመሬት ስፋት 3.070.750 ጋሻ ሲሆን ከዚህ መሬት 30 በመቶ ወይም 922.225 ጋሻ በተፈጥሮው ሁኔታ ደረቅ ፣ 70 በመቶ ወይም 2.147.525 በተፈጥሮው ሁኔታ ለምና ምርታማ ፣ 14 በመቶ ወይም 380.344 ጋሻ ቀላድ የተጣለበት መሬት ፣ 56 በመቶ ወይም 1.769.179 ጋሻ ቀላድ ያልተጣለበት መሬት መሆኑ በተጨማሪ ታውቀዋል ።

## 2. መ. የፊውዶ ቡርዣ ሥርዓት ውድቀትና የአብዮት ፍንዳታ

ከ1933 ጀምር የኢትዮጵያ ጉልተኛው መንግሥት ከአርሶ አደሩ የመሬት ግብር ለመሰብሰብ እንዲመቸው ይህንን የአገሩን ከፍተኛ የመሬት ሀብት በአምስት ልዩ ልዩ ደረጃዎችና አካባቢዎች መደበ ። በዚህ አኳያ በወሎ ፣ በደቡብ ሸዋ ፣ በአርሲ ፣ በሐረርጌና በባሌ ክፍለ ሀገራት ቀላድ በተጣለባቸው አካባቢዎች አንድ ዓይነት የመሬት ግብር ፣ በወለጋ ፣ በከፋ ፣ በሲዳሞ ፣ በኢሉባቡርና በጋሞጎፋ ክፍለ ሀገራት ቀላድ በተጣለባቸው ሥፍራዎች ሌላ ዓይነት የመሬት ግብር በወሎ ፣ በደቡብ ሸዋ ፣ በአርሲ ፣ በሐረርጌ ፣ ባባሌ ፣ በወለጋ ፣ በከፋ ፣ በሲዳሞ በኢሉባቡርና በጋሞጎፋ ክፍለ ሀገራት ቀላድ ባልተጣለባቸው አካባቢዎች ደግሞ ሌላ ዓይነት የመሬት ግብር ፣ በሰሜን ሸዋ ፣ አውራጃዎች ልዩ ዓይነት የመሬት ግብር ፣ በሰሜኑ ደጋ በጉጃም ፣ በጎንደር ፣ በትግራይና በኤርትራ ክፍለ ክፍለ ሀገራትና አውራጃዎች ሌላ ዓይነት የመሬት ግብር ሕግና ሥርዓት ደነገገ

በዚህ መሬት ግብር ሕግ መሠረት ፣ የጉልተኛው መንግሥት ከፍተኛ ግብር ይከፍላሉ በተባሉ በወሎ በደቡብ ሸዋ ፣ በአርሲ ፣ በሐረርጌና በባሌ ክፍለ ሀገ

ራት ለአሥራት፣ ለመሬት አገልግሎት ፣ ለትምህርትና ለጤና ግብር በድምሩ በአንድ ጋሻ ለም መሬት በየዓመቱ 80 ብር፣ በለም ጠፍ መሬት 64 ብር፣ በጠፍ መሬት ደግሞ 24 ብር ያስገብር ነበር ። በዚህ ዓይነት ሲሰበሰብና ሲላ በጠፍ መሬት ደግሞ 24 ብር ያስገብር ነበር ። በዚህ ዓይነት ውስብስብና መላ ቅጡ በጠፋውሕግና ሥርዓት አድሃሪው መንግሥት ከ1933 እስከ አብዮቱ ፍንዳታ ድረስ በአንድ ግብር ዓመት ከአገሩ መላው መሬትና አርሶ አደሩ ሊሰበስበው የቻለ ከፍተኛ የመሬት ገቢ መጠን በድምሩ 42.500.000 ብር ብቻ ሲሆን እርሱም በ1965 በአብዮቱ መባቻ ነበር ። በአንፃሩ ደግሞ በ1965 የአገሩ ዓመታዊ በጀት ወጭ 778.000.000 ብር ደርሶ እንደነበር ይታወሳል ።

ከኢትዮጵያ መሬት 70 በመቶ ወይም 2.147.525 ጋሻ በተፈጥሮው ሁኔታ ለምና ምርታማ ነው ተብሎዋል ። የጉልተኛው መንግሥት ሥርዓትና ማዕከላዊ ነት በሌለው ዘዴ 70 በመቶ በሆነው በለም መሬት ብቻ እንኳን በእያንዳንዱ ጋሻ 80 የመሬት ግብር ቢያስከፍል ኖሮ በአንድ ግብር ዓመት ቢያንስ 170.000 000 ብር፣ በእያንዳንዱ ጋሻ 64 ብር ብቻ ቢያስከፍል ደግሞ 130.000.000 ብር ወይም በእያንዳንዱ ጋሻ 24 ብር ቢያስከፍል ኖሮ በዓመት ቢያንስ 50.000.000 ብር ገቢ ለመሰብሰብ በቻለ ነበር ። ይህ ሁሉ ታላቅ ብሔራዊ የመሬት ሀብት በልዩ ልዩ መልክና መንገድ ማለትም በአገልግሎት፣ በምርትና በገንዘብ ለግለሰብ ጉልተኞች ገቢ በመሆኑ አድሃሪው መንግሥት በሕዝባዊ አብዮት እስ ኪደመሰስ ድረስ ከአገሩ መሬትና አርሶ አደር በድምሩ ከ42.500.000 ብር በላይ ገቢ ያገኘበት ዓመት አልነበረም ። በግርከባዊ አነጋገር በአንድ ሕብረተ ሰብ ያረጀና ያፈጀ የምርት ግንኙነት የምርት ዕድገት አፍኖ ይይዛል ሲባል ታሪካዊ እውነታ ይህ ነው ወይም እንደዚሁ ነው ።

በኢኮኖሚያዊ አነጋገር፣ ንግድ ማለት የምርት ስርጭትና ልውውጥ ማለት ነው ። በዚህ አባባል የአንድ አገር የምርት ማለትም የእርሻ ኢኮኖሚ በሆነ ሁሉ ምክንያት የማያድግ ከሆነ የንግድ ኢኮኖሚ ዘርፍ ደግሞ አያድግም ። የአንድ አገር የንግድ ኢኮኖሚ ዕድገት አንድ ምልክትና ሚዛን ደግሞ የውጭ ንግድ ሁኔታ ነው ። በዚህ ጉዳይ፣ የኢትዮጵያ የእርሻ ኢኮኖሚ ዘርፍ ከዚህ በላይ በተገለፀው ሥርዓታዊ ስንክሳር በመታመሩ ከዚህ በታች መንጠረዥ 7 እንደሚያሳየው፣ እንደ አውሮፓ ዘመን አቆጣጠር ከ1946 እስከ 1975 ድረስ በ30 ዓመታት ውስጥ የአገሩ የውጭ ምንዛሬ ለ25 ዓመታት በኪሣራ ውስጥ ነበር ።

ከዚህ በላይ የተገለፁ ኢኮኖሚያዊ ማስረጃዎች በተጨባጭ እንደሚያመለክቱ፣ የኢትዮጵያ የወደቀው መንግሥት ከእርሻና ከንግድ ከፍሎች ዘመናዊ አገርና ሕብረተሰብ ለመገንባት ዓይነተኛ መንገድና መገሪያ የሆነውን የኢንዱስትሪ ኢኮኖሚ ለማስፋፋት አስፈላጊና ተቀዳሚ ነገር የሆነ ውን ብሔራዊ ጥሬት ማለትም መዋዕለ ንዋይ ለማግኘት ሳይችል ቀረ ። ይህን መሠረታዊ ጉድለት ለማሟላት የአጼ ቀዳማዊ ኃይሌ ሥላሴ መንግሥት ከምዕራብና ከጃፓን ኢምፔሪያሊስት አገሮችና መንግሥታት የብድር ና "የእርዳታ" ገንዘብ ለመውሰድ ተገደደ ።

የኢምፔሪያሊስቶች የገንዘብ ብድርና "እርዳታ" ደግሞ በኢትዮጵያ መንግሥትና ሕብረተሰብ ላይ ከፍተኛ የሆነ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ወታደራዊና ባህላዊ ተጽዕኖና ግፊት አሳደረ ። በዚህ አኳያ፣ ለምሳሌ ከ1933 እስከ 1966 ድረስ የኢትዮጵያ የውጭ ፖሊሲ፣ የጦር፣ የፀጥታ፣ የፖሊስና የትምህርት ድርጅቶች ቁጥጥር በእንግሊዝና በአሜሪካ ኢምፔሪያሊስቶች ተጽዕኖ ሥር ዋለ ። የአገሩ የኢኮኖሚው የንግድ፣ የኢንዱስትሪና የገንዘብ ዘርፎችና ድርጅቶች በፈረ



ሠንጠረዥ 6

የኢትዮጵያ የመሬት ይዞታና ግብር ከ1933 እስከ 1966 ሲጋቸና በብር

| የመሬት ይዞታ ዓይነት | የለም መሬት ግብር ዓይነት | | | | የለም ጠፍ መሬት ግብር ዓይነት | | | | የጠፍ መሬት ግብር ዓይነት | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | አሥራት | የመሬት ግብር | ትምህርት | ጤና | አሥራት | የመሬት ግብር | ትምህርት | ጤና | አሥራት | የመሬት ግብር | ትምህርት | ጤና |
| 1. በሸዋ ፣ በጅማ ፣ በአርሲ ፣ በሐረርጌና በባሌ በአንድ ጋሻ መሬት | 30.00 | 15.00 | 15.00 | 15.00 | 30.00 | 10.00 | 12.00 | 12.00 | 10.00 | 5.00 | 4.50 | 4.50 |
| ድምር | | | | 80.00 | | | | 64.00 | | | | 24.00 |
| 2. በወለጋ ፣ በከፋ ፣ በሲዳሞ ፣ በኢሉባቦርና በጋሞ ጎፋ በአንድ ጋሻ መሬት | 30.00 | 13.50 | 13.50 | 12.00 | 30.00 | 10.00 | 12.00 | 12.00 | 10.00 | 5.00 | 4.50 | 4.50 |
| ድምር | | | | 70.50 | | | | 64.00 | | | | 24.00 |

| 3. በጎጃም ከ/ሀገሩ የጋሻ ቀላድ ያልተጣለበት የግብር ወይም የገባ መሬት በክፍት ግብር ደረጃዎች | የመሬት ግብር ዓይነትና መጠን በብር | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | አሥራት | መሬት ግ. | ትምህርት | ጤና | ድምር |
| በ1ኛ ደረጃ መሬት | 12.00 | 8.00 | 6.00 | 6.00 | 32.00 |
| በ2ኛ ደረጃ መሬት | 10.00 | 7.00 | 5.00 | 5.00 | 27.20 |
| በ3ኛ ደረጃ መሬት | 9.00 | 6.00 | 4.00 | 4.00 | 24.00 |
| በ4ኛ ደረጃ መሬት | 6.00 | 4.00 | 3.00 | 3.00 | 16.00 |
| በ5ኛ ደረጃ መሬት | 3.00 | 2.00 | 1.00 | 1.50 | 8.00 |
| በ6ኛ ደረጃ መሬት (ለቶ ለም) | 25.00 | 10.00 | 10.00 | 10.50 | 56.00 |

| 4. በዘመናዊ ግብር ደረጃዎች በተከፈለ በበጌምድር ቸቸ ርስት መሬት | የመሬት ግብር ዓይነት | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | አሥራት | መሬት ግ. | ትምህርት | ጤና | ድምር |
| በ1ኛ ደረጃ መሬት | 12.00 | 8.00 | 6.00 | 6.00 | 32.00 |
| በ2ኛ ደረጃ መሬት | 10.00 | 7.00 | 5.10 | 5.10 | 27.00 |
| በ3ኛ ደረጃ መሬት | 9.00 | 6.00 | 4.50 | 4.50 | 24.00 |
| በ4ኛ ደረጃ መሬት | 8.00 | 5.00 | 3.90 | 3.90 | 20.00 |
| በ5ኛ ደረጃ መሬት | 6.00 | 4.00 | 3.00 | 3.00 | 16.00 |
| በ6ኛ ደረጃ መሬት | 4.00 | 3.00 | 2.10 | 2.10 | 11.20 |
| በ7ኛ ደረጃ መሬት | 3.00 | 2.00 | 1.50 | 1.50 | 8.00 |
| በ8ኛ ደረጃ መሬት | 1.50 | 0.50 | 0.60 | 0.50 | 3.20 |
| በ9ኛ ደረጃ መሬት (ለቶ ለም) | 25.00 | 10.00 | 10.50 | 10.50 | 56.00 |

5. የመሬት ይዞታ የጋራ ፣ የመንደርና የቤተክህ በሆነው በሰሜን ጠቅላይ ግዛቶች በትግሬ ፣ በቤጌምድርና በትግራይ የመሬት ግብር በ1927 በዓይነት ግብሩ በሰላ ይከፈል የነበረው እሱን አሥራት ግምር በገንዘብ ተተምኖ ይከፈላል ።

6. የጋሻ ቀላድ ያልተጣለባቸው የሰሜን ጠቅላይ ግዛቶች ጠቅላላ ግዛትና አውራጃዎች የመሬት ግብርና አሥራት ድምር

| ክፍል | አሥራት | የመሬት ግብር | ድምር |
|---|---|---|---|
| ትግሬ | 618,377.00 | 147.072.00 | 765,450.00 |
| ጐጃም | 410,560.00 | 821,100.00 | 1,231,650.00 |
| ቤጌምድር | 1,185,385.00 | 46.862.00 | 1,232,247.00 |
| ሲዳሞና ጋሞ | 30,673.00 | 176,720.00 | 207,393.00 |

7. የኢትዮጵያ ጠቅላላ የመሬት ሀብት መጠን በጋሻ

| | |
|---|---|
| 1. የመሬት ስፋት | 3,070,750 |
| 2. የደረቅ መሬት መጠን (30 በመቶ) | 922,225 |
| 3. የለም መሬት መጠን (70 በመቶ) | 2,147,525 |
| 4. የቀላድ የተጣለበት መሬት መጠን (14 በመቶ) | 1,300,344 |
| 5. ቀላድ ያልተጣለበት መሬት መጠን (56 በመቶ) | 1,760,179 |

Source Ethiopia, "Land Taxes Proclamations", Nos. 70, 94, 117, 18/14 of 1942, 1947, 1951, 1959; H.S. Mann, *Land Tenure of Chore* (1965); J.C.L. Lawerence and H.S. Mann; *Land Policy Project* (1964).

ሠንጠረዥ 7

የኢትዮጵያ የውጭ ምንዛሬ ሁኔታ ከ1946 እስከ 1974 እንደ አውሮፓውያን ዘመን በሚሊዮን ብር

| የንግድ ዓመት | የተገዛ ዕቃ ዋጋ | የተሸጠ ዕቃ ዋጋ | የዋጋ ሚዛን | የንግድ ዓመት | የተገዛ ዕቃ ዋጋ | የተሸጠ ዕቃ ዋጋ | የዋጋ ሚዛን |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1946 | 94.9 | 76.2 | —18.7 | 1961 | 235.6 | 188.7 | —46.9 |
| 1947 | 121.2 | 98.6 | —22.5 | 1962 | 257.3 | 199.5 | —57.9 |
| 1948 | 124.0 | 96.6 | —27.4 | 1963 | 276.1 | 223.4 | —52.7 |
| 1949 | 119.1 | 94.3 | —25.1 | 1964 | 307.6 | 262.5 | —45.1 |
| 1950 | 105.5 | 91.3 | —14.2 | 1965 | 375.7 | 289.8 | —85.9 |
| 1951 | 147.5 | 151.9 | + 4.5 | 1966 | 404.3 | 277.0 | 125.3 |
| 1952 | 161.9 | 131.4 | —30.5 | 1967 | 357.7 | 252.7 | —104.7 |
| 1953 | 137.9 | 169.4 | +31.5 | 1968 | 432.5 | 266.0 | —166.5 |
| 1954 | 161.1 | 160.3 | + 0.2 | 1969 | 388.5 | 298.1 | —90.2 |
| 1955 | 668.0 | 162.2 | —5.8 | 1970 | 429.1 | 301.1 | —123.2 |
| 1956 | 157.1 | 151.4 | —5.7 | 1971 | 469.5 | 314.4 | —155.2 |
| 1957 | 178.4 | 192.0 | +13.6 | 1972 | 435.6 | 387.3 | —48.3 |
| 1958 | 193.6 | 156.8 | —36.8 | 1973 | 448.2 | 499.5 | +51.3[1] |
| 1959 | 208.9 | 179.2 | —29.7 | 1974 | 586.0 | 556.2 | —29.8 |
| 1960 | 219.3 | 192.6 | —26.7 | 1975 | 613.1 | 478.3 | —134.8 |
| ድምር | 2293.3 | 2104.0 | —243.1 | | 6016.1 | 4799.3 | —1268.4 |

በ30 ዓመታት የውጭ ምንዛሬ ኪሣራ ድምር 1 243.1+ —1268.4=1511.5=1,511,500,000 ብር 1,511,500,000 ማለት አንድ ቢሊዮን አምስት መቶ አሥራ አንድ ሚሊዮን አምስት መቶ ሺህ ብር የውጭ ምንዛሬ ኪሣራ

Source: Ethiopia, *Annual External Trade Statistics* (1978); Ethiopia, *Statistical Abstract* (1978).

1 በዚህ ንግዳዊ ሠንጠረዥ እንደተመለከተው ፣ የወደቀው የነፈተኛ መንግሥት በአገሩ ታሪክ ከፍተኛ የእርሻ ምርት ወደ ውጭ ገበያ በመላክ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ ያገኘበት ዓመት በ1973 በኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር በ1965 ሲሆን በአንፃሩ ደግሞ በዚሁ ዓመት በታላቁ ችግርና ችጋር ማለትም በምግብ እጦት በ200.000 የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን በረሃብ መቅሰፍት መሞታቸውና ለአብዮቱ ፍንዳታ አንድ [illegible] ይታወሳል ።



ንሳይ ፣ በእንግሊዝ ፣ በኢጣሊያን በሆላንድ ፣ በአሜሪካን ፣ በምዕራብ ጀርመን ፣ በእሥራኤልና በጃፓን ዜጐችና ኩባንያዎች ቁጥጥር ሥር ዋሉ ። በዚህ አኳያ የአገሩ ኢኮኖሚ ከዓመት ወደ ዓመት ወደ ታች ሲያድግ በአንፃሩ ደግሞ የአገሩ የሕዝብ ብዛት በየዓመቱ እየጨመረ ሄደ ። የኢኮኖሚ ችግርችና የአስተዳደር በደል በአንድነት በመላው አገሩ በየጊዜው የእርስ እድር ፣ የብሔረሰብ ፣ የወዛደር ፣ የተማሪ ፣ የወታደር አመፆችን በአድሃሪው መንግሥትና ሥርዓት ላይ አስነሱ። በመጨረሻም በ200.000 ለሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን ሞት ምክንያት የሆነው የ1965—1966 ረሀብና ችጋር የአድሃሪውን መንግሥትና ሥርዓት ዘመን ፍጻሜ አፋጠነ ።

### ክፍል ሁለት

# የኢትዮጵያ አብዮትና የሶሻሊዝም ግምባታ ዘመን

## 1. የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮት ፍንዳታ

### 1. ሀ. የአብዮቱ ወታደራዊ አመራር

የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮት በየካቲት 1966 እንደ እሳተ ጎሞራ ከፈነዳ በኋላ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ህልውና፣ ነፃነትና አንድነት ላይ ከሦስት አቅጣጫዎች ከባድ አደጋ ተሰነዘረ። አንደኛ፣ ከውስጥ የኢትዮጵያ የቀድሞ የገዥ መደብ መሳፍንታዊና ባላባታዊ መሪዎችና አባሎች ከብዙ ስውር ፖለቲካ ድርጅቶች ጋር በመደባዊ ሕብረት የሥርቶ አደሩን መደብ አብዮታዊ አመጽና ነፃነት በመቃወም አብዮቱን ለማጥፋት በአገርና በዓለም አቀፍ ደረጃ የትጥቅና የፖለቲካ ትግል አካሄዱ። ሁለተኛ፣ በሰሜን የኤርትራ ተገንጣይ ቡድኖች በአካባቢው በአፍሪካና በአረብ አድሃሪ መንግሥታት መገፋፋትና ፖለቲካዊ ድጋፍ የኤርትራን ክፍለ ሀገር ከቀይ ባህር ጋር ከኢትዮጵያ ወስደው አረባዊ ግዛት ለማድረግ ከደፈጣ ውጊያ አልፈው በአብዮታዊት ኢትዮጵያ ላይ የግምባር ጦርነት ገጠሙ። ሦስተኛ፣ በምሥራቅና በደቡብ ምሥራቅ ወራሪው የሶማሊያ መንግሥት በአካባቢው አረብ አድሃሪ መንግሥታት ድጋፍ የኢትዮጵያን አንድ ሦስተኛውን ምድር ከአያሌ ብሔረሰቦች ጋር በሽግግራዊ ወቅት ቀርጦ ለመውሰድ የወረራ ጦርነት ጀመረ።

በዚህ ቀውጢና ወሳኝ ብሔራዊ አደጋ ወቅት የኢትዮጵያ አርበኛው ወታደርና ገበሬ በብሔራዊ ሕብረትና ፊታውራሪነት የመላ አገሩን የሥርቶ አደር ሕዝብ ብሔራዊ ድጋፍ ይዘው በአገሩ ብሔራዊ ህልውና፣ ነፃነትና አንድነት ላይ እንደዚህ ከውስጥና ከውጭ የተነሱትን አድሃሪ፣ ተገንጣይና ወራሪ ኃይሎችንና ግምባሮችን እንደአመጣጣቸው አንድ በአንድ በመደምሰስ እናት አገር ኢትዮጵያን ከመቆረስ ሕዝባዊ አብዮቱንም ከአድሃሪያን ቅልበሳ በታላቅ ብሔራዊ ትግልና መስዋዕትነት አድኖታል።

ይህ የኢትዮጵያ ወታደርና ገበሬ በብሔራዊ ሕብረት በአብዮታዊ ሽግግር ወቅት የተጫወቱት ወሳኝ ብሔራዊ፣ ፖለቲካዊና አብዮታዊ ሚና የኢትዮጵያ ረጅምና ውስብስብ ታሪክ በሳይንሳዊ ምርምርና ሚዛን እንዲመረመርና እንደገና በትክክል እንዲጻፍ አስገዳጅ ታሪካዊ ሁኔታና ምክንያት ፈጥሮአል። በዚህ ረገድ፣ ኢትዮጵያ በዓለም ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ የመለዮ ለባሽ ሕዝባዊ አብዮት የመራበት አገር ነው። ይህንን የኢትዮጵያ የመለዮ ለባሽ ክፍሉ የተጫወተውን ታላቅ የፖለቲካ ሚና የሚገልጽ ታሪካዊ ልምድ ወይም ፖለቲካዊና አብ

ዮታዊ ትምህርትና ቲዎሪ ወይም ምሁር በዓለም ታሪክ እስከ ዛሬ የለም። ስለዚህ የኢትዮጵያን የአብዮት መነሻ፣ አመራርና ሂደት በትክክል በሳይንሳዊ ጥናትና ሚዛን ለማወቅ ቁልፍ የአገሩ ረጅምና ውስብስብ ታሪክ ነው።

በአገሩ ረጅምና ውስብስብ ታሪክ የኢትዮጵያ ወታደር ወይም የጦር ክፍል እንደ ዘመኑ አዝማሚያው እንደጊዜው ሁኔታ ከፍተኛ የፖለቲካ ሚና ሲጫወት የኖረ ብሎም የአገሩን የወደቀውን ዘውዳዊና መሳፍንታዊ የገዥ መደብ ለዘመናት በሥልጣን ላይ የኖረው ክፍል ነው። በዚህ አኳያ፣ አንደኛ፣ የኢትዮጵያ ጥንታዊው የአክሱማውያን ሥልጣኔ በሰሜን ኢትዮጵያ በአረቢያና በአባይ ሸለቆ ዓለም አቀፍ ሥርዓትና ሥልጣኔ ሆኖ የተስፋፋው በማዕከላዊ ደረጃ በተደራጀ ብሔራዊ ጦር ኃይል እንደነበር የአገሩ ጥንታዊ የድንጋይ ጽሑፎችና የነገሥታት ዜና መዋዕሎች ያስተምሩናል። ለምሳሌ ታላቁ የኢትዮጵያ አክሱማዊ ንጉሠ ነገሥት አጼ ኢዛና በከፍተኛ ደረጃ በተደራጁና መሐዘ፣ ሐራ፣ ደመወ፣ ፈልሐ፣ ፅራእ፣ ሕሌን፣ ምጢን፣ ዳኬን፣ ላኬንና ሰብራት የተባሉ ንጉሠ ነገሥቱ "ሰዎቼ" የሚላቸው ምርጥና ጠንካራ ወታደራዊ ድርጅቶችና ክፍሎች ነበሩት።[1]

ሁለተኛ፣ በ1270 ይኩኖ አምላክ በተባለው በአንድ የጦር አበጋዝ መሪነት የዛጉኤን መንግሥትና መሳፍንታዊ የገዥውን መደብ በመሣሪያ ኃይል ደምስሰው በአገሩ ታሪክ እስከ 1966 ድረስ ለሰባት ምዕተ ዓመታት ጸንቶ የሚኖረውን ሌላ መንግሥትና አዲስ መሳፍንታዊ የገዥ መደብ የፈጠሩ በአገሩ ከልዩ ልዩ ብሔረሰቦችና ክፍለ ሀገራት የተውጣጡ ምርጥ የአገው ነገሥታት ወታደሮች ነበሩ[2]። ሦስተኛ፣ በመካከለኛው ክፍለ ዘመን የኢትዮጵያን ብሔራዊ አንድነትና የማዕከላዊ መንግሥት ኃይልና ሥልጣን በአገሩ አስከብረው የሚኖሩና በወል ጨዋ ተብለው የሚጠሩ ምርጥ ንጉሣዊ የወታደር ድርጅቶች እንደነበሩ ይታወሳል[3]።

አራተኛ፣ እንዲሁም በመካከለኛው ክፍለ ዘመን በምሥራቅ ኢትዮጵያ ሙያቸውና ተግባራቸው ውጊያና ጦርነት የሆነ መለሳይ ተብለው የሚጠሩ ወዶ ዘማች የሐረር ወይም አዳል ወታደሮች ነበሩ። በአሥራ ስድስተኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ የመለሳይ ወታደሮችና የጦር አለቆች በኢማም አህመድ ግራኝ መሪነት የአገሩን ማዕከላዊ የነገሥታትና የሱልጣኖች ኃይል በጦር ደመሰሱ።[4]

1 E. Littmann, tr. and ed; *Sabaische, Griechische Und Altabessinische Inschriften* in *Deutsche Aksum Expedition Band IV* (1913), Inscriptions Numbers 4, 6, 7, 8, 9, 10, 11, pp. 4-35

2 አጥሜ ጊዮርጊስ፣ የጋላ ታሪክ (በሁለት ቅጾች ከ1907 በፊት ተጽፎ ያልታተመ ጽሑፍ)፣ ቅጽ 1፣ ገጽ 29።

3 J. Perruchon, tr. and ed; *Les Chronique de Zara Yaqob et de Baeda Maryam* (1893), pp. 31, 45; ታሪክ ንጉሥ ሠርፀ ድንግል *Historia Regis Sarsa Dengel* (Malak Sagad) (1563-1597), tr. and ed; by Conti Rossini (1907);
ተክለ ሥላሴ (ጸሐፊ ትእዛዝ)፣ የአጼ ሱስንዮስ ታሪክ (ያልታተመ ዜና መዋዕል)፣ ምዕራፍ 23፣ 29።

4 Arab-Faiqh, *Conquete'* pp. 111-120.



ምንም በሃይማኖት እስላሞች ቢሆኑ የመለሳይ ወታደሮችና የጦር አለቆች በቅጥር ውል የሥልጣን ባላንጣዎቹን ደምስሰው በ1563 ክርስቲያኑን መስፍን አጼ ሠርፀ ድንግልን በዙፋኑ ላይ አወጡት[5]። በተጨማሪም በ1577 በአጼ ሠርፀ ድንግል ተቀጥረው የመለሳይ ወታደሮችና የጦር አለቆች የራሳቸውን መሪ ሱልጣን መሐመድን በዋቢ ሸለቆ ጦርነት ወጉት[6]። እንዲሁም በ1578 በአጼ ሠርፀ ድንግል መሪነትና አዝማችነት ከጨዋና ሉባ ተብለው ከሚጠሩ ከኦሮሞ ወታደሮች ጋር በአንድነት ተሰልፈው የመለሳይ ወታደሮችና የጦር አለቆች በሰራዬ ጦርነት የቱርክ ወራሪዎችን ደመሰሱ።[7]

አምስተኛ፣ የወረራ ውጊያንና ጦርነትን ሙያውና ተግባሩ ያደረገውና ሉባ ተብሎ የሚጠራው የኦሮሞ ጦር ከ1520 እስከ 1600 ድረስ በ80 ዓመታት በደቡብ ከቦረና አንስቶ ዘላን ብሔረሰቡን በአገር አቀፍ ደረጃ እንደአሰራጨው በዚህ ጥናት ከዚህ በላይ በአጭርና በአጠቃላይ አይተናል። ስድስተኛ፣ በአሥራ ዘጠነኛው ምዕተ ዓመት የምኒልክ የገንደበል ወይም የነፍጠኛ ጦር በአንድ በኩል የኢትዮጵያን ምድርና ሕዝብ በአንድ ማዕከላዊ መንግሥትና ብሔራዊ ሥርዓት ሥር እንደአደራጀ በሌላ በኩል ደግሞ ኢምፔሪያሊስቶችን በአድዋ ጦር ሜዳ አሸንፎ እንደመለሰ ታሪክ የመዘገበው ነገር ነው።

የኢጣሊያን ፋሽስቶች በመትረየስ፣ በመድፍ፣ በታንክ፣ በቦምብ፣ በአይሮፕላንና በመርዛም ጋዝ በ1928 የኢትዮጵያን በዘመናዊ መሣሪያና ትምህርት ያልተደራጀውን የነፍጠኛ ጦር በትግራይና በኦጋዴን ጦር ሜዳዎች አሸንፈው አገሩንም በኃይል ለአጭር ጊዜ ለመያዝ ቻሉ። ከኢጣሊያን ፋሽስቶች ጋር በተካሄደው ብሔራዊ ነፃነት ትግል ወቅትና ሂደት በሐምሌ 1932 የኢትዮጵያ አዲሱ ብሔራዊና ዘመናዊ ጦር በሱዳን አገር በካርቱም ከተማ ተፈጠረ። አዲሱ ነፃ አውጭው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ጦር ከኢትዮጵያ አርበኞችና ከእንግሊዝ የጋራ ሕብረት አገሮች ወታደሮች ጋር ተባብሮ ወራሪ የኢጣሊያን ፋሽስቶችን ከአንድ ዓመት ባነሰ ጊዜ ውስጥ ከአገሩ አስወጣው።

ከዚያ በኋላ፣ በድህረ ጦርነት የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጦር በእንግሊዝ አማካሪዎች ሥር ያደራጁና ያሰለጠኑ የኢትዮጵያ የመጀመሪያ የጦር አሰልጣኞችና መኮንኖች የቀድሞ የነፍጠኛ የጦር አለቆችና የነፃነት አርበኞች መሪዎች ነበሩ። በዚህ ሽግግራዊ ወቅት መሳፍንታዊ የገዥው መደብ መሪዎችና አባሎች የዘመናዊ ጦር ትምህርት፣ ሙያና ተግባር የጐሣና የሃይማኖት ልዩነት ሳያደርጉ ለገባርና ለገበሬ ልጆች በመተው ራሳቸውን በአስተዳደር፣ በንግድ፣ በገንዘብና በመሬት ጉዳይ ላይ ማስማራት ጀመሩ። በዚህ ታሪካዊ ሁኔታና ሂደት አዲሱ የኢትዮጵያ ዘመናዊ ጦር ከአገሩ ሠርቶ አደር መደብ በተለይ ከገባሩና ከገበሬው ክፍል ወጣ ወይም ተፈጠረ። ስለዚህ በኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮት ፍንዳታና ሂደት በኢትዮጵያ መለዮ ለባሹና በአርሶ አደሩ መካከል የተፈጠረው ወሳኙ

5 ታሪክ ንጉሥ ሠርፀ ድንግል፣ ክፍል 2።

6 ታሪክ ንጉሥ ሠርፀ ድንግል፣ ክፍል 6።

7 ታሪክ ንጉሥ ሠርፀ ድንግል፣ ክፍል 7

ብሔራዊና መደባዊ ፣ ፖለቲካዊና አብዮታዊ የትግል አንድነት የአገሩን ታሪክ በመፍራና በጊዜ ለሚያውቅ የሚያስገርም ነገር አይሆንም ።

በዚህ አኳያ የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮት በየካቲት 1966 በድንገት እንደ እሳት ጎሞራ ከፈነዳ በኋላ የወደቀው የጉልተኛ መደብና መንግሥት መሰሪ ለባዥን ክፍል ይዞ አብዮቱንና የአብዮት ኃይሎችን ለመደምሰስ እስከ ሰኔ 21 ቀን 1966 ለአምስት ወራት ያልተሳካ ሙከራ አደረገ ። ነገር ግን በሰኔ 21 ቀን 1966 ከተለያዩ የመለዮለባሽ ክፍሎች ማለትም ከጦርና ከፖሊስ ኃይሎች በዲሞክራሲያዊ ምርጫ ተመርጠው ወደ አዲስ አበባ የተላኩ ወጣት መኮንኖችና ወታደሮች በብልሁና በቆራጡ አብዮታዊ ወጣት መኮንን በሻለቃ መንግሥቱ ኃይለማርያም (1933—) መሪነት በአዲስ አበባ ከተማ በአራተኛ ክፍለ ጦር ዋና መምሪያ ውስጥ ተሰብስበው "ኢትዮጵያ ትቅደም" በሚል ታሪካዊ መርሆ አንድ የጦርና የፖሊስ ኃይሎች አስተባባሪ ኮሚቴ ወይም ወታደራዊ ደርግ መሠረቱ[8] ።

## 1. ለ. የወታደሩ አብዮታዊ ፖሊሲና ፕሮግራም

ከሰኔ 21 ቀን 1966 እስከ መስከረም 1 ቀን 1967 ድረስ በ75 ቀናት ውስጥ ወታደራዊው አስተባባሪ ኮሚቴ ማለትም ደርግ 1/ በወደቀው መንግሥት ሕግና ፖሊሲ መሠረት በመፍራ ፣ በድርጅት ፣ በትምህርት ፣ በዓላማና በአመለካከት ተለያይተው በሚኖሩ በመለዮለባሽ ክፍሎችና አካላት መካከል "ኢትዮጵያ ትቅደም" በሚለው መርሆ መሠረት አዲስ ብሔራዊ ዓላማና ሕብረት ፈጠረ ። 2/ ቀንደኛ የነበሩትን በብዙ መቶ የሚቆጠሩ የጉልተኛው መደብና መንግሥት መሪዎችንና አባሎች በከፍተኛ ጥበብ በቁጥጥር ሥር አዋለ ። ከዚያ በኋላ በመስከረም 2 ቀን 1967 ደርጉ ንጉሡን ከዙፋን አውርዶ አድኃሪ ሕገ መንግሥቱን ከማገዱም በላይ የንጉሡን አድኃሪ ፓርላማንም ጨምሮ ዘጋ ። ቀጥሎ በመስከረም 5 ቀን 1967 የጦርና የፖሊስ ኃይሎች አስተባባሪ ኮሚቴ የኢትዮጵያ ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ በሚል ስም የአገሩ ድርጅታዊ ርዕሰ ብሔር ሆነ ።

በሊቀ መንበር የሚመራው የኢትዮጵያ ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ወይም መንግሥት የአገሩ ርዕሰ ብሔር ከሆነ በኋላ አዲስ የኢትዮጵያ ሕብረተሰብ ለመገንባት በተከታታይ አያሌ አብዮታዊ እርምጃዎችን ወሰደ ። በዚህ አንፃር ፣ አንደኛ በጥቅምት 8 ቀን 1967 ደርግ የዕድገት በሕብረት የትምህርትና የሥራ ዘመቻ አወጀ ። በዚህ መሠረት ከታህሣሥ 1967 ጀምሮ በሁለት ዓመታት ውስጥ 56.000 ተማሪዎች ፣ አስተማሪዎችና ወታደሮች በገጠር በጉልተኞች ላይ እርስ አደሮችን በማስተማርና በማደራጀት በገጠሪቱ ኢትዮጵያ የመደብ ጦርነት አቀጣጠሉ ። ብሎም ታሪካዊውን የገጠር መሬት አዋጅን በሥራ በማዋል ረገድ ወሳኝ ታሪካዊ ሚና ተጫውተው ተመለሱ ። በዘመቻው ውቅት 116 ወጣቶች ለኢትዮጵያ ጭቁኖች መደባዊ አርነት አብዮታዊ ሰማዕታት ሆኑ

---

8 ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ፣ የትግል ምዕራፍ (መስከረም 2 ቀን 1968) ፣ ገጽ 21—25 ።



ሠንጠረዥ 8

መንግሥታዊ የግብርና ፣ የንግድ ፣ የእርሻ ፣ የምርትና የማከፋፈያ ድርጅቶች ከነካፒታላቸው ከ1967 እስከ 1973

| ተራ ቁ. | የግብርና ፣ የንግድ ፣ የምርትና የማከፋፈያ ድርጅቶች | የማቋቋሚያ ሕግ አዋጅ ቁጥር | የካፒታል መጠን በሚሊዮን ብር | |
|---|---|---|---|---|
| | | | የመነሻ ካፒታል | የተፈቀደለት ካፒታል |
| 1 | የብሔራዊ ጨርቃ ጨርቅ ድርጅት | ደንብ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር 7/1967 | 119.163.692.34 | 20.000.000.00 |
| 2 | የኢትዮጵያ ማተሚያ ድርጅት | ደንብ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር 8/1967 | 6.300.000.00 | 8.000.000.00 |
| 3 | የኢትዮጵያ ምግብ ድርጅት | ደንብ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር 9/1967 | 12.161.039.00 | 25.000.000.00 |
| 4 | የብሔራዊ ብረታ ብረት ሥራዎች ድርጅት | ደንብ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር 10/1967 | 26.029.582.00 | 55.000.000.00 |
| 5 | የኢትዮጵያ የመጠጥ ድርጅት | ደንብ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር 11/1967 | 29.343.790.95 | 60.000.000.00 |
| 6 | ብሔራዊ ማመላለሻ ድርጅት | ደንብ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር 12/1967 | 9.506.230.00 | 20.000.000.00 |
| 7 | የኢትዮጵያ የሀገር ውስጥ ማከፋፈያ ድርጅት | ደንብ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር 13/1967 | 5.000.000.00 | 10.000.000.00 |
| 8 | የኢትዮጵያ አስመጪና ላኪ ድርጅት | ደንብ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር 14/1967 | 1.500.000.00 | 5.000.000.00 |
| 9 | የብሔራዊ ቆዳና ጫማ ድርጅት | ደንብ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር 15/1967 | 20.802.804.30 | 40.000.000.00 |
| 10 | የብሔራዊ ቃጫ ሥራዎች ድርጅት | ደንብ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር 16/1967 | 11.305.863.74 | 20.000.000.00 |
| 11 | የኢትዮጵያ ሆቴሎችና ቱሪዝም ድርጅት | ደንብ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር 21/1967 | 83.853.500.00 | 100.000.000.00 |
| 12 | የኢትዮጵያ ጨው ድርጅት | ደንብ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር 24/1967 | 6.482.600.00 | 15.000.000.00 |
| 13 | ብሔራዊ የማዕድን ድርጅት | ደንብ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር 26/1968 | 4.288.700.00 | 10.000.000.00 |
| 14 | ላይኛው አዋሽ የእርሻ ልማት ድርጅት | ደንብ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር 27/1968 | 8.400.000.00 | 15.000.000.00 |
| 15 | መካከለኛው አዋሽ የእርሻ ልማት ድርጅት | ደንብ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር 28/1968 | 2.967.200.00 | 8.000.000.00 |
| 16 | ሰሜን ሸለቆ የእርሻ ልማት ድርጅት | ደንብ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር 29/1968 | 7.000.000.00 | 14.000.000.00 |
| 17 | የሐረርጌ የእርሻ ልማት ድርጅት | ደንብ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር 32/1968 | 949.000.00 | 5.000.000.00 |
| 18 | ተንዳሆ የእርሻ ልማት ድርጅት | ደንብ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር 33/1968 | 16.952.000.00 | 40.000.000.00 |
| 19 | የኢትዮጵያ የልማት መገልገያዎች ድርጅት | ደንብ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር 34/1968 | 2.813.000.00 | 6.000.000.00 |
| 20 | የጥጥ የእርሻ ልማት ድርጅት | ደንብ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር 37/1968 | 3.000.000.00 | 10.000.000.00 |
| 21 | የኢትዮጵያ ሸቀጣ ሸቀጦች ድርጅት | ደንብ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር 38/1968 | 1.400.000.00 | 5.000.000.00 |
| 22 | የኢትዮጵያ የሥጋ ድርጅት | ደንብ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር 58/1970 | 100.000.00 | 10.000.000.00 |
| 23 | የኢትዮጵያ የእንጨት ሥራ ድርጅት | ደንብ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር 58/1970 | 100.000.00 | 10.000.000.00 |
| 24 | የኢትዮጵያ የመድን ድርጅት | አዋጅ ቁጥር 68/1968 | 11.000.000.00 | |
| 25 | የቤት ሥራ ድርጅት | አዋጅ ቁጥር 82/1968 | 700.000.00 | 4.000.000.00 |
| 26 | የቡና መጫ ማምረቻና ገበያ ድርጅት | አዋጅ ቁጥር 94/1968 | 250.000.00 | 3.500.000.00 |
| 27 | የእርሻ ሰብል ገበያ ድርጅት | አዋጅ ቁጥር 165/1969 | 21.070.000.00 | 100.000.000.00 |
| 28 | የኢትዮጵያ የስኳር ድርጅት | ደንብ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር 59/1970 | 500.000.00 | 200.000.000.00 |
| 29 | የኢትዮጵያ ዘርና ገበያ ድርጅት | ደንብ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር 59/1970 | 9.733.000.00 | 80.000.000.00 |
| 30 | ብሔራዊ የኬሚካል ድርጅት | ደንብ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር 59/1971 | 11.300.000.00 | 80.000.000.00 |
| 31 | የኢትዮጵያ የመድኃኒትና የሕክምና መሣሪያዎች አቅራቢ ድርጅት | አዋጅ ቁጥር 207/1973 | 20.000.000.00 | |
| | | ድምር | 405.220.308.00 | 1.073.500.000.00 |

ሁለተኛ ፡ በታህሣሥ 11 ቀን 1967 አብዮታዊ ደርግ ለኢትዮጵያ የሶሻሊዝም መመሪያ አወጀ ። የመመሪያውም አራት ዋና አላማዎች ፦

በኢኮኖሚ አንጻር ከግል ይዞታ የብዙኃኑን ጥቅም እንዲቀድምና ብዝበዛ እንደማይኖር ፡ እንዲሁም የማምረቻና የማከፋፈያ ድርጅቶችና መሬት የሕዝብ ሀብት መሆን እንዳለባቸው ፡

በሶሻል ረገድ የብሔሮችን እኩልነትና የኢትዮጵያን ባሕሎች በእኩልነት ለማዳበር ፡

በፖለቲካ በኩል ሕዝቡ ራሱን በራሱ ለማስተዳደር እንዲችል ማደራጀት ፡ የማንኛውንም ወገን የውጭ ተጽዕኖ መቋቋም ፡

በውጭ ፖሊሲ ረገድ በሌሎች አገሮች ጉዳይ ጣልቃ አለመግባትና በተለይም የአፍሪካን ሕዝብ ልማት አንድነትና ነፃነት ለማስገኘት በሚደረገው ጥረት መተባበር ናቸው ።

ሶስተኛ ፡ በታህሣሥ 23 ቀን 1967 ደርግ ሶስት የንግድ ባንኮችን ፡ ሶስት የገንዘብ ድርጅቶችንና አሥራ አራት የኢንሹራንስ ኩባንያዎችን ፡ በጥር 26 ቀን 1967 ደግሞ 72 የግል የማምረቻና የማከፋፈያ ድርጅቶችን በሕዝብ ይዞታና በመንግሥት ቁጥጥር ሥር አደረገ ። በሚቀጥሉ ወራትና ዓመታት እነዚህ መሠረታዊ የገንዘብ ፡ የኢንሹራንስ ፡ የማምረቻና የማከፋፈያ ተቋሞች ፡ ኩባንያዎችና ድርጅቶች ከዚህ በላይ በሠንጠረዥ 8 እንደሚታየው በመንግሥት ሥር እንደገና ተደራጁ ።

አራተኛ ፡ በየካቲት 25 ቀን 1967 ደርግ የጉልተኛውን መደብ የኢኮኖሚ መሠረት በመደምሰስ የሰፊውን አርሶ አደር ሕዝብ ከጉልተኛው መደብና ሥርዓት ለአንዴና ለመጨረሻ አርነት ያወጣውን ታላቁን የገጠር መሬት አዋጅ አወጣ። በአጭርና በአጠቃላይ አነጋገር ታላቁ የየካቲት 25 ቀን 1967 የገጠር መሬት አዋጅ በኢትዮጵያ ምድርና ታሪክ ኢያሌ መሠረታዊና በላቂ ሁኔታዎችን ያስከተለ የአርነት ፡ የአንድነት ፡ የፍትሕ ፡ የእኩልነት ፡ የዲሞክራሲ የክብር ፡ የኃይልና የሀብት አዋጅ ነው ።

ከታላቁ የአብዮት ፍንዳታ በፊት የኢትዮጵያ ሕዝብ "ጢሰኛ" ፡ "ገባር" ፡ "ባርያ" ፡ "ባላባት ፡" "ጉልተኛ" ፡ "መኳንንት" ፡ "መስፍን" ፡ ወዘተ...ተብሎ ለዘመናት በመደብ የተከፈለ የበዝባዥና የተበዝባዥ አገርና ሕብረተሰብ ነበር ። የዚህ ሁሉ መሠረትና መነሻ የመሬት ይዞታ ሥሪትና ሥርዓት ነበር ። ታላቁ የየካቲት 25 ቀን 1967 የገጠር መሬት አዋጅ ይህንን ሁሉ ከኢትዮጵያ ምድርና ታሪክ ለአንዴና ለመጨረሻው አስቀረ ። ይህም ብቻ አይደለም ። የኢትዮጵያ ምድር ከ1270 እስከ 1900 ድረስ ለሰባት ምዕተ ዓመታት የገዛት የሥልጣን ፡ የእርስ በርስ ፡ የሃይማኖት ፡ የነገሥታት ፡ የሱልጣኖች ፡ የባላባትና የመሳፍንት ጦርነቶች የተካሄዱበት ታላቅ በሰው አዕምሮና አንደበት መግለጽ የሚያስቸግር የሕይወት ፡ የንብረት ፡ የሀብትና የባህል ጥፋት የተፈጸመበት አገርና ሕብረተሰብ ነበር ። የዚህ ሁሉ ታሪካዊ ምንጭ ፡ መሠረትና ምክንያት መሬት ነበር ። በዘመኑና በሥርዓቱ ፍጻሜ ለዚህ ሁሉ ታሪካዊ ግፍና በደል ታላቁ የየካቲት 25 ቀን 1967 የኢትዮጵያ የገጠር መሬት አዋጅ አብዮታዊ መፍትሄና መድኃኒት አስገኘ ። በመሆኑም አዋጁ የጭቁን መደብ አርነት አዋጅ ነው ።

9 ደርግ ፡ የትግል ምዕራፍ (1968) ፥ ገጽ 54—55 ።



ከዚህ በላይ በሰንጠረዥ 6 በቅድመ አብዮት በኢትዮጵያ በአምስት ልዩ ልዩ ዓይነቶች የተከፈለ የመሬት ግብር እንደ ነበር ተገልጾዋል ። በዚህ ውስብ ስብና ወገናዊ በሆነ ግብር ሕግና ሥርዓት የወደቀው የጉልተኛ መንግሥት ከአብዮት በፊት በ33 ዓመታት ውስጥ ከአገሩ ከ 3.070.750 ጋሻ መሬት በአሥራት ፡ በመሬት ፡ በትምህርት ፡ በጤና ፡ በእርሻ ፡ በከብትና በገበያ ግብር ስም በአንድ ዓመት ሊሰበስብ የቻለው ከፍተኛ የመሬት ግብር ገቢ መጠን በገንዘብ 42.500.000 ብር ብቻ እንደነበር በተጨማሪ ተገልጾዋል ። በአንድ አገርና ሕብረተሰብ ግብር የብሔራዊ ዜግነት ፡ ሀብት ፡ ዲሞክራሲ ፡ እኩልነትና ፍትሕ መሠረትና ምልክት ነው ። ነገር ግን ከዚህ በላይ የተገለጸው የኢትዮጵያ የጉልተኛው መንግሥት የመሬት ይዞታና ግብር ሥርዓት በኢትዮጵያውያን መካከል የዜግነትን የእኩልነትን የዲሞክራሲንና የፍትሕን መብትና ክብር ያጎደለ የግፍ የበደልና የብኩንነት ሕግና ሥርዓት ነበር ። ታላቁና ታሪካዊው የየካቲት 25 ቀን 1967 የኢትዮጵያ የገጠር መሬት አዋጅ ማለትም የአርነትና የነፃነት አዋጅ ለዚህ ሁሉ ችግር ታሪካዊ ብሔራዊና አብዮታዊ መፍትሔ አስገኘ ።

በመጨረሻም ታላቁና ታሪካዊው የየካቲት 25 ቀን 1967 የኢትዮጵያ የገጠር መሬት ማለትም የአርነት አዋጅ የአገሩ የሀብትና የኃይል ምንጭና መሠረት ገጠርና ገበሬ መሆኑን በትክክል በአኃዝና በቁጥር አሳየ ። በዚህ ረገድ ከገጠር መሬት አዋጅ በኋላ በመጀመሪያ ሁለት ዓመታት ዕድገት በሕብረት ዘመቻና አግባብ ባላቸው መንግሥት መሥሪያ ቤቶች አማካይነት በሀያ በሀያ ጋሻ መሬት እየተከለለ የአገሩ የገበሬ ክፍል በአገር አቀፍ ደረጃ በገበሬ ማኅበራት ተደራጀ ።

በዚህ ድርጅታዊ መዋቅርና አሠራር መሠረት በወቅቱ በነበሩ በተገንጣዮችና በሱማሊያ ወራሪ መንግሥት ጦርነቶች ምክንያት የኤርትራ ፡ የሐረርጌና የባሌ አርቦ አደሮች ፡ ከዚህ የሚከተለው ሠንጠረዥ እንደሚያሳየው ፡ ገና ሙሉ በሙሉ ሳይደራጁ በአገሩ ከ7.000.000 በላይ የሚቆጠሩ የገበሬ ቤተሰቦችን በአባልነት የያዙ ከ25.000 የሚበልጡ የገበሬ ማኅበራት ሲቋቋሙ ፤[10] በዚያኑ ወቅት አብዮታዊ መንግሥት ለአገርና ለአብዮት ጥበቃ በመላው አገሩ በዘመናዊ መንገድ የታጠቀና በ500.000 የሚቆጠር የገበሬ የሕዝባዊ ሠራዊት ወይም ሚሊሻ አደራጀ[11] ። በወቅቱ በነበረው ጦርነት ምክንያት ገና የኤርትራ ፡ የሐረርጌና የባሌ ክፍለሀገራት ገበሬዎች ሙሉ በሙሉ በማኅበራት ሳይደራጁ ፡ በ25. 000 000 ማኅበራት ለተደራጁ 7. 000 000 የገበሬ ቤተሰቦች ከባልና ሚስት ሌላ ለእያንዳንዱ ገበሬ ቤተሰብ በአማካይ ሶስት ሶስት ልጆች ብቻ በመመደብ ማለትም ከባልና ሚስት ጋር ለእያንዳንዱ ገበሬ ቤተሰብ አምስት አባሎች በመስጠት 7. 000.000 በ5 ቁጥር ቢበዛ በትንሹ የኢትዮጵያ የገጠር ሕዝብ ብቻ በ35. 000.000 ሊቆጠር እንደሚችል መገመት ይቻላል ። በሌላ በኩል ፡ ከዚህ በታች የአገሩ የከተማ ማኅበራት ምሥረታና ድርጅት በአኃዝና በቁጥር እንደሚያሳየው ፡ በከተማ የሚኖረው የኢትዮጵያ ሕዝብ ብዛት በትንሹ 4.000.000 እንደሚደርስ ይገመታል ። ስለዚህ በ1966 የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮት ከሥርዓት ባርነት አርነት ያወጣው ሕዝብ ብዛት በትንሹ በ40.000.000 የሚገመት ነበር ብሎ ማስብ ከአግባብ ውጭ ላይሆን ይችላል ።

10 በሚያዝያ 1970 የአገሩ የገበሬ ማህበራት በአንድነት በአገር አቀፍ ደረጃ በመላ ኢትዮጵያ ገበሬዎች ማህበር (መኢገማ) ተደራጁ ።

11 ደርግ ፡ የትግል ምዕራፍ ሦስተኛ ዓመት (መስከረም 2 ቀን 1970) ገጽ 1 ፡ 20 ፡

መገለጫ 9

ከገበሬና ከከተማ ማህበራት በተገኘው ማስረጃ መሠረት ፤ በ1966 በአብዮቱ ፍንዳታ ወቅት የኢትዮጵያ ሕዝብ ብዛት ግምት

| ተራ ቁ. | ክፍለ ሀገራት | የገበሬና የከተማ ማህበራት ብዛት | የገበሬ ቤተሰብ ብዛት | የገበሬ ቤተሰቦች ቁጥር በ5 ሲባዛ | ጠቅላላ ሕዝብ ብዛት |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ሸዋ | 6147 | 1.843.000 | 1.843.000×5 | 9.215.000 |
| 2 | ወሎ | 1671 | 968.384 | 968.384×5 | 4.841.920 |
| 3 | ሲዳሞ | 1539 | 627.348 | 627.348×5 | 3.136.740 |
| 4 | ሐረርጌ | 1455 | 582.393 | 582.393×5 | 2.911.965 |
| 5 | ጎጃም | 3033 | 529.678 | 529.678×5 | 2.648.930 |
| 6 | ከፋ | 1646 | 458.442 | 458.442×5 | 2.292.210 |
| 7 | ወለጋ | 2264 | 449.797 | 449.797×5 | 2.248.985 |
| 8 | ጎንደር | 2399 | 427.209 | 427.209×5 | 2.136.045 |
| 9 | ትግራይ | 1268 | 381.471 | 381.471×5 | 1.907.355 |
| 10 | ጋሞጎፋ | 720 | 240.472 | 240.472×5 | 1.202.360 |
| 11 | አርሲ | 1132 | 207.246 | 207.246×5 | 1.036.230 |
| 12 | ኢሉባቦር | 984 | 193.449 | 193.449×5 | 967.245 |
| 13 | ባሌ | 498 | 59.045 | 59.045×5 | 295.225 |
| 14 | ኤርትራ | 12 | 5.000 | 5.000×5 | 25.000 |
| | ድምር | 25001 | 7.075.588 | 7.075.588×5 | 35.377.940 |
| 15 | የአዲስ አበባ ከተማ | የከተማ ማህበራት ብዛት 288 | የሰው ብዛት 1.200.000 | 1.200.000 | 1.200.000 |
| 16 | 314 የክ/ሀ ከተሞች | የከተማ ማህበራት ብዛት 969 | የሰው ብዛት 2.623.244 | 2.623.244 | 2.623.244 |
| | ጠቅላላ ድምር | 26 258 የገበሬና የከተማ ማህበራት | | የገጠርና የከተማ ሕዝብ ብዛት በከፊል[12] | 39.201.184 |

የተገኘበት ፤ ከየካቲት እስከ የካቲት (1969) ፤ አዲስ ዘመን (ሐምሌ 21 ቀን 1973) ፤ በትንተና ።

12

ማስገንዘቢያ ፤ ዛሬ በ1975 በኤርትራና በትግራይ በባሌና በሐረርጌ ክፍለ ሀገራት የገበሬ ማህበራት በብዛትም በጥራትም ከ1969 በበለጠ ደረጃ መደራጀታቸው በግልጽ የታወቀ ነገር ስለሆነ ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጠቅላላ ብዛት በዚህ መገለጫ ላይ ከተመለከተው ከ40,000,000 ይበልጥ እንደሆነ እንጂ ያንሳል ማለት አስቸጋሪ ጉዳይ ነው ። ያም ሆነ ይህ ትክክለኛውን የሕዝብ ብዛት ጊዜና ታሪክ ነገ ያሳያል ። እስከዚያ ጊዜ ድረስ በዚህ ጥናት ይህ ጊዜያዊ ግምት በፍርሃል ።



አምስተኛ፥ በሐምሌ 19 ቀን 1967 ደርግ በኢትዮጵያ የከተማ ቦታና ትርፍ ቤቶችን በሰፊ አዋጅ በመንግሥት ቁጥጥር ሥር የኢትዮጵያ ሕዝብ የጋራ ሀብትና ንብረት አደረገ ። የገጠር መሬት አዋጅ ለገበሬ ማህበራት ድርጅት ታሪካዊ መነሻና ምክንያት እንደሆነ ሁሉ ሐምሌ 19 ቀን 1967 የከተማ ቦታና የትርፍ ቤቶች አዋጅ ደግሞ ለኢትዮጵያ ከተማ ነዋሪዎች ማህበራት (ከነማት) ምሥረታና ድርጅት ሕጋዊና ታሪካዊ መሠረትና ምክንያት ሆነ ። በአገሩ ከ1967 እስከ 1971 ድረስ በአብዮቱና በፀረ አብዮት ኃይላት መካከል በሚደረገው ታላቅ መደባዊ ጦርነት የኢትዮጵያ ከነማት ከመኢሶንና ከመላ ኢትዮጵያ ሠራተኞች ማህበር (መኢሠማ) ጋር የሚጫወቱትን ታላቅ ሕዝባዊና አብዮታዊ ሚና ከዚህ በታች አግባብ ባለው ምዕራፍና ጊዜ እናያለን ።

ስድስተኛ፥ በሚያዝያ 12 ቀን 1968 ደርግ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም (መሰረተኛ ፕሮግራም) ከማውጣቱም በላይ በተጨማሪም የሕዝብ ጉዳይ ጊዜያዊ ጽሕፈት ቤት (የሕዝብ ድርጅት ጽሕፈት ቤት) በአዋጅ አቋቋመ ። ከሰኔ 21 ቀን 1966 ጀምሮ "ኢትዮጵያ ትቅደም" በሚል መርሆ ሕዝባዊ አብዮቱን ሲመራ የቆየው አብዮታዊ ደርግ በሚያዝያ 12 ቀን 1968 መሰረተኛ ፕሮግራም ፊውዳሊዝም፥ ኢምፔሪያሊዝምና ቢሮክራቲክ ካፒታሊዝም የኢትዮጵያ ሦስት ደመኛ የመደብ ጠላቶች ናቸው የሚል ግልጽና ሥር ነቀል የሆነ የፖለቲካ አቋምና ፖሊሲ ወሰደ ። ይህ የደርጉ ሥር ነቀል ፖሊሲ በኢትዮጵያ አብዮትና ሕዝብ ላይ የውስጥና የውጭ አድኃሪ ኃይላትን አስተባበረ ።

## 1. ሐ. ፀረ አብዮት ኃይላት

### 1. ሐ. 1. የአብዮቱ የውስጥ ተቃዋሚ ጠላቶች

በአጭርና በአጠቃላይ አነጋገር ከዚህ በላይ የተገለፁ የደርጉ የዕድገት በሕብረት ዘመቻ፥ የሶሻሊዝም ፍልስፍና፥ የገንዘብ፥ የንግድ፥ የምርትና የግል ፋብሪካ ድርጅቶች ውርስ፥ የገጠር መሬት አዋጅ፥ የከተማ ቦታና የትርፍ ቤቶች አዋጅ፥ የመሰረተኛ ፕሮግራም አዋጅና የሕዝብ ድርጅት ጽሕፈት ቤት አዋጅ እርምጃዎች የኢትዮጵያን ምድር፥ ሕዝብና ሕብረተሰብ ከላይ እስከታች በሁለት ተፃራሪ መደቦች ማለትም በአብዮቱና በፀረ አብዮት ሠፈሮች በመከፈል አገሩን ታላቅ የመደቦች ጦርነት ሜዳ አደረጉት ።

በዚህ አኳያ አንደኛ፥ ራሱን የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ) ብሎ የሚጠራ አንድ ስውር ድርጅት ደርግን በመገርሰስ ኃይል ከሥልጣን አውርዶ በትረ መንግሥቱን እይዛለሁ በሚል ዓላማና ምኞት በአገር አቀፍ ደረጃ የፖለቲካ ግድያና የኢኮኖሚ አሻጥር ጀመረ ። የአገሩን ወጣቶች ወደ ወንጀልና ሞት አሰማራ ። በኢትዮጵያ ብሔራዊ ህልውና ነፃነትና አንድነት ላይ ከኤርትራ ተገንጣዮችና ከሱማሊያ ወራሪ መንግሥት ጋር የጦርነት ግምባር ፈጠረ ። በዓለም መድረክ ላይ የኢትዮጵያ የአብዮት አመራር ፋሺዝም ነው የሚል ዓለም አቀፍ ቅስቀሳ አካሄደ ። የአገሩን የመኢሠማ፥ የመኢሶን፥ የከነማትና የሕዝብ ድርጅት ጽሕፈት ቤት አባሎችንና መሪዎችን እንዲሁም ምሁራንና የመንግሥት ባለሥልጣናት በብዙ ገደለ ። የገንዘብ፥ የንግድ፥ የምርት፥

የማከፋፈያ ፣ የመገናኛ ፣ የትራንስፖርትና የትምህርት መገልገያዎችን ተቋሞችን ድርጅቶችን እንዲሁም ታሪካዊ መዛግብትን በማጥፋት በአገሩ ላይ ከፍተኛ የሆነ የኢኮኖሚና የባህል አሻጥር ፈጸሙ ።

ሁለተኛ ፣ ከመንግሥት ሥልጣንና ሥራ የተባረሩ የገጠር መሬት ፣ የከተማ ቦታና ትርፍ ቤት እንዲሁም የገንዘብና የምርት መሣሪያዎችና ድርጅቶች በአብዮታዊ ሕግና ውሳኔ የተወሰደባቸው የቀድሞ ጉልተኞች ፣ ባለባቶች ፣ መሳፍንቶች ፣ መኳንንቶች ፣ ሹማምንቶችና ከበርቴዎች በሕብረት የኢትዮጵያ ዲሞክራቲክ ዩኒአን (ኢ.ዲ.ዩ) በሚል አድሃሪና ቀልባሽ ድርጅት ሥር በአገርና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተደራጅተው በኢትዮጵያ አብዮትና ብሔራዊ ነፃነት ላይ ጦርነት ከፈቱ ። በሱዳን መንግሥት ፈቃድ ከዚያ ጐረቤት አገር ከእምዱርማን ሬዲዮ ጣቢያ የፕሮፓጋንዳ ዘመቻ በኢትዮጵያ ምድር ላይ አስተጋቡ ። በተጨማሪ ከሱዳን ጠረፍ በወረራ ገብተው በ1969 የጐንደር ክፍለ ሀገርን በከፊል ያዙ ።

ሦስተኛ ፣ ኢሕአፓና ኢዲዩ ከኤርትራ ተገንጣዮችና ከሱማሊያ ወረራ መንግሥት ጋር ግምባር ፈጥረው በኢትዮጵያ አብዮትና አገር ላይ እንደዚሁ በየአከባቢው የወረራ ጦርነት ፣ የፖለቲካ ግድያና የኢኮኖሚ አሻጥር ሲያካሄዱ ፣ በአዲስ አበባ ከተማ ደርግ ራሱ አንድ ታላቅ የመደብና የሥልጣን ጦርነት ሜዳና መድረክ ሆነ ። በዚህ አኳያ ለምሳሌ የአብዮቱን ሥር ነቀል ሕዝባዊ ይዘትና ሂደት ለመለወጥ ፣ የገጠርና የከተማ መሬት አዋጅ ለመለወጥ ፣ በመለስተኛ ፕሮግራም የታወጀውን የአገሩን የብሔረሰቦች አንድነትና እኩልነት ፖሊሲ በመቃወም ፣ አገሩን ከሶሻሊስት ጐዳና ወደ ኢምፔሪያሊዝምና ካፒታሊዝም መንገድና ሠፈር ለመመለስ ብሎም የኢሕአፓንና የኢዲዩን ክፍሎችና አባላት ወደ መንግሥት ሥልጣን ለማምጣት በሐምሌ 1968 እና በጥር 1969 በደርጉ ውስጥ በፀረ አብዮት ወገን መሪዎችና አባላት በከፍተኛ ደረጃ የተቀነባበሩ ሁለት ተከታታይ ኩዴታዎች ማለትም የመንግሥት ግልበጣ ሴራዎች በደርጉ በጓድ ሊቀ መንበር መንግሥቱ ኃይለማርያም በሚመራው አብዮታዊ ወገን ኃይል ከሸፈ ።

የደርጉ ፀረ አብዮተኞች ለሁለተኛው ጊዜ ያካሄዱት የመንግሥት ግልበጣ ሙከራ በጥር 26 ቀን 1969 በደርጉ አብዮታዊ ክንፍና ኃይል ከተደመሰሰ በኋላ አብዮቱ በመሀል አገር በኢሕአፓና በኢዲዩ ፀረ አብዮት ክፍሎችና ኃይላት ላይ በወሳኝ መልሪያ ትግል የኃይል ሚዛንና ድል መገኘት ጀመረ ። በዚህ ረገድ አብዮታዊ መንግሥት በሕዝብ ድርጅት ጽሕፈት ቤት አማካይነት በአገር አቀፍ ደረጃ ለተደራጁ ለመኢገማ ፣ ለመኢሠማና ለከነማት ሕዝባዊ ድርጅቶችና አባላት በኢሕአፓና በኢዲዩ ላይ መሣሪያ ሰጣቸው ። እንደዚሁ የታጠቁ ሕዝባዊና መንግሥታዊ ድርጅቶች በአጭር ጊዜ ውስጥ ማለትም በ1969 የኢሕአፓንና የኢዲዩን ድርጅታዊ መዋቅርና አሠራር በመሣሪያ ኃይል በመደምሰስ አብዮቱን ወሳኝ በሆነ ወቅትና መንገድ ከውስጥ ቀልባሽ ኃይላትና ጠላቶች አዳኑት ። ቀጥሎ የኢትዮጵያ አብዮታዊ መንግሥትና ሕዝብ ብሔራዊ ቁጣውን ፣ ኃይሉንና ክንዱን ከመሀል አገር በምሥራቅ ፣ በደቡብ ምሥራቅና በሰሜን ጦር ግምባሮች ወደ ሱማሊያ ወራሪዎችና ወደ ኤርትራ ተገንጣዮች አዞረ ።



## 1. ሐ. 2. የሱማሊያ ወራሪ መንግሥት

የሱማሊያ ወራሪ መንግሥት ከኢትዮጵያ የአገሩን አንድ ሦስተኛ የሚሆነውን የኦጋዴን ክፍልና የኬንያን ሰሜናዊ ክፍል ከጅቡቲ ጋር ጨምሬ "ታላቅ የሱማሊያ አገር" እፈጥራለሁ በሚል ብሔራዊ ግላግና አትድ መሠረት ፣ እስከ 1969 ድረስ ለአሥራ ሰባት ዓመታት በአከባቢው የሳይንሳዊ ሶሻሊዝም ሥርዓት እከታተላለሁ በሚል ማታለያ ዘዴ ከሶቪዬት ሕብረት ሩሲያ በአገኘው ዘመናዊ የጦር መሣሪያ ብሔራዊ ጦሩን ለወረራ ጦርነት አደራጀ ። ይህንን የሱማሊያ ብሔራዊ የወረራ ፖሊሲና ዝግጅት በትክክል የሚያውቀው የኢትዮጵያ አብዮታዊ መንግሥት የአገሩን ዘውዳዊ ሥርዓት ደምስሶ በትረ መንግሥቱን ከያዘ በኋላ ወዲያውኑ በታህሣሥ 1967 በቀየሰው በአገሩ አዲስ ሶሻሊስት ፍልስፍናና ብሔራዊ ፖሊሲ መመሪያ ሱማሊያን ጭምር ለአፍሪካ ቀንድ አገሮች በሙሉ ለተበሊያዊ ሕብረትና ትብብር ጥሪ አቀረበ ።

ነገር ግን ወራሪው የሱማሊያ መንግሥት በፕሬዝዳንት ዚያድ ባሬ መሪነት ከአብዮታዊት ኢትዮጵያ የቀረበውን የአፍሪካ ቀንድ ሰላም ፣ ፀጥታ ፣ ሕብረትና ትብብር ጥሪ ባለመቀበል የኢትዮጵያ ሕዝብና መንግሥት በሰሜን በኤርትራ ተገንጣዮች በምዕራብ በኢዲዩ ወንበዴዎችና በሱዳን ደጋፊዎች በመሀል ደግሞ በኢሕአፓ ፀረ አብዮተኞችና ሽብረ ፈጣሪዎች በሁሉም አካባቢ ተወጥሮ በነበረበት ጊዜ በታላቅ ብሔራዊ መከራና ጭንቀት ወቅት በአካባቢው አድሃሪ የአረብ መንግሥታት እርዳታ የኢትዮጵያን በምሥራቅና በደቡብ ምሥራቅ ክልሎች በታች የሚገኙትን ክፍል ሕዝቦችና ብሔረሰቦች በመሣሪያ ኃይል [illegible] በሚል እምነት ከ1969 ኢጋማሽ ጀምር በኢትዮጵያ ላይ የወረራ ዝግጅትና ሥምሪት ጀመረ ። ይሁን እንጂ የሱማሊያን የወረራ ጦርነት ለመቋቋም የኢትዮጵያ አብዮታዊ መንግሥትና ሕዝብ በአፋጣኝ አያሌና ወሳኝ ብሔራዊ ፣ ወታደራዊና ዲፕሎማሲያዊ እርምጃዎች ወሰደ ።

አንደኛ ፣ አብዮታዊ መንግሥት በውጭ ፖሊሲ ግምባር ለኢትዮጵያ አብዮትና ብሔራዊ ህልውና ነፃነትና አንድነት በአድሃሪያንና በኢምፔሪያሊስቶች ዓለም አቀፍ ሴራና ከበባ ላይ የዓለም የሶሻሊስት አገሮችንና የተራማጅ ኃይሎችን የሞራልና የማቴሪያል እርዳታ ለማግኘት ወሳኝ ብሔራዊ ዘመቻ አካሄደ ። በዚህ ዘመቻ መሠረት ሶቪዬት ሕብረት ሩሲያ ፣ የኩባ ፣ የየመን ፣ የምሥራቅ ጀርመንና ሌሎችም ሶሻሊስት አገሮች ፣ መንግሥታትና ሕዝቦች በአድሃሪያንና በኢምፔሪያሊስቶች ሴራና ከበባ ላይ ከኢትዮጵያ አብዮታዊ መንግሥትና ሕዝብ ጐን ተሰለፉ ።

ሁለተኛ ፣ በሚያዝያ 4 ቀን 1969 ለኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ በሬዲዮና በቴሌቪዥን በአስሙት ታሪካዊ ንግግር ጓድ ሊቀ መንበር መንግሥቱ ኃይለማርያም "ታፍራና ተከብራ የኖረችው ኢትዮጵያ ተደፍራለች!" በማለት የእናት አገር ጥሪ አሳለፉ ። በዚህ ጥሪ መሠረት የኢትዮጵያ ሕዝብ ቀፎው እንደ ተመታ ንብ አብዮቱንና እናት አገሩን ከአድሃሪያንና ከኢምፔሪያሊስቶች ሴራና ወረራ ለማዳን "እናት ኢትዮጵያ ወይም ሞት" በሚል መፈክርና መርሆ ሥር ለሕጋዊና ትክክለኛ ጦርነት ከዳር እስከ ዳር እንደ አንድ ሰው ተነሳ ።

ሦስተኛ ፣ ከጓድ ሊቀ መንበር መንግሥቱ እናት አገር ጥሪ በኋላ አብዮታዊ መንግሥት በአዲስ አበባ ከተማ በስተምዕራብ ዳር በጦር ሥጋ ሜዳ ላይ ከነበ

ሎዎች ፣ ከሠራተኞችና ከከተማ ነዋሪዎች የተወጣጡ የሚሊሺያ ማለትም የሕዝባዊ ጦር አባሎች በዘመናዊ ወታደርነት ትምህርትና ሙያ በፍጥነት የሚሰለጥኑበት የታጠቅ ጦር ሠፈር መሠረተ ። በዚህ ታሪካዊ ጦር ሠፈር እስከ ሰኔ 18 ቀን 1969 በሁለት ወራት ውስጥ በ300,000 የሚቆጠሩና ከአገሩ ከ80 በላይ ብሔረሰቦችና ጎሳዎች የተወጣጡ የኢትዮጵያ የሕዝባዊ ሠራዊት አባሎች በዘመናዊ የጦር መሣሪያ አጠቃቀምና በጦርነት ሳይንስ ሰልጥነው ለዘመቻ ግዳጅና ሥምሪት ተዘጋጁ ።

አራተኛ ፣ የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮት በ1966 ከመፈንዳቱ በፊት ለ22 ዓመታት የኢትዮጵያን የጉልተኛ መንግሥት በተጽዕኖ ሥር አድርጐ የኖረው የአሜሪካን መንግሥት ከአብዮቱ ፍንዳታ በኋላ ከውስጥና ከውጭ በኢትዮጵያ አብዮትና ብሔራዊ አንድነት ላይ የሚያሴሩትን ኃይላትና መንግሥታት በልዩ ልዩ መንገድ ከመርዳቱም በላይ ፣ እንደ አውሮፓ ዘመን አቆጣጠር በ1953 በሁለቱ አገሮች መካከል በተደረገውና ለሀያ አምስት ዓመታት ጊዜ በሚቆየው በወታደራዊና በመሣሪያ ስምምነት ውል መሠረት የኢትዮጵያ አብዮታዊ መንግሥት ዋጋውን በቅድሚያ የከፈለበትን የጦር መሣሪያ አልሰጥም ከማለት አልፎ በወቅቱ ከኢሕአፓ ፣ ከኢዲዩና ከኤርትራ ገንጣዮች ጋር ተባብረው የኢትዮጵያን አብዮትና ብሔራዊ ሀልውና በመሣሪያ ለማጥፋት በከፍተኛ ዝግጅት ላይ ለነበሩ ለሱማሊያና ለሱዳን መንግሥታት የመሣሪያና የፖለቲካ ድጋፍ በመስጠቱ በሚያዝያ 13 ቀን 1969 የኢትዮጵያ አብዮታዊ መንግሥት ቃኘው ጣቢያ ፣ ማግ ፣ ናምሩና ዩ ኤስ አይ ኤስ የተባሉ የአሜሪካ አራት የጦር ፣ የስለላና የፕሮፓጋንዳ ድርጅቶችን ከመዝጋቱም በላይ በእነዚሁ ድርጅቶች የሚሠሩ የውጭ ዜጎች በስምንት ቀናት ጊዜ ውስጥ ኢትዮጵያን ለቀው እንዲወጡ ወሳኝ እርምጃ ወሰደ ። በተጨማሪም የኢትዮጵያ አብዮታዊ መንግሥት በሚቀጥለው ወር ውስጥ የአሜሪካ ፣ የግብጽና የእንግሊዝ የመከላከያ የባሕር ፣ የምድር ጦርና የአየር ኃይል አታሼ ጽሕፈት ቤቶች እንዲዘጉ ከማድረጉም በላይ በብዙ መቶ የሚቆጠሩ የአሜሪካን መንግሥት ሠራተኞች ከኢትዮጵያ እንዲወጡ አደረገ ።


አምስተኛ ፣ ከሶቪዬት ሕብረት ሩሲያ መንግሥትና ከኮሚኒስት ፓርቲ በቀረበላቸው ግብዣ መሠረት ፣ ከሚያዝያ 25 ቀን 1969 ጀምረው ጓድ ሊቀ መንበር መንግሥቱ ኃይለማርያም የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ሊቀ መንበር የኢትዮጵያን ከፍተኛ ባለሥልጣናት አስከትለው በሶቪዬት ሕብረት ሩሲያ የአምስት ቀናት ይፋ ጉብኝት አደረጉ ። በጉብኝቱ ወቅት በወዛደራዊ ዓለም አቀፋዊነት ደምብ መሠረት በሁለቱ ሶሻሊስት አገሮች መካከል በተደረገው ወዳጅነት ስምምነት የሶቪዬት ሕብረት ሩሲያ መንግሥት ለኢትዮጵያ ዘመናዊ የጦር መሣሪያ እርዳታ ሰጠ ።

በሌላ በኩል የኢትዮጵያ አብዮታዊ መንግሥትና ሕዝብ በመሀል አገርና በምዕራብ ከኢሕአፓና ከኢዲዩ ወንበዴዎችና ሽብር ፈጣሪዎች ጋር የሞትና የሕይወት ትግል ሲያካሄዱ ከየካቲት 1969 ጀምሮ የሱማሊያ ወራሪ መንግሥት ከምሥራቅና ከደቡብ ምሥራቅ ጠረፎች ሰርጎ ገብ ወታደሮች እያስገባ በኢትዮጵያ ላይ የወረራ ጦርነትና የኢኮኖሚ አሻጥር ማካሄድ ጀመረ ። በመጨረሻም የሱማሊያ መንግሥት የጅቡቲ—አዲስ አበባ የምድር ባቡር ሀዲድ መስመር ከአስቆረጠ በኋላ በሐምሌ 16 ቀን 1969 መደበኛ ወታደሮቹ በኢራቅና በሶርያ ወታደሮች እየተረዱ በሚግ ተዋጊ አይሮፕላን ፣ በታንክ ፣ በከባድ መድፍ ፣ በብረት ለበስ ተሽከርካሪ ፣ በሮኬትና በፀረ አይሮፕላን ገዳይ የሆነ የወረራ ጦርነት በመክፈት ወዳ


በ1970 ከሱማሊያ ወራሪ ሠራዊት በኦጋዴን ጦርነት የተማረከ መሣሪያ







በ1970 ከሱማሊያ ወራሪ ሠራዊት በእጋዴን ጦርነት የተማረከ መሣሪያ



ትዮጵያ ምድር ከ300 እስከ 700 ኪሎ ሜትር ዘልቆ ገቡ ። ነገር ግን የኢትዮጵያ አየር ኃይል የሱማሊያን አየር ኃይል በጦርነቱ መጀመሪያ ከጥቅም ውጭ ሲያደርገው የኢትዮጵያ መደበኛና ሚሊሺያ ወታደሮች ለጠላት የማይበገርና የማይሸነፍ የድንጋይ አጥር በመሆን ታላቅ የሕይወትና የንብረት ዋጋ ከፍለው የአገሩን ሁለት ዋና ስትራቴጂያዊ የምሥራቅ ከተሞች ማለትም ሐረርና ድሬዳዋ በወራሪው ጠላት እጅ እንዳይወድቁ አደረጉ ።

የኢትዮጵያ ዝነኛው የአየር ኃይል የሱማሊያን የአየር ኃይል ከደመሰሰው በኋላ የኢትዮጵያ መደበኛ ጦርና የሚሊሺያ ሠራዊት በጥቂት ወራት ውስጥ በቂና አፋጣኝ ዝግጅት አድርገው በ1970 መጀመሪያ ወራሪውን ጠላት ከአገሩ ጠራርገው አወጡት ። በዚህ ጦርነት የኩባና የየመን ዲሞክራቲክ ሪፑብሊክ ወታደሮች በወዛደራዊ ዓለም አቀፋዊነት ደምብ መሠረት ከኢትዮጵያ ወታደሮች ጎን በመሰለፍ የሱማሊያን ወራሪ ጦር በመደምሰስ ተግባር ከፍተኛ ሚና በመጫወት ለኢትዮጵያ ሕዝብ ታላቅ ወዳጆችና ባለውለታዎች ሆነዋል ።

## 1. ሐ. 3. የኤርትራ ተገንጣዮች

በደአመት ፣ በሰባ ፣ በግዕዝና በግሪክ ቋንቋዎች የተጻፉ ብዙ የኢትዮጵያ ጥንታዊ የድንጋይ ጽሑፎች ፣ ብዙ ጥንታዊ የግሪክ ፣ የሮማውያንና የአረብ የታሪክ ጸሐፊዎችና ምሁራን ፣ በመካከለኛው ዘመን በግዕዝ ቋንቋ በብራና የተጻፉ ብዙ የኢትዮጵያ የነገሥታ ዜና መዋዕሎችና ከአገሩ አያሌ ገዳማት የተገኙ የሰማዕታትና የቅዱሳን ገድሎች ፣ ከአሥራ ስድስተኛው ምዕተ ዓመት ጀምሮ በየጊዜው በአውሮፓ መልዕክተኞች ፣ አገር ጐብኚዎችና ሚስዮናውያን የተጻፉ ብዙ መጻሕፍት እንዲሁም ብዙ የአከባቢው ጥንታዊ ካርታዎች በሙሉ በአንድነት በሰሜን የኤርትራ ክፍለ ሀገር በቀይ ባሕር ላይ ከዳህላክና ከምፅዋ ደሴቶች ጋር ከጥንት ጀምሮ የኢትዮጵያ ውስጣዊ አካልና ብሔራዊ ግዛት እንደሆነ በትክክል ያረጋግጣሉ ።

ይህ ሁሉ ሲሆንና ሲባል በክፍለ ሀገሩ በመካሄድ ላይ ያለው የኤርትራ ወንበዴዎችና ተገንጣዮች ችግር የተጀመረው በአለፈው ምዕተ ዓመት መጨረሻ በኢትዮጵያ ሰሜንና ምሥራቅ ጠረፎች የአገሩ አራት ጥንታዊ የጠረፍ ግዛቶች “ኤርትራ” ፣ የፈረንሳይ ሱማሊያ” ፣ የእንግሊዝ ሱማሊያ” እና “የኢጣሊያን ሱማሊያ” ተብለው ከአያሌ ብሔረሰቦች ጋር በታሪካዊ ግፍና ከእናት አገር ኢትዮጵያ ተቆርጠው በቀጥታ በወራሪዎችና በኢምፔሪያሊስቶች እንደቅኝ ግዛቶች በተያዙ ጊዜ ነው ።

እንደ አውሮፓ ዘመን አቆጣጠር ከ1889 እስከ 1952 ለ63 ዓመታት ኤርትራ በኢጣሊያንና በእንግሊዝ ኢምፔሪያሊስቶች እጅ ኮሎኒያዊ ግዛት ሆና በነበረበት ዘመን በሙሉ በጣም ደሀ ኮሎኒ ከመሆኑ የተነሳ የውጭ ምንዛሬውና በጀቱ ሁልጊዜ በኪሣራና በዕዳ ውስጥ ነበር ። ነገር ግን የኤርትራ አርበኞችና ሰማዕታት ከ1889 እስከ 1952 ድረስ ለዘመናት ከወራሪዎች ፣ ከኢምፔሪያሊስቶችና ከፋሽስቶች ጋር ለኢትዮጵያ ጠረፍ ግዛት ብሔራዊ ነፃነትና አንድነት እየተዋጉ በከፈሉት መስዋዕት ክፍለ ሀገሩ በ1952 ማለትም በኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር 1945 በብሔራዊ ነፃነት እንደገና ከእናት አገር ኢትዮጵያ ጋር ከተዋሀደ በኋላ ፣ ስትራቴጂያዊ የጠረፍ ግዛት በመሆኑ የኢትዮጵያ መንግሥት ከተቀሩ 13ቱ

ደቡብ ክፍለ ሀገራት እጅግ በጣም ከፍተኛ የሆነ ብሔራዊ ሀብት ፣ ገንዘብና ንብረት ወስዶ በማፍሰስ በአጭር ጊዜ ውስጥ ኤርትራ በትምህርት ፣ በንግድ ፣ በኢንዱስትሪ ፣ በከተማ ልማትና በማህበራዊ ኑሮ በመላው ኢትዮጵያ ከአዲስ አበባ ቀጥሎ በሁለተኛ ደረጃ የሚታይ ሀብታም ክፍለ ሀገር ሆነ ። የክፍለ ሀገሩም ተወላጆች በቁጥር በመላው ኢትዮጵያ ከየትኛውም ሌላ አካባቢና ክፍለ ሀገር ተወላጆች በላይ በመንግሥት ፣ በእርሻ ፣ በንግድና በኢንዱስትሪ ሥራዎችና መስኮች በጣም ከፍተኛ የሆነ የሀብት ፣ የሥልጣን ፣ የኃይልና የክብር ሥፍራ ያዙ ።

ይህ ሁሉ ሲሆንና ሲባል ራሳቸውን "አረቦች" ነን የሚሉ ምንደኛ የሆኑ የኤርትራ ወንበዴዎችና ተገንጣዮች በክፍለ ሀገሩ ለአከባቢው አድኃሪ አረብ መንግሥታትና ለዓለም አቀፍ ኢምፔሪያሊዝም የጥፋት መልእክተኞችና ወኪሎች በመሆን በክፍለ ሀገሩ ላለፉት 22 ዓመታት ባካሄዱት በጥፋት ጦርነት በታላቅ ብሔራዊ ጥረትና ሀብት የተገነባውን የኤርትራ ክፍለ ሀገር አሥመራን በረንቱንና የምጽዋ ደሴትን ጭምር ከአራት ከተሞች ሌላ ፣ ከኢኮኖሚና ከማህበራዊ ኑሮ አንፃር በፍጹም ደምስሰውታል ።

በዚህ አኳያ ፣ በ1966 የኢትዮጵያ ታላቁ ሕዝባዊ አብዮት እንደ እሳተ ገሞራ ከፈነዳ በኋላ ፣ ከአብዮቱ ጋር የኢትዮጵያን ብሔራዊ ሀልውና ፣ ነፃነትና አንድነት ከምድረ ገጽ ለማጥፋት የሚፈልጉ የአካባቢው አድኃሪ የአረብና የአፍሪካ መንግሥታትና ዓለም አቀፍ ኢምፔሪያሊዝም የኤርትራን ምንደኛና ወንበዴ ተገንጣዮችን እንደ የጥፋት መሣሪያና መልእክተኞች አድርገው መጠቀም ጀመሩ። በመሆኑም የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮት ከፈነዳ በኋላ የኤርትራ ምንደኞች ፣ ወንበዴዎችና ተገንጣዮች ከአካባቢው አድኃሪ መንግሥታትና ከዓለም አቀፍ ኢምፔሪያሊዝም ከፍተኛ የሆነ የመሣሪያና የገንዘብ እርዳታ አግኝተው በአብዮታዊ ኢትዮጵያ ሕዝብና መንግሥት ላይ ከደፈጣ ውጊያ አልፈው በ1967 የግምባር ጦርነት ከፈቱ ። በዚህ ተግባራቸው በኢትዮጵያ ላይ ከሱማሊያ ወራሪ መንግሥት ከኢሕአፓ ሽብር ፈጣሪዎችና ከኢዲዩ ወንበዴዎች ጋር የጥፋት ግምባርና ሕብረት ፈጠሩ ። ነፍሰ ገዳይ መልእክተኞቻቸው በመሀል አገር ሰርገው እየገቡ ብዙ የኢኮኖሚ አሻጥር ፈጸሙ ፣ ብዙ የመኢሶን ፣ የመኢጣግና የከነማት መሪዎችን ፣ የመንግሥት ባለሥልጣኖችንና አብዮታዊ ምሁራንን በብዛት ገደሉ ። እንዲሁም በርዕሰ ብሔሩ በጓድ ሊቀመንበር መንግሥቱ ኃይለማርያም ላይ ብዙ ያልተሳካ የግድያ ሙከራ አደረጉ ።

ከዚህ ሁሉ በላይ የኢትዮጵያ አብዮታዊ መንግሥትና ሕዝብ በመሀል አገር ከኢሕአፓ ሽብር ፈጣሪዎች ፣ በምዕራብ ከኢዲዩ ወንበዴዎችና ወራሪዎች በምሥራቅና በደቡብ ምሥራቅ ከሱማሊያ ወራሪ ጦር ጋር ብሔራዊ የሞትና የሽረት ትግል ሲያካሄድ ፣ የኤርትራ ተገንጣዮች ከ1967 እስከ 1970 ድረስ ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት አራት ከተሞች በስተቀር ክፍለ ሀገሩን ሙሉ በሙሉ በቁጥጥራቸው ሥር አድርገው በክፍለ ሀገሩ ከፍተኛ የሆነ የሕይወትና የንብረት ጥፋት አደረሱ ። የኢትዮጵያ አብዮታዊ ነፃ አውጪው ጦር በምሥራቅና በደቡብ ምሥራቅ የሱማሊያን ወራሪ ጦር ደምስሶ በ1970 መጨረሻ እስኪደርስባቸው ድረስ በአምስት ዓመታት ውስጥ የሚከተለው ሠንጠረዥ በቁጥር እንደሚያሳየው ፣ በኤርትራ ምንደኛና ወንበዴ ተገንጣዮች በክፍለ ሀገሩ በ243 000 ሰዎች ላይ የሞት ፣ የመቁሰልና የስደት አደጋ እንደአደረሱ በወቅቱ በኢትዮጵያ አብዮታዊ መንግሥት በይፋ ተገልጿል ።



ሠንጠረዥ 10

የኢጣሊያን ፋሽስቶች ፣ የኤርትራ ተገንጣዮችና የሱማሊያ ወራሪ መንግሥት በኢትዮጵያ ላይ በጦርነት ያደረሱት ጥፋት በንጽጽር

| ተራ ቁ. | የጦርነት ዘመን | የኢትዮጵያ ጠላቶች | የሕይወትና የንብረት ጉዳት | |
|---|---|---|---|---|
| | | | የሞት ፣ የመቁሰልና የስደት ጉዳት የደረሰበት የሕዝብ ብዛት | የንብረት ጉዳት በብር ሲተመን |
| 1 | 1928-1933 | የኢጣሊያን ፋሽስቶች | 760.300 | 652.296.138[13] |
| 2 | 1967-1970 | የኤርትራ ተገንጣዮች | 243.000 | 2.500.000.000 |
| 3 | 1969-1970 | የሱማሊያ ወራሪ መንግሥት | 2.400.000 | 2.184.900.000 |
| | | ድ ም ር | 3.403.000 | 5.337.196.138 |

Source: United Nations, *Les Revendications de L'Ethiopie Conlernat Les Ancienne Colonies Italiennes: Documentation Presentees Par ca Delegation de L'Ethiopie*, A/C.1/W8 (October 2W, 1948), pp. 47-49 b Computation; "Chairman Reviews Situation in Eritrea", The ythiopian Herald, (June 8, 1978); "Text of Chairman's Address on Six Enniversary of Revolutionary Day", *The Ethiopian Herald*, (September A3, 1980), by Computation.

## 1. ሐ. 4. የኢኮኖሚ አሻጥረኞች

የመንግሥትንና የሕዝብን ንብረት ሀብትና ገንዘብ በመዝረፍና በመበዝበዝ ከዚህ የሚከተለው ሠንጠረዥ በተጨባጭ እንደሚያሳየው ፣ በኢትዮጵያ አብዮትና ሕዝብ ላይ ከኤርትራ ተገንጣዮችና ከሱማሊያ ወራሪ መንግሥት ቀጥሎ በጣም ከፍተኛ የሆነ የኢኮኖሚ ጉዳት ያደረሱ የአገሩ ደመኛ ጠላት የኢኮኖሚ አሻጥረኞች ማለትም የቢሮ ሌቦች ፣ በዝባዥ ነጋዴዎች የባንክ ዘራፊዎች ፣ የመንግሥት ግብር የማይከፍሉ አጭበርባሪዎች ፣ ጉቦኞችና ኮንትሮባንዲስቶች ናቸው ።

13. ይህ ማስታወሻ በሚቀጥለው ገጽ በግርጌ ይገኛል ።

ሠንጠረዥ 11

ከ1966 እስከ 1972 ድረስ በኢኮኖሚ አሻጥረኞች የተዘረፈና የተበዘበዘ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሀብት መጠን

| ተራ ቁ. | ብሔራዊ ሀብት ዘራፊዎችና የዘረፋው ዓይነት | የዘረፋው ዘመን | የተዘረፈው ሀብት መጠን በ ብ ር | በገንዘብ ወንጀል |
|---|---|---|---|---|
| 1 | በአገር ውስጥ ገቢ መሥሪያ ቤት ለመንግሥት ገቢ ያልሆኑ የግብር ገንዘብ | 1966—1971 | 177,634,794,00 | |
| 2 | በቢሮ ሠራተኞችና በነጋዴዎች የተዘ ረፈ የመንግሥትና የሕዝብ ገንዘብ | 1967—1972 | 353,821,259,77 | |
| 3 | ያልተሰበሰበው የኢትዮጵያ የመድን ድርጅት ገንዘብ | 1968— | 141,905,528,00 | |
| 4 | ከባንኮች የተዘረፈ ገንዘብ | | 1,165,138,32 | |
| 5 | ከኮንትሮባንዲስቶች የተያዙ ዕቃዎች ግምት በብር | 1967—1972 | 32,676,313,20 | |
| 6 | በአንድ ዓመት ውስጥ ወደ ጐረቤት አገሮች በኮንትሮባንድ መንገድ የተወሰዱ በ1.445.451 የሚገመቱ ላሞች ፣ በጐችና ፍየሎች ጠቅላላ ግምት በብር | 1972—19 | 145,864,000,00 | |
| 7 | በፍርድ ቤት ቅጣት ከወንጀለኞች የተሰበሰበ የመቀጫ ገንዘብ | | 33,063,684,00 | |
| 8 | በ20 ታላላቅ ቢሮክራሲያዊ ሌቦች የተዘረፈ የመንግሥትና የሕዝብ ገንዘብ መጠን | | 4,374,678,00 | |
| 9 | በገንዘብ ወንጀል ወደ ፍርድ ቤት የቀረቡ የከሶች ብዛት | | | 1753 |
| | ድ ም ር | 1966—1972 | 889,805,406,16 | 1753 |

የተገኘበት ፤ ከፀረ ምዝበራና ብኩንነት ኢንዚብሽን (በአዲስ አበባ ከተማ ማዘጋጃ ቤት ፤ በጥቅምት 1973) ፤ የአዲስ ዘመን "የፍትሕና ሕብረተሰብ" ሳምንታዊ ዓምድ (1972—1973)

(ከገጽ 67 የዞረ ማስታወሻ)

13 ኢትዮጵያ ለጦር ካሣ ጥያቄ ለተባበሩት መንግሥታት ማህበር በኢጣሊያን መንግሥት ላይ በአቀረበችው ሰነድ የ760.300 በኢጣሊያኖች የሞት አደጋ የደረሰባቸው ሰዎች ሕይወት በወቅቱ በነበረው ተመን በ652.296 138 ብር ሲገመት ፣ ኢጣሊያኖች በኢትዮጵያ ላይ ያደረሱት ጠቅላላ የሕይወት ፣ የንብረት ፣ የሀብትና የገንዘብ ጥፋት በገንዘብ በወቅቱ በነበረው ሂሣብ 185.000.000 ፓውንድ ስቴርሊንግ ወይም 1.110.000.000 የማሪያቴሬዛ ብር ተገምቶዋል ። በሌላ በኩል ለራሳቸው ጥቅም ሲሉ የኢጣሊያን ፋሽስቶች በኢትዮጵያ በአምስት ዓመታት ጊዜ ወረራ በመንገድ ፣ በንግድ ፣ በኢንዱስትሪ ፣ በእርሻ ፣ በከተማና በኮንስትራክሽን ሥራዎችና መስኮች ያፈሰሱት ገንዘብ ከዚያ በላይ ተገምቶዋል ። በሥራና በሥልጣኔ ደረጃ ገና ከተፈጥሮ ደረጃ ብዙ እርምጃ ወደ ፊት ያልተራመዱ የኤርትራና የሱማሊያ ወንበዴዎችና ወራሪዎች ከጥፋት ባሻገር ግምባታ ሥራ እንደሚሠሩ አይጠበቅባቸውም ።



ከዚህ በላይ በሠንጠረዥ 8 የኢትዮጵያ የ31 የገንዘብ ፣ የንግድ ፣ የምርትና የማከፋፈያ ድርጅቶች ጠቅላላ የመነሻ ካፒታል 455 229 303.00 ብር እንደሆነ በዝርዝር ተገልጾዋል ። ከ1966 እስከ 1970 ድረስ በሰባት ዓመታት ጊዜ ውስጥ በቢሮ ሠርተኞች ፣ በነጋዴዎች ፣ በባንክ ወንበዴዎችና በኮንትሮባንዲስቶች የተዘረፈው የኢትዮጵያ የመንግሥትና የሕዝብ ገንዘብ ምንም ምዝገባውና ግምቱ በከፊል ቢሆን እንኳ 890 000 000 ብር ማለትም ከአገሩ ኢንዱስትሪ ካፒታል በሁለት እጥፍ የሚበልጥ ብሔራዊ ንብረት ፣ ሀብትና ገንዘብ መሆኑን ከዚህ በላይ በተጨባጭ ማየት ይቻላል ።

ይህንን ዓይነት ታላቅ የብሔራዊ ሀብትና ንብረት ዘረፋና ምዝበራ ለማቆም የኢትዮጵያ አብዮታዊ መንግሥት የጠቅላይ አዲተር መሥሪያ ቤት ከማጠናከር ባሻገር በአዋጅ አንድ ልዩ ፍርድ ቤትና በአገር አቀፍ ደረጃ የሠርቶ አደር ቁጥጥር ኮሚቴ ሕግና መዋቅር ዘርግቶዋል ።

## 1. ሐ. 5. የተፈጥሮ አደጋ

በሽግግራዊ ወቅት የኢትዮጵያን አብዮትና ሕዝብ የተፈታተኑት አድኃሪ የኢሕአፓ ፣ የኢዲዩ ፣ የኤርትራ ፣ የሱማሊያ ፣ የአረብ ፣ የኢምፔሪያሊዝም ፣ የነጋዴና የቢሮክራሲ ኃይላትና የጥፋት መልእክተኞች ብቻ ሳይሆኑ የተፈጥሮ ሁኔታም ጭምር ነው ። በዚህ ረገድ ፣ የ1965—1966 ታላቁ ረሀብ በ200 000 ታም ጭምር ... የሚቆጠሩ የኢትዮጵያውያን ሕይወት ማጥፋቱና ይህም ሁኔታ ለኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮት ፍንዳታ የራሱን አስተዋጽኦ ማድረጉ ይታወሳል ። ከዚህ የሚከተለው ሠንጠረዥ እንደሚያሳየው ፣ ከአምስት ዓመታት በኋላ በ1972 ደግሞ

ሠንጠረዥ 12

በ1972 በተለያዩ ክፍለ ሀገራት በድርቅና በረሀብ የተጐዱ ሰዎች ብዛት

| ተራ ቁጥር | ክፍለ ሀገራት | በድርቅ የተጐዱ ሰዎች ብዛት |
|---|---|---|
| 1 | ኤርትራ | 1,002,000 |
| 2 | ትግራይ | 963,000 |
| 3 | ወሎ | 950,000 |
| 4 | ጐንደር | 90,000 |
| 5 | ሸዋ | 70,000 |
| 6 | ሐረርጌ | 1,000,500 |
| 7 | ባሌ | 515,000 |
| 8 | ሲዳሞ | 270,000 |
| 9 | ጋሞጐፋ | 227,500 |
| | ድ ም ር | 5,089,000 |

የተገኘበት ፤ "Over 5 Million Drought Victims Need Assistance", *The Ethiopian Herald* (April 30, 1980).

በዘጠኝ ክፍለ ሀገራት ከ5 000 000 በላይ በሚቆጠሩ ሰዎች ላይ እንደገና የድርቅና የረሀብ ችግር ደረሰ ። እንደገና በ1975 በወሎ ፣ በጐንደርና በትግራይ ክፍለ ሀገራት በ1 050 000 በሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን ላይ የረሀብ ችግር ደረሰ ።

በመሆኑም አድኃሪያንን ብቻ ሳይሆን ተፈጥሮንም በቁጥጥራችን ሥር እናደርጋለን በሚለው በጓድ ሊቀ መንበር መንግሥቱ ኃይለማርያም መሪነትና መርሆ የኢትዮጵያ አብዮታዊ መንግሥትና ሕዝብ ከአድኃሪና ኢምፔሪያሊስት ኃይላት ሌላ ከዚህ ከተፈጥሮም ሁኔታ ጋር ወሳኝ ትግል መካሄድ ግዴታ ሆነበት ።

## 1. ሐ. 6. ስለ ስውር የፖለቲካ ድርጅቶች ሚና

ከኢትዮጵያ ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ዲሞክራሲያዊ አሠራርና አግባብ ባለው መንገድ በትረ መንግሥቱን ተቀብሎ አገሩን የሚመራ የኢትዮጵያ ሠርቶ አደሮች ፓርቲ በማርክሲዝም-ሌኒኒዝም ሳይንስ(ማሌ) መርሆና መሠረት ለመፍጠር ይረዳሉ ተብለው በደርጉ ሙሉ ፈቃድና ድጋፍ በ1968-1969 በሕዝብ ድርጅት ጽሕፈት ቤት ውስጥ ራሳቸውን የመላው ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ (መኢሶን) ፣ የኢትዮጵያ ጭቁኖች አብዮታዊ ትግል (ኢጭአት) ፣ ማርክሳዊ ሌኒናዊ ሪቮሉሽናዊ ድርጅት (ማሌሪድ) ፣ አብዮታዊ ሰደድ (ሰደድ) እና የወዛደር ሊግ (ሊግ) ብለው የሚጠሩት አምስት ሕቡዕ ማለትም ስውር የኢትዮጵያ ማርክሲስት ሌኒኒስት ድርጅቶች (ኢማሌድ) ተፈጠሩ ።[1]

በ1968—1969 የመኢሶግ ፣ የመኢገግና የከንግት ሕዝባዊ ድርጅቶችን በማደራጀት ተግባር ብሎም የኢሕአፓንና የኢዲዩን ኃይላት በማጋለጥ ትግል መኢሶን ፣ ኢጭአት ፣ ማሌሪድ ፣ ሰደድና ሊግ በወቅታዊና በታክቲካዊ ሕብረት ተባብረው ከሠሩ በኋላ በሥልጣን ጥያቄ እርስ በርሳቸው እየተጋጩ ለዘመናት በሥቃይ ፣ በጊዜ ፣ በታሪክና በሥርዓት አንድ የሆነውን የኢትዮጵያን ሕዝብና ሕብረተሰብ በመደብ ሳይሆን በድርጅትና በጐሣ የመከፋፈል ውስጣዊ የፖለቲካ ዘመቻ ጀመሩ ።

በዚህ አኳያ ከአምስቱ ኢማሌድርጅቶች መኢሶን በ1969 ከረምት አገሩ በሶማሌ ጦር በተወረረበት ብሔራዊ አደጋ ወቅት ሸፍቶ ወደ ጫካ በመግባት በአገሩ ብሔረሰቦችና ሕዝባዊ ድርጅቶች ውስጥ የመደብ ልዩነትና ትግል ሳይሆን የጐሣ ልዩነትና ትግል ማስተማርና ማስፋፋት ጀመረ ። ከተቀሩት አራቱ ኢማሌ ድርጅቶች ማሌሪድ ፣ ሰደድና ሊግ በጊዜያዊ ሕብረት አራተኛውን ማለትም ኢጭአትን "ጠባብ የብሔረተኝነት" ስሜት" ያለው ድርጅት ነው በማለት ከኢማሌድ ሰርዘውት ሦስቱ በድርጅታዊና ርዕዮተዓለማዊ ጥራት የኢትዮጵያን የማርክሲስት ሌኒኒስት ድርጅቶች ሕብረት (ኢማሌድሕ) ለመፍጠር ብሎም የኢትዮጵያን ሠርቶ አደሮች ፓርቲ(ኢሠፓ) ለመመሥረት እንደሚታገሉ ለአገሩ ሕዝብ በጋራ መግለጫ አስታወቁ ። ነገር ግን ከአጭር ጊዜ በኋላ ከሦስቱ ኢማ

1 ኢሠፓአኮ ፣ ኢሠፓአኮ በፓርቲ ምስረታ ሂደት ፣ ከአንደኛው እስከ ሁለተኛው ጉባኤ (1975) ፣ ገጽ 16—19 ።



ሌድሕ አባል ድርጅቶች ደግሞ ሊግ በሰደድ ውስጥ ሰርጎ በመግባት የአብዮት ቅልበሳ ሴራ ሲያካሂድ ተገኘ ።

ይህ በአጭርና በአጠቃላይ የተገለጸው የኢትዮጵያ የማርክሲስት ሌኒኒስት ድርጅቶች ሥራና ታሪክ የኢትዮጵያን አብዮታዊ መንግሥት ፣ ሕዝብና ጦር እጅግ በጣም አድርጎ አስቆጣ ። በመሆኑም በታህሣሥ 8 ቀን 1970 የኢትዮጵያ አብዮታዊ መንግሥት ስውር ድርጅቶቹን በሙሉ አፍርሶ ለኢሠፓ ምሥረታ የኢትዮጵያን ሕዝብና ሕብረተሰብ በስውር መንገድ ሳይሆን በይፋ የሚያደራጅ ማለትም የኢትዮጵያ ሠርቶ አደሮች ፓርቲ አደራጅ ኮሚሽንን (ኢሠፓአኮ) በአዋጅ ቁጥር 174/1972 መሠረተ ።

## 2. የኢትዮጵያ አብዮት ድል አድራጊነትና የሶሻሊዝም ግምባታ ትግል

### 2. ሀ. መግቢያ ፣ የሶሻሊዝም ግምባታ መንገድና መሣሪያዎች

የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮት በኢትዮጵያ ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ መሪነትና አዝማችነት በውስጥ አድኃሪ ኃይላትና በዓለም አቀፍ ኢምፔሪያሊዝም ሥርዓት ማለትም በኢሕአፓ ፣ በኢዲዩ ፣ በኤርትራ ተገንጣዮች በኢኮኖሚና በቢሮክራሲያዊ አሻጥረኞች በአካባቢው አድኃሪ የአፍሪካና የአረብ መንግሥታት ፣ በሶማሊያ ወራሪ መንግሥት ፣ በአድኃሪ ድርጅቶችና ሐአሜሪካን ስለላ ድርጅት ሲ.አይ.ኤ. በአጭሩ በውስጥና በውጭ የመደብ ጠላቶች የተሸረበ የጥፋት ሴራዎችን እንደ አመጣጣቸው አንድ በአንድ በመደምሰስና በማክሸፍ ድል አደረጋቸው ። የኢትዮጵያ አብዮታዊ መንግሥትና ሕዝብ ይህንን በመደብ ጠላቶቹ ላይ የተጎናጸፈውን አብዮታዊና ብሔራዊ ድል በመስከረም 2 ቀን 1971 በአራተኛው የአብዮት በዓል ቀን በታላቅ ብሔራዊ ስሜት ፣ ዝግጅትና ክብር በአገር አቀፍ ደረጃ አከበረ ።

ድል አድራጊው የኢትዮጵያ አብዮታዊ መንግሥትና ሕዝብ እንደዚህ የውስጥና የውጭ የመደብ ጠላቶቹን ማለትም ፀረ አብዮት ኃይላትን በውጊያ ግምባር ታላቅ የሕይወትና የንብረት መስዋዕት ከፍሎ ከደመሰሳቸውና ካከሸፋቸው በኋላ ተጥሎ ብሔራዊ ኃይሉን ፣ ሀብቱንና ጥረቱን በሙሉ ለመደብ ትግልና ለሶሻሊዝም ግምባታ በከፍተኛ ዘዴና ደረጃ ማደራጀትና ማዘጋጀት ጀመረ ። በዚህ አንፃርና ተግባር ፣ የመደብ ትግሉን ማፋፋም ፣ የማይበገር ያገር መከላከያ ኃይል መፍጠር ፣ ጠንካራ የሆነ የሠርቶ አደር ፓርቲ ምሥረታና ጠንካራ የሆነ ብሔራዊ ሶሻሊስት ኢኮኖሚ ግምባታ በኢትዮጵያ የሶሻሊዝም ግምባታ መንገዶችና መሣሪያዎች እንደሆኑ በአብዮታዊ መንግሥት ፖሊሲ አቅጣጫና አሠራር በትክክል ተገልጸዋል ።

### 2. ለ. ያገር መከላከያ ኃይል ግምባታ ትግል

የኢትዮጵያ የማይበገር ያገር መከላከያ ኃይል የአገርና የአብዮት ዋስትና ነው ። በዚህ ረገድ የኢትዮጵያ ምድርና ሕዝብ በጥንት በአክሱማውያን ዘመን የነበረው ጠንካራ የባህርና የምድር ጦር ድርጅት ከአሥራ ስድስተኛው ምዕተ ዓመት እስከ ሀያኛው ምዕተ ዓመት ድረስ ለ400 ዓመታት ከምር

ቅጋል ፣ ከቱርክ ፣ ከግብጽ ፣ ከሱዳን ፣ ከኢጣሊያንከእንግሊዝና ከፈረንሳይ ወራሪዎችና ኢምፔሪያሊስቶች በሥፍራው በጊዜ ያልተቋረጠ ከፍተኛ ጥቃትና ጥፋት ደርሶበታል ። በዚህ ረገድ ከ1820 እስከ 1950 ድረስ በ130 ዓመታት ውስጥ ብቻ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከግብጽ ፣ ከሱዳን ፣ ከእንግሊዝና ከኢጣሊያን ወራሪዎች ኢምፔሪያሊስቶችና ፋሽስቶች ጋር በ60 የሚቆጠሩ ጦርነቶች ተዋግቶዋል ። የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮት በ1966 ከፈነዳ በኋላ ደግሞ የአካባቢው አድሃሪ የአፍሪካና የአረብ መንግሥታትና ዓለም አቀፍ የኢምፔሪያሊዝም ሥርዓት ከውስጥ ፀረ አብዮተኞች ጋር ግምባር ፈጥረው የኢትዮጵያን ብሔራዊ ህልውና ፣ አንድነትና ነፃነት ከዓለም ገጽ ለማጥፋት ያልተሳካ ዓለም አቀፍ ሙከራ እንደአደረጉ ከዚህ በላይ በአጭሩ አይተናል ። ይህ ዓይነት አደጋ በኢትዮጵያ ምድርና ሕዝብ ላይ ለወደፊት እንዳይመጣ ብሔራዊ ዋስትና የሚሆነው ነገር ጠንካራ ያገር መከላከያ ድርጅት ብቻ መሆኑን በትክክል በማወቅ የኢትዮጵያ አብዮታዊ መንግሥት ኃያል የሆነ ያገር መከላከያ ድርጅት ለመገንባት በአለፉት ዓመታት ብዙ ድርጅታዊና መሠረታዊ እርምጃዎችን ወስዶዋል ።

በዚህ አንፃርና ተግባር አንደኛ ፣ የአገሩ የምድር ፣ የአየርና የባህር ጦር ኃይሎች በቁጥር ፣ በድርጅት ፣ በትምህርትና በመሣሪያ እጅግ በጣም ተጠናክረዋል ። ሁለተኛ ፣ አንድ አዲስና ታላቅ ሕዝባዊ ጦር ሠራዊት ተፈጥሮዋል ። ሦስተኛ ፣ በጦሩ ውስጥ የፖለቲካና የርዕዮተ ዓለም ትምህርት በከፍተኛ ደረጃ በመስፋፋት ላይ ይገኛል ። ጦርነት የመደብ ትግል መሆኑን የኢትዮጵያ አብዮታዊ ጦር በልምድና በቲዎሪ እየተማረ ነው ። አብዮታዊ ጦር ተዋጊም አምራችም ነው የሚለው የማርክሲስት ሌኒኒስት ቲዎሪ በኢትዮጵያ አብዮታዊ ጦር ውስጥ ተግባራዊ ትምህርትና ልምድ በመሆን ላይ ነው ። አራተኛ ፣ አብዮታዊ መንግሥት ሕብረተሰቡን ለአገርና ለአብዮት ጥበቃ የሚያበቃውን ወታደራዊ ትምህርትና ድርጅት በአገር አቀፍ ደረጃ ማስፋፋት ጀምሮዋል ።

የኢትዮጵያን ያገር መከላከያ ድርጅት ግምባታን ዓላማና ተግባር በሚመለከት ጉዳይ በ1973 ኢሠፓአኮ ያሳለፈው የፖሊሲ ውሳኔ እንዲህ ይላል ። በኢሠፓአኮው ብሔራዊ ውሳኔ አባባል ፣

“የሶሻሊዝም ግንባታ ትግላችን ሊሰምር የሚችለው በአንድ በኩል ክንዳችንን አስተባብረን በኢኮኖሚው ረገድ ያልተቆጠበ ጥረት በማድረግ ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ይህንኑ ጥረታችንን ለማደናቀፍ ወደ ኋላ የማይሉትን ኢምፔሪያሊዝምንና እንዲሁም የውስጥና የውጭ አድሀርት ኃይላትን እንቅስቃሴ ነቅቶ በመጠበቅ ሊሰነዘርብን የሚቃጣውንም ጥቃት ለመመከት የምንችለውን ኃይላችንን አጠናክረን ስንገኝ ብቻ መሆኑን በመገንዘብ የኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ ሁለተኛ መደበኛ ስብሰባ የሚከተለውን ውሳኔ አሳልፏል ።

“1. የጠላትን ግፊትና ወረራ ለመከላከል በሚያበቃን ደረጃ የመከላከያ ኃይላችንን በአፋጣኝ የማደራጀት አስፈላጊነቱ የአብዮታችን መዳበር ወይም የመቀልበስ ጥያቄ በመሆኑ አብዮታዊ ጦራችንን በአዲስ አቋም የማጠናከሩ ሥራ ቀጥሎ በአፋጣኝ በሰው ፣ በድርጅትና በትጥቅ ብቁ ሆኖ እንዲገኝ ፣

“2. የመከላከያ አቋማችን ብቃት በአብዮታዊው ጦር ብቻ የሚወሰን ሳይሆን የመላውን ሠርቶ አደር ንቁ ተሳትፎ የሚጠይቅ ነው ።



ባለፉት የትግል ዓመታት አብዮታውያንና አገር ወዳድ ሁሉ የእናት ሀገር ጥሪን ተቀብለው በተግባር ያስመሰከሩት አኩሪ የጀግንነት ታሪካችን ነው ። ሠርቶ አደሩ አብዮታዊት እናት አገሩን ምንጊዜም ቢሆን ሊሠነዘርበት ከሚቃጣ ጥቃት ምከታ ብቁሆኖ ለመገኘት የሚያስችለው የተቀነባበረ አሠራር ማደራጀቱ ወቅታዊ ሆኗል ። ለዚህም ማንኛውም አብዮታዊ ዜጋ አብዮታዊት እናት አገሩን ለመከላከል የሚችልበትና የሚበቃበት የብሔራዊ ውትድርና አገልግሎት በአፋጣኝ እንዲመሠረትና ለዚሁ የሚያስፈልገው ዝግጅት በአፋጣኝ ተጠናቅቆ ሥራ ላይ እንዲውል ፣

“3. ሠርቶ አደሩ በሚሠራበት አካባቢዎች ሁሉ ራሱን ከጦርነትም ሆነ ከሌላ ሰው ሠራሽና የተፈጥሮ አደጋ ሊከላከልና ሊደርስበት የሚችለውን ጉዳት ለመቀነስም ሆነ ለማስቀረት የሚያስችለውን የሲቢል መከላከል (ሲቢል ዲፌንስ) እንዲመሠረትና ለዚህም አስፈላጊው መመሪያና ዝግጅት እንዲቀየስ ፣

“4. የውስጥም ሆነ የውጪ ጠላቶቻችን ፊት ለፊት ከሚያነሱት ወረራና ጦርነት ባሻገር የረቀቀ ደባና ሴራ ማካሄዳቸው ባለፉት የትግል ዓመታት የተገነዘብነው ሲሆን ፣ ዛሬም እንደማይተኙልን በመረዳት እንቅስቃሴያቸውንና ሴራቸውን በወቅቱ ለመቅጨት ማንኛውም የአብዮቱ ወገን ሁሉ ሳይዘናጋ በየአለበት የአብዮቱ ዘብ በመሆን ነቅቶ እንዲጠብቅ[2] ።”

## 2. ሐ. የኢትዮጵያ ሠርቶ አደሮች ፓርቲ (ኢሠፓ) ምሥረታ ትግል

### 2. ሐ. 1. የፓርቲ ጥያቄ በኢትዮጵያ አብዮት

“ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት አሁን ይቋቋም” ፣ “ደርግ ፋሽስት ነው” በማለት ኢሕአፓ የተባለውና ሽብር ፈጣሪው የነፍሰ ገዳዮች ፣ የሌቦች ፣ የወንጀለኞችና የወንበዴዎች ድርጅት የብዙ ኢትዮጵያውያንን ንጹሕ ደም በቤት ፣ በመንገድ ፣ በቢሮ ፣ በከተማ ፣ በገጠርና በጦር ሜዳ እንደ ውሃ ያፈሰሰው ፣ የደርጉ ፀረ አብዮተኛ አባላትና ቡድኖች በሐምሌ 1968 እና በጥር 1969 ሁለት ያልተሳኩ ኩዴታዎች ያካሄዱ ፣ ደርግ አብዮታዊ አመራር ለመስጠት የማይችል “የንዑስ ከበርቴ” ድርጅት ነው ፣ ቢሮክራሲ ማለትም መንግሥታዊ አሠራርና አስተዳደር ይጥፋ ወይም ይፍረስ ፣ “እርሱ ጠባብ ነው” ፣ “እርሱ ትምክህተኛ ነው” ፣ “ያ የጠባቦች ድርጅት ነው” ፣ ያ የትምክህተኞች ድርጅት ነው” በማለት በሥፍራው ፣ በጊዜ ፣ በታሪክና በባህል አንድ አካልና አንድ አገር የሆነውን የኢትዮጵያ ሕዝብ በመደብ ሳይሆን በጎሣና በፖለቲካ ድርጅት እየከፈሉ በማርክ

---

2 ኢሠፓአኮ ፣ የኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ ሁለተኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች (1973) ፣ ገጽ 47—49 ።

ሊዝምና በሌኒኒዝም ስም ፣ በአብዮትና በኢትዮጵያ ስም በ1969 እና በ1970 የተነሱ ስውር የፖለቲካ ድርጅቶች ሁሉ የፈለጉት ዋና ነገር በሆነ ሁሉ መንገድና ምክንያት በደርግ ምትክ በትረ መንግሥቱን በግል ድርጅት ለመያዝ እንደ ነበር በዚያ " በታላቁ መከራ ዘመን" ማለትም ከ1969 እስከ 1970 ድረስ በኢትዮጵያ የእነዚህን ድርጅቶች ፖሊሲ ፣ ሥራና ቅስቀሳ ላየና ላስተዋለ ሁሉ ግልጽ ነገር ነው[3] ።

ነገር ግን የኢትዮጵያ ጀግናው ወታደርና ገበሬ ብሔራዊ ፣ ፖለቲካዊና መደባዊ ግምባር ፈጥረው አገሩን የሥልጣን ጥመኛ ከሆኑ ወንበዴዎችና ድርጅቶች አደጋ ወሳኝ በሆነ ወቅትና መንገድ አዳኑት ። በዚህ አንፃር የኢትዮጵያ ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ በመስከረም 1967 በትረ መንግሥቱን ከያዘበት ጊዜ ጀምሮ የኢትዮጵያ ሠርቶ አደር ሕዝብ ከዳር እስከ ዳር በመደብ አኳያና መድረክ ተደራጅቶ የሠርቶ አደሮች ፓርቲ ሳይፈጠር በትረ መንግሥቱን በሆነ ሁሉ ምክንያትና መንገድ ለሌላ ሕብረተሰብ ክፍል አሳልፎ እንደማይሰጥ በኢትዮጵያ ጭቁን ሰፊ ሕዝብ ስም የማይታጠፍ ቃል ገባ ። ሁለተኛ፣ ደርጉ በየካቲት 25 ቀን 1967 የገጠር መሬት አዋጅ ማለትም የእርሻ አዋጅ ለዘመናት ለወደቀው ጉልተኛ መደብ ጭሰኛና ገባር ያደረጋቸውን መሬት መልሰው በአብዮታዊ አዋጅ በነፃ ስለአገኙ የኢትዮጵያ ገበሬዎች ደግሞ ከደርጉ ጋር የማይታጠፍ ፖለቲካዊና መደባዊ ቃል ገቡ ።

ከዚህም የተነሣ የኢትዮጵያ ገበሬዎች ከአብዮታዊ መንግሥት ጐን ተሰልፈው የኢሕአፓንና የኢዲዩን ወንበዴዎች ደመሰሱ ። ሁለተኛ ፣ "ታፍራና ተከብራ የኖረችው ኢትዮጵያዊ ተደፍራለች" የሚለው ታሪካዊ የእናት አገር ጥሪ ከአገሩ አብዮታዊ መሪ ከጓድ መንግሥቱ ኃይለማርያም ከደረሳቸው በኋላ ከመላው አገሩ በራሳቸው ምርጫና ፈቃድ የተሰበሰቡና በ300 000 የሚቆጠሩ የኢትዮጵያ ገበሬዎች በሁለት ወራት ውስጥ የውትድርና ትምህርት በታጠቅ ጦር ሠፈር ተምረው በምሥራቅ ፣ በደቡብ ምሥራቅ ፣ በምዕራብና በሰሜን ጦር ግምባሮች በሱማሊያ ወራሪዎች በኢዲዩ ወንበዴዎችና በኤርትራ ተገንጣዮች ላይ ከመደበኛው ጦር ሠራዊት ጐን ተሰልፈው እንደ መብረቅና ጐርፍ ወረዱ ። ሦስተኛ ፣ በማርክሲዝም ሌኒኒዝም ፣ በአብዮትና በኢትዮጵያ ስም የተነሱ ስውር የፖለቲካ ድርጅቶች በሥልጣን ፍላጎት ፀረ አብዮት ድርጅቶች መሆናቸው በአብዮታዊ መንግሥት በይፋ ከተገለጸ በኋላ አሁንም የኢትዮጵያ ገበሬዎችና የገበሬ ማህበራት ከአብዮታዊ መንግሥት ጐን ተሰልፈው ጠንካራ ክንዳቸውን በፀረ አብዮት ኃይላት ላይ አነሱ ።

በተጨማሪም ስውር የፖለቲካ ድርጅቶች በግል ሳይሆን ፣ በአብዮትና በኢትዮጵያ ስም ወደ አብዮት ሠፈር ገብተው ደርግን ከሥልጣን በማውረድ በአቋራጭ መንገድና ዘዴ በትረ መንግሥትን ይዘው በኢትዮጵያ ሕዝብ ጫንቃ ላይ ለመውጣት ያካሄዱት የፖለቲካ ተንኮልና አሻጥር የኢትዮጵያን አብዮታዊ ጦር በኃይል አስቆጣው ። በዚህ ምክንያት በኢሠፓአኮ ምሥረታ ዋዜማ የአብዮታዊ ጦር የኃይልና የእዝ አዛዦችና መኮንኖች በአዲስ አበባ በቤተ መንግሥት በልዩ ጉባኤ በመሰብሰብ የአገሩን ውስጣዊ ሁኔታዎች በዝርዝር ገምግመው በአሳለፉት

---

3 ኢሠፓአኮ ፣ በፓርቲ ምስረታ ሂደት ፣ ገጽ 17—19 ።



መግለጫ የአብዮቱን መንገድና ሂደት ለማደናቀፍ ለሚሞክሩ ፀረ አብዮትና ፀረ አንድነት ኃይላትና ድርጅቶች ጥብቅና ግልጽ ማስጠንቀቂያ ሰጡ ።

ሁለተኛ ፣ የጦር ኃይሎች ፣ ካድሬዎችና ኮሚሳሮች ማለትም የአብዮታዊ ጦር የፖለቲካ ክፍልና ጉዳይ አባሎችና ተወካዮች በ1971 መጨረሻ ጥር መከላከያ ሚኒስቴር ውስጥ በአራት ቀናት ሴሚናር የአገሩንና የአብዮቱን ወቅታዊ ሁኔታ በዝርዝርና በጥልቀት ገምግመው በአወጡት ታሪካዊ መግለጫ በሕዝባዊ አብዮት መንገድና ሂደት ላይ የሚቆሙ ፀረ አብዮትና አንድነት ኃይላትንና ክፍሎችን ለመደምሰስ በተጠንቀቅ የሚገኙ መሆናቸውን በግልጽና በይፋ ከማስታወቃቸውም በላይ ጓድ ሊቀ መንበር መንግሥቱ ኃይለማርያም የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግና የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሊቀ መንበር ፣ የአብዮታዊ ጦር ኃይሎች ጠቅላይ አዛዥ በአሻጥረኛ ስውር ድርጅቶች ፈንታ የሚፈጠረውን ኢሠፓአኮ በማዕከላዊነት እንዲያደራጁና እንዲመሩ መረጡአቸው ።

## 2. ሐ. 2. የኢሠፓአኮ ምሥረታና ተግባራት

ከዚህ በኋላ የኢትዮጵያን ሠርቶ አደር ሕዝብና መደብ በሠራተኛ ፣ በገበሬ፣ በከተማ ነዋሪዎች ፣ በወጣቶች ፣ በሴቶችና በሙያ ማህበራት አደራጅቶ ኢሠፓን የሚፈጥር ኢሠፓአኮ በታህሣሥ 8 ቀን 1972 በሊቀመንበር መንግሥቱ ኃይለማርያም ማዕከላዊነት በአብዮታዊ መንግሥት በአዋጅ ቁጥር 174/1972 የአገሩ ብቸኛ የፖለቲካ ድርጅት ሆኖ ሲቋቋም የቀደሞ ስውር የፖለቲካ ድርጅቶች በሕግ ፈረሱ ። ከዚያ በኋላ የስድስት ወራት ድርጅታዊ ፖለቲካዊና ርዕዮተዓለማዊ ዝግጅት ተደርጐ በሰኔ 1972 የኢሠፓአኮ የመጀመሪያው ታሪካዊ ጉባኤ በአዲስ አበባ በታላቁ ቤተመንግሥት ግቢ በአጼ ምኒልክ ሠራዊት ግብር አዳራሽ ውስጥ ተደረገ ።

በዚህ በታሪካዊ ጉባኤ የኢሠፓአኮ ሰባት የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት ፣ ከ120 በላይ የሚቆጠሩ የኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ አባላትና የኮሚቴው ዋና ዋና መምሪያዎችና የመምሪያ ክፍሎች ለኢትዮጵያ ሕዝብ በይፋ ተገለጹ ። በዚህ መሠረት ሰባቱ የኢሠፓአኮ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት ከዚህ የሚከተሉት ናቸው[4] ።

ጓድ ሊቀ መንበር መንግሥቱ ኃይለ ማርያም
የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግና የኢሠፓአኮ ሊቀመንበር
የአብዮታዊ ጦር ኃይሎች ጠቅላይ አዛዥ ፣

ጓድ ፍቅረ ሥላሴ ወግደረስ
የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ዋና ጸሐፊና
የኢሠፓአኮ የርዕዮተ ዓለም መምሪያ ኃላፊ ፣

---

4 "የኢሠፓአኮ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት" ፣ ሠርቶ አደር ቅ. 1 ፣ ቁ. 2 (ሰኔ 17 ቀን 1972) ።

ጓድ ፍሥሐ ደስታ
የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ረዳት ዋና ጸሐፊና
የሚኒስትሮች ምክር ቤት ምክትል ሰብሳቢ ፣

ጓድ ብ/ጄኔራል ተስፋዬ ገብረ ኪዳን
የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ቋሚ ኮሚቴ አባልና የሀገር መከላከያ ሚኒስትር ፣

ጓድ ብርሃኑ ባይህ
የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ የቋሚ ኮሚቴ አባልና የኢሠፓአኮ የውጭ ጉዳይ መምሪያ ኃላፊ ፣

ጓድ አዲስ ተድላ
የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ የቋሚ ኮሚቴ አባልና
የብሔራዊ አብዮታዊ የምርት ዘመቻ ማዕከላዊ ፕላን ጠቅላይ መምሪያ ምክትል ሊቀመንበር ፣

ጓድ ለገሠ አስፋው
የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ የቋሚ ኮሚቴ አባልና የኢሠፓአኮ የድርጅት መምሪያ ኃላፊ ።

የአገሩ ብቸኛው የፖለቲካ ድርጅት ኢሠፓአኮ በሰኔ 1972 ከተደረገው ከአንደኛው ጉባኤ በታህሣሥ 1975 ሁለተኛው ጉባኤ እስከደረገበት ድረስ በሁለት ዓመታት ተኩል ጊዜ ውስጥ የኢትዮጵያን ሕዝብና ሕብረተሰብ በአንድ ማዕከላዊ ፖለቲካ አመራር ሥር ለማደራጀት በርዕዮተ ዓለማዊ ፣ በመንግሥታዊ ፣ በፖለቲካዊ ፣ በኢኮኖሚያዊ ፣ በዓለም አቀፋዊና በድርጅታዊ መስኮችና ዘርፎች ብዙ ትግሎችና እርምጃዎች አካሄደ ።

አንደኛ ፣ ተፈጥሮን ፣ ሰውን ፣ እውቀትን ፣ ሕይወትን ፣ ታሪክን ፣ ሁኔታዎችን ፣ ትምህርትን ፣ ሥራን ፣ ወዘተ... በሚመለከት መሠረታዊ ጉዳይ ሕብረተሰቡን ከአለፈው አድሃሪ ፊውዳላዊ አመለካከትና ተጽእና ነፃ ለማውጣት ብሎም በሕብረተሰብ ዘንድ በማርክሲዝም ሌኒኒዝም ሳይንስና ትምህርት መርሆና መሠረት የሠርቶ አደሩን መደብ ርዕዮተ ዓለም ለማስተማርና ለማስፋፋት በሠርቶ አደር ጋዜጣ፣ በመስከረም መጽሔት ፣ በኩራዝ መጻሕፍት ድርጅት በዜና ማሰራጫ መሣሪያዎችና ድርጅቶች በአብዮታዊ መፈክሮችና ጽሑፎች ፣ በውይይት ክበቦች ፣ በትምህርት ቤቶችና በጥናታዊ ሴሚናሮች አማካይነት እንዲሁም አብዮታዊና ተራማጅ መጻሕፍትን ወደ ኢትዮጵያ ቋንቋዎች በማስተርጎም ኢሠፓአኮ በአጭር ጊዜ ውስጥ ከፍተኛ የሆነ አብዮታዊና ርዕዮተ ዓለማዊ ተግባር አከናውኖዋል። ቅስቀሳ አካሄዶዋል ። ከዚህም የተነሣ ዛሬ በሕብረተሰቡ ዘንድ የማርክሲዝም ሌኒኒዝም ትምህርትና ሳይንስ የሕይወትና የተግባር መመሪያ እየሆነ መጥቶዋል ።

ሁለተኛ ፣ የኢትዮጵያን ሕዝብ በማህበራት ፣ በመሥሪያ ቤትና በሙያ ለማደራጀት ኢሠፓአኮ ብዙ ተግባራዊ ጥረት አድርጎዋል ። በዚህ አኳያና ተግባር የአብዮታዊት ኢትዮጵያ የወጣቶች ማህበር (አኢወማ) እና የአብዮታዊት ኢትዮጵያ የሴቶች ማህበር (አኢሴማ) በአገር አቀፍ ደረጃ ሲደራጁ ፣ ምስቱ አንጋፋ ሕዝባዊ ድርጅቶች ማለትም የመላ ኢትዮጵያ ሠራተኞች ማህበር (መኢሠማ) ፣ የመላ ኢትዮጵያ ገበሬዎች ማህበር (መኢገማ) እና የከተማ ነዋሪዎች ማህበራት (ከነማት) ተጠናክረው በአዲስ መዋቅር ተደራጅተዋል ።



በመንግሥት መሥሪያ ቤቶችና በፋብሪካዎች እንዲሁም በጦርና በፖሊስ ኃይሎችና ድርጅቶች የውይይት ክበቦችና መሠረታዊ ድርጅቶች ተስፋፍተዋል ። የአርበኞች ፣ የመምህራን ፣ የጋዜጠኞች ፣ የሕግ ባለሙያዎች ፣ የጤና ባለሙያዎች ፣ የደራሲያን ፣ የሙዚቃ ባለሙያዎች ፣ የተዋንያንና የሠአሊዎች ማህበራት በየሙያቸውና በየመስካቸው በኢሠፓአኮ መመሪያ መሠረት በአገር አቀፍ ደረጃ ተጠናክረው ተደራጅተዋል ። በተጨማሪም በአዋጅ ቁጥር 236/1975 የኢትዮጵያ ብሔረሰቦች ጥናት ኢንስቲትዩት ተቋቁሟል ።

በአጭሩ ዛሬ በኢትዮጵያ በአምስቱ ታላላቅ ሕዝባዊ ድርጅቶች ማለትም በመኢሠማ ፣ በመኢገማ ፣ በከነማት ፣ በአኢወማና በአኢሴማ በሀያ አንዱ ዋና መንግሥታዊ መሥሪያ ቤቶች ማለትም ባገር አስተዳደር ፣ ባገር መከላከያ ፣ በውጭ ጉዳይ ፣ በትምህርት ፣ በኢንዱስትሪ ፣ በግብርና ፣ ባገር ውስጥ ንግድ ፣ በውጭ ንግድ ፣ በገንዘብ ፣ በትራንስፖርትና መገናኛ ፣ በማስታወቂያና መርሐብሔር ፣ በቡናና ሻይ ልማት ፣ በመንግሥት እርሻዎች ፣ በሥራናማህበራዊ ጉዳይ ፣ በማዕድንና ኃይል ምንጭ ፣ በከተማ ልማትና ቤት ፣ በሕግና ፍትሕ ፣ በጤና ፣ በባህልና ስፖርት ጉዳይ ፣ በሕዝብና ሀገር ደህንነትና በኮንስትራክሽን ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች ፣ በአሥሩ መካከለኛ መሥሪያ ቤቶች ማለትም በካሣ ፣ በጡረታ ፣ በመንግሥት ሠራተኞች ማስተዳደሪያ ፣ በከፍተኛ ትምህርት ፣ በሳይንሥና ቴክኖሎጂ ፣ በቱሪዝምና ሆቴሎች ፣ በስፖርትና አካል ማሰልጠኛ ፣ በዕርዳታ ማስተባበሪያና ማቋቋሚያ ፣ በሕፃናትና በውሃ ልማት ኮሚሽን መሥሪያ ቤቶችና ከዚህ በላይ በሠንጠረዥ 8 በተገለጹት በገንዘብ ፣ በንግድ ፣ በምርትና በማከፋፈያ ድርጅቶች በመለስተኛ ሙያ ማህበራት ማለትም በአርበኞች ፣ በመምህራን ፣ በደራሲያን ፣ በጋዜጠኞች ፣ በሕግ ባለሙያዎች ፣ በጤና ባለሙያዎች ፣ በሙዚቃ ባለሙያዎች ፣ በተዋንያንና በሠዓሊዎች ማህበራት አማካይነትና ውስጥ የኢትዮጵያ ሕዝብና ሕብረተሰብ በሙሉ ከሕፃናት ኮሚሽን እስከ አርበኞች ማህበር የተደራጀ ሲሆን "በአሁኑ ጊዜ በመኢሠማ ፣ በመኢገማ ፣ በአኢወማ ፣ በአኢሴማና በከነማት የአመራር አካላት ውስጥ ከአንድ ሚሊዮን ሦስት መቶ ሺ በላይ ሰዎች ይገኛሉ ።[5]

ከዚህ በላይ የተገለፁ የታላቁ ሕዝባዊ አብዮታችን ውጤቶች የሆኑ የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ድርጅቶችና የውይይት ክበቦች ታሪካችንና ሕብረተሰባችንን በዓይነት በመለወጥ ላይ ይገኛሉ ። በእነዚህ ሕዝባዊ ድርጅቶችና ውይይት ክበቦች የጎሣ ፣ የቋንቋ ፣ የጾታና የሃይማኖት ልዩነት የለም ። የድርጅቶችና የውይይት ክበቦች መሠረትና ኃይል የኢትዮጵያ ሠርቶ አደር ሕዝብ መደባዊና ብሔራዊ አንድነት ነው ። በመሆኑ እነዚህ ሕዝባዊ ድርጅቶችና የውይይት ክበቦች የዲሞክራሲና የእኩልነት መድረኮችና መማሪያዎች ናቸው ። ዛሬ የኢትዮጵያ ሕዝብ በየአካባቢው በእነዚህ ሕዝባዊ ድርጅቶችና ውይይት ክበቦች አማካይነት በተለይም በመኢገማ ፣ በመኢሠማና ፣ በከነማት አማካይነት የአከባቢውን የፀጥታ ፣ የፍርድ ፣ የሕግ ፣ የምርት ፣ የገበያ ፣ የትምህርት ፣ የጤና ፣ የመገናኛ ፣ የልማት ፣ ጉዳዮች ከላይ ከአብዮታዊ መንግሥትና ከኢሠፓአኮ በሚሰጠው ደምብና

5 "ጓድ ሊቀ መንበሩ ያቀረቡት ማዕከላዊ ሪፖርት" ፣ ሠርቶ አደር ፣ ቁ. 4 ፣ ቁ. 12 (ታህሣሥ 26 ቀን 1975) ።

ሠንጠረዥ 13

የኢትዮጵያ መንግሥታዊና ሕዝባዊ መሥሪያ ቤቶች ፣ ድርጅቶችና ማህበራት በ1973

| ተራ ቁ. | ሕዝባዊ ድርጅቶች | የማህበራት ብዛት | የአባላት ብዛት | የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች | ኮሚሽኖችና ድርጅቶች |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | መኢገማ | 25.000 | 7.000.000 | ሀያ አንዱ ያገር አስተዳደር፣ ያገር መከላከያ ፣ የውጭ ጉዳይ የትምህርት፣የኢንዱስ ትሪ ፣ የግብርና ፣ ያገር ውስጥ ንግድ ፣ የውጭ ንግድ ፣ የገንዘብ ፣ የትራ ንስፖርትና የመገናኛ ፣ የማስታወቂያ መርሐብ ሔር ፣ የቡናና ሻይ ልማት የመንግሥት እርሻዎች የሥራና ማህበራዊ ጉዳይ የማዕድንና ኃይል ምንጭ የከተማ ልማትና ቤት የሕግና ፍትሕ ፣ የጤና የባህልና ስፖርት ፣ የሕ ዝብና ሀገር ደህንነት ፣ የኮንስትራክሽን ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች | አሥሩ የቡና ፣ የጡረታ የመንግሥት ሠራተኞች፣ ማስተዳደሪያ የከፍተኛ ትምህርት ፣ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ፣ የቱሪዝምና ሆቴሎ ች ፣ የስፖርትና አካል ማጎልመኛ ፣ የዕር ሻታ ማስተባበሪያና ማቋ ቋሚያ ፣ የሕፃናትና የውሃ ልማት ኮሚሽን መሥሪያ ቤቶችና በ30 የሚቆጠሩ የገንዘብ ፣ የንግድ ፣ የምር ትና የማከፋፈያ ድርጅት መሥሪያ ቤቶች |
| 2 | አኢሴማ | ? | 5.000.000 | | |
| 3 | አኢወማ | 16.190 | 3.000.000 | | |
| 4 | ከነማት | 1.260 | 3.823.244 | | |
| 5 | መኢሠማ | 1.916 | 234.946 | | |
| 6 | የመንግሥት ሠራተኞች | የውይይት ክበቦች ብዛት ? | 128.610 | | |
| 7 | ኢመግ/የኢት. መምህራን ማ/ | 16 | 54.000[6] | | |
| 8 | የመለዮ ለባሽ ክፍል | የውይይት ክበቦች ? | | | |
| | ሀ. የጦር ኃይሎች | የውይይት ክበቦች ? | ? | | |
| | ለ. የፖሊስ ኃይል | የውይይት ክበቦች ? | ? | | |
| | ሐ. ሚሊሺያ | (በ1968-1969 በክፍለ ሀገ ራት የተደራጀ ሠራዊት) | ? | | |
| | መ. ሕዝባዊ ሠራዊት | | 500.000[7] | | |
| 9 | የሕፃናት ኮሚሽን | ? | ? | | |
| 10 | ሌሎች ማህበራት ፣ የጋዜጠኞች ፣ የደራሲያን ፣ የእርበኞች የሕግ ባለሙያዎች የጤና ባለሙያዎች የሙዚቃ ባለሙያዎች ፣ የተዋንያን ፣ የማኅሌዎች | | | | |

የተገኘበት ምንጭ ፣ የመኢገማና የከነማትና ማስረጃዎች ከዚሁ በላይ ሠንጠረዥ 9 ፣ አኢወማ የአኢሴማ ከአዲስ ዘመን ጋዜጣ (ነሐሴ 27 ፣ 28 1972) የመኢሠማ ከአዲስ ዘመን ጋዜጣ (ነሐሴ 24 ቀን 1973) የመንግሥት ሠራተኞች ማስተዳደሪያ ኮሚሽን (በኅዳር 1973) መኢመማ "Over 2 million students enrolled in Elementary and Secondary Schools", *The Ethiopian Herald* (July 26, 1980); "ETA Highlights Path of Struggle", *The Ethiopian Herald* (Feb. 19, 1980); "4,607 Teachers from the National Colleges", *Yezertu Ethiopia* (Hamle 4, 1973 E.C.)

6. የኢመግ አባላት መምህራን ከ128,610 መንግሥት ሠራተኞች ጋር በአንድነት ተደምሯል ።
7. የሕዝባዊ ሠራዊት ቀጥር የተወሰደው ፣ ደርግ ፣ የትግል ምዕራፍ ሦስተኛ ዓመት (መስከረም 2 ቀን 1970) ገጽ 1 ።



መመሪያ መሠረት እስከምንም ወጫዊ ወይም ሕጋዊ ተጽዕኖና ኃይት እርሱ ራሱ በባለቤትነት በመወሰን ላይ ይገኛል ። ከሁሉ በላይ የኢትዮጵያ ጭቁን ሰፊ ሕዝብ የጭቁኖች መደባዊ አንድነትና ድርጅት ኃይልና ድል መሆኑን በአብዮ ታዊ ትግልና ልምድ በመረዳት ላይ ይገኛል ። ስለዚህ በዚህ ወገኑ ሕዝባዊና ድርጅታዊ መሠረትና መዋቅር በቅርቡ ወገኑ ኢሠፓ እንደሚመሠረት እሙን ነገር ነው ።

ሦስተኛ ፣ በጥር 1969 የደርጉ አብዮታዊ ወገን በግድ ሊቀ መንበር መንግሥቱ ኃይለማርያም መሪነት በፀረ አብዮተኞች ክንፍ ላይ ወሳኝ አብዮታዊ ድል ከተጎና ጸፈበት ብሎም አብዮቱ ከተከላካይነት ወደ አጥቂነት ከተሸጋገረበት ጊዜ ጀምሮ በአብዮታዊት ኢትዮጵያና በዓለም ሶሻሊስት አገሮች ፣ በኮሚኒስት ፓርቲዎች በዓለም አቀፍ ተራማጅ ድርጅቶች ፣ በብሔራዊ እርነት ንቅናቄዎችና በተራማጅ ታዳጊ አገሮች መካከል በየጊዜው እያደገ የመጣ የወዝደራዊ ዓለም አቀፋዊነት ግንኙነትና ትብብር ኢሠፓአኮ ከተመሠረተበት ጊዜ አንስቶ የበለጠ እየተጠና ከረ መጥቷል ።[8]

በዚህ ረገድ በጥር 1969 አብዮቱ በውስጥ አድኃሪ ኃይላት ወሳኝ ድል ከተ ቀዳጀበት ጊዜ ጀምሮ የሶቪዬት ሕብረት ፣ የጀርመን ዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ ፣ የሀንጋሪ ፣ የቡልጋሪያ ፣ የኩባ ፣ የቼኮዝሎቫኪያ ፣ የሞንጎሊያ ፣ የፖላንድ ፣ የቬትናምና የዲሞክራቲክ የመን የመንግሥታትና የፓርቲ መሪዎች የማቴሪያል ፣ የፖለቲካና የመንፈስ እርዳታ በመስጠት በአድኃሪያንና በኢምፔሪያሊስቶች ላይ ከኢትዮጵያ አብዮት ጐን መሰለፋቸው ይታወሳል ።

በተጨማሪም በአፍሪካ ፣ በመካከለኛ ምሥራቅና በላቲን አሜሪካ የሚገኙ ብዙ ፣ የደቡብ አፍሪካ ፣ የደቡብ ምዕራብ አፍሪካ ፣ የምዕራብ ሰሐራ ፣ የሶማሊያ ዲሞክራቲክ መድኅን ፣ የፍልስጤም ፣ የጉቲማላና የኤልሳልቫዶር የብሔራዊ ነፃነት ንቅናቄዎች ፣ ድርጅቶችና ግምባሮች ፣ የዓለም ሰላም ምክር ቤት ፣ የአፍ ሪካና የእስያ ሕዝቦች የትግል አንድነት ድርጅት ፣ የላቲን አሜሪካ ፣ የአፍሪካና የእስያ ሕዝቦች የትግል አንድነት ድርጅት ፣ የዓለም ሠራተኞች ማህበር ፌዴሬሽን ፣ የአፍሪካ ሠራተኞች ማህበር አንድነት የዓለም ሴቶች ዲሞክራቲክ ፌዴሬሽን ፣ የዓለም ወጣቶች ዲሞክራቲክ ፌዴሬሽን ፣ የዓለም ተማሪዎች ማህ በርና የመላ አፍሪካ ተማሪዎች ማህበር ፣ ተራማጅ የታንዛኒያ ፣ የአልጀሪያ ፣ የአ ፍጋኒስታን ፣ የላኦስ ፣ የካምፑቺያ ፣ የኒካራጓ ፣ የሕዝባዊት ኮንጎ ፣ የአንጎላ ፣ የሞዛምቢክና የቤኒን መንግሥታትና መሪዎች በልዩ ልዩ መንገድና ደረጃ ድጋ ፋቸውን ለኢትዮጵያ አብዮት ገልጸዋል ።

ምንም በይፋ ፓርቲ ባይባል ኢሠፓአኮ የሚያከናውነው የኮሚኒስት ወይም የሠርቶ አደር ፓርቲ ተግባር በመሆኑ በ1972 ከተፈጠረበት ወዲህ ከሶቪዬት ሕብረት ኮሚኒስት ፣ ከኩባ ኮሚኒስት ፣ ከጀርመን ሶሻሊስት አንድነትና ከየመን ሶሻሊስት ፓርቲዎች ጋር የትብብር ስምምነት ሰነዶች ሲፈርም ፣ ገና በአገሩ ቸው የመንግሥት ሥልጣን ካልያዙ ከግሪክ ኮሚኒስት ፣ ከጀርመን ኮሚኒስት ፣

8 ኢሠፓአኮ ፣ ወዝደራዊ ዓለም አቀፋዊነትና የኢትዮጵያ አብዮት ፣ (ታኅሣሥ 1975) ገጽ 21—74 ።

ከኢጣሊያ ኮሚኒስት ፣ ከፖርቱጋል ኮሚኒስት ፣ ከአዲሱ የእንግሊዝ ኮሚኒስት ከፈረንሳይ ኮሚኒስት ፣ ከኢራቅ ኮሚኒስትና ከአውስትራሊያ ሶሻሊስት ፓርቲዎች ጋር የትግል አንድነትና የትብብር ግንኙነት መሥርቶዋል ።

ይህ በአብዮታዊት ኢትዮጵያና በዓለም ሶሻሊስት አገሮችና በኮሚኒስት ፓርቲዎች ፣ በዓለም አቀፍ ተራማጅ ድርጅቶች ፣ በብሔራዊ አርነት ንቅናቄዎች እንዲሁም በተራማጅ ታዳጊ አገሮች መካከል የተፈረመው የወዛደራዊ ዓለም አቀፋዊነት ትብብርና ግንኙነት ዛሬ የኢትዮጵያ አብዮት ብሎም ኢሠፓአኮ በዓለም ተራማጅ አገሮችና ሕዝቦች ዘንድ ያገኘውን ከፍተኛ ተቀባይነት ያሳያል ። ይህ ኢሠፓአኮ በአገር ቤትና በዓለም ያገኘው ከፍተኛ ጥንካሬና ድል የኢሠፓ ምሥረታ ጊዜ መቃረቡን የሚያሳይ አንድ ምልክት ነው ።

## 2. መ. የሶሻሊስት ኢኮኖሚ ግምባታ ትግል

### 2. መ. 1. የኢኮኖሚና የባህል ዘመቻ ጥሪ

ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮት በአብዮታዊ ደርግ አመራርና ዘመን የውስጥና የውጭ ጠላቶቹን ማለትም ኢሕአፓን ፣ ኢዲዩን ፣ በአሥራ ሦስት ጠላት መንግሥታት ድጋፍ በጥፋትና በወረራ ጦርነት የተነሱ የኤርትራ ተገንጣዮችንና የሱማሊያ ወራሪ መንግሥትን ፣ የኢኮኖሚ አሻጥረኞችን ፣ በደርጉ ውስጥ የተነሱ ፀረ አብዮተኞችንና አሻጥረኛ ስውር የፖለቲካ ድርጅቶችን እንደአመጣጣቸው ሁሉንም አንድ በአንድ ደምስሶ ኃያልነቱንና ድል አድራጊነቱን አስመስክሮዋል ። በተጨማሪም ኃያሉና ድል አድራጊው አብዮታችን ለሶሻሊዝም ግምባታ አስፈላጊና አመቺ ሁኔታዎችን ፈጥሮዋል ። በዚህ አንፃርና ተግባር ከዚህ በላይ በአጭርና በአጠቃላይ እንደአየነው ፣ የኢትዮጵያ የማይበገር ያገር መከላከያ ኃይል ለመገንባትና ጠንካራ የሠርቶ አደሮች ፓርቲ ለመመሥረት አመቺ የውስጥና የውጭ ሁኔታዎች ተፈጥሮዋል ። በኢትዮጵያ የሶሻሊዝምን ሥርዓት እውን ለማድረግ ሌላው ወሳኝ ነገርና ተግባር ከውጭ ተጽዕኖና ግፊት ነፃ የሆነ ጠንካራ ብሔራዊ ኢኮኖሚ የመገንባት ጉዳይ ነው ።

መስከረም 2 ቀን 1971 በአራተኛው የኢትዮጵያ አብዮት በዓል ላይ በአደረጉት ንግግር፣ ጠንካራ ብሔራዊ ኢኮኖሚ ግምባታ በሚመለከት መሠረታዊ ወሳኝ ነገር ፣ ጓድ ሊቀ መንበር መንግሥቱ ኃይለማርያም “የሰፊው ሕዝብ ወገን የሆንከ” አብዮታዊት ኢትዮጵያን የምትወድ ዜጋ ሁሉ ለአዲስ የምርት እንቅስቃሴ በአጭር ታጥቀህ ተነሳ” በማለት ለኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊና ብሔራዊ የዘመቻ ጥሪ ማድረጋቸው ይታወሳል ። በሊቀ መንበሩ ጥሪ ቃል ፤

“በከፍተኛ አብዮታዊ ወኔ የምንያያዘው ትግል ካለፍናቸው ግብግቦች ፣ በድል አድራጊነት ከተወጣናቸው ጦርነቶች ያላነሰ መሥዋዕትነት የሚጠይቀን ነው ። ይህ የሚጠብቀን ትግል ፣ ይህ የሚጠብቀን ጦርነት የአድሃሪው ሥርዓት ቅርስ ከሆኑት ከረኃብ ፣ ከበሽታ ፣ ከመሐይምነት ፣ ከሥራ አጥነት ፣ ከሴተኛ አዳሪነት ጋር የምንገጥመው ነው ።

“እስካሁን የገጠሙንን አድሃሪ ጦርነቶች በሕዝባዊ አብዮታዊ ጦርነቶች ለመመከትና በአሸናፊነት ለመወጣት “አብዮታዊት እናት አገር ወይም ሞት”



ብለህ ጉልበትህን ፣ ገንዘብንና ክንድህን አስተባብረህ እንደ ተነሣህ ሁሉ ፣ ዛሬም ተነሥ ። በረኃብ የጠወለገውን ወገንህን ስቃይ እየሰማህ ፣ በበሽታ የሚቀቀውን ጣዕር እየሰማህ ከተውንም ሰላም ሊኖርህ ይችላልን ? ኋላ ቀር የሆነውን የምርት ኃይል ሊያሳድግ የሚችለው ወገንህ በድንቁርና ጭለማ ተውጦ እንደ ምን ብሩህ ተስፋ ይኖርሃል ? ራሱን ጠቅሞ ሕዝባዊት ኢትዮጵያን ለመገንባት ለሚያደርገው ጥረት ድርሻ ሊያበረክት የሚችለው ወገንህ ለዕለት ጉርሱ እንኳን ቀስትና አጥቶ በሥራ ፈትነት ሲንከራተት ማየት እንዴትን ይቻልሃል ? አምራችና የኅብረተሰብ አለኝታ ልትሆን የምትችለው ወገንህ ሰብአዊነቷ ተደፍሮ በሴተኛ አዳሪነት እየተቆራመደች ነፃ ልትሆን ትችላለህ ?

“በዚህም ግምባር ድል አድራጊነትህን እስካረጋገጥክ ድረስ ተድሞውን የተነሣህበት ዓላማ ተግባራዊ ሆኗል ለማለት አይቻልም ። የተራበው ካልበላ ፣ የታመመው ካልተፈወሰ ፣ ሥራ ፈትና ሴተኛ አዳሪዋ ሥራ ላይ ተሠማርተው አምራች ካልሆኑ የሶሻሊዝም ፈር እከተላለሁ ማለት ዘበት ነው ። ይህን እውን ለማድረግ ነገ ፣ ተነገወዲያ ሳትል ታጠቅ! ተነሥ!

“ከመደብ ጠላቶችህ ተነጥለው የማይታዩትን ረኃብን ፣ በሽታን ፣ መሐይምነትን ፣ ሥራ ፈትነትን ፣ ሴተኛ አዳሪነትን ከምድረ ኢትዮጵያ ጨርሶ ለማስወገድ ለኢኮኖሚና ለባህላዊ ዘመቻ ታጠቅ !”[1]

## 2. መ. የወዛደር ርዕዮተ ዓለምና የምርት ኃይል ዕድገት ጥያቄ

ሰው ራሱን አካባቢውን የሚለውጥ ኃይል ነው ። ይህ ሲሆንና ሲባል ሰው ራሱን ሆነ አካባቢውን የሚለውጠው በትምህርትና በእውቀት መግሪያ ነው ። በመሆኑም በኢትዮጵያ ሶሻሊስት ሥርዓትና ሕብረተሰብ ለመገንባት የመጀመሪያው ወሳኝ እርምጃ የወዝ አደር ርዕዮተ ዓለምና የምርት ኃይል ዕድገት ነው። በዚህ ምክንያት የኢትዮጵያ አብዮታዊ መንግሥት ሕብረተሰቡን ከመሃይምነት ነፃ ለማውጣትና በአገሩ ትምህርትን ለማስፋፋት ብሎም የርዕዮተ ዓለም ፣ የምርትና የባህል ዕድገት መሣሪያ ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት አድርጎዋል ። በዚህ አንፃርና ተግባር፣ ከዚህ የሚከተሉ ሠንጠረዦች በተጨባጭ እንደሚያሳዩን በአብዮቱ መጀመሪያ ዓመታት አብዮታዊ መንግሥት ለትምህርትና ለርዕዮተ ዓለም ድርጅቶችና ተቋሞች ለትምህርት ቤቶችና ድርጅቶች ከፍተኛ በጀት በመመደብ በአጭር ጊዜ ውስጥ በመላው አገሩ የትምህርት ቤቶች ፣ የተማሪዎችና የአስተማሪዎች ቁጥር በከፍተኛ ደረጃ እንዲያድግ አድርጎታል ። ከምድረ ኢትዮጵያ መሃይምነት ለማጥፋት ብሎም ከወዛደራዊ ርዕዮተ ዓለም ጋር የምርት ኃይልን ለማሳደግ ብሔራዊ የመሠረተ ትምህርት ዘመቻ አውጆዋል ።

የምርትና የባህል ዕድገት ነቀርሳ የሆነውን መሃይምነትን ከምድረ ኢትዮጵያ ለማጥፋት ብሎም ሕዝባዊና ወዛደራዊ ርዕዮተ ዓለምን በአገሩ ለማስረጹትና ለማስፋፋት አብዮታዊ መንግሥት በሐምሌ 1 ቀን 1971 ብሔራዊ የመሠ

1 መንግሥቱ ኃይለማርያም (ርዕሰ ብሔር) ፣ በአራተኛው የኢትዮጵያ አብዮት በዓል ንግግር ፣ አዲስ ዘመን ፣ (መስከረም 2 ቀን 1971) ።

## ሠንጠረዥ 14

ለትምህርት ፣ ለርዕዮተዓለም ፣ ለቅስቀሳና ለድርጅት ተቋሞችና ሥራዎች በአብዮታዊ መንግሥት የተመደበው በጀት በሚሊዮን ብር ከ1967 እስከ 1974

| ተራ ቁ. | በጀት ዓመት | ትምህርት ሚ/ር | የከፍተኛ ትምህርት ተቋሞች | | | ከሀልና ስፖርት /ሚ/ር | ማስታወቂያና መርሐ ብሔር /ሚ/ር | ሕዝብ ድርጅት ጽ/ቤትና ኢሠፓአኮ | የከቲት ት/ቤት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | አ.አ.ዩ. | አሥመራ ዩ | ከት/ከሚሽን | | | | |
| 1 | 1967—1968 | 141967601 | 22250067 | 200000 | | 5064181 | 12161888 | 5000000 | 2006000 |
| 2 | 1968—1970 | 156176118 | 25494321 | 200000 | 533912 | 5630282 | 15208408 | 7000000 | 2096440 |
| 3 | 1970—1971 | 165448220 | 28799468 | 200000 | 1180931 | 7340503 | 16222209 | 7000000 | 1696440 |
| 4 | 1971—1972 | 174153718 | 31791612 | 500000 | 6794394 | 7967162 | 16633247 | 7000000 | 1896440 |
| 5 | 1972—1973 | 227358654 | 41690927 | 1181206 | 7343317 | 11383767 | 20300800 | 15241211 | 1799797 |
| 6 | 1973—1974 | 268864735 | 45921690 | 3227159 | 8044071 | 12496084 | 21203333 | 22559251 | 1810477 |
| | ድምር | 1133969054 | 215352975 | | | 49881979 | 101729879 | 63800462 | 11305594 |

የተገኘበት ፣ የኢትዮጵያ አብዮታዊ መንግሥት የ1967—68 ፣ የ1969—70 ፣ የ1970—71 ፣ የ1971—72 ፣ የ1972—73 ፣ የ1973—74 የመደበኛ በጀት ወጪዎች በነጋሪት ጋዜጣ (የ1967—1974) ፣

በዚህ ሠንጠረዥ በተዉባው እንደሚታየው ፣ ከ1967 እስከ 1974 ድረስ በስድስት በጀት ዓመታት የኢትዮጵያ አብዮታዊ መንግሥት ሕብረተሰቡን ለማስተማርና ለማደራጀት ከ1,576,000,000 ብር ወጭ አውጥቶዋል ። በአንድ በኩል የአገሩን ብሔራዊ ሀልውና ነፃነትና አንድነት የመከላከል ጦርነት ፣ እያካሄደ በሌላ በኩል ደግሞ የኢኮኖሚና የባህል ዕድገት ዘመቻ እንደሚያካሄድ ሲታሰብ ፣ የኢትዮጵያ አብዮታዊ ሕዝብና መንግሥት ሕብረተሰቡን ለማስተማርና ለማደራጀት በሽግግራዊ ወቅት በእውነቱ እጅግ በጣም ከፍተኛ ጥረት አድርጉዋል ።



## ሠንጠረዥ 15

በኢትዮጵያ የትምህርት ቤቶች ፣ የተማሪዎችና የአስተማሪዎች ብዛት በ1966 እና በ1972

| ተራ ቁ. | ትምህርት ቤቶች ፣ ተማሪዎችና አስተማሪዎች | የትምህርት ዘመን | | ዕድገት ከ1966 እስከ 1972 በፐርሰንት እስከ 1972 በቁጥር | ዕድገት ከ1966 እስከ 1972 በፐርሰንት | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 1966 | 1972 | | | |
| ሀ | የትምህርት ቤት ብዛት | | | | | |
| | 1. ከ1ኛ እስከ 6ኛ ክፍል | 2,760 | 5,213 | 2,453 | | 88.9% |
| | 2. ከ7ኛ እስከ 8ኛ ክፍል | 420 | 714 | 294 | | 70.0% |
| | 3. ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል | 120 | 160 | 49 | 66 | 40.8% |
| | ድምር | 3,300 | 6,096 | 2,796 | (በማከይ) | 196.7% |
| ለ | የተማሪዎች ብዛት | | | | | |
| | 1. ከ1ኛ እስከ 12ኛ ክፍል | 859,800 | 1,811,100 | 951,300 | | 110.6% |
| | 2. ከ7ኛ እስከ 8ኛ ክፍል | 101,800 | 186,100 | 84,300 | | 82.9% |
| | 3. ከ9ኛ እስከ 6ኛ ክፍል | 82,300 | 185,000 | 102,900 | 106 | 125.0% |
| | ድምር | 1,043,900 | 2,282,200 | 1,138,500 | (በማከይ) | 318.4% |
| ሐ | የአስተማሪዎች ብዛት | | | | | |
| | 1. ከ1ኛ እስከ 6ኛ ክፍል | 18,600 | 30,600 | 12,000 | | 64.5 |
| | 2. ከ7ኛ እስከ 8ኛ ክፍል | 3,200 | 4,640 | 1,440 | | 45.0 |
| | 3. ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል | 3,000 | 4,350 | 1,350 | 52 | 45.01 |
| | ድምር | 24,800 | 39,590 | 14,790 | (በማከይ) | 154.5 |

የተገኘ ምንጭ ፣ የዛሬይቱ ኢትዮጵያ (መስከረም 24 ቀን 1972) በትንተና ።

ሠንጠረዥ 16

ከ1971 እስከ 1972 በመጀመሪያዎቹ ሦስት የመሠረተ ትምህርት ዘመቻ ዙሮች በኢትዮጵያ ማንበብና መጻፍ የቻሉ ጉልማሶች ብዛት

| ተራ ቁ. | ክፍለ ሀገራት | ብሔራዊ የመሠረተ ትምህርት ዘመቻ 1ኛ 2ኛና 3ኛ ዙር — 1ኛው ዙር የተማሪዎች ብዛት | 1ኛው ዙር የአስተማሪዎች ብዛት | 1ኛው ዙር የጣቢያ ብዛት | 2ኛው ዙር የተማሪዎች ብዛት | 2ኛው ዙር የአስተማሪዎች ብዛት | 2ኛው ዙር የጣቢያ ብዛት | 3ኛው ዙር የተማሪዎች ብዛት | 3ኛው ዙር የአስተማሪዎች ብዛት | 3ኛው ዙር የጣቢያ ብዛት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ሸዋ | 1,248,893 | 47,468 | 6,964 | 541,570 | 29,000 | 5,031 | 634,932 | 14'323 | 4,482 |
| 2 | ሲዳሞ | 771,796 | 46,147 | 8,964 | 41,597 | 16,714 | 1,572 | 57,429 | 1'014 | 98 |
| 3 | ወሎ | 753,463 | 15,889 | 3,713 | 300,761 | 13,160 | 4,184 | 76,614 | 1'060 | 827 |
| 4 | ወለጋ | 666,834 | 25,193 | 2,612 | 154,012 | ? | ? | 79,149 | 1'257 | 658 |
| 5 | አርሲ | 334,609 | 10,714 | 3,283 | 127,809 | 4,444 | 685 | 20,088 | 319 | 138 |
| 6 | ጐጃም | 263,357 | 11,251 | 877 | 22,775 | 1,392 | 667 | 346,745 | 1'557 | 710 |
| 7 | አዲስ አበባ | 250,103 | 23,143 | 3,394 | ? | ? | ? | ? | ? | ? |
| 8 | ሐረርጌ | 241,815 | 11,175 | 868 | 216,238 | 11,978 | ? | 155,017 | 1'731 | ? |
| 9 | ከፋ | 239,147 | 6,861 | 971 | 97,938 | 3,866 | ? | 36,898 | 1'093 | 109 |
| 10 | ጋሞጐፋ | 190,319 | 6,068 | 681 | 44,078 | 2,801 | 350 | 70,480 | 462 | 48 |
| 11 | ኢሉባቦር | 186,602 | 5,675 | .670 | 94,564 | 4,653 | ? | 26,518 | 405 | ? |
| 12 | ባሌ | 161,822 | 3,223 | 330 | 53,514 | 2,121 | ? | 46,865 | 445 | ? |
| 13 | ጎንደር | 141,010 | 5,399 | 424 | 104,323 | 4,519 | 607 | 218,323 | 2'785 | 1'029 |
| 14 | ትግራይ | 115,187 | 5,941 | 720 | 60,917 | 5,941 | 728 | 95,553 | 7'760 | 1'121 |
| 15 | ኤርትራ | 104,334 | 14,047 | 355 | 56,718 | 3,441 | 365 | 28,958 | 991 | 231 |
| 16 | የጦር ኃይሎች | 24,532 | 3,522 | ? | ? | ? | ? | ? | ? | ? |
| 17 | አሰብ | 9,626 | 2,293 | 141 | 6,001 | 2,086 | 28 | 1,086 | 68 | 13 |
| | ድምር | 5,403,443 | 244,009 | 34,559 | 1,922,815 | 160,316 | 14,217 | 1,894,894 | 35,270 | 13,464 |

የተገኘበት ምንጭ ፤ ብሔራዊ የመሠረተ ትምህርት ዘመቻ 1ኛ ፤ 2ኛና 3ኛ ዙር (ሚያዝያ 1972) ፤ ከገጽ 13 ፤ የ2ኛና የ3ኛ ዙር ዘመቻ ማስረጃዎች ፤ ከዕድ ጥበባት ኤክስፖ 1973 ባህልና ስፖርት ጉዳይ ሚኒስቴር ፤ አዲስ አበባ)

ረተ ትምህርት ዘመቻ አስጀመረ ። በዚህ ታሪካዊ ዘመቻ ከ1971 ጀምሮ በሰባት ዓመታት ውስጥ መሃይምነትን ከምድረ ኢትዮጵያ ለማጥፋት ብሔራዊ ዕቅድ ተደርጉዋል ። በዚህም እንዣርና ተግባር ከ1971 እስከ 1972 በመጀመሪያ ሶስት ዘመቻ ዙር ብቻ በአገር አቀፍ ደረጃ ከ5.000.000 የሚበልጡ ጉልማሶች ማን በብና መጻፍ በመቻል ከመሃይምነት ጨለማ ነፃ መውጣታቸውን ከዚህ በላይ ሠንጠረዥ 16 በግልጽ ያሳያል ።

በሁሉም ደረጃዎች ማለትም በመሠረተ ትምህርት በመደበኛና በከፍተኛ ትምህርት ቤቶችና ድርጅቶች "ትምህርት ለምርት" "ትምህርት ለምርምር" "ትምህርት ለመደብ ትግል" በሚል ብሔራዊና ተግባራዊ መርሆ በሶሻሊስት ኢትዮጵያ ተማሪዎች ትምህርትን እንደ ምርትና ርዕዮተ ዓለም መማሪያ አድር ገው እንዲመሩ ተደርጉዋል ። ይህ የትምህርት ተግባራዊ ምርታዊና ርዕዮተ ዓለ ማዊ አገልግሎት በአጭር ጊዜ ውስጥ በአገሩ በምርትና በባህል ዕድገት መሠረ ታዊ ለውጥ እንደሚያስከትል የነገሩ ሁኔታና ሂደት ያሳያል ።

## 2. መ. 3. የኢኮኖሚና የባህል ዘመቻ

የኢትዮጵያ አብዮታዊ መንግሥት ፥ ከመሠረተ ትምህርት ዘመቻ ስምሪት ዘጠኝ ወራት ፥ ከኢሠፓአኮ ምሥረታ አሥራ ሶስት ወራት በፊት በጥቅምት 19 ቀን 1971 የብሔራዊ አብዮታዊ የምርት ዘመቻና የማዕከላዊ ፕላን ጠቅላይ መምሪያ (የኢኮኖሚና የባህል ዘመቻ) በአዋጅ ቁጥር 156/1971 ዓ. ም. በርዕሰ ብሔሩ በጓድ ሊቀ መንበር መንግሥቱ ኃይለማርያም ሊቀመንበርነት መሠረተ ። የአዋጁ መግለጫ እንደሚለው የዘመቻው ማለትም የምርት ዘመቻና የፕላን ጠቅላይ መምሪያ አበይት ዓላማዎች የሚከሉት ናቸው ።

## 2. መ. 3. 1. የኢኮኖሚና የባህል ዘመቻ ዓላማዎች

"1/ ዋናና ተቀዳሚ በሆኑ የሀገሪቱ የኢኮኖሚና የማህበራዊ ጉዳይ ችግር ላይ በማተኮር ችግሮቹን አብዮታዊና ፈጣን በሆነ መንገድ ለመፍታት የሚያ ስችል ዕቅድ ማውጣትና መፈጸሙንም ማረጋገጥ ።

"2/ ለዚህም ዕቅድ ማስፈጸሚያ በዘመቻ መልክ ሰፊው ሕዝብ ፥ ሕዝባዊና መንግሥታዊ ድርጅቶች በዘመቻው እንዲካፈሉ ማድረግ ፥

"3/ በልዩ ልዩ የኢኮኖሚ ዘርፎች ያለው የሀገሪቱ ምርት ባፋጣኝ እንዲያ ድግ ለማድረግ መመሪያ በማውጣት ፥ ለዕቅዱ ማስፈጸሚያ የሚያስፈልገውን ሁሉ በማቀናበር ፥ አብዮታዊ በሆነ መንገድ በሥራ መተርጐሙንም ማረጋገጥ፥

"4/ አብዮታዊ አሠራርን በመከተል የልማቱን እንቅስቃሴ የሚመሠረትባ ቸውንና የሚካሄድባቸውን ቦታዎች በቅርብ በመመልከት የችግሮችን ክብደት በመመዘን ቅድሚያ እየሰጠ መፍትሔ እንዲያገኙ ማድረግ ፥

"5/ ለዘመቻው መሳካት አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች ከሀገር ውስጥና ከውጭ ገር የሚገኙበትን መንገድ በመቀየስ እንዲሟሉ ማድረግ ፥

"6/ በሀገሪቱ ዋናና ተቀዳሚ ችግሮች በዘመቻ የሚከናወነውን ሥራ በመገምገምና ከሀገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማገናዘብ እንዲሁም የሀገሪቱን የረጅም ጊዜ የኤኮኖሚ ግቦች መሠረት በማድረግ የሀገሪቱን የአጭር፣ የመካከለኛና የረጅም ጊዜ የኤኮኖሚ ዕቅዶች በማዘጋጀትና በሥራ እንዲተረጐም አስፈላጊውን ሁሉ መፈጸም ።

"7/ በፖለቲካና በኤኮኖሚው መስክ የሚደረገው ትግል ተዋህዶው ለወዛደሩ ፓርቲ መቋቋም ብሎም ለሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ መመሥረት ዋርኒያውን ለመቀየስ እንዲቻል ማድረግ፣

"8/ ዘመቻው ከግቡ እንዲደርስ አስፈላጊ የሆኑ ደንቦች ትእዛዞችና መመሪያዎች በማውጣት፣ ሰፊው ሕዝብ በዘመቻው የሚሳተፍበትን መንገድ በመቀየስ፣ ስለዘመቻው ዓላማና በዘመቻውም ስለሚከናወኑበት ተግባሮች ቅስቀሳ ማድረግ ።

"ከዚህ በላይ የተጠቀሱት አበይት ዓላማዎች በአጭር ጊዜ ውስጥ ባንድ በኩል አገሪቱን ካለችበት የኤኮኖሚ ችግር ለማውጣት የሚጠበቅብንን መሥዋዕትነት ሲያስገነዝቡን፣ በሌላ በኩል ደግሞ በዚህ በትግል ሂደት ውስጥ በምንቀስመው ልምድና ትምህርት ፣ ለዘለቄታው የአገሪቱን የኤኮኖሚ አውታሮች አጠናክረን መልክ የምናሲዝበት የትግል ወቅት መሆኑን ያስታውሱናል ።"[2]

ከዚህ በላይ ለተዘረዘሩት መሠረታዊና ብሔራዊ ዓላማዎች የተቋቋመው ታሪካዊ የኤኮኖሚና የባህል ዘመቻ ጠቅላይ መምሪያ ከመዋቅር አንፃር፣

1. የጠቅላይ መምሪያ ጉባኤ፣
2. የጠቅላይ መምሪያው ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ፣
3. የጠቅላይ መምሪያው ጽሕፈት ቤት፣
4. የክፍለ ሀገር የምርት ዘመቻና የፕላን መምሪያ፣
5. የአውራጃውና የወረዳ የምርት ዘመቻና የፕላን ጉባኤ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴዎች

የተባሉ በአገር አቀፍ ደረጃ ከላይ እስከ ታች የተዘረጉ አምስት መሠረታዊና ድርጅታዊ አካሎች አሉት ። በተጨማሪም በኢኮኖሚና በባህል ዘመቻ መዋቅርና ስምሪት ሁለቱ የመኢገማና የከነማት ሕዝባዊ ድርጅቶች ከፍተኛ የሆነ ተግባርና የጎላነት ድርሻ አላቸው ። ስለዚህ የኢኮኖሚና የባህል ዘመቻ ብሔራዊ፣ ሕዝባዊ አብዮታዊና ዲሞክራሲያዊ የሆነ የኢትዮጵያ አብዮታዊ መንግሥትና ሕዝብ በሕብረት ለሶሻሊዝም ግምባታ የቀየሰው የመጀመሪያ ተግባራዊ ምዕራፍና እርምጃ ነው ።

በአጭሩ በአለፉት ዓመታት የኢትዮጵያ አብዮታዊ መንግሥትና ሕዝብ ከዚህ የመደብ ትግል አካልና ውጤት ከሆነው ከኢኮኖሚና ከባህል ዕድገት ዘመቻ ያገኘው ብሔራዊ ልምድና ትምህርት እጅግ በጣም ብዙና መሠረታዊ ነው ። አንደኛ፣ በአብዮቱ መጀመሪያ በአድኃሪያን አሻጥርና ጦርነት ክፉኛ የተ

---

2 የብሔራዊ አብዮታዊ የኢኮኖሚና የባህል ዘመቻ አዋጅ መግለጫ (ጥቅምት 19 ቀን 1971) ።



ጎዳው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ኢኮኖሚ ተመልሶ የዕድገት ፈር ይዟል ። ሁለተኛ፣ ለሠርቶ አደሩ ፓርቲ ምሥረታ፣ ለአገርና ለኢኮኖሚ ግምባታ የኢትዮጵያ ሕዝብና ሕብረተሰብ በአንድ ብቸኛ የፖለቲካ ድርጅት ማለትም በኢሠፓአኮ ሥር ከላይ እስከ ታች ተደራጅተዋል ። ሦስተኛ፣ የኢኮኖሚና የባህል ዘመቻ በአለፉት ዓመታት በአገሩ ለሕዝባዊ ኪነት፣ ለስፖርትና ትምህርት ዕድገትና መስፋፋት ከፍተኛ የሆነ አስተዋጽኦ አድርጉዋል ።

በዚህ እንፃርና ተግባር የትምህርት ቤቶች፣ የተማሪዎችና የአስተማሪዎች ብዛት በ1966 ከነበረው ጋር ሲመዛዘን ዛሬ ከእጥፍ በላይ አድጉዋል ። በመሠረተ ትምህርት ዘመቻ አማካይነት ከ10 000 000 በላይ ጐልማሶች ማንበብና መጻፍ ችለዋል ። ከአገሩ አያሌ ቋንቋዎች አሥራ አምስት የትምህርትና የስነ ጽሑፍ ቋንቋዎች ወደ መሆን ደረጃ ደርሰዋል ።

አራተኛ፣ ለወደፊት ጠንካራ የሆነ ሶሻሊስት ኢኮኖሚና ሕብረተሰብ ለመገንባት በሚደረገው አብዮታዊና ብሔራዊ ትግል ብዙ ተግባራዊ ልምድና ትምህርት ከኢኮኖሚና ከባህል ዘመቻ ተገኝቷል ። በዚህ ረገድ፣ በኢኮኖሚና በባህል ዕድገት ዘመቻ እቅድና መርሆ መሠረት በአብዮታዊ መንግሥት በሕዝባዊ ድርጅቶችና በክፍለ ሀገር አስተዳደር ሕብረትና ትብብር የሶሻሊስት ኢኮኖሚ ግምባታ መሠረትና መዋቅር በአገር ደረጃ ተዘርግቷል ። አብዮታዊ መንግሥት ለኢኮኖሚ ዕድገት መሠረትና መገፊያ በሆኑ በመንገድ፣ በድልድይ፣ በሕንፃ፣ በማዕድን፣ በኃይል፣ በውሃ ልማት፣ በትምህርት፣ በጤና፣ በእርሻ፣ በኢንዱስትሪ በንግድ ሥራዎችና መስኮች ብዙ ብሔራዊ ጥሪት ወይም መዋዕለ ንዋይ መፍሰሱን ከአለፉት ዓመታት ወዲህ ለካፒታል ወጭ ከመደበውና ከሚመድበው ከፍተኛ ብሔራዊ በጀት ምደባና በሚያወጣው መመሪያ በተጨባጭ ማየት ይቻላል ።

## 2.መ. 3. 2. የኢሠፓአኮ የኢኮኖሚና የባህል ዕድገት መመሪያ

በዚህ አኳያ ከኢኮኖሚና ከባህል ዘመቻ የተገኘውን ተግባራዊ ልምድና ትምህርት መሠረት በማድረግ፣ በኢትዮጵያ ጠንካራ ሶሻሊስት ኢኮኖሚ፣ ሥርዓትና ሕብረተሰብ ግምባታን ስትራቴጂ፣ ታክቲክና መመሪያ በሚመለከት ነገር በ1973 የኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ ሁለተኛ መደበኛ ስብሰባ ከዚህ የሚከተለውን መሠረታዊ ውሳኔ ማሳለፉ ይታወሳል ። የኮሚቴው ውሳኔ በትክክል እንደአስቀመጠው፣

"1. በሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ለሶሻሊስት ኢኮኖሚ ግንባታ የማቴሪያልና የቴክኒክ መሠረት ለመፍጠር የሚያስፈልገውን የጥሪት ክምችት ለማዳበር ምንጫችን የግብርናው ኢኮኖሚ ቢሆንም ዘርፉ ባለበት የተበታተነና አነስተኛ የምርት አደረጃጀት ሁኔታ ይህንን እውን ማድረግ ስለማይቻል የግብርናውን ክፍለ ኢኮኖሚ ለከፍተኛ ምርት ዕድገት ለማደራጀት በገጠር የሶሻሊስት የምርት ግንኙነት ለመገንባትና የካፒታሊዝምን ማቆጥቆጥ ለመከላከልና የሶሻሊዝምን ድል አድራጊነት ለማረጋገጥ ለአምራች ኅብረት ሥራ ማኅበራት መስፋፋትና መጠናከር ከፍተኛ ትኩረት እንዲሰጥ፣

"2. የሀገሪቱ የልማት ስልት መሠረት የአምራቾች ኅብረት ሥራ ማስፋፋት እንደመሆኑ ይህን በአስተማማኝ በተግባር ለመተርጐምና የግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ የምርት ውጤት በከፍተኛ ደረጃ እየዳበረ መሄዱን ለማረጋገጥ ፤

ሀ. በየዘመኑ ለልማት የሚመደበው መዋዕለ ንዋይ ከምን ጊዜውም በበለጠ በኅብረት ሥራ ማኅበራት ላይ እንዲያተኩር ።

ለ. የኅብረት ሥራ ማኅበራትን የምርት ውጤት በከፍተኛ ደረጃ ለማዳበር የተሻሻሉ መሣሪያዎችና አገልግሎቶች በማቅረብ ረገድ ቅድሚያ እንዲሰጣቸው ።

ሐ. ማኅበራቱን ለማስፋፋትና ለማጠናከር የሚያስፈልገው የሰው ኃይል በብዛትና በጥራት የሚሰለጥንበት ማሰልጠኛ ተቋሞች እንዲጠናከሩና እንዲቋቋሙ ።

መ. አብዮታውያን ሁሉ በያሉበት የኅብረት ሥራ ማኅበራትን ለማስፋፋት የሚደረገውን ጥረት በከፍተኛ ደረጃ እንዲያራምዱ።

"3. ከግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ ቀጥሎ ቅድሚያ የሚሰጠው የኢንዱስትሪ ክፍለ ኢኮኖሚ እንደመሆኑ የኢንዱስትሪ ምርት ውጤት በብሔራዊ ኢኮኖሚ ውስጥ ያለውን ድርሻ ደረጃ በደረጃ በማሳደግ የኢኮኖሚውን የምርት አወቃቀር ለመቀየር ለከባድ ኢንዱስትሪ መስፋፋት መሠረት ለመፍጠርና እያደገ የሚሄደውን የሠርቶ አደሩን የማቴሪያል ፍላጐት ለማርካት በመነሻው ወቅት የኢንዱስትሪ ልማት ሥልታችን በቀላልና በጐጆ ኢንዱስትሪዎች መስፋፋት ላይ እንዲያተኩር ።

"4. ከጠቅላላው የኢንዱስትሪ ምርት ውጤት ውስጥ 50 በመቶውን አስተዋጽኦ የሚያደርገውንና ምርታማነቱም በዝቅተኛ ደረጃ የሚገኘውን የዕደጥበብ ዘርፍ የምርት አደረጃጀት ወደ ከፍተኛ ደረጃ ለማሸጋገር ለዕደጥበብ አምራቾች የኅብረት ሥራ ማህበራት መስፋፋትና መጠናከር ከፍ ያለ ትኩረት እንዲሰጥ ።

"5. የኢንዱስትሪዎችን መስፋፋት ከሚወስኑት ሁኔታዎች መካከል ዋነኛው የሀገሪቱ የኃይል ማመንጨት ችሎታ በመሆኑ የሀገሪቱ የኢኮኖሚ ዕድገት በኃይል እጥረት የተነሳ መደናቀፍ እንዳያጋጥመው ከአሁኑ ጀምሮ ተጨማሪ የኃይል ማመንጫ ጣቢያ ማቋቋም ስለሚያስፈልግ ሀገሪቷ ባላት የተፈጥሮ ሀብት ማለትም በውሃና በእንፋሎት ኃይል ላይ የተመሠረተ አነስተኛ ፤ መለስተኛና ከፍተኛ የማመንጫ ጣቢያዎች ለማቋቋም ትኩረት እንዲሰጥ ።

"6. ሀገሪቱ ያላትን ከፍተኛ የማዕድን ሃብት በመፈለግ በማጥናትና ብሎም በማልማት ኢንዱስትሪዎች ከጥገኝነት ነፃ እንዲወጡና ለጠንካራ ሶሻሊስት ግንባታ የሚያስፈልገውን ጥሪት ክምችት ለማፍራት በማዕድን ፍለጋና ልማት ረገድ አፋጣኝ እርምጃ እንዲወሰድ ።

"7. መሠረታዊ የፍጆታ ዕቃዎች እጥረት ብሎም የእነዚህ ዋጋ መናር የሚመነጨው ከምርት አነስተኛነት ብቻ ሳይሆን ከምርት አሰረጫ



ጨትና አጠቃቀም ጉድለትም በመሆኑ የንግዱን ዘርፍ ሶሻሊስታዊ ይዘት በማጠናከር ሠርቶ አደሩ ሕዝብ ከነጋዴው ብዝበዛ ለማላቀቅ በምርት ሥርጭት መስክ የተሰማሩት መንግሥታዊና ሕዝባዊ ድርጅቶች እንዲጠናከሩ ።

"8. ሶሺያሊስት ኅብረተሰብ ለመመሥረት በተያያዝነው የግንባታ ምዕራፍ የምርት ግንኙነትን ከመለወጡ ትግል ጐን ለጐን የምርት ኃይሎችን በከፍተኛ ደረጃ ለማዳበር የሠርቶ አደሩን ምርታማነት ለማሳደግ ሳይንስና ቴክኖሎጂን ለማስፋፋትና በሀገሪቱ ችግሮች ላይ ያተኮሩ በተለይም ለግብርናው ዘርፍ ትኩረት የሚሰጡ የምርምር ሥራዎች እንዲስፋፉ ።

"9. የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ዕድገት በሽግግሩ ወቅት ኢኮኖሚ ሕግጋት ላይ በመመሥረት በሳይንሳዊ ዘዴ ለመምራትና በክፍላተ ኢኮኖሚዎች መካከል የሚፈጠረው ተዛምዶ ሶሻሊስት ኅብረተሰብ ለመገንባት የሚያስችል መሆኑን ለማረጋገጥ በረጅም ጊዜ ዕቅድ (ፕላን)መመራት አስፈላጊ እንደመሆኑ በዝግጅት ላይ የሚገኘው የ10 ዓመት የልማት ዕቅድ በተቀየሰው የልማት ስትራቴጂ ላይ ተመሥርቶ የዲሞክራቲክ አብዮቱን ፕሮግራም ለማገባደድ የፕላኑ ዝግጅት ተጠናቅቆ ተግባራዊነቱ እንዲፋጠን ።

"10. የተዘረጋውን ሰፊ የማዕከላዊ ፕላን መዋቅር በየጊዜው በማጠናከርና በማሻሻል በዲሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት መርሀ መሠረት ሰፊው ሕዝብ በድርጅቶች አማካይነት በፕላን ዝግጅትና አፈጻጸም ያለው ተግባራዊ ተሳትፎ እንዲሰፋ በምንገነባው ሶሺያሊስት ኅብረተሰብ ውስጥ ብሔራዊ ኢኮኖሚውን መምራትና በማስተዳደር በኩል ማዕከላዊ ፕላን ያለውን ወሣኝ ሚና በትክክል በመገንዘብ አስፈጻሚ መሥሪያ ቤቶችና ድርጅቶች ማዕከላዊ ፕላን ለሚጠይቀው የአሠራር ዲሲፕሊን ተገዥ እንዲሆኑ የሚያስችል ሁኔታ እንዲፈጠር ።

"11. ዛሬ በኢኮኖሚ ውስጥ ያለውን የማኔጅመንት ድክመት ለመወጣትና ወደፊት እየተራመደ ለሚካሄደው ታሪካዊ ግንባታ ምዕራፍ ተገቢውን የማኔጅመንት ድጋፍ ለማስገኘት ምርምር የአማካሪነት አገልግሎትና የሥልጠና ፕሮግራምን በማቀናጀት የሚያካሄድ ተቋም እንዲቋቋም ።"[3]

የኢትዮጵያ አብዮታዊ መንግሥትና ሕዝብ በውስጥና በውጭ አድሃሪ ኃይላት ተወጥሮ በታላቅ ብሔራዊ አደጋ ውስጥ በነበረበት ቀውጢ ወቅት በወዛደራዊ ዓለም አቀፋዊነት መርሆ መሠረት የፖለቲካ እርዳታ በመስጠት ታላቅ ባለውለታዎች የሆኑ ሶሻሊስት አገሮችና መንግሥታት እንዲሁም የኢትዮጵያ የሶሻሊዝም ግምባታ ትግል የተሳካ እንዲሆን በልዩ ልዩ መስኮችና መንገዶች ከፍተኛ የገንዘብ ፤ የመሣሪያና የቴክኒክ እርዳታ ሰጥተዋል ። እየሰጡም

---

3 ኢሠፓአኮ ፤ *የኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ ሁለተኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች*(1973 ገጽ 31—34 ።

ናቸው ። ለምሳሌ በዚህ ረገድ ፤ በኢኮኖሚና በባህል ዘመቻ ስምሪት በዓል በጥር 26 ቀን 1971 ፤ ጓድ ሊቀ መንበር መንግሥቱ ኃይለማርያም በይፋ እንደአስሙት፤

እንጋቶቹ ሶሻሊስት ሩፑብሊክ ሶቪየት ኅብረት ፤ የጀርመን ዲሞክራቲክ ሪፑብሊክ ፤ የቼኮዝሎቫኪያ ፌደራል ሶሻሊስት ሪፑብሊክ ፤ የሐንጋሪ ሕዝባዊ ሪፑብሊክ ፤ የፖላንድ ሕዝባዊ ሪፑብሊክ ፤ የቡልጋሪያ ሕዝባዊ ሪፑብሊክ ፣ ዛሬ ለምንጀምረው ዘመቻ ከክፍያ ነፃ የሆነ ገንዘብ ፤ ልዩ ልዩ የማምረቻ

### ሠንጠረዥ 17

እስከ 1975 ከሶሻሊስት አገሮች ለኢትዮጵያ በልዩ ልዩ መንገድና መልኮች ከተሰጠ ከገንዘብ ፤ ከምርት መሣሪያ ፤ ከቴክኒክና ከትምህርት እርዳታዎች በከፊል።

| ሶሻሊስ አገሮች | ነፃ ትምህርት የተማሪ ብዛት | የባለሙያዎች እርዳታ | በልዩ ልዩ መልክና መስክ የተሰጠ የገንዘብ እርዳታ በሚሊዮን ብር |
|---|---|---|---|
| ሶቪየት ሕብረት | 3155 | ብዙ አማካሪዎች በልዩ ልዩ መስኮች | 795 ሚ. ብር በክሬዲትና በስጦታ መልክ |
| ኩባ | 3321 | 892 | |
| ጀርመን ዲ. ሪፑብሊክ | 530 | ብዙ በልዩ ልዩ መስኮች | 798.26 ሚ. ብር በክሬዲት መልክ |
| ቼኮዝሎቫኪያ | 454 | 101 ኤክስፐርቶች | 49.4 ሚ.ብ. በክሬዲትና በስጦታ መልክ |
| ቡልጋሪያ | 242 | | 50 ሚ. ብ. በብድርና በስጦታ መልክ |
| ሀንጋሪያ | 191 | 30 ኤክስፐርቶች | 20.07 ሚ.ብ. በክሬዲት መልክ |
| ዩጎዝላቪያ | 140 | 20 ኤክስፐርቶች | 255.84 ሚ.ብ. በክሬዲት መልክ |
| ሮማንያ | ? | ? | 30ሚ. ዶላር በክሬዲት (60 ሚ.ብር.) |
| ፖላንድ | ? | ? | 10 ሚ. ዶላር በክሬዲት (20 ሚ. ብር) |
| ድምር 9 አገሮች | 8033 ተማሪዎች በ7 አገሮች | ከ952 በላይ ሰዎች | 2038.5 ሚሊዮን ብር በክሬዲትና በስጦታ |

የተገኘበት ፤ ምንጭ ፤ ኢሠፓአኮ ፣ ወዛደራዊ ዓለም አቀፋዊነትና የኢትዮጵያ አብዮት (1975) ፤ ገጽ 33—34 ፤ በትንተና ።



መሣሪያዎችና ቁሳቁሶችን በመስጠት ፤ ልዩ ልዩ ፋብሪካዎች በማቋቋም ፤ በልዩ ልዩ የልማት ፕሮጀክቶች በመተባበር ፤ ልዩ ልዩ ባለሙያዎችን በመሥጠትና ኢትዮጵያውያንንም በልዩ ልዩ ሙያ በማሠልጠን እኛ ልናመርታቸው ወይም በሌለንበት ወቅት ልናገኛቸው የማንችለውን የማምረቻ መሣሪያዎች በፍጥነት በማሟላት በማቅረብ ከፍተኛ ዕርዳታ አድርገውልናል ። ብዙ የተስፋ ቃልም ሰጥተውናል ማለታቸው ይታወሳል ።[4]

ከዚህ በላይ የኢትዮጵያን ሕዝባዊ አብዮት ታሪካዊ መነሻ ፤ ይዘት ፤ ሂደትና ውጤት እንዲሁም የአብዮቱን ዓለም አቀፍ ገጽታና ግንኙነት በሥፍራና በጊዜ በአጭርና በአጠቃላይ መልክ ለማሳየት ሙከራ ተደርጓል ። ከዚህ በታች ደግሞ የአብዮቱን ታሪካዊ መነሻ ፤ ሂደትና ውጤት በአንድ በተወሰነ አካባቢ ማለትም በከምባታና ሀዲያ አውራጃ እንደ ኬዝ ጥናት (as a case study) በስፋትና በዝርዝር በማጥናት አብዮቱ በአንድ ኋላ ቀር ገጠር ያስከተለው መሠረታዊ ለውጥና ዕድገት ምን እንደሆነ በሳይንሳዊ ምርምርና ሚዛን በመግለጽ የአብዮቱን ኃያልነትና ድል አድራጊነት በትክክል ለማሳየት ጥረት ተደርጓል ። እንደዚህ ያለ የአንድ አካባቢ ዝርዝር ምርምርና ጥናት ሌላ አካባቢዎችንም በተመሳሳይ ዘዴና ደረጃ በማጥናት የአብዮቱን ኃይልና ድል በከፍተኛ ደረጃ በተጨባጭ ለማሳየት ትምህርታዊ አስተዋጽኦ ሊያደርግ እንደሚችል ማለትም በምሳሌነት ሊያገለግል እንደሚችል የደራሲው ጽኑ ተስፋ ነው ።

4 ኢሠፓአኮ ፣ ወዛደራዊ ዓለም አቀፋዊነት ፣ ገጽ 29—30 ።





ጓድ ሊቀመንበር መንግሥቱ ኃይለ ማርያም
የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግና
የኢሠፓአኮ ሊቀመንበር የአብዮታዊ ጦር ኃይሎች ጠቅላይ አዛዥ
በ1975 የኢሠፓአኮን ሁለተኛ ጉባኤ በንግግር ሲከፍቱ ።
ተገኘበት ፤ የፕሬስ መምሪያ ፎቶግራፍ ክፍል (አዲስ አበባ 1975) ።

ክፍል ሦስት

# የጉልተኛ ሥርዓት በከምባታና ሀዲያ አውራጃ ከ1884 እስከ 1966

## 1. የሥርዓቱ ምሥረታና ጠባዩ

የከምባታና ሀዲያ አውራጃ በሸዋ ክፍለ ሀገር ከሚገኙ አሥራ አንድ አውራጃዎች አንዱ ሲሆን ፤ በሰሜን ከጨቦና ጉራጌ አውራጃ፤ በምሥራቅ ከሐይቆችና ቡታጅራ አውራጃ በደቡብ ከወላይታ አውራጃ ፤ በምዕራብ ደግሞ ከከፋ ክፍለ ሀገር ጋር የሚዋሰን አንድ ትንሽ ተራራማና ለም አገር ነው ። የአውራጃው ስፋት 9 171 ጋሻ ወይም 366 840 ሄክታር የሕዝቡ ብዛት ፤ በ1972 በአውራጃው ኤክስፖ በዝርዝር እንደቀረበው ፤ ከ2 500 000 በላይ ሲሆን ፤ በ1975 የተደረገው ቆጠራ እንደሚያሳየው የቤት እንስሳት ብዛት ደግሞ ከ2 300 000 ይበልጣል ። በአውራጃው በቁጥር የተለያየ ብዛት ያላቸው የሀዲያ ፤ የከምባታ ፤ የአዘርነት በርበሬ ፤ የወላይታ ፤ የጉራጌ ፤ የእንደጋኝ ፤ የአላባ ፤ የኦሮሞና የአማራ ማለትም ዘጠኝ ብሔረሰቦችና የብምረሰብ አባሎች ይኖራሉ ። ከእነዚህ የሀዲያና የከምባታ ብሔረሰቦች ፤ የየሚከተለው የቋንቋ ሠንጠረዥ እንደሚያሳየው በደቡብ ሸዋና በሲዳሞ ክፍለ ሀገራት ከቡርጂ ፤ ከጌዴኦ ፤ ከሲዳማ ፤ ከአላባና ከማረቆ ወይም ሊቢዶ ብሔረሰቦች ጋር የቀረበ ባህላዊና ታሪካዊ ግንኙነት አላቸው ።

ሠንጠረዥ 18

በሸዋና በሲዳሞ ክፍለ ሀገራት ከከምባታና ሀዲያ ብሔረሰቦች ጋር የቋንቋ ግንኙነት ያላቸው ብሔረሰቦች

| ተራ ቁ. | ብሔረሰቦች ቋንቋ | የቋንቋዎች ማለትም የቃላት ግንኙነትና ተመሳሳይነት ከመቶ | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ከምባትኛ | ጥምባርኛ | አላብኛ | ሲዳምኛ | ጌዴኦኛ | ቡርጂኛ | ሊቢዲኛ | ቀቤንኛ |
| | ሀዲይኛ | 61 | 58 | 58 | 58 | 51 | 41 | ? | ? |
| | ከምባትኛ | | 86 | 82 | 64 | 54 | 40 | ? | ? |
| | ጥምባርኛ | | | 82 | 64 | 58 | 41 | ? | ? |
| | አላብኛ | | | | 67 | 57 | 42 | ? | ? |
| | ሲዳምኛ | | | | | 63 | 47 | ? | ? |
| | ጌዴኦኛ | | | | | | 45 | ? | ? |
| | ሊቢዲኛ(ማረቆ) | | | | | | | | |
| | ቀቤንኛ (በወልቅጤ አካባቢ) | | | | | | | | |

Source: F. P. Cotterell, *Born At Midnight* (1973), p. 109.



የከምባታና ሀዲያ አውራጃ ሴት በ19ኛው ምዕተ ዓመት
From J. Borelli, *Èthiope Meriodionale* (1890)



በ1870ዎቹና በ1880ዎቹ ዓመታት ውስጥ የሸዋው መስፍን ንጉሥ ምኒልክ ለብሔራዊ አመራር ከጎንደር ፣ ከትግራይና ከጐጃም መሳፍንቶችና ነገሥታት ጋር እየተፎካከሩ የአገሩን የመሀል ፣ የምሥራቅ ፣ የደቡብና የምዕራብ ክፍል ግዛቶች በአንድ ማዕከላዊ መንግሥት ሥር ለማምጣት ወሳኝ ታሪካዊ ትግል በሚያደርጉበት ዘመን የሀዲያው መሪ ኢማም ሀሰን እንጃሞ ከጉራጌው መሪ ከኢማም ኡመር በቅሳ ጋር የፖለቲካ ሕብረት ፈጥሮ በመሀል ደቡብ ኢትዮጵያ የሀዲያ ፣ የከምባታ ፣ የአላባ ፣ የጉራጌ የስልጤና የሲዳሞ(የማረቆ) ሰዎችንና አገሮችን በአ ንድ ማዕከላዊ መንግሥትና ግዛት ለማምጣት በአካባቢው ታላቅ ጦርነት በማካ ሄድ ላይ ነበር ።[1]

በዚህ ምክንያት ራስ ጐበናን ፣ ራስ ዳርጌን ፣ ራስ መኮንንን ፣ ራስ ወልዴን ፣ ደጃዝማች ወዳጄ ጐበናን ፣ ደጃዝማች በሻህ አቦዬን ፣ ፊታውራሪ ሀብተጊዮርጊስን ጭምር በ12 ለሚቆጠሩ ለንጉሥ ምኒልክ ምርጥና ዕውቅ የጦር መሪዎችና አዝ ማቾች በአዋሽና በጊቤ ወንዞች መካከል የሚገኙ ፣ አገሮችንና ሕዝቦችን ለማስገ በር ከ1867 እስከ 1884 ድረስ የአሥራ ሰባት ዓመታት ጦርነት ወሰደ ። በዘ መኑ በሌሎችም በጦር ኃይል በተያዙ አካባቢዎች ይደረግ እንደነበር ፣ በመሀል ደቡብ ኢትዮጵያ የማረቆ የጉራጌ ፣ የአላባ ፣ የከምባታና የሀዲያ አገሮችና ሕዝቦች ከተሸነፉ በኋላ መሬታቸው በማዕከላዊ መንግሥት ስምና ሥር ሲያዝ ሕዝቡ ገባር ማለትም የመንግሥት አገልጋይ እንዲሆን ተደረገ ።

ከጦርነቱ በኋላ የዛሬው የከምባታና ሀዲያ አውራጃ ከምባታ ፣ ሌሞና ሻሾጐ ተብሎ የሁለት ልዩ ደጃዝማች አገር ተደረገ ። በደቡብ የዛሬው የአንጋጫ የታሜ ቢራ ፣ የሰቄ ፣ የአዋ ሸለቆ ወረዳዎች በአንድነት ከምባታ ተብለው የደጃ ዝማች ተሰማ ዳርጌ ግዛት ተደረጉ ። ደጃዝማቹም አንጋጫን የግዛቱ ከተማ አድርጎ ቀረቀረ ። በሰሜኑና በምዕራብ የዛሬው የሊሙ ፣ የኮንተቦና የጦምባሮ ወረዳዎች በአንድነት ሌሞና ሻሾጐ ተብለው የደጃዝማች በሻህ አቦዬ ግዛት ተደረጉ ። ደጃዝማች በሻህ ከዛሬ ሊሞ ሆስፒታል በስተምሥራቅ በሚገኘው አምባ ላይ አናን የግዛቱ ከተማ አድርጎ ቀረቀረ ።

ከአድዋ ጦርነት በኋላ የሁለቱም ደጃዝማች ግዛቶች ከምባታ ፣ ሌሞና ሻሾጐ በአንድነት ተደርበው ለአድዋው ጀግና "ለብልህ ዓይኑ ጥሩነፍጠኛ" ለራስ አባተ ቧያለው በግዛት ተሰጡ ። ራስ አባተ የአንጋጫንና የአናን ከተሞች

1 Guebre Selassie, *Chronique de Menelik II*, 2 Vols. (1930), I, p. 124; J. Borelli, *Ethiople Meriodionale* (1890); pp. 88,135, 254-256, 400; Arab-Faqih, *Conquete*, p. 224; E. Cerulli, tr. and ed; *Falk Literature of the Galla of Southern Abyssinia* (1922), pp. 71, 74, 88, 163-164; J. S. Trimingham, *Islam in Ethiopia* (1952), p. 182; Braukamper, *Hadiya*, MAP. 19, p. 262; Map. 21, p. 278;

አጥሜ ፣ ጋላ ቅጽ 2 ፣ ገጽ 41—42 ፣ 71—72 ፣ ከሳሙው (ፊታውራሪ) ፣ ማኪታወኝ (የራስ ጐበናና የራስ መኮንን ወታደር በመሆን በዘመኑ በተካሄዱ በአያሌ በውስጥና በውጭ ጦርነቶች ተካፋይ በነበረ በአንድ ኢትዮጵያዊ ተጽፎ ገና ያልታተመ ትምህርታዊ ሰነድ ፣ ይህ ደራሲ የሰነዱን የእጅ ኮፒ አግኝቶኛል) ።

ሠንጠረዥ 19

የጉራጌ ፣ የማረቆ ፣ የስልጢ ፣ የሀዲያ ፣ የከምባታና የአላባ ጦርነቶች ከ1867 እስከ 8884

| የጦርነት ዓመታት | የጦር መሪዎችና አዝማቾች | ጦርነት የተካሄደባቸው አካባቢዎችና አገሮች |
|---|---|---|
| 1867 | ? | በቀፀኔ በጣሬው ሶዶ አካባቢ |
| 1869 | ንጉሥ ምኒልክና ... | ወለኔ ፣ በሙሁር ፣ በቀቤና በዱላ ፣ በዶቢ ፣ በመስቃን ፣ በእግ በየጨሬት ፣ በአክልል በገደባኖ ፣ በጉመር ፣ በቾሀ ፣ በውርር ፣ በእነሞር ፣ በኢነር ። |
| 1871 | ? | በኡልባራግ ፣ በስልጢ ፣ በአዘርነት በርበሬ ። |
| 1878 | ንጉሥ ምኒልክ ፣ ራስ ወልዴ ራስ ጉበና ደጃች ገርማሜ ፣ ራስ መኮንን ፣ ቀኛ. ውቤ ፣ | በማረቆ ፣ በስልጢ ፣ በዘርነት በርበሬ ፣ በሻሸጉ ፣ በእነሞር ፣ በኢነር ፣ በሌሞ (የዛሬ ሊሙ)፣ በመስመስ፣ በስር (አሁን በስህተት ጥምባሮ ተብሎ የሚጠራ) ። |
| 1881 | ደጃች ገርማሜ ፣ ራስ ጉበና ፊታ. ሀብተጊዮርጊስ | በቀቤና ፣ በቾሀ ፣ በጉመር ፣ በእነሞር ፣ በኢነር ፣ በየጨሬት ፣ በስልጢ ። |
| 1883 | ራስ ወልዴ | በእነሞር ፣ በኢነር ፣ በእንደጋኝ በሌሞ ፣ በሻሸጉ ፣ በከምባታ በዱባሞ ፣ በዶንጋ ፣ በቀምበሬ ወይም ጥምባሮ (ዛሬ ታሪካዊ ባልሆነ ምክንያት የእም ሸለቆ ተብሎ የሚጠራ) ። |
| 1884 | ደጃች ወዳጆ | በአለበ ። |

*Source:* Braukamper, *Hadiya*, Maps, 19 and 21; አጥሜ ፣ ጋላ ቅጽ 2 ።

በመተው በአውራጃው መካከል በሞቾዋ ተራራ ላይ ሆማዕናን የግዛቱ መቀመጫ አደረገ ። ከ1888 እስከ 1904 ድረስ በአሥራ ስድስት ዓመታት ጊዜ ውስጥ ራስ አባተና ጭፍሮቹ በከምባታ በሌሞና በሻሸጉ የገባር ሥርዓትን በከፍተኛ ደረጃ መሠረቱ ። የሚከተለው የገባር አገልግሎት እንደሚያሳየው ፣ በራስ አባተ ዘመን በአውራጃው በ16 000 የሚቆጠሩ የገባር ቤተሰቦች ነበሩ ።



ሠንጠረዥ 20

የገባር ብዛትና አገልግሎት በከምባታና ሀዲያ አውራጃ በ1907

| | መሬትና ገባር የተሰጣቸው ጉልተኞች (የመሬት ዓይነት ሥሪት) | የመሬት ልክ በ ጋ ሻ | የገባር ቤተ ሰብ ብዛት |
|---|---|---|---|
| 1 | የሻምበል ማለት የበታች ሹማምንቶች መሬት | 3 442 | |
| 2 | የባላባት ማለት የሀገርና የጉሣ መሪዎችና አለቆች መሬት | 1 156 | |
| 3 | የሰሞን ማለትም የቤተ ክርስቲያን መሬት | 273 | |
| 4 | የሻለቃ ማለትም ያገር ገዥው መሬት | ? | |
| 5 | ለትክክለኛ ሹማምንቶችና ወታደሮች አገልግሎት የተሰጡ ገባሮች | | 11 424 |
| 6 | የሻለቃ ገባሮች | | 1 694 |
| 7 | የባላባት ገባሮች | | 694 |
| 8 | የንጉሡ ገባሮች | | 146 |
| 9 | የገባር ውስጥ ቀላድ | | 1 711 |
| 10 | ወጭው ያልታወቀ ገባሮች | | 197 |
| | ድ ም ር | ከ4 817 ...ጋሻ በላይ | 15 866 የገባር ቤተሰቦች |

የተገኘበት ፣ "ከምባታና ሊሞ በ1907" ፣ ከነጋድራስ ገብረየስ መዝገብ አምስተኛው ደብተር ገጽ 147—148 (በቀድሞ ጽ/ሚኒስቴር ፣ አዲስ አበባ) ።

## 2. የገባርና የጉልተኛ መደባዊ ትግል

በጦርነት ተሸንፈው ከተያዙ በኋላ በተለይ ከራስ አባተ ግዛት በኋላ የከምባታና ሀዲያ ገባሮች አመጽ በጉልተኛው መንግሥትና ሥርዓት ላይ በሥፍራና በጊዜ ያልተቋረጠ ጉዳይ ሲሆን የአመጹ ሁለት ዋና ምንጮችና ምክያቶች መሬትና ግብር ነበሩ ። በዚህ አኳያ አንደኛ ፣ በዘመነ ምኒልክ ፍጻሜ በሽግግራዊ ወቅት የአገሩ የጉልተኛው መደብ መሪዎችና አባሎች በበትረ መንግሥት ጥያቄ ከነወታደሮቻቸው ከየአካባቢው በአዲስ አበባ ተሰብስበው እርስ በርሳቸው በሥልጣን ጦርነት ሲተናነቁ የአውራጃው ሕዝብ በየአካባቢው በአመጽ ተነስቶ መሬቱን ወስዶ እንደገና ለተወሰነ ጊዜ የራሱ አደረገ ። ሁለተኛ ፣ የአገሩ የገዥው መደብ መሪዎችና አባሎች በ1928 በወራሪ ጠላት ተሸንፈው ከነንጉሣቸው አገሩን ጥለው ከሸሹ በኋላ ለአርባ ዓመታት በገባር ሥርዓት ሲሰቃይ የኖረው የከምባታ ፣ የሀዲያና የእንደጋኝ ሻገር ሕዝብ በአመጽ የሆሣዕናን ከተማ አቃጥሎ መሬቱን በመውሰድ የጉልተኛው መደብና መንግሥት በ1933 ተመልሶ እስከመጣ ድረስ እንደገና የራሱ አደረገ ።

ምስተኛ ፤ የአውራጃው ገባር ሕዝብ የጉልተኛውን መደብ ባህልና ሃይማኖት በግድም በውድም መቀበል እምቢ አለ ። በዚህ አኳያ ፤ ከአገሩ ረጅምና ውስብስብ ታሪካዊ ዕድገትና ሂደት አንፃር ሲታይ ፤ ከአዋሽ ወንዝ በስተደቡብና ምዕራብ በሚገኙ ብሔረሰቦች ዘንድ የአገሩ ሁለት የተደራጁ ሃይማኖቶች ማለትም ክርስትናና እስልምና ታሪካዊ መሠረትና ባህላዊ ይዞት አልነበራቸውም ። ምንም የጉልተኛው መደብ ባህሉንና ሃይማኖቱን እንዲቀበሉለት የሕግ ግፊትና ተጽዕኖ ቢያደርግ የምዕራብና የደቡብ ኢትዮጵያ ብሔረሰቦች ለምሳሌ በወለጋ ፤ በሀዲያ ፤ በከምባታ ፤ በወላይታ ፤ በከፋ ፤ በጋሞ ጐፋ ፤ በቡርጂ ፤ በሲዳሞ ፤ በጌዲኦ ወዘተ... የመንግሥቱን ሃይማኖትና ፕሮፓጋንዳ እምቢ በማለት በኋላ ከውጭ በሚሲዮናውያን አማካይነት የመጣውን የፕሮቴስታንትና የካቶሊክ ሃይማኖቶች በፈቃዳቸው ወሰዱ ። እነዚህ ብሔረሰቦች የመንግሥቱን ሃይማኖት እምቢ ያሉበት ዋና ምክንያት የዚህ ሃይማኖት ክፍል በብሔረሰቦቹ በመሬት ጉዳይ በመግባቱ ሲሆን ከውጭ የመጡ ሃይማኖቶችን የተቀበሉበት ዋና ምክንያት ደግሞ ሃይማኖቶቹን ያመጡ ሚሲዮናውያን በመጠንም ቢሆን እንኳን ለአካባቢው ትምህርት ፤ መድኃኒትና አንዳንድ ማህበራዊ አገልግሎቶች ይዘው ስለመምጣታቸው ነው ። ከእነዚህ ባህላዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች ባሻገር የአካባቢው መይም ገባር ለሃይማኖታዊ ምርምርና ምርጫ የሚያበቃው ትምህርት አልነበረውም ።

በዚህ አኳያ የሚሲዮን ትምህርት በሱዳን ኢንተርየር ሚሽን አማካይነት ወደ ሀዲያ ፤ ከምባታ ፤ ወላይታና ሲዳሞ የገባው በ1920 ሲሆን በ1928 ኢጣሊያኖች አገሩን በወረሩ ከያዙ በኋላ ሚስዮኖቹን ከአካባቢው ብሎም ከአገሩ አስወጣቸው ። ሚሲዮኖቹ ከ1920 እስከ 1928 ለስምንት ዓመታት በከምባታና ሀዲያ አውራጃ በነበሩበት ጊዜ ሹጉጤ ዱና ፤ ሰብር ምሶር ረጠቦ አመሌ የተባሉ ምስት ወጣቶች ለሚስዮናቹ ተቀጥረው ሲሠሩ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ፤ ፊደል ፤ ንባብና ጽሕፈት ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ጋር ተምረው ነበር ። በ1928 ሚሲዮኖቹ ከአገሩ ከወጡ በኋላ ምስቱ ወጣቶች በአውራጃው የወንጌል ስብከትና የመንደር ትምህርት ጀመሩ ። ጠላት ከአገሩ በ1933 ሲወጣ በእነ ሹጉጤና በተከታዮቻቸው ብርቱ ጥረት በአውራጃው በ20 000 የሚቆጠሩ በሃይማኖታዊ ማህበር የተደራጁ የወንጌል ምዕመናንና በመንደር ትምህርት ከመሃይምነት ነፃ የወጡ ጉልማሶች ነበሩ ። በ1934 በአቶ አባጉሌ ኑነም የሚመሩ የማህበሩ ተወካዮች ሄደው ከትምህርትና ከሥነ ጥበብ ሚኒስቴር የማህበሩ አባሎች በገንዘባቸውና በጉልበታቸው የመንደር ትምህርት ቤቶች በአውራጃው በየትም ቦታ ከፍተው ሊማሩና ሊያስተምሩ ይችላሉ የሚል መንግሥታዊ የመንደር ትምህርት ፈቃድ አገኙ ። በዚህ ታሪካዊ መንገድና ሂደት ከ1928 ጀምሮ በከምባታና ሀዲያ አውራጃ ገጠር መሠረተ ትምህርት ተስፋፋ ። በኋላ ተማሪዎችና ገበሬዎች በአብዮቱ ዋዜማ ግምባር ፈጥረው በጉልተኞች ላይ የሚያካሂዱትን ትግል ከዚህ በታች አግባብ ባለው ምዕራፍ ጊዜ እናያለን ።

## 3. የመሬት ዘረፋና የሕዝብ ስደት ከ1933 እስከ 1966

በጠላት ወረራ ጊዜ የአገሩ የጉልተኛው መደብ መሪዎችና አባሎች ከንጉሣቸው ጋር ከአገሩ በሽሽት ከወጡ በኋላ የአውራጃው ሕዝብ ሆሳዕናን እያተካ ለአርባ ዓመታት በጉልተኛው መንግሥት ተይዞበት የኖረውን መሬት አስምንም ድርድርና ገደብ መልሶ እንደወሰደ ከዚህ በላይ አይተናል ። ይህንን እርምጃና ድርጊት እንደ



ታላቅ ወንጀልና ብሔራዊ ክህደት በመቁጠር በድህረ ጦርነት የጉልተኛው መንግሥት "ጠፍ መሬት" ነው በሚል ሽፋን በመንግሥታዊ በተልና ትጣት እርምጃ ከከምባታና ሀዲያ አውራጃ ሕዝብ መሬት በዘረፋ መውሰድ ጀመሩ ።

ይህ ከሕዝቡ በዘረፋ የተወሰደ መሬት ለመንግሥት ባለሥልጣኖችና ሹማምንቶች ማለትም የንጉሡ ባለውለታዎች ናቸው ተብለው በደሀ መሬትና ገንዘብ ለሚሸለሙ ጉልተኞች በስጦታ እንዲሰጣቸው "የቤተ መንግሥት መርጃ መሬት" በሚል ሥሪትና ጽሕፈት ቤት ሥር እንዲያዝ ከንጉሡ ልዩ ትእዛዝ ተሰጠ ። የመንግሥቱን ምሳሌ በመከተል የአውራጃው ጉልተኞችና ባለሥልጣናት ደግሞ በሆነ ባልሆነ ምክንያት የሕዝቡን መሬት መዝረፍ ጀመረ ።

አብዛኛውም ጊዜ "ጠፍ መሬት" ነው በሚል ሽፋን መንግሥትና ጉልተኞች ከአውራጃው ሕዝብ የዘረፉት መሬት ትንንሽ የግለሰቦችና የቤተሰቦች ግላ ፤ የመንደር ሕዝብ በወል ለግጦሽ ለገበያ ፤ ለመቃብር ፤ ለጉባኤና ለሌላም ማህበራዊና ሕዝባዊ አገልግሎት የሚጠቀምበት ቦታ ነበር ። በዚህ ነገር ላይ በአውራጃው "የቤተ መንግሥት መርጃ መሬት" ሹም ከነበረው ከአንድ ከፍተኛ ባለሥልጣን በመጋቢት 1940 በአዲስ አበባ ለቤተ መንግሥት ጽሕፈት የተጻፈው አንድ ረጅም ደብዳቤ የሚከተለውን ማብራሪያ ይሰጣል ። በሹሙ ቃል ፤

"በከምባታ አውራጃ ከሚገኘው የመንግሥት መሬት አገረገዥዎች ሳይመሩ ቀርተው ውዝፍ የሆነው የግር ዋጋና የመጋዘን እህል የመቀበል ሥራ ብን ጀምር አገረገዡው ደጃዝማች....ከምባታ ባሉ ጊዜ ግማሹን መሬት በበላይ ፈታድ ግማሹን በፈታዳቸው ሰጥተዋል ።

"አገረገዡው አዲስ አበባ ከሄዱ በኋላ ዋናው ጸሐፊ አቶ... እንደዚሁ ግማሹን በማዘዣ የሚበልጠውን መሬት በፈታዱ ሰጥቶ ጨርሶታል ። የተሰጡትም የመሬቶች ዓይነት ዝርዝር ከዚህ እንደሚከተለው ነው ።

"1ኛ/ ለቤተ መንግሥት መርጃ እንዲሆን በካርኒ የግር ዋጋ ያስከፈል ናቸው።

"2ኛ/ ከምባታ ከቀና ጀምር አንድ ቀን ግረኛ ነክቷቸው የማያውቁትን ጠፍና ውድም በርስት ክፍል ሹም ሒግብ የቀሩትን መሬቶች ፤

"3ኛ/ ገምት ሆኖ ያልተገመተ ቀላድ ያልወደቀበት ሰረገ (ማለትም የግጦሽ መሬት) ለባለውለታ ለመስጠት ዓይነት የሌለው ፤

"4ኛ/ የገባር የግምት ጠፍ ባለ ርስቱ ለቆት በመንግሥት እጅ ሆኖ ትክክለኛ ወታደር በማደሪያው ላይ ተደራቢ አድርጐ አርባ አምሳ ዘመን ሙሉ በጠፍነት ይበላው ለነበረው ለባለውለታ ሊሰጥ የማይቻል ነው ። ለባለውለታውም ቢሆን ለመስጠት ደምቡ የሚያዘው የጋሻ መሬት ስለነበር በመንግሥት ላይ ያለውን ጉዳትና ጥቅም ሳያስቡ በፊትም ደጃዝማች...ና ዋናው ጸሐፊ አቶ... አሁንም ደጃዝማች...ና ዋናው ጸሐፊ አቶ... አርባ ሁለት ጠፍ ለአንድ ሰው አሥራ አምስት ጠፍ ለአንድ ሰው ይኸውም በግምት ለያንዳንዱ ሰው የተሰጠው ምስት አራት ጋሻ የሚሆን ነው ።"[2] በተጨማ

2 በከምባታና ሀዲያ አውራጃ "ከቤተ መንግሥት መርጃ የርስት ክፍል ጽ/ቤት በሆሣዕና ለቤተ መንግሥት ጽ/ቤት በአዲስ አበባ በመጋቢት 6 ቀን 1940 በቁጥር 15 የተጻፈ ደብዳቤ "የቤተ መንግሥት መርጃ ስለሚሸጡ ቁርጥራጭ መሬቶች፣ በሚል ፋይል ቁጥሩ ከ1801—1850፣ የአውራጃው ርስት ክፍል ሆሣዕና፣ ከዚህ በኋላ "የቤተ መንግሥት መርጃ መሬቶች ፋይል ቁጥር 1801—1850" ተብሎ ይጠቀሳል ።

ሪም ይህ ታሪካዊ ሰነድ ጨምር እንደሚያስረዳተምረን ፤ ከ1934 እስከ 1940 ድረስ በስድስት ዓመታት ውስጥ "የከምባታ አውራጃ ሠራተኞች ከአንድ እስከ አሥር ሆነው አላግባብ ተኮናትረው የነበረው 5,500 ጋሻ በእርስት ክፍል እንድንረከብ ከገርማዊነታቸው ከታዘዘው መሬት ውስጥ ለሰው ሰጥቶዋል" ።[3]

በከምባታና ሀዲያ አውራጃ የሚኖሩ ጉልተኞችና የተሾሙ ከፍተኛ ባለሥልጣኖች በአንድ ወገን እንደዚህ የሕዝቡን መሬት ሲዘርፉ በሌላ በኩል ደግሞ በአውራጃ ውስጥ ጠፍና ግብረጠል መሬት ነው በሚል ወንጀል ከሕዝቡ የተዘረፈውን መሬት "የቤተ መንግሥት መርጃ መሬት" ነው የሚል ልዩ ሕግና ትእዛዝ ከንጉሡ መጣ ። በዚህ ንጉሣዊ ሕግና ትእዛዝ መሠረት ከ193 7 እስከ 1942 ድረስ በአምስት ዓመታት ውስጥ ከአውራጃው ጭቁን ሕዝብ 5289[4] ቁርጥራጭ መሬቶች ማለትም ማሳዎች በአንድ "የቤተ መንግሥት መርጃ መሬት" በሚል አዲስ ስምና ሥሪት ተዘርፎ ተያዘ ።

በእውነቱ የሆነ እንደሆነ ፣ ከዚህ በላይ እንደተባለ ፣ እነዚህ 5289 ቁርጥራጭ መሬቶች የተባሉት ትንንሽ ማሳዎችና ቦታዎች ጠፍና ግብረ ጠል መሬቶች ሳይሆኑ በልዩ ልዩ ደጋማ አካባቢዎች የአውራጃው ሕዝብ በሕብረት ለመቃብር ፣ ለገበያ ፣ ለግጦሽ ፣ ለሌላም ማኅበራዊ አገልግሎቶች የሚጠቀምባቸው የጋራ የመንደር ይዞታዎችና ሥፍራዎች ነበሩ ። በተጨማሪም እነዚህ መሬቶች የሠፊው ሕዝብ ንብረቶች መሆናቸውን በአውራጃው ውስጥ በመሬት ዘረፋ ወንጀል የተሰማሩ ባለሥልጣኖች ራሳቸው በትክክል ያውቁ ነበር ። ለምሳሌ በነሐሴ 19 ቀን 1941 ከአንጋጫ ወረዳ ግምጃ ቤት በሆሣዕና ለአውራጃው ግምጃ ቤት በቁጥር 156 የተጻፈው ደብዳቤ እንዳስቀመጠው ፣

"እነዚህ ሠረገና ውድቅ ጠፍ ተብለው የሚጠሩ መሬቶች ሁኔታ እንደዚህ ነው ።

"1ኛ/ ሠረገ ማለት ከቅኚ በፊት የነበሩት በየሕዝቡ እርስት መካከል እየተለካ በጉድባ እየተከበበ ለከብት መውጫና ለመቃብር ተብሎ የቀረ ነበር ። ይኸው መሬት በቀላድ ሆነ በግምት ተለክቶ መዝገብ ሳያውቀው በ37 ዓ. ም. እንደብዛቱና ማነሱ እየተመለከትን በቀላድና በግምት በካርኒ ሠርተን በመዝገብ ሞላናቸው ።

"2ኛ/ ውድቅ የተባሉት በቅኚ ጊዜ መሬት ሲገመት ባለርስቱ ስለጠፋ እርስቱ የመንግሥት ሆኖ አንድ ጠፍ ሁለት ጠፍ እየተባለ በመዝገብ ተጽፎ በኋላ ወታደር በየማደሪያው ላይ እንደማዕርጉ እየተጨመረለት ሲተዳደርበት ኖሮ ላይ እንደጻፍነው በ37 ዓ. ም. እንደብዛታቸውና ማነሳቸው

3 ከዚህ በላይ በተጠቀሰው ሰነድ ውስጥ ።

4 በከምባታና ሀዲያ አውራጃ ከቤተ መንግሥት መርጃ የርስት ክፍል ጽ/ቤት ሆሣዕና ለአውራጃው ግዛት ጽ/ቤት ሆሣዕና በመጋቢት 28 ቀን 1943 በቁጥር 653/43 የተጻፈ ደብዳቤ / በቤተ መንግሥት መርጃ መሬቶች ፋይል ቁጥር 1801—1850) ።



መሬቶቹን እየተመለከትን እንደ ግምት መሬት መድበን በካርኒ ያሠፈርናቸው መሬቶች ናቸው ።"[5]

በመጀመሪያ ከእነዚህ ከአውራጃው ሕዝብ ከተዘረፉ ከ5289 ቁርጥራጭ መሬቶች 1000 ለወታደሮች እንዲሰጡ ተወሰኑ ። በዚሁ መሠረት በአውራጃው ርስት ክፍል "ቁርጥራጭ መሬቶች" በተባለ ፋይል ውስጥ 538 የመሬት ፈላጊ ወታደሮች ስሞች ተመዝግበዋል ። በተጨማሪም አንድ ከቤተ መንግሥት መርጃ የርስት ክፍል ጽ/ቤት በጥር 28 ቀን 1943 ለአውራጃው ግዛት ጽ/ቤት የተጻፈው ደብዳቤ ለ60 ወታደሮች ቁርጥራጭ መሬቶች እንደተሰጡ ያሳያል ። ነገር ግን ከዚያ በኋላ

ለቤተ መንግሥት መርጃ ተብለው በከምባታ አውራጃ የሚገኙ አምስት ሺህ ሁለት መቶ ሰማንያ ዘጠኝ የግምት መሬቶች ቁርጥራጭ በመሆናቸው ለባለውለታ ለመስጠት ስለማይስማሙ "ባለገሩም ከራስ አባቱ ጀምሮ ቤት ሠርቶ አትክልት ተክሎ የያዘው ስለሆነ ግኝው ተፈቅዶለት ቢገዛው ይሻላል" ተብሎ ከላይ በአዲስ አበባ በንጉሡ ልዩ ትእዛዝ ተወሰነ ።[6]

ውሳኔውንም በሥራ ላይ እንዲያውለው ፈታውራሪ .... በአውራጃው ከዘመነ ገዓር ጀምሮ ከፍተኛ ባለሥልጣንና ጉልተኛ የነበረውንና በ1928 እስከ 1929 በመሬትና በግብር ጥያቄ ላይ ከአውራጃው ሕዝብ ጋር ለአንድ ዓመት ከተዋጉት ሥር ደጃዝማቾች ፣ ፊታውራሪዎችና ግራዝማቾች አንዱ ተሾመ ።

ከዚህ በላይ በተገለፀው ሁኔታ የቤተ መንግሥት መርጃ ተብሎ ከአውራጃው ሕዝብ የተዘረፈውን መሬት ለራሱ ለተዘረፈው ሕዝብ እንደገና መልሶ እንዲሸጥ በንጉሡ የተሾመው ፊታውራሪ ... ወሰንና ገደብ በሌለው ሥልጣኑ 5289 ቁርጥራጭ መሬቶች ከተባሉ ማሳዎች አልፎ የአውራጃው ሕዝብ በየቦታው የራሱን መሬት በአዲስ እያስመዘገበ መልሶ እንዲገዛው በግልጽና በስውር በማስገደድ በትንሽ ጊዜ ውስጥ ከአውራጃው ብዙ ሕዝብ መሬቱንም ፣ ቤቱንም ንብረቱንም አጥቶ ወደ ሌላ ክፍለ ሀገራትና ሥፍራዎች እንዲሰደዱ የሚያደርግ አዲስ ሁኔታና ሂደት ፈጠረ ። ለምሳሌም ፣ በዚህ ፊታውራሪ.... የአውራጃውን ሕዝብ በየአካባቢው በዘረፋ የተያዘበትን የራሱን መሬት መልሶ እንዲገዛ በአስገደደበት ጥያቄ ከአውራጃ ግዛት ግምጃ ቤት ለአርሲ ጠቅላይ ግዛት ግምጃ ቤት በጥር 23 ቀን 1945 የተጻፈው ደብዳቤ እንደሚከተለው ያብራራል ። ደብዳቤው እንደሚለው ፣

"በከምባታ አውራጃ ቤተ መንግሥት መርጃ የርስት ክፍል ሹም ቁርጥራጭ መሬት በመንግሥት ስም እንዲሸጥ ተፈቅዶልኛል በማለት ለሚያደርጉት የሥራ አፈጻጸም የታዘዙትን በመከተል ሳይሆን ከአሥር ዓመት በላይ ገብሮበት የሚኖረውንና ርስትነቱም በስሙ የሚጸናለትን ፣ ሁኔታው ሳይታወቅ የገበርከበትም

5 ከአንጋጫ ወረዳ ግምጃ ቤት ለአውራጃ ግምጃ ቤት በነሐሴ 19 ቀን 1941 በቁጥር 156 የተጻፈ ደብዳቤ (በቤተ መንግሥት መርጃ መሬቶች ፋይል ቁጥር 1801—1850) ።

6 ከአርሲ ጠቅላይ ግዛት ጽ/ቤት ለአውራጃው ግዛት ጽ/ቤት በህዳር 13 ቀን 1942 በቁጥር 5/883 የተጻፈው ደብዳቤ (በቤተ መንግሥት መርጃ መሬቶች ፋይል ቁጥር 1801—1850) ።

ማስረጃ በእጅህ ቢኖር ለመሬቱ ዋጋ ትከፍላለህ በማለት ከአንዳንድ ሰው እስከ ዘጠኝ መቶ ብር ያስከፈሉ ይገኛል ። ይኸውም በብዙ ሺህ የሚቆጠር ሕዝብ ነው ። ምንም ባለርስቱ ባልታወቀ ድንገተኛ ዕጻ ላይ ቢወድቅ ከእቤቱታ መታገሡ የራሱ ፋንታ ይሁን እንጂ በደንብ ይሁን ያለደንብ ለተሸጠው መሬት በታወቀው ስለ መሬት ግብር አዋጅ በንጉሠ ነገሥቱ ሕጋዊ መከፈል የሚገባውን ግብርና አስራት እንዲሁም የተማሪ ቤት ታክስ ያለ ሕግ ታሪፉን በማጉደል ይቀበሉታል ።"[7]

አድኅሪው መንግሥትና ሥርዓት በከምባታና ሀዲያ አውራጃ ሕዝብ ላይ የፈጸመው ግፍና በደል ይህ ብቻ አልነበረም ። በተጨማሪም በፊታውራሪ..... መሪነት በመሬት ዘረፋ ተግባር የተመራው "የቤተ መንግሥት መርጃ የርስት ክፍል ጽሕፈት ቤት" የአውራጃውን ሰዎች የገዛ መሬታችሁን ግዙ በማለት በግድም በውድም የመሬቱን ዋጋ ገንዘብ ከተቀበለ በኋላ ለሰዎቹ መሬት መግዛታቸውን የሚያረጋግጥ ብሎም የመሬቱ ባለይዞታዎች ማለትም ባለቤቶች መሆናቸውን የሚያጸና ሕጋዊ ደረሰኝ አልሰጥም አለ ። በዚህ በሕጋዊ ደረሰኝ ጥያቄ ላይ ባጳጉሜ 5 ቀን 1946 በቁጥር 6742/4 በተጻፈው ደብዳቤ የአውራጃው ግዛት ጽ/ቤት የቤተ መንግሥት መርጃ የርስት ክፍል ጽ/ቤት ሹሙን ፤

"በዚህ አውራጃ ግዛት በናንተ በኩል የሚገኘው ቁርጥራጭ መሬት እንዲሸጥ ተፈቅዶ የተሸጠው መሬት ውል በሚፈጸምበት ጊዜ በውሉ መዝገብ ላይ አልፈርምም ያሉበትን ምክንያት በጽሑፍ እንዲገለጽልን "[8] በማለት ጠየቀው ። ለዚህም ጥያቄ በጥቅምት 11 ቀን 1947 በቍጥር 62/47 በተጻፈው ደብዳቤ ሲመልስ ፤ የመሬት ዘራፊው ፊታውራሪ... በመንግሥት ስም እርሱ ራሱ ለሕዝብ በሸጠው መሬት ውል መዝገብ ላይ "በኃላፊነት እንድፈርም የተጠየቅሁትን ለመፈጸም ለእኔ ብቻ ሳይሆን ለወደፊት ትውልድም ከባድ ችግር የሚፈጥር[9] " ጉዳይ ነው በማለት መሬት ለሸጠላቸው ሰዎች የመሬቱን ዋጋ ከተቀበለ በኋላ የውሉን ሕጋዊ ሰነድ በፊርማው የማያጸድቅ ሕጋዊ ዘራፊና ቀማኛ ባለሥልጣን መሆኑን በቃሉ ገለጸ ።

በዚህ ምክንያት የከምባታና ሀዲያ ሕዝብ በብዙ ወረዳዎች የራሱን መሬት መልሶ እንዲገዛ ታዞና ተገዶ ከብቱን በመሸጥ ከነጋዴዎች ገንዘብ በአራጣ በመበደር የመሬቱን ዋጋ ለመንግሥት ከከፈለ በኋላ መሬቱን የሸጠው የመንግሥት መሥሪያ ቤትና ሹም በራሱ በመንግሥቱ ሕግና ደምብ መሠረት የገኘውን ሕጋዊ ውል በባለሥልጣኑ ፊርማና በመንግሥት ማህተም ባለመጽደቁ የገኘው ባለቤትነት በገፈኛው መንግሥት ዘንድ ሕጋዊ አይደለም ስለተባለ እስከ ታላቁ

7 ከአውራጃ ግዛት ግምጃ ቤት ለአርሲ ጠቅላይ ግዛት በጅሮንድ በጥር 23 ቀን 1945 በቁጥር ከ/219/16 የተጻፈው ደብዳቤ (በቤተ መንግሥት መርጃ መሬቶች ፋይል ቁጥር 1801—1850) ።

8 የአውራጃው ግዛት ጽ/ቤት ለመንግሥት መርጃ የርስት ክፍል ጽ/ቤት በጳጉሜ 5 ቀን 1946 በቁጥር 6742/4 (በቤተ መንግሥት መርጃ መሬቶች ፋይል ቁጥር 1801—1850) ።

9 የቤተ መንግሥት መርጃ የርስት ክፍል ሹም ፊታውራሪ..... ለአውራጃ ግዛት ጽ/ቤት በጥቅምት 11 ቀን በቁጥር 62/47 በጻፈው ደብዳቤ (በቤተ መንግሥት መርጃ መሬቶች ፋይል ቁጥር 1801—1850) ።




የየካቲት 25 ቀን 1967 የመሬት ማለትም የአርነት ፤ የፍትሕ ፤ የእኩልነትና የዲሞክራሲ አዋጅ ድረስ በአውራጃው አብዛኛው ሕዝብ መሬቱንና ገንዘቡን በአንድነት ተዘርፎ በመንግሥትና በጉልተኛው መሬት በጪሰኝነት ሰፍሮ ሲቀመጥ፤ ከ1946 ጀምሮ በብዙ መቶ ሺህ የሚቆጠር ሕዝብ ደግሞ አውራጃውን ሙሉ በሙሉ ለቆ በከተማና በኢንዱስትሪ ሥፍራዎች በቅጥር ሥራና በወዛደርነት ለመኖር ወደ ጂማ ፤ ወደ ሲዳሞ ፤ ወደ አዋሳ ፤ ወደ ሻሸመኔ ፤ ወደ አዲስ አበባ ፤ ወደ ናዝሬት ፤ ወደ ወንጂና ሸዋ ፤ ወደ ድሬዳዋና ወደ መተሃራ በነዋሪነት ተሰደደ ።

ከዚህም የተነሣ ዛሬ ከአሰብ ጀምሮ እስከ ጋምቤላ ድረስ በአዋሽና በስምጥ ሸለቆዎች ዘመናዊ የእርሻ ፤ የንግድና የኢንዱስትሪ ድርጅቶች በአሉበት ቦታዎች ሁሉ አብዛኛው ሠራተኞች በመሬት ችግር ከከምባታና ሀዲያ አውራጃ በፍለጋ የሄዱ ሰዎች ሲሆኑ ፤ በወንጂ ፤ በሸዋና በመተሃራ ሸንኮራ አገዳ ማሳዎች ከሚሠሩ ወዛደሮች ምናልባትም 90 በመቶው የከምባታና ሀዲያ ተወላጆች መሆናቸው ሀቅ ነው ። በዚህ አኳያ ከአካባቢው በ1950ዎቹ ዓመታት የወባ ትንኝ እስኪጠፋ ድረስ ከ1946 ጀምሮ በአዋሽ ሸለቆ በወባ በሽታ ያለቀው የከምባታና ሀዲያ ሕዝብ ብዛት ምን ያህል እንደሆነ በትክክል የሚታወቅበት መንገድ እስከ ዛሬ ባይኖርም በወንጂና ሸዋ ፋብሪካዎች ዙሪያ በሚገኙ በአምስት የመቃብር ቦታዎች የሚታዩ የመቃብር ድንጋዮችና ምልክቶች ብዛትና በናዝሬት ከተማ በኃይለማርያም ማሞ ሆስፒታል ከ1940ዎቹ ዓመታት ጀምሮ ከሚገኙ ከበሽተኞችና ከሙታን መዝገቦች በብዙ ሺህ ሕዝብ እንደአለቀ በከፊል መገመት ይቻላል ።

## 4. የተማሪዎችና የገበሬዎች አመጽ በአብዮቱ ዋዜማ

በታሕሣሥ 1962 ገፈኛው የጉልተኛ መንግሥት በዩኒቨርስቲ ተማሪዎች የጭፍጨፋ ግዲያ ፈጽሞ ዩኒቨርሲቲውን ከዘጋ በኋላ በአብዮቱ ዋዜማ የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች በአድኃሪው መንግሥትና ሥርዓት ላይ በየአካባቢው አገር አቀፍ አመጽ እንደአካሄዱበት ይታወሳል ። በዚህ ወቅት የከምባታና ሀዲያ ተማሪዎች በሌላ አካባቢዎች እንደተደረገ ሁሉ ፤ ከገበሬዎች ጋር የትግል ግምባር ፈጥረው በአውራጃው ጉልተኛችና ባለሥልጣኖች ላይ ከ1964 ጀምረው በከፍተኛ ደረጃ የትጥቅ ትግል አካሄዱ ።

ይህንን አመጽ በመግረፍ ኃይል ለማጥፋት የአውራጃው የመንግሥት ባለሥልጣኖች ፤ ባላባቶችና የጉልት መሪዎች በአነገረኸው ሰብሳቢነት በጥቅምት 1965 በሆሳዕና ከተማ በአውራጃው ጽሕፈት ቤት በአንድነት በልዩ ፀጥታ ጉባኤ ተሰብስበው የአውራጃው ተማሪዎችና ገበሬዎች በአመጽ ወንጀል በአስቸኳይ በፖሊስ ኃይል እንዲደበደቡ ባለ 98 ገጽ መግለጫና ውሳኔ ወደ ሸዋ ጠቅላይ ግዛት ላኩ ። የጉባኤው ውሳኔ በአብዮቱ ዋዜማ በከምባታና ሀዲያ አውራጃ በጉልተኛ በገበሬ መደቦች መካከል የተካሄደውን የተደራጀ የትጥቅ ትግል የሚያሳይ ታላቅ ታሪካዊ ሰነድ ስለሆነ የውሳኔው ሙሉ ቃል አለእርማት እንደሚከተለው ቀርቧል ።



ደራሲው በመጋቢት 28 ቀን 1969 የኢትዮጵያ አርበኞች የድል መታሰቢያ ቀን በአዲስ አበባ አብዮት አደባባይ የአባት አርበኞችን ፎቶግራፍ ሲያነሳ ።
የተገኘበት ፤ የፕሬስ መምሪያ ፎቶግራፍ ክፍል (አዲስ አበባ 1975) ።

## 5. የከምባታና ሀዲያ አውራጃ ጉባኤ የፖለቲካ ውሳኔ 1965

በጥቅምት 1965 የአውራጃው ልዩ ጉባኤ የተማሪዎችንና የገበሬዎችን አመጽ አስመልክቶ ያሳለፈው ውሳኔ ሙሉ ቃል (ከጥቅምት 15 ቀን 1965 ከምባታ አውራጃ ጽ/ቤት ልዩ ጉባኤ ገጽ 81—89) ፡፡

"በዚህ አውራጃ ግዛት በአንጋጫ ወረዳ በዋሰራና በቃጫ ቢራ ም/ወረዳ ግዛቶች በየቀበሌው መንገዶችን እንሠራለን በማለት ተማሪዎች የግል ኮሚቴ አቋቁመው አዲስ መንገድ እንከፍታለን በማለት በሀገሩ ነዋሪ ሕዝብ እርስትና ሃብት እንዲሁም ልዩ ልዩ አትክልቶችን ያለባለቤቱ ፈቃድ ባልተጠና ሁኔታ እየጨፈጨፉ በማበላሸታቸውና ማንኛውም ተላላፊ መንገደኛ እያስገደዱ ያለው ዱታው ገንዘብ በማስከፈል አልሰጥም ያለውን የተቀመጠበትን በቅሎ በመንጠቅ ልብሱን በመግፈፍ የሚወስዱበትና የሚያዋርዱት ለመሆኑ ከወረዳ ግዛት ፖሊስና ከወረዳውም ግዛት ጽ/ቤት በቀረበው ሪፖርት መሠረት በአጥፊዎች ላይ ማስረጃው በፖሊስ ጣቢያ በኩል ተሰምቶ በምርመራው ክትጣራ በኋላ ለፍርድ ቤት በማስቀረብ ተገቢ ቅጣታቸውን እንዲቀበሉ እንዲያደርጉ ቀደም ብሎ ከአውራጃው ግዛት ለወረዳው ግዛትና ለአውራጃው ፖሊስ መምሪያ የተደጋገመ ትእዛዝ ለመስጠቱ ማህደር ጉዳዩ ለጉባኤ ቀርቦ በንባብ ተሰምቶ ከፖሊስም ሆነ ከወረዳ ግዛቱ የቀረበው ሪፖርት ለጠቅላይ ግዛቱና ፖሊስ ዋና መምሪያ መስከረም 24/65 ዓ. ም. በቁጥር ም/12/65፣ 2ኛ በቁጥር ም/72/65 በተጻፈ ደብዳቤ አማካይነት ተገልጾአል ፡፡

"ነገር ግን የፀጥታው ሁኔታ እየተባባሰ በመሄዱ አስጊና አሣሣቢ መስሎ ስለታየ የ6ቱ ወረዳ ገዥዎችን፣ ም/ወረዳ ገዥዎችንና የ6ቱ ወረዳ ፖሊስ አዛዦችን ባላባቶችና አፈር መልከኞች፣ ሠንጋቆሮዎች፣ ጭቃሹሞችና ታላላቅ የሐገር ሽማግሌዎች ቀርበው ባሉበት ሃሣብ ለሃሣብ ተወያይተው አንድ ውሳኔ ለመስጠት እንዲቻል በቁጥር 486/18 ጥቅምት 2/65 ዓ. ም. በተጻፈ ደብዳቤ በተሰጠው ትእዛዝ መሠረት የሆነ ስብሰባ ነው ፡፡

"የነገሩ ዝርዝር ሁኔታ ከጉባኤው ስብሳቢ ከተከበሩ ፊታውራሪ... የአውራጃው ገዥ በየክፍሉ ወረዳ ተማሪዎች ከወላጆቻቸው ጋር ተባባሪ ሆነው መንገድ እንሠራለን እያሉ የሰላማዊውን ሰው ንብረት በመዝረፍና ማንኛውም አትክልት እየቆረጡ በማበላሸት የመኖሪያ ቤቱን በማፍረስ ጉዳት ያደርሣሉ ሕገወጥ ወንጀል ይፈጽማሉ ተብሎ ከየክፍሉ ወረዳ ግዛት የተደጋገመ ሪፖርት ቀርቧል ፡፡

"ይህ ሁሉ ሲፈጸም እናንተ ባላባቶችና አፈር መልከኞች፣ ቆሮዎች፣ ታላላቅ የሐገር ሽማግሌዎች፣ እንዲሁም የተማሪ ወላጆች ተማሪዎች ለሚያደርጉት ሕገወጥ ተግባር ምን ዓይነት እርምጃ እንደወሰዳችሁ እንድትገልጹልን ጥሪ ስለአደረግንላችሁ መጥታችኋል ፡፡ ስለዚህ ተገቢውን ውሳኔ ሰጥቶ ለበላይ ባለሥልጣን ለማስተላለፍ ነው የጠራናችሁ ብለው በስብሰባው ለተገኙት ሕዝቦች ካስረዱ በኋላ ጥያቄው ቀጥሎ ወንጀሉም በብዛት የተፈጸመው ክፍል 1ኛ/ በአንጋጫ ወረዳ ግዛት፣ 2ኛ/ በቀዲዳ ወረዳ ግዛት፣ 3ኛ/ በጥምር ወረዳ ግዛት፣ 4ኛ/ በሲቄ ወረዳ ግዛት፣ 5ኛ/ በሊሙ ወረዳ ግዛት በሊሟና ሻሸጐ ም/ወረዳ ግዛት በአቶ ... ባላባትነት ውስጥ መፈጸሙን ከላይ በጉባኤ ፊት ቀርቦ የተፈጸመው አድራጐት ከዚህ ቀጥሎ ያለው ነው ፡፡

"1ኛ/ ተግሬዎችና ግብረአበሮቻቸው የሆኑት ወላጆቻቸውና ሌሎችም መንገድ እንሠራለን በማለት ምክንያት ያልታወቀ የውስጥ ስምምነት አድርገው የመንግሥቱ ክፍል ባለሥልጣን ያላመነበት ውል ተፈራርመው ጉዳዩን የማያውቀውን ሰላማዊውን ሕዝብ የእነርሱ ሕገ ወጥ አሠራርና ተግባራቸውን ተባባሪ ለማድረግ ፈረሙ እያሉ በማስገደድ የሚያስፈርሙ ለመሆኑና አልፈርምም ያለውን ከመንግሥት ሕግና ሥርዓት ውጭ በማዋረድ ንብረቱን በመዝረፍ ባለንብረቱንም በእግር ብረትና በገመድ ማሠራቸውን ፤

"2ኛ/ ከመንግሥት ባለሥልጣኖች የተላከ በማስመሰል ለሕዝቡ መሰብሰቢያና መስበኪያ ዘዴ በመፈለግ የባለሥልጣን ቁጥጥር በሌለበትና ሩቅ በሉ የገጠር ገበያዎች ላይ የአካባቢውን ነዋሪ የአድር ድንኳን ሰብስበው በማስተከል ሕዝቡ በብዛት ሲሰበሰብ ደብሉ ሰትለው አዋጅ አዋጅ ብለው በመናገር፤ ሀ/ በአንጋጫ ወረዳ ግዛት አርዶሉ ገበያ፤ ለ/ በጥንባሮ ወረዳ ግዛት፤ ሐ/ በሊሙ ወረዳ በሊግና ሻሸጉ ም/ወረዳ ግዛት እርሙ ቀበሌ ለሀገር ጉዳይ ውይይት ለማድረግ ራሳችንን በራሳችን ለመርዳት ምናደርገው ሸንጉ ላይ እንድትገኙ ባትገኙ ግን በእያንዳንዳችሁ ላይ ቅጣት ይፈጸምባችኋል ብለው በየገበያ ላይ አዋጅ ማናገራቸውን ፤"

"3ኛ/ ከላይ በአዋጅ የአናገሩትን ትእዛዝ ተቃዋሚ ሆና የዝርዝር ጉዳዩን ተንኮልነት አውቆትና ተረድቶ በሃሳባቸው አልስማማም ያለውንና ለከፍሉ ወረዳ ግዛት ወይም ፖሊስ ጣቢያና ፍርድ ቤት ሄዶ በራሱና በሕዝቡ ላይ ያደረሱትን በደል የሚያመለክተውን ሠላማዊ ሰው ተከታትለው በመያዝ ያለኛ ፈቃድ ለምን ሄደህ ለመንግሥት ባለሥልጣኖች አመለከትክ በማለት ከ20 እስከ 70 ብር በገንዘብ መቀጫ ፤ ተጥለው በሌሊት እቤቱ ድረስ እየሄዱ ሰፍረው በማደር እቤቱ ውስጥ ያለውን በሬ በማረድ ባለቤቱን አስረውና አስታይተው ያረዱትን በሬ በመብላት የቀጡትን ገንዘብ ለመቀበላቸው ፤

"4ኛ/ የተንግስብትም ዓላማ መንገድና ድልድዮች እንሠራለን የሚል ምክንያት ሆና የጥንቱን የሕዝብ መመላለሻ እውራ ጉዳና መንገድ በመተው ለገንዘብ ማግኛ ዘዴ በመፈለግ የመንገዱን አቅጣጫ ለውጠው የህዝብ አትክልትና ሰብል እንዲሁም የመኖሪያ ቤት የሚጠፋበትን አቅጣጫ በመያዝ የቅያሱን ሥራ በስፋት ከ30 እስከ 40 ሜትር ነው የሚተየሰው በማለት ለሕዝቡ እያማዩና እያስፈራሩ ገንዘብ የሰጣቸውን ሰው የመንገዱን አቅጣጫ ከሰብሉና ከንብረቱ ላይ ዘወር አድርገው መንገዱን ወደ ቀድሞው መንገድ እየመለሱ ገንዘብ ያልተሰጣቸውን ሰው በእርሱና በንብረቱ ላይ አዲስ መንገድ በመቀየስ ቡበዙ ድካምና ጥረት አልምቶ የሚጠቀመውን የባህር ዛፍ፤ የቡና፤ የእንጨትና የእንሰት አትክልቶችን ከወገቡ ላይ በመቁረጥና ሌላውንም አትክልቶች በመነቃቀል ልዩ ልዩ ሰብሉችንም ነቃቅለው ከጥቅም ውጭ ማድረጋቸውንና የመኖሪያ ቤታቸውን አፈራርሰው ሕዝቡን መጠጊያ በማሳጣታቸው በተለይም የገና ገና የአቶ...ና የአቶ...ን የዝንጅብል አትክልቶች ነቃቅለው ከጥቅም ውጭ ከማድረጋቸውም በላይ የአቶ....ን የቤታቸውን ዙሪያ የጥርብ አጥር አፍርሰው አንድ ላይ በመቆለል ቤንዚን አርከፍክፈው በእሳት ለማቃጠላቸው ፤"



ሠንጠረዥ 21

በከምባታናሀ ዲያ አውራጃ ወረዳዎች በየቀኑ የሚውሉ ገበያዎች ብዛት

| ቀን | በአውራጃው ወረዳዎች የሚቆሙ ዕለታዊ ሳምንታዊ ገበያዎች ብዛት | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | አንጋጫ ወረዳ | ቀዲዳ ጋሜላ ወረዳ | ቃጫ ቢራ ወረዳ | ከንተበ ወረዳ | ሊሙ ወረዳ | እሞ ሸለቆ ወረዳ | ሲቂ ወረዳ | ጥምባሮ ወረዳ | ድምር |
| ሰኞ | 4 | 1 | 4 | 4 | 4 | 6 | 4 | 5 | 32 |
| ማክሰኞ | 2 | 4 | 4 | 4 | 6 | 7 | 3 | 6 | 39 |
| ሮብ | 4 | 4 | 4 | 6 | 5 | 5 | 2 | 5 | 35 |
| ሐሙስ | 4 | 7 | 2 | 6 | 2 | 2 | 3 | 11 | 37 |
| ዓርብ | 5 | 5 | 1 | 5 | 4 | 4 | 1 | 7 | 32 |
| ቅዳሜ | 4 | 7 | 5 | 6 | 4 | 5 | 2 | 12 | 45 |
| እሁድ | 8 | 1 | 2 | 5 | 1 | 3 | 1 | 1 | 22 |
| ድምር | 31 | 29 | 22 | 39 | 26 | 32 | 16 | 47 | 242 |

የተገኘበት ፡ ከአቶ አለማየሁ ሊራንሶ ጥናት (አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ 1972) እነዚህ በ1964—1966 የፖለቲካ ትግል መድረኮች በመሆን ያገለገሉ የከምባታና ሀዲያ አውራጃ ገበያዎች ከአብዮቱ ፍንዳታ ወዲህ በኢኮኖሚያዊና በማህበራዊ አገልግሎቶች እያደጉ በመሄድ የገጠር መንደሮችና ከተሞች እየሆኑ ናቸው ።

“5ኛ/ በስብሰባው ላይ ከተደረገው ጥያቄ ከየክፍሉ ወረዳ ግዛት በተሰጠው መልስ አቶ...በልማት መልክ ባዘጋጁት በሞተር ኃይል የሚሠራ የእህል ወፍጮ ሳመጠቀም ሕዝቡ ከመኖሪያ ቤቱ እህሉን ለማስፈጨት በሚሄድበት ጊዜ ከመንገድ ላይ እየተጠባበቁ በዚህ ክፍል በተከሉት ወፍጮ ማንም ሰው እንዳይሰፈጭ ብለው ከማስገደዳቸው በላይ አስፈጭቶ የተገኘውን የቤቱንም ሆነ የወንዱን ዱቄት የያዙበትን ስልቻና ጆንያውን በመቅደድ ዱቄቱን በየሜዳው ላይ እየበተኑ በደል ከማድረሳቸውም በላይ የውፍጮ ቤቱን ዘግተው አሽገው የባላወፍጮውንም ሆነ የአካባቢውን ሕዝብ ጥቅም መከልከላቸው ፤

“6ኛ/ እነዚህ ተማሪዎች መሰል ተከታዮቻቸውንና ወላጆቻቸውን ይዘው በየቀበሌው እየተዘዋወሩ ስብሰባ በሚያደርጉበት ጊዜ ከየአካባቢው ነዋሪ ሕዝብ በማስገደድ መብልና መጠጥ የሚያቀርቡ ለመሆኑና በወላጆቻቸው ደጋፊነት ድንኳን እየተተከለላቸው በማደር ሠንጋና መሲና እየታረደላቸው ግብዣ መደረጉን ፤

“7ኛ/ ማናቸውም ባለርስት በየቦታው ለመንግሥት ግብርና ታክስ በየዓመቱ እየከፈለ በሚተዳደርበት ርስት ላይ በሲሶ አራሽ ጢሰኝነት ሠፍረው የሚገኙትን ሕዝቦች እርስቱ የአያትና የቅድመ አያታችን ነው ። እሱ ከየት አመጣው አሁንም እርስቱ የናንተ ስለሆነ የመሬቱን አበል ጥቅም እንዳትከፍሉ ለማለታቸው ፤

“8ኛ/ ማናቸውም ሰው በርስቱ ወይም በንግዱ ለመንግሥት የእርሻ ሥራ ታክስ እንዳይከፈል በሕግ ተደንግጓል እያሉ ተማሪዎች ምስጢሩና ሁኔታው ለወላጆቻቸውና ለሐገሬው ሕዝብ በማይገባ አኳኋን አስመስለው በማስረዳትና በመናገር የመንግሥቱን እርሻ ሥራ ገቢ ታክስ እንዳትከፍሉ እያሉ ለመስበካቸው ፤

“9ኛ/ በ5ቱ ወረዳ ግዛቶች ክፍል የሚገኙ ተማሪዎች ቀደም ብሎ ተምረው የወጡትም ሆኑ አሁንም በትምህርት ላይ የሚገኙ ከመቶ ሃምሣው በልዩ ልዩ ሃይማኖት ተከፋፍለው በሚገኙ የሚሽን ት/ቤት የሚገኙ ከመሆናቸውም በላይ ወላጆቻቸውም በፕሮቴስታንት ሃይማኖት ያመኑ በመሆኑ ከጥንት ተያይዞ የመጣውን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ሃይማኖት ለማጥፋት የፕሮቴስታንት ሃይማኖት ለማስፋፋት አቅደው በሚያደርጉት ዘመቻ የኦርቶዶክስ ሃይማኖትን አንለውጥም የሚሉትን ሰዎች አስረው በማሰቃየት የራሳቸውን ፀጉር ውኃ ሣይነካው በደረቁ በመላጨት ፤ የአንገታቸውን የክርስትና ሃይማኖት ምልክት የሆነውን ማተብ በመበጠስ የቅድስት ማርያምን ማህበርተኞች ጽዋ በመስበርና የጽዋውንም ልብስ ቀዳደው ለመጣላቸው ያለውድ በግድ ማሳመናቸውን ፤

‘10ኛ/ በመንግሥት የውስጥ አስተዳደር ሥር ውስጥ ገብተው የም/ወረዳ ገዥነት ፤ የባላባትነት ፤ የአፈር መልከኛነት ፤ የሰንጋቆሮነት ፤ የጭቃ ሹምነት ሥራ በሥልጣናቸው ደልድለው ለመሾማቸው ፤ ከዚህም በስተቀር እርስ በራሳቸው ፕሬዝዳንት ፤ ሊቀመንበር ፤ ምክትል ሊቀመንበር ፤ ኮሎኔል ፤ ሻለቃ ፤ ሻምበል ፤ የመቶ አለቃ ፤ ሃምሣ አለቃ ፤ አስር አለቃ ፤ አስገዳጅ የተማሪ ፖሊስ እየተባባሉ ተሿሽመው በሰላም የሚኖረው ሕዝብ በማታለል የሚያወናብዱ ለመሆኑ ፤



“11ኛ/ ከላይ እንደተገለጸው መንገድና የድልድዮች ሥራ እስታከው ወደ ገበያ ለንግድ ሆነ ለእርሻ ሥራ ወይንም ለመንግሥት የሥራ ጉዳይ ከአንድ ቦታ ወደ አንድ ቀበሌ የሚተላለፈውን ማናቸውም መንገደኛ በሰውም ሆነ በከብት በነፍስ ወከፍ እያስገደዱ በሕግ ያልታወቀ የቀረጥ ገንዘብ በኩቴ ያለደረሰኝ የሚቀበሉ ለመሆኑ ፤

“12ኛ/ በጥንባር ወረዳ ግዛት በኩል ፖሊሶች ተከሣሹን ወንጀለኛ ለመያዝ ወይም ምስክሮችን ለማስገደድ በሄዱበት ጊዜ ለምን መጣችሁ ብለው ድምጽ በሌለው የጦር መሣሪያ ከበው ፀብ በመንሳት የፖሊሶችን መሣሪያና ንብረት ለመዝረፍ ሲሞክሩ ፖሊሶቹ በንቃት በልዩ ልዩ ዘዴ ተከላከለው ማምለጣቸው ፤

“13ኛ/ በዚሁ ወረዳ ግዛት በወይዘሮ ... ባላባትነት ነዋሪ የክፍሉ ጭቃሹም አቶ... የተባለውን ሰው በቸችና በአመለታ ቀበሌ የሚገኙ ተማሪዎች ከቀኑ 12 ሰዓት በሚሆን ጊዜ እመኖሪያ ቤቱ ድረስ ከመቶ ሃምሣ በላይ የሆኑ በመሄድ እቤቱ ገብተው ባለቤቱን ይዘው በማሰር በሬውን አርደው ከአካባቢው ነዋሪ ሕዝብ እራትና መጠጥ በማስመጣት ባለቤቱ ለመስቀል በዓል ያዘጋጀውን አንድ እንስራ ቅቤ በመዝረፍ በመኖሪያ ቤቱ ውስጥ በግሩፕ (በቡድን) ተከፋፍለው ሲበሉ አድረው በማግሥቱ ጠዋት ወደ የክፍላቸው ሲበተኑ ታስሮ ካደረበት መፈታቱንና አምስት የቀንድ ከብቶች በዚያው ቀን ለመዝረፋቸው ፤

‘14ኛ/ በአንጋጫ ወረዳ በዓይናለም ም/ወረዳ ግዛት ፀሐፊ አቶ.... የተባሉትን ሰው ከም/ወረዳው ግዛት በአውራጃ ግዛት ለሚደረገው ጉባኤ የውዝፉን የመንግሥት ግብርና ከዓለምገና ወላሞ የመንገድ ሥራ ድርጅት ገንዘብ ይዘው ለመምጣት ሲዘጋጁ በተማሪዎች ተከበውና መተላለፊያ መንገድ አጥተው መቅረታቸው በጽሑፍ ገልጸዋል ።”

“15ኛ/ በአንጋጫ ወረዳ ግዛት አቶ... የተባሉትን የሠንጋቆር ወኪል የሆኑ ወደ ግል ርስታቸው ሄደው የመሬት ግብርና የዓለምገና ወላሞ የመንገድ ሥራ ገንዘብ ሲሰበስቡ ቁጥራቸው በርከት ያለ ተማሪዎችና የራሳቸውም ጢሰኞች ከቦዋቸው ከአሽከራቸው ላይ ጠመንጃውን ነጥቀው ሲወስዱ በሽጉጥ ተከላክለው መሣሪያቸውን ማስመለሳቸውንና ሕይወታቸውን በራሳቸው ቤተሰቦች እርዳታ ማዳናቸውን በዚህም ጊዜ የክፍሉ ም/ወረዳ ገዥና የወረዳው ፖሊሶች ደርሰው ነገሩን በዘዴ አብርደው መመለሳቸውን ፤

“16ኛ/ በአንጋጫ ወረዳ ግዛት የዋሰራ ም/ወረዳ ግዛት መዛግብት ያሉበት ቢሮና የወረዳውን ፖሊስ ጣቢያ አጥር ተማሪዎችና ግብረአበሮቻቸው በሰልፍ መጥተው ለማፍረስ ሙከራ ማድረጋቸው ፤

“17ኛ/ በዚሁ ክፍል የሕግ ጠበቃ የሆኑት አቶ....የተባሉትን ሰው ከመኖሪያ ቤታቸው ይዘዋቸው የፈጢኝ አስረው ወደ ተማሪዎች ስብሰባ ቦታ ሲወስዱ ቤተሰቦቻቸው ሲከላከሉ ከእርሳቸው ቤተሰቦች አራቱን ያህል በዱላ ፈንክተውና አቁስለው የታጠቁትም ሽጉጥ ነጥቀው አቶ....ንም በገመድ የፈጢኝ አስረው እንደ ከብት እየጐተቱ 10 ብር ከፍለው 60 ብር ካልከፈልክ በማለት ሲወስዱቸው በመንገድ ላይ ፖሊሶች ደርሰው

ወደ ማቢያ በመውሰድ የታሰሩትን ፈትተው ሕይወታቸውን በሕግ እርዳታ ያዳኑአቸው ለመሆኑ ፥

"18ኛ/ ማንም ሰው ወደ ፍርድ ቤት እንዳይሄድ በወንጀልም ሆነ በፍትሐብሔር በልዩ ልዩ አቤቱታ የሚቀርበው ክስ ሁሉ በተማሪዎች ሊቀ መንበር በኩል ብቻ እንዲታይ ከማድረጋቸው የተነሣ በመንግሥቱ በኩል መግባት የሚገባውን ዳኝነትና መቀጫ ወደ ግል ጥቅማቸው በማድረግ በርስት ክፍያ የቀረበውንም አቤቱታ ተቀብለው ጥቅም ባገኙበት ክፍል ሰፋ አድርገው በመስጠት የአንዱን ይዞታ ለአንዱ በማከፋፈል ለመሥራታቸው ፥

"19ኛ/ ጉዳዩን ገባ ብለን እንደተመለከትነውና እንዳጠናነው ይህ የተማሪዎች አድማ የተቀሰቀሰው በየቀበሌው ልዩ ልዩ ሚሽን ሃይማኖት በብዛት ሰለላ በየአጥቢያው የግል ት/ቤት በየሃይማኖታቸው ስም በሚያደርጉት የገንዘብ አስተዋጽኦ በተቋቋመው ት/ቤት ውስጥ በሃላፊነት የሚሠሩትና በአስተማሪነት የሚቀጠሩት በጠባያቸው ሆነ በትምህርት ችሎታቸው ብቁ ናቸው ተብለው የተመረጡ ሣይሆን ከፈተና የወደቁና በልዩ ልዩ የጠባይ ጉድለት ከትምህርት ቤት የተባረሩ የሀገር ተወላጆች በመሆናቸው ገና ትምህርት ጀማሪ የሆኑትን ሕፃናት የአካባቢ ነዋሪዎችን በተንኮል መርዝ የተሸፈነ ትምህርት እየሰጡ የእነርሱን አርአያ ወርሰው ሰላማዊውን ሕዝብና የመንግሥትን አስተዳደር ሥነ ሥርዓትን ደምብ ለማቃወስ የሚጥሩት የኦርቶዶክስ ሃይማኖትንም ለማጥፋት የሚጥሩ ለመሆናቸው በቀረበው ሪፖርትና በተሰጠው የሕዝብ ድምጽ ምስክርነት ለማመን ተችሏል ።"

"ስለዚህ ትምህርት ቤት ይዞታ ቢባል ሕዝቡ በቂ ት/ቤት ያላገኘና ወደፊትም ለትምህርት ያለውን ዕድል የሚያደናቅፍ ስለሚሆን በየቀበሌው በግል ፈቃዳቸው የተከፈቱት የሚሽን ት/ቤቶች ሁሉ በየክፍላቸው የትምህርት ቤት ድሬክተሮች በወረዳው ግዛት አማካይነት እየቀረቡ ፥

ሀ/ በተማሪዎችና በአስተማሪዎች ለሚደረገው ሕገወጥ ሥራ ፥

ለ/ ስለመምህራኖቹ የትምህርት ደረጃ ፥

ሐ/ ስለታማኝነታቸው ያላቸውን ዋስትና እየቀረቡ በመመዝገብ ፈቃድ እንዲያገኙና የሥራቸውን ውጤት ሪፖርት በየወሩ ለወረዳው ግዛት እንዲያቀርቡ ፥

መ/ የአውራጃው ት/ቤቶች ሥራ አስኪያጅ በመንግሥትም ሆነ በግል ት/ቤቶች ውስጥ በሚገኙ መምህራንና ተማሪዎች ላይ በየጊዜው ጥብቅ ቁጥጥር እያደረጉ ባላቸው መምሪያ መሠረት ተገቢውን እርምጃ እየወሰዱ በጠቅላላውም ስለዚህ ጉዳይ ያለውን ስሜትና አስተያየት በየጊዜው በሪፖርት መልክ እያዘጋጀ ለአውራጃው ግዛት እንዲያቀርብ ፥

"ከዚህ ጋር አብሮ ሊወሰድ የሚገባው እርምጃ በግል ት/ቤት መምህራንን እያሉ የሚያስተምሩት ሰዎች የትምህርት ደረጃቸው ለሚያስተምሩበት ክፍል በቂ መሆኑንም አጥንቶ ተገቢውን ትእዛዝ እንዲሰጥ ። ይህንንም ያልንበት ምክንያት የትምህርት ደረጃቸው ሣይፈቅድላቸው ከአ



ምስተኛና ከስድስተኛ ክፍል እየወጡ እለችሎታቸው አራተኛና ምስተኛ ክፍል እየገቡ ያስተምራሉ ስለተባለ ነው ። እንዲሁም በመጥፎ ጠባይ ጉድለት ከሥራም ሆነ ከት/ቤት የሚባረሩትን ተማሪዎች ዝርዝርና አድራሻቸውን እየለየ በጽሑፍ ለአውራጃው ግዛት እንዲገልጽ ።

"20ኛ/ በአንጋጫ ወረዳ ግዛት የማጀት ክፍል ሰንጋቆር አቶ አቢሶ ሌጋሞና አንዳንድም ጭቃሹሞች ለወንጀል ሠሪዎች ደጋፊና አስተባባሪዎች ለመሆናቸው በስብሰባ ላይ የተመሰከረባቸው ከመሆኑም በላይ የአንጋጫን ከተማ በወረሩበት ቀን አብረው በመሰለፍ ወንጀል የፈጸሙ ስለሆነ የተጀረው ምርመራ በክፍሉ ፖሊስ አዛዥ አማካይነት ተጣርቶ ለፍርድ ቤት እንዲቀርቡና በተለይም ሠንጋቆርው የተሰጠው አደራ በመዘንጋት የወንጀለኞች ግብረአበር በመሆኑ ለፈጸመው ወንጀል ምርመራው እስኪጠናቀቅ ድረስ በቆርነቱ መብቱ ገብቶ ይሥራ ቢባል በራሱም በሌሎቹም ላይ ለቀረበው ክስ የሚፈልጉትን ማስረጃዎች የሚበትንና እንዲሰወሩ ከማድረጋቸውም በላይ በማስረጃቹም ላይ የሹመት መብቱን ሥልጣን ተገን አድርጉ በደል የሚያደርስባቸው መስሎ ለጉባኤው ስለታየ ከሰንጋቆርነቱ መብት ታግዷል ። በምትኩም የወረዳው ግዛት ለሥራ ይጠቅማል የሚለውን ሰው መርጦ አስቀምጦ በጽሑፍ እንዲያቀርብ ታዟል ።

"21ኛ/ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 20 ተራ አንድ በአንድ ተዘርዝር በተነገረው ቃል መነሻነት ፥

ሀ/ ለመንግሥት ግብርና እሥራት አሰባሰብ ፥

ለ/ በአስተዳደርና የፀጥታ ሥራ ፥

ሐ/ ለዓለምገና ወላሞ የመንገድ ሥራ ድርጅት የእርዳታ ገንዘብ አሰባሰብ ፥

መ/ በጠቅላላው ይህን በመሳሰለው ጉዳይ ብዙ ወደፊት ከባድ ችግር ማስከተሉን ከየክፍሉ የቀረቡት ባላባቶችና መልከኞች ሰንጋቆርዎች ፥ ጭቃሹሞች ፥ ታላላቅ የሀገር ሽማግሌዎች በሰፊው ዘርዝረው በጉባኤው ላይ የማጠቃለያ የምስክርነት ቃላቸውን ከመስጠታቸውም በላይ በጉዳዩ አስቸኳይ እርምጃ ካልተወሰደና በቂ የፖሊስ ኃይል ከነሙሉድርጅቱ በየወረዳው ግዛት ቋሚ ሆኖ እንዲመደብ ካልተደረገ በስተቀር ለንብረታቸውና ሕይወታቸው ጭምር አስጊ መሆኑን በሰፊው አብራርተው ቃል ሰጥተዋል ።"

"ነገር ግን ይህን እያወቁ በፈጸሙት ጥፋት እያንዳንዱ በማስረጃ እየተጣራ ለሕግ በማቅረብና ተገቢ ቅጣት ማስወሰን ሲቻል በየወረዳው ግዛት የሚገኘው የፖሊስ ኃይል ከአራት የማይበልጥ በመሆኑ ወንጀለኞቹንም ሆነ ማስረጃዎቹን ለመሰብሰብ ከአቅማቸው ባላይ ሆኖ በመገኘቱ ወንጀሉ እየተስፋፋ ሊሄድ የቻለው አብይ ጉዳይ ሆኖ ተገኝተዋል ።

"ከባላባቶችም ሆነ ከሐገር ሽማግሌዎች የተነገረው የፖሊስ ኃይል ተጨምሮ በአስቸኳይ ከፍተኛ እርምጃ ካልተወሰደ አሁን በማስፋፋት ላይ የሚገኘውን የወንጀል ድርጊት በአጭሩ ካልተቀጨ ወደ ፊት ኃይሉ እየጠነከረ ከአንዱ ክፍል ወደ ሌላው ክፍል እየተዛመተ ባለው ሕይወትና ንብረት ሆነ በመንግሥት

የውስጥ አሠራር ሥራ ላይ ጉዳትና በደል ከማድረሱም በላይ ለመሬት ግብር
ታክስ አሰባሰብ እስጊ ሆኖ ተገኝቷል ።

"ከዚህም በቀር ስሙን በየቀበሌው ባሉት ተማሪዎች በማድረግ ወንጀሉን
የሚፈጽሙትና የአድማው መሪ የሆኑት በዚህ አውራጃ ግዛት ያሉት ብቻ ሳይ
ሆኑ ከሌላም ጠቅላይ ግዛት በሥራ ላይ የሚገኙ በእረፍት ጊዜአቸው አሳበው
የሚዘዋወሩ የሀገሩ ተወላጆች ነን የሚሉ መምህራንና ተማሪዎች እንዳንድም
ከት/ቤት በፈተና የወደቁ ተማሪዎችና አልፎ አልፎም ብዙ ሥራ ፈቶችና ወረ
በሎች ተማሪ ነን እያሉ ፀጉራቸውን በማሳደግ ጢማቸውን በማጉፈር በወላጆ
ቻቸውና በቤተሰቦቻቸው የተደገፈ ኃይል ይዘው የሰው ንብረት የሚያጠፋ ለመ
ሆኑ ተረጋግጧል ።

"እንዲሁም የሚያደርጉትን ጥፋት ለመሸፈንና ሕጋዊ ለመምሰል እርስ በራ
ሳቸውን የአስር አለቃ ፣ የሃምሳ አለቃ ፣ የመቶ አለቃ ፣ ሻምበል ፣ ሻለቃ ፣ ኰሎ
ኔል እያሉ በመሻሻም ባንዲራ በመያዝ ምስጢሩ ባልታወቀ ሁኔታ ሰላማዊውን
ሰው አታለውታል ።

"ይህም ራሱ ወንጀል በመሆኑ ምርመራውን በየደረጃው ለማጠራት የሚቻ
ለው ሙሉ የፖሊስ ኃይል ሲኖር ነው ። በጠቅላላው ለተነገረው የፀጥታ ጉድ
ለት በየቀበሌው ተዘዋውሮ የተበላሸውን ፀጥታ ጉድለት ለማቃናት በቂ በራሪ
ጓድ ከሙሉ ድርጅት ጋር አስፈላጊ በመሆኑ ተቀማጭነቱ በአውራጃው ግዛት
ሆማዕና ከተማ ሆኖ በስድስቱ ወረዳ ግዛት በአስፈላጊው ቦታ እየተዘዋወረ እር
ምጃ ለመውሰድ የሚችል ኃይል ከሙሉ ድርጅት ጋር በአስቸኳይ ተልኮ ወንጀ
ለኞችን ለመቋቋም የሚችል ኃይል እንዲኖር ያስፈልጋል ።

"በክረምት ወራት በውኃ ሙላትና በበጋም ለመኪና ሆነ ለሕዝቡ መመላ
ለሻ ያስቸግራሉ የሚባሉ መንገድና ድልድዮች ካሉ በወረዳ ገዥዎች እየተጠኑ
በአገሪው ነዋሪ ሕዝብ እርዳታና ትብብር በማያስጋና የሰው ንብረት በማይጉዳ
መልክ እንዲሠሩ ። ይህ ታይቶ በሰው ንብረትና ሀብት ላይ ጉዳት የሚያደርስ
ሥራ ተማሪዎች ነን ባዮች ኃላፊነት ሲሠሩ ቢገኙ የየአንዳንዱ ክፍል ሹም
በኃላፊነት ተጠያቂ መሆኑ በጉባኤው ላይ ተነግሮአቸዋል ።

"ማናቸውም የወንጀል ክስ ወንጀሉ በተፈጸመበት ክፍል አቅራቢያ
ባለው ፖሊስ ጣቢያ መመስከርና በግዛቱም ትብብር በጊዜው ማለት በእለቱ
ምርመራው ተጣርቶ መቅረብ ሲገባ አንዳንድ ባለጉዳዮች ከበላይ መሥሪያ ቤት
ትዕዛዝ አምጥተናል ለማለት ያህል አልፈው በማመልከቻቸው በትክክሉ ሊያዝ
የሚገባው ወንጀለኛ ከማምለጡም በላይ ማስረጃውን ለመሰብሰብ ጊዜ ስለሚ
ፈጅ ይኸው ታውቆ ወደፊት በደል የደረሰበት ሰው ሁሉ እዚያው በክፍሉ ባለው
ወረዳ ፖሊስ ጣቢያ ክሱን እየመሠረተ ማስረጃውን ከሚአሰማ በስተቀር
አልፎ ለአውራጃው ሆነ ለጠቅላይ ግዛት እንዳያመለክት ። ምናልባት የምርመራ
ክፍል አዛዥ ይበድለኛል ወይንም ከወንጀለኞች ጋር የተለየ ዝምድና አለው ፣
ማስረጃም ይበላሽብኛል ቢል በቂ ምክንያት ካለው ለአውራጃው ግዛት ወይም
ለአውራጃው ፖሊስ አዛዥ አመልክቶ ሌላ መርማሪ ሊወስድ የሚችል መሆኑን
ይህ ውሳኔ ለሕዝቡ በስብሰባ ላይ ተገልጾለታል ።

"በዛሬው ዕለት በተደረገው ከፍተኛ የፀጥታ ስብሰባ እንዲቀርቡ ታዘው
እንቢ በማለት የቀሩት የክፍሉ ሹማምንቶች ለወንጀለኞቹ ግብረአበር መስለው
ስለተገመቱ አቅርቦ ለመጠየቅና ሁኔታቸውን ተረድቶ አስፈላጊውን መመሪያና



የማስጠንቀቂያ ትእዛዝ በመስጠት በሚያስቸኩል በዘበኛ ታጅበው በሸኚ ደብ
ዳቤ ወደ አውራጃው ግዛት በአስቸኳይ እንዲላኩ አዘናል ።

እስካሁን በተደረገው ስብሰባ ሕዝቡ ያቀረበው የምስክርነት ቃል የብዙ
ሰዎች ስምና አድራሻ ሥራቸው እየተገለፀ ልዩ ልዩ ወንጀል ለመፈጸማቸውና
የአድማው መሪ ሆነው ለማሠራታቸው የተመሰከረባቸው ስለሆነ በግዛት ፖሊስ
አዛገኞች አማካይነት ጥብቅ ምርመራና ክትትል እየተደረገ አስፈላጊ ምርመራ
እየተጣራ ማስረጃቸው የተሟላና ምርመራ ያለቀለት ፍርድ ቤት እንዲቀርቡ ፣
ያልተያዙም እየታደኑ እንዲያዙና ለባለመብቱ ፍርድ ቤት እንዲያቀርቡ ስንል
ልዩነት በሌለው በአንድ ድምጽ ወስነናል ።

" <u>የጉባኤው ትእዛዝ</u>

ይህ ቃለ ጉባኤ ተገልብጦ ፣

1ኛ/ ለሸዋ ጠቅላይ ግዛት ጽ/ቤት
2ኛ/ ለሸዋ ጠቅላይ ግዛት ፖሊስ ዋና መምሪያ
3ኛ/ ለኢት.ን.ነ. መንግሥት ያገር ግዛት ሚኒስቴር
4ኛ/ ለኢት.ን.ነ. መንግሥት የሕዝብ ፀጥታ ጥበቃ ሚኒስቴር
5ኛ/ ለፖሊስ ሠራዊት ጠቅላይ ዋና መምሪያ
6ኛ/ ለከምባታ አውራጃ ፖሊስ መምሪያ
7ኛ/ ለስድስቱ ወረዳ ገዥዎች
8ኛ/ ለሸዋ ጠቅላይ ግዛት ጽ/ቤቶች ጽ/ቤት
9ኛ/ ለኢት.ን.ነ. መንግሥት የትምህርትና ሥነ ጥበብ ሚኒስትር
10ኛ/ ለከምባታ አውራጃ ግዛት ት/ቤቶች ጽ/ቤት ከሸኚ ደብዳቤ ጋር እንዲ
ተላለፍ አዘናል ።

ማህተም ፣ በሸዋ የከምባታ አውራጃ ግዛት መዝገብ ቤት
ቀን ፣ 1/3/1965 ዓ. ም.
የደብዳቤው ቁጥር ፣ 1012/11"

## ያገሬ ገዥው ደብዳቤ ለጠቅላይ ግዛት እንደራሴ

ቁጥር 1012/11
ቀን 1/3/65
ከምባታ አውራጃ ግ/ጽ/ቤት
ሆሳዕና

"ለክቡር ራስ.................................
የሸዋ ጠቅላይ ግዛት እንደራሴ
አዲስ አበባ

ክቡር ሆይ ፣

"በዚህ አውራጃ ግዛት በየክፍሉ ወረዳ ግዛቶች ስለአለው ፀጥታ ሁኔታ ተወያይቶ አንድ ዓይነት እርምጃ ለመውሰድ የአምስቱን ወረዳ ገዥዎችና የፖሊስ አዛዦችን እንዲሁም ምክትል ገዥዎችንና ባላባቶችን ፣ አፈር መልከኞችን ፣ ሡንጋቆሮዎችን ፣ ጭቃሹሞችንና ታላላቅ የሃገር ነዋሪ ሽማግሌዎችን እንዲሰበሰቡ አድርጌ በጉዳዩ ከጥቅምት 15/65 ዓ. ም. እስከ ጥቅምት 19/65 ዓ. ም ድረስ በአውራጃው ግዛት መሥሪያ ቤት በተደረገው ጉባኤ በየክፍሉ ተማሪዎችና ግብረ አበሮቻቸው ለፈጸሙት ድርጊት ተማሪዎች መንገድ እንሠራለን ብለው በተነሣሱት ዓላማ ገንዘብ ያልሰጣቸውን ሰው የጥንቱን መንገድ በመተው በቤትና በአትክልቱ ላይ በመቀየስ አትክልቱን ለማበላሸታቸውና ቤቱንና አጥሩንም ለማፍረሣቸው እንዲሁም የአቶ....አጥር በእሳት ለማቃጠላቸው ፣ ለግል ጉዳይ በየመንገዱ የሚተላለፈውን ሰላማዊ ሰው በነፍስ ወከፍ 0.20 ሣንቲም ገንዘብ እያስገደዱ ለመውሰዳቸው ፣ አልሰጥም ያላቸውን በመንገዱ እንዳይሄድ አግደው በማቆየት ከበቅሎ በማስወረድ የለበሰውን ልብስና ያደረገውን ባርኔጣ በመንጠቅ ለርስትም ሆነ ለወንጀል ክርክር ጉዳይ ወደ ወረዳው ግዛት የሚሄደውን ሰው እንዳይሄድ በመንገድ ጠብቀው በመከልከል ባላጋራውን አስጠርተው ዳኝነት እያዩ ለመወሰናቸው ፣ ቅጣትም ከ50 እስከ 70 ብር እየወሰኑ ለማስከፈላቸው በስብሰባው የቀረቡት ታላላቅ ሽማግሌዎችና ባላባቶች በሰጡት ቃል ተረጋግጧል ።

"እንዲሁም አቶ.... የተባለውን የክፍል ጭቃሹም ቤት ከ150 በላይ ሆነው ማታ በ12 ሰዓት ገብተው እርሱን አስረው በሬውን አርደው ለመስቀል በዓል ያዘጋጀውን አንድ እንስራ ቅቤ በመውሰድ ሴሊቱን ሠንጋውን ሲበሉ አድረውና አምስት የቀንድ ከብቶችም ሴሊቱን ዘርፈው የወሰዱበት ካለመታወቁም በላይ በያንዳንዱ ቀበሌ የተፈጸመውን ወንጀል አንድ በአንድ አድራጊዎቹ በየወረዳው ግዛት ፖሊስ ጣቢያ በምስክር ለመረጋገጡ እስብሰባው ላይ ተገልጾአል ።

"የክፍሉ ወረዳ ግዛት ቲሰብሰቦና ተዘርዝሮ ለተገለጸው ፀጥታ በትኩስ ደርሶ ለመያዝ እንዳይቻል የወንጀል ግብረአበሮቹ ከ200 እና ከ300 በላይ ከመሆናቸው ይልቅ ያገሬው ሕዝብ አጋልጦ ሊሰጣቸው ካለመቻሉም በላይ በአንድ ወረዳ ግዛት ውስጥ የተመደቡት ፖሊሶች ከሦስትና ከአራት የማይበልጡ በመሆናቸው ወንጀለኞቹን ሊቋቋማቸው እንዳልቻሉ ታውቋል ።

"በስብሰባው የምስክር ቃላቸውን የሰጡት ባላባቶች ፣ አፈርመልከኞች እንዲሁም ሡንጋቆሮዎችና ጭቃሹሞች ፣ የሀገር ሽማግሌዎች ባጠቃላይ ሁኔታ የሰጡት አስተያየት በአስቸኳይ የፖሊስ ኃይል ተጨምሮ በየወረዳው ግዛት በመዘ



ዋወር የተበላሸው ፀጥታ በቶሎ ካልተቀጨ ለወደፊቱ የመንግሥቱን ግብርና የርሻ ታክስ እንዲሁም ማንኛቸውም የመንግሥት ትዕዛዞች የዓለምገና ወላሞ መንገድ የእርዳታ ገንዘብ ያለበትን ሰው በየቀበሌው ተዘዋውሮ ለማዘዝና ለማስገባት አለመቻሉን በሰጡት ቃል ላይ አረጋግጧል ።"

"ስለዚህ በጉባኤ ስብሰባ ውሳኔ የተሰጡትን ቃለ ጉባኤ ትክክል ግልባጭ 89 ገጽ የሆነ ከዚህ ጋር እያቀርብኩ በክቡርነትዎ በኩል በጉዳዩ በብርቱ ታስቦበት ተቀማጭነቱ ሆሳዕና ከተማ ሆኖ በየወረዳውና በየቀበሌው ተዘዋውሮ ፀጥታውን የሚያስከብር በራሪ ጓድ ከሙሉ ድርጅቱ ጋር በአስቸኳይ እንዲመደብልን አስፈላጊው መሆኑን በአክብሮት እያሳሰብኩ ፣

"የተጠየቀው ኃይል እስኪመጣ ድረስ ያውራጃው ፖሊስ አዛዥ ያለውን ኃይል በማብቃቃት በየክፍሉ ያለውን ፀጥታ ከወረዳ ገዥዎች ጋር በመተባበር በአጥፊዎቹ ላይ የሕግ እርምጃ እንዲወስዱ በዚህ ደብዳቤ ኮፒ ትዕዛዝ ሰጥቻለሁ ።

ከማክበር ሰላምታ ጋር
ማህተም በሸዋ የከምባታ አውራጃ ግዛት ፣
ፊርማ ፣ ፊታውራሪ........ የከምባታ አውራጃ ገዥ

"ግልባጭ ፣

ለሸዋ ጠ/ግዛት ፖሊስ ዋና መምሪያ
ለኢት.ን.ነ. መንግሥት ያገር ግዛት ሚኒስቴር
ለኢት.ን.ነ. መንግሥት የሕዝብ ፀጥታ ጥበቃ ሚኒስቴር
ለፖሊስ ሠራዊት ጠቅላይ ዋና መምሪያ
ለኢት.ን.ነ. መንግሥት የትምህርትና ሥነ ጥበብ ሚኒስቴር
ለሸዋ ጠ/ግዛት ት/ቤቶች ጽ/ቤት
አዲስ አበባ

ለከምባታ አውራጃ ፖሊስ መምሪያ
ለከምባታ አውራጃ ት/ቤቶች ጽ/ቤት
ለስድስቱ ወረዳ ገዥዎች
ከ89 ገጽ አባሪ ጋር
ሆሳዕና
ባያሉበት"

ከዚህ በላይ የተጻፈው ታሪካዊ ዶኩሜንት በአብዮቱ ዋዜማና መባቻ በከምባታና ሀዲያ አውራጃ የነበረውን መደባዊ የኃይል አሰላለፍ የትግል ስልትና ታክቲክ በግልጽ ያሳያል ። በዚህ አኳያ አንደኛ ፣ በአውራጃው የጉልተኛው መደብ አባሎችና ደጋፊዎች ማለትም ታላላቅ የሀገር ሽማግሌዎች የተባሉ የጉማሪዎች ፣ ሡንጋቆሮዎች ፣ አፈርመልከኞችና ጭቃሹሞች የተባሉ ዝቅተኛ የመንግሥት ባለሥልጣኖችና የመሬት ከበርቴዎች ፣ ባላባቶች ፣ የሕግ ጠበቆች ፣ የሃይማኖት መሪዎች የምክትል ወረዳ ፣ የወረዳና የአውራጃ ገዥዎችና የፖሊስ አዛዦች በአውራጃው ገዥ ሰብሳቢነትና መሪነት በሆሳዕና ከተማ ከጥቅምት 15 እስከ 19 ቀን 1965 ለአምስት ቀናት በልዩ ፀጥታ ጉባኤ ተሰብስበው ተማሪዎችና ወላጆቻቸው ተባብረው የመንግሥት ግብር እንዳይሰበሰብ ፣ ጪሰኞች በጉልተኞችና በመንግሥት ባለሥልጣኖች ላይ ጥቃት አድርሰዋል ፣ በመንደርና

በገበያ በግልጽና በገሃድ ፀረ መንግሥትና ፀረ ሥርዓት የሆነ ቅስቀሳና አዋጅ አካሄደዋል በማለት በፖሊስ ኃይል እንዲደበደቡ ውሳኔ አሳለፉ ።

ሁለተኛ ፤ በውሳኔ ዶኩሜንት በግልጽና በዝርዝር እንደተገለጸው ፤ ከጭቁን አርሶ አደር መደብ የወጡ ተማሪዎች ከደሀ ገበሬዎችና ጢሰኞች ጋር ግምባር ፈጥረው ከሆማዕና ከተማ ውጭ ይዘው በአውራጃው ወረዳዎች ፤ መንደሮች ፤ መንገደችና ገበያዎች ጉልተኞችንና የመንግሥቱን የበታች ባለሥልጣናትን ማለ ትም ባላባቶች ፤ ጭቃሹሞችን ፤ ጸሐፊዎች ፤ ፖሊሶችን ፤ የእህል ወፍጮ ባለቤ ቶች በመግሪያ ማጥቃትና መጥለፍ ጀመሩ ። የሀብታሞች ሀብትና ንብረት መዝ ረፍና ማቃጠል ጀመሩ ። የጉልተኞችን መሬት እየወሰዱ ለጢሰኞች መስጠት ጀመሩ ። በመንገድና በየአካባቢው በሚገኙ በአውራጃው ገበያዎች በድንኳን ተሰብስበው ደበሎ እየሰቀሉ በገሃድ ፀረ መንግሥት ቅስቀሳ ሲያካሄዱ የሚያቆ ማቸው መንግሥታዊ ድርጅትና ኃይል አልነበረም ። የአውራጃው ሰፊ ሕዝብ ከተማሪዎችና ገበሬዎች ጐን በመሰለፍ የመንግሥቱን ወገን በመርዳት ፈንታ ማጥቃት ጀመረ ።

በአጭርና በአጠቃላይ በከምባታና ሀዲያ አውራጃ በጉልተኞችና በጭቁኑ ሕዝብ መካከል የመደብ ትግል እንደዚህ በከፍተኛ ደረጃ ሲካሄድ ታላቁ የኢት ዮጵያ ሕዝባዊ አብዮት በየካቲት 1966 እንደ እሳተ ጐሞራ ፈነዳ ።



ክ ፍ ል   አ ራ ት

# አብዮቱና የኢኮኖሚው ዘመቻ በከምባታና ሀዲያ አውራጃ 1966-1975

## 1. የአብዮቱ ፍንዳታና የመደብ ትግል ከ1966 እስከ 1971

ከዚህ በላይ እንደተገለጸው ፤ በአብዮቱ ዋዜማና መባቻ የከምባታና ሀዲያ አውራጃ ገበሬዎችና ተማሪዎች ከአውራጃው ጉልተኞችና ባለሥልጣናት ጋር በከ ፍተኛ ደረጃ እየታገሉ የአውራጃውን ወረዳዎች በቁጥጥራቸው ሥር አድርገው ስለነበር ፤ በየካቲት 1966 የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮት እንደ እሳተ ጐሞራ ከፈ ነዳ በኋላ በአጭር ጊዜ ውስጥ ከአውራጃው ገጠር ባላባቶችንና ጉልተኞችን ሙሉ በሙሉ በማባረር መሬቱን ለአንዴና ለመጨረሻ ወሰዱ ። በ1967 በአብ ዮታዊ መንግሥት የተላኩ የዕድገት በሕብረት ዘማቾችና ታላቁ የየካቲት 25 ቀን 1967 የገጠር መሬት አዋጅ የገበሬዎችን ድርጅት በጉልተኞችና በአድሃ ሪያን ላይ በኃይል አጠናከሩ ። ከዚያ በኋላ የአውራጃው ገበሬዎች ከቀድሞ ጉል ተኞችና አድሃሪያን ያስፈቱትን መግሪያ ታጥቀው በ1968 በወረዳ በህዳር 1969 ደግሞ በአውራጃ ደረጃ የአብዮት በዓል አከበሩ ።

ነገር ግን የአውራጃው ሕዝብ በ1969 የአብዮቱን በዓል በታላቅ ዝግጅትና ሰልፍ ከአከበረው በኋላ ከመንግሥት ሥልጣንና ከአውራጃው የተባረሩ የቀድሞ ጉልተኞችና ባለሥልጣናት ፤ የኢሕአፓና የኢዲዩ ወኪሎችና በ1969 አገሩ ከም ሥራቅና ከደቡብ ምሥራቅ በሱማሊያ ጦር ከተወረረ በኋላ በአገሩና በአብዮቱ ላይ ሸፍቶ ወደ ጫካ የገባውና ራሱን የመላው ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ (መኢሶን) በማለት የሰየመው ስውር የፖለቲካ ድርጅት በተናጠልና በሕብረት የከምባታና ሀዲያ አውራጃ የፀረ አብዮት ኃይላት ሠፈርና ግምባር ለማድረግ ብዙ የሴራና የአሻጥር እቅዶችንና እርምጃዎችን በአውራጃና በአገር አቀፍ ደረጃ ቀየሱ ።

ነገሩ እንደገና ለማስታወስ ያህል ፤ ከእነዚህ ፀረ አብዮትና ፀረ አንድነት ኃይላትና ድርጅቶች ራሱን ኢሕአፓ ብሎ የሰየመው ሽብር ፈጣሪ ድርጅት ተማሪዎችንና ወጣቶችን በፀረ አብዮት ሠፈር አሰልፎ በግዲያና በሽብር ታክ ቲክ ከደርግ በትረ መንግሥትን ለመያዝ በይፋ በትጥቅ ሲታገል ፤ በአንፃሩ ራሱን መኢሶን በማለት የሰየመው የፖለቲካ ስውር ድርጅት ግን በነሐሴ 1969 እስኪሸፍት ድረስ በልዩ ዘዴ በአብዮቱ ሠፈር ውስጥ በመግባት የአገሩን ገበሬዎችና ወዛደሮች በሥሩ አደራጅቶ የሰፊው ሕዝብ ፓርቲ ነኝ በማለት ከደርግ በትረ መንግሥቱን ለመውሰድ ይፈልግ ነበር ። የዚህ ድርጅት መሪ ዎች በብሔራዊ አደጋ ወቅት በአብዮቱና በአገሩ ላይ ሸፍተው ወደ ጫካ ከገቡ በኋላ የድርጅቱ ሌላ አባሎችና ተከታዮች በአገሩ ገበሬዎችና ወዛደሮች ውስጥ

በመደብ ልዩነትና ትግል ፈንታ የጐጣ ልዩነትና ጦርነት ማስተጣር ጀመሩ ። የዚህ ድርጅት ፀረ አብዮትና ፀረ አንድነት ሴራ በከምባታና ሀዲያ አውራጃ ብቻ ሳይሆን በመላው አገሩ በገበሬዎች በሠራተኞችና በብሔረሰቦች መካከል ልዩነት በመፍጠር የጭቁኖችን መደባዊ አንድነትና ትግል ወደ ጠባብ ጐጣዊና ሃይማኖታዊ ጦርነት ለመለወጥ ቢሞክርም በኋላ ድርጅቱ ራሱ በአብዮታውያን ብርቱ ትግል ተሸነፈ ።

የኢሕአፓና የኢዲዩ ወኪሎችና ተከታዮች ደግሞ ከቀድሞ ጉልተኞችና ባለሥልጣናት ጋር መደባዊ የፀረ አንድነት ሕብረት ፈጥረው በከምታና ሀዲያ አውራጃ በከፍተኛ ደረጃ የተቀነባባረ ስውር የአብዮት ቅልበሳ መዋቅርና መረብ በመዘርጋት ከ1970 እስከ 1971 መጀመሪያ ድረስ ለሁለት ዓመታት በአውራጃው የአብዮቱን ሂደት ለማደናቀፍ ፣ የብሔረሰቦችና የሃይማኖት ጦርነት ለማስነሳት ፣ በአውራጃው ሕዝብና በአብዮታዊ መንግሥት መካከል የፀጥታ ችግር ለመፍጠር ብዙ ያልተሳካ ሙከራ አደረጉ ። የከምባታና ሀዲያ አውራጃ ሕዝብ ጠባብና ጐጣኛ ነው ፣ የከምባታና ሀዲያ ብሔረሰቦች እርስ በርሳቸው ሊዋጉ ነው ፣ የአውራጃው ሕዝብ ከመንግሥት ለሚሾሙ አስተዳዳሪዎች አይታዘዝም ፣ አውራጃው “መጢ ሃይማኖት” የሞላበት የፀረ አብዮተኞችና የጠባቦች አገር ነው ወዘተ... እያሉ የሀሰት ወሬ በመፍጠር የአውራጃውን ጭቁን ሕዝብ በአብዮታዊ መንግሥት በስህተት ሲያስመቱ ብዙ ያልተሳካ ትግል አካሄዱ ። ከአብዮታዊ መንግሥት ተሹመው የሚመጡ አስተዳዳሪዎች ተቀምጠው ሊሠሩ የማይችሉበት ሁኔታ ፈጠሩ ። በዚህ አኳያ ፤ ለምሳሌ ከመስከረም 1 ቀን 1967 እስከ መጋቢት 1 ቀን 1970 ድረስ በሶስት ዓመት ተኩል ውስጥ አብዮታዊ መንግሥት የሾማቸው ስድስት አስተዳዳሪዎች በፀረ አብዮተኞችና በአሻጥረኞች ሁከትና ረብሻ ምክንያት አውራጃውን ማስተዳደር አቃታቸው ።

ይህ ሁሉ ከሆነ በኋላ በመጨረሻ በነሐሴ 1970 አብዮታዊ መንግሥት ጓድ ጴጥሮስ ገብሬን (1940— ) የሲዳሞ ክፍለ ሀገር ቋሚ ደርግ አባልን የከምባታና ሀዲያ አውራጃ አስተዳዳሪ አድርጉአቸው ሾመ ። ከነሐሴ 1970 እስከ ሚያዝያ 1971 ድረስ በዘጠኝ ሽግግራዊ ወራት በአብዮታዊ መንግሥት መመሪያና ብርቱ ትብብር አዲሱ አስተዳዳር ከአውራጃው ታጋይ ሕዝብ ጋር 1/ ብርቱና ጥብቅ ፀረ አብዮት ምንጠራ ዘመቻ 2/ የአውራጃውን አጠቃላይ የፖለቲካ የኢኮኖሚና የማህበራዊ ኑሮ ሁኔታዎች ጥናትና ግምገማ አካሄደ ። በአብዮታዊ መንግሥት ፣ በአዲሱ አውራጃው አስተዳደርና በአውራጃው ታጋይ ሕዝብ ትብብር በተወሰደው ብርቱ የፀረ አብዮት ኃይላት ምንጠራ ዘመቻ በሚያዝያ 1971 በአውራጃው የፀረ አብዮት ኃይላት ሠፈር ፣ ኃይልና መዋቅር ለአንዴና ለመጨረሻው ሲደመሰስ ፣ በምንጠራው ወቅትና ሂደት በአውራጃው ከብዙ ፀረ አብዮት ድርጅቶችና ግለሰቦች የጭቁኑን ሰፊ ሕዝብ ሕይወትና ንብረት ለማጥፋት የተሰበሰቡ 991 ልዩ ልዩ የተኩስ መሣሪያዎች ብዙ ታይፕራይተሮችና ማባዣ ማሽኖች ከጦር ሜዳ መነጽሮች ጋር ተያዙ ።

የፀረ አብዮትና የፀረ አንድነት ድርጅቶችና ኃይላት በአብዮታዊ መንግሥትና በታጋይ ሕዝብ አንድነት ፣ ኃይልና ትብብር እንደዚህ ከተደመሰሱ በኋላ የአውራጃው ሕዝብና አስተዳደር በሕብረት ከላይ አብዮታዊ መንግሥት በጥቅምት 1971 ባወጀው በብሔራዊ ኢኮኖሚና ባህል ዘመቻ መሠረት ፣ መዋቅርና መርሆ የአውራጃውን የኢኮኖሚና የባህል ዕድገት ዘመቻ ጀመረ ። ከዚህ በሚቀጥለው ክፍል የዘመቻውን ይዘት ፣ ደረጃ ፣ ሂደትና ውጤት በዝርዝር እናያለን ።



ሠንጠረዥ 22

የከምባታና ሀዲያ አውራጃ አስገባሪዎች ፤ ገዥዎችና አስተዳዳሪዎች ከ1878 እስከ 1970

| ተራ ቁ. | አስገባሪዎችና ፣ ገዥዎችና አስተዳዳሪዎች | የግዛትና አስተዳደር ዘመን | ተራ ቁ. | አስገባሪዎች ፣ ገዥዎችና አስተዳዳሪዎች | የግዛትና አስተዳደር ዘመን |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ራስ ወልዴ አሻግሬ | 1878—1883 | 18 | ፊታውራሪ ተስፋዬ እንቁሥላሴ | 1941—1947 |
| 2 | ራስ ጉበና ዳጭ | 1878 | 19 | ደጃዝማች ቪፈራው ወንድማገኘሁ | 1947—1948 |
| 3 | ደጃዝማች ወዳጆ ጉበና | 1883—1886 | 20 | ደጃዝማች ዘለቀ ደስታ | 1948—1951 |
| 4 | ደጃዝማች በሻህ አቦዬ | 1886—1888 | 21 | ደጃ/ ቪፈራው ወንማገኘሁ እንደገና | 1951—1952 |
| 5 | ደጃዝማች ተሰማ ዳርጌ | 1887—1888 | 22 | ፊታውራሪ ካሣ ኪዳነ ማርያም | 1952 |
| 6 | ራስ አባተ ቧያለው | 1888—1901 | 23 | በጅሮንድ ዘውዴ ሙላት | 1952—1954 |
| 7 | ደጃዝማች አያሌው ብሩ | 1901—1902 | 24 | ደጃዝማች ዮሐንስ ግርማይ | 1954—1955 |
| 8 | ራስ አባተ ቧያለው እንደገና | 1903—1903 | 25 | ደጃዝማች ዘውዴ ጥላሁን | 1955—1960 |
| 9 | ራስ ልዑል ሰገድ አጥናፍ ሰገድ | 1904—1907 | 26 | ፊታውራሪ ሩጋ አሻሚ | 1960—1965 |
| 10 | ደጃዝማች ወልደገብርኤል በሻህ | 1907—1909 | 27 | ፊታውራሪ ተድላ ታምራት | 1965—1966 |
| 11 | ራስ ጌታቸው አባተ | 1910—1919 | 28 | ኮሎኔል ደመቀ ተሰማ (6 ወር) | 1967 |
| 12 | ደጃዝማች መሸሻ ወልዴ | 1919—1928 | 29 | የመቶ አለቃ ገብረየሱስ በቀለ | 1967—1968 |
| 13 | የጠላት ወረራና የዘመነ ገባር ፍዳሚ | 1928—1933 | 30 | ሻለቃ አሰፋ በርሄ | 1968—1969 |
| 14 | ራስ እደፍርስ ናደው | 1933 | 31 | ሻለቃ ደሳለኝ ሽርካ (6 ወር) | 1969—1970 |
| 15 | ደጃዝማች ዳምጠው መሸሻ | 1934—1938 | 32 | አቶ ዓለማየሁ ታቦር | 1970 |
| 16 | ፊታውራሪ ገብረሕይወት መሸሻ | 1938 | 33 | ሻምበል ሰለሞን ቦጋለ (3 ወር) | 1970 |
| 17 | ፊታውራሪ ክፍሌ ዳዲ | 1938—1940 | 34 | ጓድ ጴጥሮስ ገብሬ | 1970— |

## 2. የኢኮኖሚና የባህል ዘመቻ ዝግጅትና ድርጅት በከምባታና ሀዲያ አውራጃ ከ1971 እስከ 1975

### 2. ሀ. የአውራጃውን የልማት ደረጃ የሚያፈጥኑና የሚወስኑ መሠረታዊ የአካባቢው ሁኔታዎች

ከዘመናዊ እርሻ ንግድና ኢንዱስትሪ አንፃር ፣ የከምባታና ሀዲያ አውራጃ ሕዝብ ካለፈው ጉልተኛ መንግሥትና ዘመን የወረሰው ብሎም ለኢኮኖሚና ለባህል ዕድገት መሠረትና መነሻ የሚሆን ለዓይነት አንድ ድርጅት የለም ። ይልቁንም በዚያን አስጨናቂ ዘመንና ሥርዓት በአውራጃው የተከሰቱ መሠረታዊና መንቲያ ችግሮች የመሬት ጥበትና የሰው ብዛት ሲሆኑ ፣ በቋንቋ ፣ በታሪክና በባህል አንድ የሆነውን የአላባን ሕዝብና ወረዳ በ1952 ከአውራጃው ቆርጦ ወደ ሌላ አካባቢ በመውሰድ የወደቀው መንግሥት ለሁለቱም ችግሮች ሥርዓታዊ ምንጭና መንስኤ ሆኗል ።

መከራ ብልሃት ይፈጥራል እንደሚሉት የከምባታና ሀዲያ ሕዝብ የመሬት እጥረትና የሰው ብዛት ያስከተላቸውን መንቲያ ችግሮች ለማቋቋም የአካባቢውና የጊዜው ተጨባጭ ሁኔታዎች በፈቀዱት መጠን ብዙ ተግባራዊ ጥረቶች አድርገዋል ። አንደኛ ለከምባታና ሀዲያ አውራጃ ሕዝብ በአለፈው መከራ ዘመን ከጠባብ መሬት ለጉልተኛ አገልግሎት ፣ ለመንግሥት ግብርና ለራሱ ህልውና የሚያስፈልገውን ሠርቶ ለማግኘት ጠንካራና የማይታክት ሠራተኛ መሆን የመኖርና የመሆን ግዴታ ሆነበት ። ከዚህም የተነሳ የከምባታና ሀዲያ አውራጃ ሕዝብ ጠንካራ የሆነ የሥራ ፍቅር ፣ ልምድና ባህል ያለው አምራች ሕዝብ ነው ። ሁለተኛ ፣ የከምባታና ሀዲያ አውራጃ ሰዎች ለመሬት ጥበት መፍትሔ ይሆናሉ በማለት ለልጆቻቸው ንግድና ትምህርት በትጋት ያስተምራሉ ።

ሦስተኛ ፣ ያለው መሬት ዓመቱን በሙሉ ስለማያሠራቸው ብዙ የከምባታና ሀዲያ ሰዎች በዓመት ውስጥ ለተወሰኑ ወራት ከአውራጃው ወደ ውጭ እየሄዱ የቅጥርና የዶሞዝ ሥራዎችን እየሠሩ ለመንግሥታዊ ግብርና ለራሳቸው ሕይወት የሚያስፈልጋቸውን ገንዘብና ዕቃ ያገኛሉ ። በአጭርና በአጠቃላይ የከምባታና ሀዲያ አውራጃ ሕዝብ በመሬት ችግር ምክንያት በልዩ ልዩ መንገድና ሥፍራ ያገኘው የጠንካራ ሥራ ፣ የትምህርትና የንግድ ልምድና ባህል ፣ ከዚህ በታች በተጨባጭ እንደሚታየው ፣ አሁን በአውራጃው በመካሄድ ላይ ለአለው ለኢኮኖሚና ለባህል ዘመቻ መሳካት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያደረገለት ነው ።

በዚህ አንፃርና ተግባር ፣ ዛሬ በከምባታና ሀዲያ አውራጃ ለልማት ፣ ለግል ለመንግሥታዊና ለሕዝባዊ ድርጅቶች ለሚያስፈልግ ለማንኛውም የእንጨት ፣ የድንጋይና የሕንፃ ሥራ በጣም ልዩ ሥራ ካልሆነ በስተቀር ባለሙያዎች ከአውራጃው ውጭ አይመጡም ። እንደዚህ ያሉ ለኢኮኖሚና ለባህል ዕድገት አስፈላጊና መሠረታዊ የሆኑ ተግባራዊ ሥራዎችን በአጭር ጊዜ ውስጥ በመጠነኛ ዋጋ የሚሠሩ ባለሙያዎች በከምባታና ሀዲያ አውራጃ ሞልተዋል ። ለዚህ አባባል የኢትዮጵያ የኢኮኖሚና የባህል ዘመቻ በ1971 ከታወጀ ወዲህ በከምባታና ሀዲያ አውራጃ ከተሞችና ወረዳዎች ከእንጨትና ከድንጋይ የተሠሩ ብዙ የግል ፣ የከተማ ፣ የመንግሥትና የሕዝብ ቤቶችና ሕንፃዎች እንዲሁም መንገዶች ድልድዮች ጥሩ ማስረጃዎችና ምሳሌዎች ይሆናሉ ።



ሠንጠረዥ 23

የመሬት ፣ የሰውና የእንስሳት ሚዛን በከምባታና ሀዲያ አውራጃ በ1975

| | ያውራጃው ወረዳዎች | የወረዳ ስፋት በጋሻና በሄክታር | | የወረዳ ሕዝብ ብዛት | ያውራጃው እንስሳት ብዛት በአጠቃላይ | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በጋሻ | በሄክታር | | የቀንድ ከብት | የጋማ ከብት | ፍየል | በግ |
| 1 | የኮንተብ ወረዳ | 2131 | 85249 | 452690 | 1691187 | 151917 | 267719 | 258906 |
| 2 | የሊሙ ወረዳ | 1528 | 61120 | 382150 | | | | |
| 3 | የጥምባሮ ወረዳ | 1326 | 53040 | 469300 | | | | |
| 4 | የእሞሸለቆ ወረዳ | 1157 | 46280 | 157150 | | | | |
| 5 | የሲቄ ወረዳ | 893 | 35720 | 278810 | | | | |
| 6 | የአንጋጫ ወረዳ | 760 | 30400 | 367780 | | | | |
| 7 | የቀዲዳ ጋሜላ ወረዳ | 740 | 29640 | 214900 | | | | |
| 8 | የቃጫ ቢራ ወረዳ | 555 | 22200 | 217500 | | | | |
| 9 | የሆሳዕና ከተማ | 80 | 3200 | (ከሊሙ ሕዝብ ጋር) | | | | |
| | ድምር ፣ 9 ወረዳዎች | 9117 | 36684 | 2540280 | 2369809 የቤት እንስሳት በድምር | | | |

የተገኘበት ፣ የከምባታና ሀዲያ ኢክስፖ 1972 (ሆሳዕና የካቲት 1972) ፣ የከምባታና ሀዲያ አውራጃ የኢሠፓአኮ ጽ/ቤት (ሆሳዕና መጋቢት 1975) ፣ የከምባታና ሀዲያ የግብርና ሚኒስቴር ተጠሪ ጽ/ቤት (ሆሳዕና 1972 ፣ 1975) ።

ሠንጠረዥ 24

የዓለምገና — ወላይታና የወልቅጤ — ሆሣዕና የመኪና መንገዶች ሥራና አገልግሎት

| ተራ ቁ. | የመንገድ ስም | የተሠራበት ዘመን | የመንገድ ርቀት በኪሎ ሜትር | የተሠራበት ዋጋ በብር | የሠራው ሕዝብ |
| --- | --- | --- | --- | --- | --- |
| | ዓለምገና—ወላሞ መንገድ<br>ሀ. ከአዲስ አበባ ሆሣዕና<br>ለ. ከሆሣዕና እስከ ሶዶ ጭምር | 1954—1964 | 250 ኪሎሜትር<br>50 ኪሎሜትር | 3730000 ብር | የመናገሻ ፣ የጨቦና የጉራጌ የሐ ይቆችና ቡታጅራ ፣ የከምባታና ሀዲያ አውራጃዎች |
| | የጉራጌ መንገዶች<br>ሀ. ከወልቅጤ እስከ ሆሣዕና<br>ለ. የሰባት ቤት ጉራጌ የወረዳ መጋቢ መንገዶች | 1954—1973 | 300 ኪሎሜትር<br>126 ኪሎሜትር<br>181 ኪሎሜትር | 7630000 ብር | የሰባት ቤት ጉራጌና የከምባታና ሀዲያ ሕዝብ<br>የጉራጌ መንገዶች ድርጅት |
| | ጠቅላላ ድምር | 1954—1973 | 607 ኪሎሜትር | 11360000 ብር | የአራት ሸዋ አውራጃዎች ሕዝቦች |

የተገኘበት ፤ የዓለምገና—ወላሞ መንገድ ድርጅት) ያልታተመ ዶክሜንት ፤ አዲስ አበባ ፤ 1973) ፤ የጉራጌ መንገዶች ሥራ ድርጅት (የድርጅቱ የገንዘብ ገቢና ወጭ ዘገባ ብቻርት ፤ አዲስ አበባ ፤ 1973) ።



ሌላ በከምባታና ሀዲያ አውራጃ በመካሄድ ላይ ያለውን የኢኮኖሚና የባህል ዕድገት ዘመቻ ያፋጠኑ መሠረታዊ ነገሮች ፣ የአውራጃው ሕዝብ በአብዮቱ ዋዜማ ከጉረቤት አውራጃዎች ጋር ተባብሮ በጉልበቱና ገንዘብ የሠራቸው ሁለት ክፍለ ሀገር ፣ አውራጃና ወረዳ አቋራጭ ማለትም የዓለምገና — ወላይታና የወልቅጤ — ሆሣዕና የመኪና መንገዶች ናቸው ። ዛሬ በእነዚህ መንገዶች በምንት ከፍተኛ የክፍለ ሀገር አውቶቡሶች ጭምር አንድ መቶ የሚሆኑ የግል ፣ የድርጅት ፣ የሕዝብና የመንግሥት መኪናዎች የሆሣዕና ከተማን ከአዲስ አበባ፣ ከሸዋ ፣ ከሲዳሞና ከጋሞጐፋ ከተሞችና ከከምባታና ሀዲያ አውራጃ ወረዳ ከተ ሞች ጋር በሥራና በንግድ በየቀኑ ያገናኛሉ ።

ከዚህ በላይ ታሪካቸው በአጭርና በአጠቃላይ የተገለፀና በሆሣዕና ከተማ የሚገናኙ የዓለምገና—ወላይታና የወልቅጤ ሆሣዕና የመኪና መንገዶች በደቡብ ሸዋ አውራጃዎችና ሰዎች ብሔራዊ ሕብረትና ትብብር በጊዜው ባይሠሩ ኖር ዛሬ በከምባታና ሀዲያ አውራጃ በከፍተኛ ደረጃ የሚታየው የኢኮኖሚና የባህል ዘመቻ ሥምሪትና ውጤት ምናልባትም በዚህ ዕድገት ሁኔታና ሂደት አይታይም ነበር ።

## 2. ለ. የድርጅት ፣ የርዕዮተ ዓለምና የምርት ግንኙነት

ሕዝባዊ አንድነትና ድርጅት ኃይል ነው ። ለሕዝባዊ አንድነትና ድርጅት ኃይል የሚሰጠው ወሳኝ ነገር ደግሞ የሕዝቡ የአመለካከት ወይም ርዕዮተ ዓለ ማዊ አንድነትና ዓላማ ነው ። በርዕዮተ ዓለማዊ መሠረት ፣ ዓላማና አንድነት የተደራጀ ሕዝብና ሕብረተሰብ ጠንካራና ድል አድራጊ ሕዝብና ሕብረተሰብ ብቻ ሳይሆን ምርታማም ነው ። ስለዚህ ሕዝባዊ ድርጅትና ወዛደራዊ ርዕዮተ ዓለም የኢኮኖሚና የባህል ዕድገት መሠረቶችና መግሪያዎች ናቸው ። በመሆኑም ዛሬ በኢትዮጵያ ሶሻሊስት አገርና ሕብረተሰብ ለመገንባት በሚደረገው አብዮታዊና ብሔራዊ ትግል ሕዝባዊ ድርጅቶች ወዛደራዊ ርዕዮተ ዓለም የኢኮ ኖሚና የባህል ዕድገት ሁለት ወሳኝ ቅድመ ሁኔታዎች ናቸው ።

በዚህ አንፃርና ተግባር ፣ ዛሬ በሶሻሊስት ግምባታ ወቅት የኢትዮጵያ ሕዝ ብና ሕብረተሰብ ከሕፃናት ኮሚሽን እስከ አርበኞች ማህበር ድረስ በመኢሠማ፣ በመኢገማ ፣ በከነማት ፣ በአኢወማ ፣ በአኢሴማና በውይይት ክበቦች በአገር አቀፍ ደረጃ መደራጀቱን ከዚህ በላይ በሠንጠረዥ 13 አይተናል ። በተጨማ ሪም እነዚህ ሕዝባዊ ድርጅቶችና የውይይት ክበቦች በኢትዮጵያ ሕዝብና ሕብ ረተሰብ ዘንድ ወዛደራዊ ርዕዮተ ዓለም ለማስረጫትና ለማስፋፋት ዛሬ በአገሩ አመቺ ሁኔታና ጊዜ እንደፈጠሩ አይተናል ። በዚህ መንገድና ሂደት በኢትዮጵያ አዲስ ሶሻሊስት ኢኮኖሚና ባህል ብሎም አዲስ ሕብረተሰብ መገንባት ይቻላል

ይህንን ብሔራዊ የድርጅት የኢኮኖሚና የባህል ዕድገት ዘመቻ መርሆ በመከተል የከምባታና ሀዲያ አውራጃ ሕዝብ ከወረዳ እስከ አውራጃ ደረጃ የተ ደራጀ ሲሆን ፣ ይህ የሕዝባዊ ድርጅት ሥራ ከ1971 ጀምሮ ፣ ከዚህ በታች እን ደሚታየው ፣ በአውራጃው ለኢኮኖሚና ለባህል ዘመቻ ታላቅ መሠረትና መግሪያ ሆኗል

ሠንጠረዥ 25

የከምባታና ሀዲያ አውራጃ ሕዝባዊ ድርጅቶችና ማህበራት በ1975

| ተራ ቁ. | ወረዳ | የገበሬ ማህበራት | | የወጣት ማህበራት | | የሴቶች ማህበራት | | የገበሬ የአገልግሎት ሕብረት ሥራ ማህበራት | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ማህበራት | አባላት | ማህበራት | አባላት | ማህበራት | አባላት | ማህበራት | አባላት | ተጠቃሚ ሕዝብ | ካፒታል በብር |
| 1 | ኮንተብ | 93 | 38,816 | 95 | 12,415 | 95 | 38,934 | 17 | 38,430 | 184,370 | 435,580.18 |
| 2 | ሊሙ | 74 | 40,584 | 81 | 15,069 | 81 | 43,866 | 20 | 40,593 | 146,171 | 382,345.55 |
| 3 | ጥምባሮ | 64 | 31,389 | 66 | 16,074 | 66 | 27,136 | 12 | 27,920 | 162,882 | 201,252.87 |
| 4 | አዋ ሽለቆ | 31 | 16,503 | 31 | 7,504 | 31 | 10,514 | 3 | 13,764 | 64,195 | 49,670.30 |
| 5 | ሲቄ | 44 | 22,168 | 45 | 14,759 | 45 | 57,375 | 9 | 18,731 | 115,759 | 238,366.54 |
| 6 | እንጋሜ | 37 | 18,948 | 39 | 8,091 | 39 | 16,927 | 9 | 18,948 | 122,988 | 363,421.92 |
| 7 | ቀ. ጋሜላ | 37 | 21,606 | 39 | 11,634 | 39 | 16,000 | 5 | 17,565 | 93,405 | 277,023.61 |
| 8 | ታምበሮ | 26 | 16,361 | 28 | 8,997 | 28 | 14,794 | 3 | 11,200 | 48,938 | 216,895.06 |
| | | 406 | 206.375 | 424 | 94.543 | 424 | 225.546 | 78 | 187.151 | 938,870 | 2,164,555.96 |

| ተራ ቁ. | ከተማ | የከተማ ነዋሪዎች ማህበራት | |
|---|---|---|---|
| | | ማኅበራት | አባላት |
| 1 | ሆሳዕና | 4 | 25,215 |
| 2 | ዱራሜ | 1 | 6,540 |
| 3 | ሾኔ | 1 | 4,390 |
| 4 | ጂንጂቶ | 1 | 2,577 |
| 5 | ጎምቦቾ | 1 | 2,300 |
| 6 | እንጋሜ | 1 | 1,230 |
| 7 | ሞርሱጦ | 1 | 1,000 |
| | ድምር | 10 | 43,252 |

| ተራ ቁ. | የገበሬ አምራች ሕብረት ሥራ ማህበራት | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ወረዳ | የማህበር ስም | አባላት | መሬት በሄክታር | ካፒታል በብር |
| 1 | ታምበሮ | ዱራራማ | 111 | 119,67 | 27,973.80 |
| 2 | ሲቄ | አምቡርስ አንጂሉ | 74 | 86,30 | 14,191.00 |
| 3 | ሲቄ | ትካሬ አምቡርሴ | 46 | 50,00 | 9,210.06 |
| 4 | ቀ. ጋሜላ | በዛና ቤናሬ | 54 | 35,16 | 648.00 |
| 5 | እንጋሜ | ቀዕላማ | 170 | 510,00 | 5,495.00 |
| 6 | እንጋሜ | ሆቢቾ ሚሊሳ | 10 | 12,00 | 929.00 |
| 7 | ቀ. ጋሜላ | አንበሳ | 12 | 11,00 | 420.00 |
| 8 | ቀ. ጋሜላ | አምበ | 9 | 8,43 | ! |
| 9 | አዋ ሽለቆ | ጡንጦ | 15 | 13,50 | .405.00 |
| | ድምር | | 401 | 846.09 | 58,972.60 |

የተገኘበት ፤ ከከምባታና ሀዲያ አውራጃ የገበሬ ፤ የወጣት ፤ የቤቶችና የከተማ ነዋሪዎች ማህበራት ጽሕፈት ቤቶች በሆሳዕና (መጋቢት ፤ 1975) ከምባታና ሀዲያ አውራጃ የግብርና ሚኒስቴር ተጠሪ ጽሕፈት ቤት በሆሳዕና (መጋቢት ፤ 1975) የዱራሜ ከተማ ቀበሌ ጽሕፈት ቤት መጋቢት ፤ 1975) ፤ የከምባታና ሀዲያ አውራጃ ኢሠፓአኮ ጽሕፈት ቤት (መጋቢት ፤ 1975)



## 3. የኢኮኖሚና የባህል ዘመቻ ምርትና ውጤት

### 3. ሀ. የኢኮኖሚና የባህል ዘመቻ በሆሳዕና ከተማ

ሆሳዕና በ1888 በዋቸሞ ተራራ ላይ የተመሠረተ የከምባታና ሀዲያ አውራጃ ርዕሰ ከተማ ነው ። የከተማው ክልል ስፋቱ 80 ጋሻ መሬት ሲሆን ከተማው ከአዲስ አበባ በ250 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በደቡብ ምዕራብ ፣ ከወልቂጤ በ130 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በደቡብ ይገኛል ። የከተማው ከፍታ ከባህር ወለል 2,380 ሜትር ፣ አማካይ ዓመታዊ የዝናብ መጠን 1,100 ሚ.ሊ. ሜትር ሲሆን የዓመቱ አማካይ ሙቀት ደግሞ እስከ 16 ዲግሪ ሴንቲ ግሬድ ይደርሳል ። ከጥቅምት 1970 ጀምሮ የሆሳዕና ከተማ ሕዝብ በከተማው ምሥራቃዊ ዳር በውኃና ፍሳሽ አገልግሎት ባለሥልጣን በዘመናዊ ዘዴና መጣሪያ ከተገደበው ውኃ ንጹህ የመጠጥ ውኃ በቦምባ ያገኛል ። ለሆሳዕና ከተማ የግድቡ ውኃ መጠንና አገልግሎት የሚወሰነው በከተማው ላይ በዓመት በሚዘንበው ዝናብ መጠን ስለሆነ ፣ በአንድ ዓመት ውስጥ በከተማው በየወሩ የሚዘንበው የዝናብ መጠን ምን ያህል እንደሆነ ከዚህ በሚከተለው ሠንጠረዥ ማስተዋል አስፈላጊ ነገር ነው ።

ሠንጠረዥ 26

በሆሳዕና ከተማ በዓመት ውስጥ በየወሩ የሚዘንበው የዝናዋ መጠን በሚሊ.ሜትር

| የዓመቱ ወራት | በየወሩ የሚዘንበው ዝናብ መጠን በሚሊ. ሜትር | በዓመት የሚዘንበው ዝናብ መጠን በሚሊ. ሜትር |
|---|---|---|
| 1. መስከረም | 154 ሚ. ሜ. | 1 166 ሚ. ሜ. |
| 2. ጥቅምት | 67 ሚ. ሜ. | |
| 3. ህዳር | 22 ሚ. ሜ. | |
| 4. ታህሣሥ | 29 ሚ. ሜ. | |
| 5. ጥር | 31 ሚ. ሜ. | |
| 6. የካቲት | 29 ሚ. ሜ. | |
| 7. መጋቢት | 105 ሚ. ሜ. | |
| 8. ሚያዝያ | 136 ሚ. ሜ. | |
| 9. ግንቦት | 108 ሚ. ሜ. | |
| 10. ሰኔ | 135 ሚ. ሜ. | |
| 11. ሐምሌ | 159 ሚ. ሜ. | |
| 12. ነሐሴ | 192 ሚ. ሜ. | |

Source: *Ethiopian Geographical Journal*, Vol. 2, No. 2, p. 35

የሆሣዕና ከተማ በ1888 ከተመሠረተበት እስከ ዛሬ ድረስ በ87 ዓመታት ውስጥ አራት ልዩ ልዩ የዕድገት ሁኔታዎችንና ደረጃዎችን አልፎዋል ። አንደኛ ከ1888 እስከ 1928 ድረስ በዘመነ ገባር ፣ ከዚህ በላይ በሠንጠረዥ 22 እንደሚታየው ፣ ስድስት ራሶችና ደጃዝማቾች ሆሣዕናን እንደ የጦር ሠፈር ይዘው የከምባታና ሀዲያ አውራጃን በማዕከላዊ መንግሥት ስምና ሥር በገባር ሕግና ሥርዓት ገዝተዋል ። በእነዚህ ራሶችና ደጃዝማቾች ግዛትና ዘመን ሆሣዕና የጦር ሠፈር ከመሆን ባሻገር የከተማ መልክና ይዘት አልነበረውም ። በግንቦት 1928 እርሱንም የአውራጃው አመጸኛ ገባሮች አቃጥለውት ሄዱ ። በዘመነ ገባር የከተማው ማዕከል ማለትም የራሶችና የደጃዝማቾች መኖሪያ አሁን የሆሣዕና ሆስፒታል ከተሠራበት ቦታ በስተ ምዕራብ ደቡብ ከባለወልድ ቤተ ክርስቲያን ጐን የከተማው የመጠጥ ውኃ ጋን የተሠራበት ሥፍራ ነበር ። በመሆኑም የከተማው ነዋሪዎች እስካሁን አካባቢውን "አሮጌው ግቢ" በማለት ይጠሩታል ።

ሁለተኛ ፣ ከ1928 መጨረሻ እስከ 1933 መጀመሪያ ድረስ ሆሣዕና በከምባታና ሀዲያ አውራጃ የኢጣሊያኖች ዋናው ከተማ ሆነ ። ኢጣሊያኖች በውስጡ ዘመናዊ መንገዶችና የድንጋይ ሕንፃዎችን በመሥራት ለሆሣዕና ለመጀመሪያ ጊዜ የከተማ መልክና ቅርጽ ሰጡት ። በዚህ ጊዜ ማለትም በ1930 የሆሣዕና ሕዝብ ብዛት 12.000 ይደርስ እንደነበር በዘመኑ አንድ ኢጣሊያዊ ጽፎዋል ። ኢጣሊያኖች በከተማው እናት ላይ የቀድሞ የራሶችንና የደጃዝማቾችን ግቢና ሠፈር በመተው በሰሜናዊ ምሥራቅ ዛሬ የአዲስ አበባ—ሆሣዕናና የወልቅጤ—ሆሣዕና የመኪና መንገዶች የሚገኙበትን አካባቢ የሆሣዕና የአስተዳደር ፣ የንግድና የባህል ማዕከል አድርገውት ሄዱ ።

ሦስተኛ ፣ በድህረ ጦርነት ከ1933 እስከ 1966 ድረስ ጥቂት የአውራጃው ጉልተኞች ፣ የመንግሥት ባለሥልጣኖች ፣ ባላባቶችና ነጋዴዎች የሆሣዕና ከተማን መሬት በቅርሜ ተከፋፍለው ከተማው እንዳያድግ በሥርዓታዊ ሰንሰለት አስሮ አቆዩት ። በዚህ ረገድ ለምሳሌ በአብዮቱ ዋዜማ በ1960 የተዘጋጀለት የከተማው የማስተር ፕላን በሥራ ላይ እንዳይውል ጉልተኞች ከለከሉት ። በዚህ ምክንያት በ1966 የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮት እንደ እሳተ ጐሞራ በፈነዳ ጊዜ የሆሣዕና ከተማ የመጠጥ ውኃ በየቀኑ በሰውና በእንስሳት ጀርባ ከወንዝ የሚመጣለት ፣ የመኪና መንገድና የኤሌክትሪክ መብራት ያልገባለት ፣ የዘመናዊ ሆቴል ድርጅትና አገልግሎት የሌለውና በ10.000 የሚቆጠሩ ሰዎች የሚኖሩበት በባህር ዛፍ የተሸፈነ ትንሽ የገጠር ከተማ ነበር ። አብዮቱ በየካቲት 1966 ከፈነዳበት እስከ ሚያዝያ 1971 ድረስ በሽግግራዊ ወቅት ትንሹ የሆሣዕና ከተማ በአብዮቱ ወገኖችና በፀረ አብዮት ኃይላት መካከል የታላቅ መደብ ጦርነት ሜዳ ሆነ ።

አራተኛ ፣ በሚያዝያ 1971 የፀረ አብዮት ኃይላት በአብዮቱ ወገኖች ሙሉ በሙሉ ከተደመሰሱ በኋላ ፣ በጥቅምት 1971 የኢትዮጵያ አብዮታዊ መንግሥት በአወጀው በኢኮኖሚና በባህል ዕድገት ዘመቻ መዋቅርና መርሆ መሠረት ከዚህ በታች የሚገለፀው የሆሣዕና ከተማ ዕድገት ዘመቻ በአውራጃው ሕዝብና በአብዮታዊ መንግሥት ትብብር ተጀተረ ።

---

Ministry of Interior, *Municipalities Department: General Analysis and the Report On the Master Plan for Hosaena* (1968), p. 15.




ሠንጠረዥ 27


በኢኮኖሚና በባህል ዘመቻ ከ1971 እስከ 1975 በሆሣዕና ከተማ ለግል ለሕዝባዊ ለመንግሥታዊ ድርጅቶችና አገልግሎት የተሰጠ መሬት በካሬ ሜትር

| | የግል ፣ ሕዝባዊና መንግሥታዊ ድርጅቶችና መሥሪያ ቤቶች በሆሣዕና ከተማ | መሬት በካሬ |
|---|---|---|
| 1 | የስፖርት ክልል | ሜትር |
| 2 | የሆሣዕና ሆስፒታል ክልል | 288,000 |
| 3 | የመዋዕለ ሕፃናት ሥፍራ | 70,000 |
| 4 | የውኃ ልማት ቦታ | 57,000 |
| 5 | የትምህርት ቦታ | 45,000 |
| 6 | የስፖርት ሆቴል ክልል | 22,000 |
| 7 | የከነማት ሥፍራ | 20,000 |
| 8 | ያውራጃው የትምህርትና የባህል ማዕከል ክልል | 17,000 |
| 9 | የሕክምና ባለሙያዎች መኖሪያ ክልል | 15,000 |
| 10 | የአውራጃው ትምህርት ቤቶች ጽሕፈት ቤት ክልል | 9,761 |
| 11 | የአውራጃው የገበሬ ፣ የወጣትና የሴት/የመኢገግ ፣ የአኢወማና የአኢሴማ ጽ/ቤቶች ክልል | 8,350 |
| 12 | የኢሠፓአኮ ጽሕፈት ቤት ክልል | 8,280 |
| 13 | የሆሣዕና ሸማኔዎች ማህበር ቦታ | 7,025 |
| 14 | የአውቶቡስ ተራ /(መኪና ማቆሚያ ሥፍራ) | 6,320 |
| 15 | የእርሻ ሰብል ገበያ ኮርፖሬሽን የሆሣዕና ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት ቦታ | 6,000 |
| 16 | የግል ሆቴሎች ቦታ | 5,671 |
| 17 | የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ፣ መብራትና ኃይል ባለሥልጣን የሆሣዕና ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት ቦታ | 4,371 |
| 88 | የሆሣዕና የልብስ ሰፊዎች ማህበር ቦታ | 4,000 |
| 19 | የኢትዮጵያ ያገር ውስጥ ማከፋፈያ ድርጅት የሆሣዕና ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት ቦታ | 4,000 |
| 20 | የኢትዮጵያ የንግድ ባንክ የሆሣዕና ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት ቦታ | 3,922<br>3,131 |
| 21 | የዕርዳታ ማስተባበሪያና ማቋቋሚያ ኮሚሽን ቦታ | 3,088 |
| 22 | የቤተ መስጊድ ቦታ | 3,000 |
| 23 | የፍርድ ቤት ቦታ | 2,415 |
| 24 | የቄራ ድርጅት ቦታ | 925 |
| 25 | የአናጢዎች ማህበር ቦታ | 810 |
| | ድ ም ር | 615,899 ካሬ ሜት |

የተገኘበት ፤ የሆሣዕና ማዘጋጃ ቤትና የሆሣዕና ከነማት ልዩ ጽሕፈት ቤት (በግ ቦትን 1973 ፤ እና በመጋቢት 1975) ።



በጓድ ሊቀመንበር መንግሥቱ ኃይለ ማርያም
የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግና
የኢሠፓአኮ ሊቀመንበር የአብዮታዊ ጦር ኃይሎች ጠቅላይ አዛዥ
ሰብሳቢነት የ1975 የምርትና የባህል ዘመቻ ግምገማ ሲካሄድ ።
የተገኘበት ፣ የፕሬስ መምሪያ ፎቶግራፍ ክፍል (አዲስ አበባ 1975)




**አረንጓዴው የሆሣዕና ከተማ በምዕራብ ከሆስፒታሉ ሥፍራ ባሻገር ወደ ምሥራቅና ደቡብ ሲታይ በ1973**

በዚህ እንዳንዳና ተግባር የፀረ አብዮት ኃይላት በአብዮቱ ብርቱ ሠፈርና ክንድ ለአንዴና ለመጨረሻው ከተደመሰሱ በኋላ ከከተማው ክልል ከግማሽ በላይ ማለትም 45 ጋሻ ወይም 1.800 ሄክታር መሬት የሚሸፍነውና የከተማው የ1960 የማስተር ፕላን በፍጥነት በሥራ ላይ እንዲውል ሲደረግ ፣ በተጨማሪም ከአብዮቱ ፍንዳታ በፊት የአውራጃው ሕዝብ ከጐረቤት አውራጃዎች ጋር በመ ተባበር በከፍተኛ ገንዘብና ጉልበት ወጭ ያሠራቸው የዓለምገና - ወላይታና የወ ልቅጤ - ሆሣዕና የመኪና መንገዶች በየቀኑ የሆሣዕና ከተማን ከአውራጃው ወረዳ ከተሞችና እንዲሁም ከአዲስ አበባ ፣ ከሸዋ ፣ ከሲዳሞና ከጋሞጐፋ ክፍለ ሀገራት ከተሞች ጋር በማገናኘት ለሆሣዕና ከተማ ዕድገት በተለይ ለከምባታና ሀዲያ አውራጃ በአጠቃላይ ኢኮኖሚያዊና ባህላዊ ዕድገት ልዩ አገልግሎት መስጠት ጀመሩ ። ከዚሁም ሌላ ለከተማው ሕዝብ ንጹህ የመጠጥ ውኃ በቦምባ ገባለት ። የኤሌክትሪክ መብራትም ገባለት ።

እነዚህና ሌሎችም ለአንድ ከተማ ልማትና ዕድገት የሚያስፈልጉ መሠረ ታዊ ነገሮችና ሁኔታዎች በከፊልም ቢሆን እንኳን ስለተሞሉ በብሔራዊው ኢኮ ኖሚና ባህል ዘመቻ መሠረት በሆሣዕና ከተማ ከዚህ የሚከተሉ ሁለገብ ኮኖሚና የባህል ዕድገት እንቅስቃሴዎችና እርምጃዎች በአውራጃው ሕዝብና በአብዮታዊው መንግሥት ትጋትና ትብብር ተጀመሩ ። በዚህ አኳያና ወቅት በሆሣዕና ከተማ የ1960 ማስተር ፕላን በሥራ ላይ በዋለበት አካባቢ በድምሩ ከ600.000 ካሬ ሜቴር በላይ መሬት ለሕዝባዊና ለመንግሥታዊ ድርጅቶችና አገልግሎት ተሰጥቶ በሥራ ላይ እንዳዋለ ከዚህ በላይ ሠንጠረዥ 27 ያሳያል ።

የከምባታና ሀዲያ አውራጃ አስተዳደርና ሕዝብ በብሔራዊ ኢኮኖሚና ባህል ዘመቻ መርሆ የቀየሰውን የራሱን የአውራጃ የኢኮኖሚና የባህል ዘመቻ እቅድና እርምጃ ለኢትዮጵያ ሕዝብና ሕብረተሰብ በይፋ ለማሳየት በየካቲት 1972 በሆ ሣዕና ከተማ "የከምባታና ሀዲያ አውራጃ ኤክስፖ 1972" አደራጀ ። በኤክስ ፖው ወቅትና መድረክ በሆሣዕና ከተማ ከኢኮኖሚና ከባህል ዘመቻ አንፃር ብዙ የልማት እቅዶች በጥንስስ ደረጃ ለሕዝብ ታዩ ። በሚቀጥለው ዓመት ማለትም በግንቦት 1973 የከምባታና ሀዲያ አውራጃ ሕዝብ የ1973 የሸዋ ክፍለ ሀገር ዓመታዊ የስፖርት በዓል በሆሣዕና ከተማ በተሟላ ድርጅትና ዝግጅት አስተና ገደ ። በ1972 ኤክስፖ በ1973 ስፖርት በዓል ወቅት ሂደትና አማካይነት በሆሣ ዕና ከተማ በጥንስስ ደረጃና ተግባራዊ በመሆን ለኢትዮጵያ ሕዝብ በልዩ ልዩ መንገዶችና መግሪያዎች የታዩና የተገለፁ ዋና ዋና የልማት ሥራዎችና ድርጅ ቶች በከፊል ከዚህ የሚከተሉ ናቸው ።

አንደኛ ፣ በከምባታና ሀዲያ አውራጃ የትምህርትና የባህል ማዕከል በ350 ካሬ ሜትር ሥፍራ ላይ በ50,000 ብር ወጭ በጥርብ ድንጋይ የተገነባው የትም ህርት ማበልጸጊያ ማዕከል በየካቲት 1972 በኤክስፖው ወቅት ተመርቆ አገልግሎት መስጠት ጀመረ ። ሁለተኛ ፣ በትምህርትና በባህል ማዕከል ከትምህርት ማበ ልጸጊያ ማዕከል ጐን በ1000 ካሬ ሜትር ቦታ ላይ በ75.000 ብር ወጭ በጥርብ ድንጋይ የተሠራው የሆሣዕና ሁለገብ አዳራሽ ሥራው አልቆ በግንቦት 1973 በአ በአገልግሎት ላይ ዋለ ። ሦስተኛ ፣ ከሆሣዕና ሁለገብ አዳራሽና በሆሣዕና ሆስፒ ታል መካከል በ525 ካሬ ሜትር ላይ በ120.000 ብር ወጭ በድርብ ድንጋይ የተሠራው የከምባታና ሀዲያ አውራጃ የመኢገማ ፣ የኢሠማና የኢሴማ ጽሕ ፈት ቤቶች ሕንፃ በ1974 አገልግሎት መስጠት ጀምረዋል ። አራተኛ ፣ የውሃ ዋና ሥፍራ ጭምር የተሟላ ድርጅት ያለው ታላቅ ዘመናዊ ስታዲየም በ198,



ጓድ ጴጥሮስ ገብሬ የከምባታና ሀዲያ አውራጃ አስተዳዳሪ የከምባታና ሀዲያ አውራጃ ኤክስፖ 1972 የመግቢያ ንግግር ሲያደርጉ



በከንባታና ሐዲያ አውራጃ ኤክስፖ 1972 የተገኙ ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣኖች

945 ብር ወጭ ተሠርቶ በግንቦት 1973 አገልግሎት መስጠት ጀምሮዋል ። አም
ስተኛ ፣ አሥር በአውራጃው ወረዳዎች ስሞች የተሰየሙ ባህላዊ ጉጆዎችን ፣
አንድ ልዩ ባህላዊ አዳራሽና አሥር በሸዋ ክፍለ ሀገር እህት አውራጃዎች ስሞች
የተሰየሙና ከጥርብ ድንጋይ የተሠሩ መኝታ ቤቶችን ጭምር የተሟላ ድርጅት
ያለው "የከምባታና ሀዲያ ስፖርት ሆቴል" በ276.000 ብር ተሠርቶ ከግንቦት
1973 ወዲህ ለእንግዶችና ለሆሳዕና ነዋሪዎች የተሟላ የዘመናዊ ሆቴል አገል
ግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል ።

ስድስተኛ ፣ ከከምባታና ሀዲያ አውራጃ ሕዝብ የተዋጣውን 152,975
ብር ጨምሮ የኢትዮጵያ ያገር ውስጥ ማከፋፈያ ድርጅት በ249,000 ብር ወጭ
ያሠራው ሙሉ ድርጅት ያለው የሆሳዕና ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት ለአውራ
ጃው ሕዝብ በተለይም ለሕዝባዊና ለመንግሥታዊ ድርጅቶች አስፈላጊ የንግድ
ዕቃዎችን በማቅረብ ረገድ ጥሩ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል ። ሰባተኛ፣
ከአብዮቱ ፍንዳታና ከኢኮኖሚና ከባህል ዘመቻ ሥምሪት ወዲህ በአውራጃው
ገበሬዎችን በማደራጀትና በማስተማር ረገድ ከፍተኛ አገልግሎት በመስጠት
ላይ ለሚገኘው ለግብርና ሚኒስቴር ተጠሪ መሥሪያ ቤት ከዓለም ባንክ በእርዳታ
በተገኘው ገንዘብ ከአዲስ አበባ ወደ ሆሳዕና ከተማ መግቢያ ላይ በ170,000 ብር
ወጭ እጅግ በጣም ዘመናዊ የሆነ ጽሕፈት ቤት ተሠርቶዋል ። ስምንተኛ ፣ በአ
ውራጃው ሕዝብና በአብዮታዊ መንግሥት ትብብር ከአንድ ዓለም አቀፍ ድር
ጅት የተገኘውን የሆስፒታልና የሕክምና ዕቃዎች እርዳታ ጭምር በአሥር ሚሊ
ዮን ብር በሚቆጠር ወጭ 250 አልጋዎች ያሉት ታላቁ የሆሳዕና ሆስፒታል በከ
ተማው አናት ላይ በ8900 ካሬ መሬት ላይ መሠራቱን ከዚህ በታች አግባብ
በአለው ሥፍራና ጊዜ በዝርዝር እናያለን ።

ከዚህ በላይ በአጭርና በአጠቃላይ ለተገለፁ በሆሳዕና ከተማ ለተሠሩ
ልማት ሥራዎች ከሚያስፈልገው ገንዘብና ጉልበት ሥራ ሙሉ በሙሉ እንኳን
ባይሆን አማዛኙ የመጣውና የሚመጣው በአውራጃው ስምንቱ ወረዳዎች ከሚ
ኖሩ ገበሬዎች ነው ። የከምባታና ሀዲያ አውራጃ ገበሬዎች በስምንቱ ወረዳዎች
በአውራጃው ርዕሰ ከተማ ለተሠሩና ለሚሠሩ ልማት እቅዶችና ሥራዎች ከፍ
ተኛ የገንዘብና የጉልበት መዋጮና አስተዋጽኦ ከማድረጋቸው ባሻገር ፤ በብሔ
ራዊው የኢኮኖሚና ባህል ዘመቻ መሠረትና መርሆ ለየወረዳቸቸው ኢኮኖሚ
ያዊና ባህላዊ ልማት የሚያስፈልገውን የገንዘብና የጉልበት መዋጮና አስተዋጽኦ
ያደርጋሉ ።

በዚህ እንቅርና ተግባር ለየከምባታና ሀዲያ አውራጃ በአውራጃው የምርት
ዘመቻና ፕላን ኮሚቴ መሪነት ከላይ ከአብዮታዊ መንግሥት የሚሰጠውን የኢኮ
ኖሚና የባህል ዘመቻ ደምብና መመሪያ የእቅድና የተግባር መርህ አድርጉ እንደ
ሚከተለው ሁሉ ፤ የአውራጃው ወረዳዎች ደግሞ ከላይ የአውራጃውን የልማት
መመሪያና ምሳሌ እየተከተሉ ይሠራሉ ። በዚህ አኳያ ፤ በከምባታና ሀዲያ አው
ራጃ በወረዳው አስተዳደርና በገበሬ ማህበራት መካከል የሚታየው የዓላማና
የተግባር ሕብረት የአውራጃውን አጠቃላይ የልማት ሥራ የሚያንቀሳቅስ መሠ
ረታዊ የሕዝብና መንግሥት ሕብረት መሆኑን ይህ ደራሲ የአውራጃውን ወረዳ
ዎች እየዞረ በ1972 እና በ1975 በጐበኘበት ወቅት ለማየት ችሎዋል ።

ከከተማው አጠቃላይ ዕድገት አኳያ ሲታይ የማስተማር ፕላን አገልግሎት
በአውራጃው ሕዝብና በአብዮታዊ መንግሥት ትብብር የተዘረጉ የልማት እቅዶ
ችና ሥራዎች ዛሬ በሆሳዕና ከተማ ያስከተሉ ሁኔታዎች እያሴና መሠረታዊ



የከምባታና ሀዲያ አውራጃ የኢሠፓአኮ የመንግሥታዊና የሕዝባዊ ድርጅቶች የምርትና
የባሕል ዘመቻ ኮሚቴዎች የአመራር አባላት በአንድነት በ1975

### ሠንጠረዥ 28

በኢኮኖሚና በባህል ዘመቻ በአውራጃው ለሚካሄዱ ለልዩ ልዩ የልማት ሥራ ዎችና ለማህበራዊ ጉዳዮች የከምባታና ሀዲያ አውራጃ ሕዝብ ያዋጣው ገንዘብ በከፊል እስከ 1975

| ተራ ቁ. | የልማት እቅዶችና ሥራዎች | ለልማት ሥራዎች ከሕዝብ የተዋጣ ገንዘብ በብር |
|---|---|---|
| 1 | ለመንገድና ለድልድይ ሥራዎች ማለትም ለኢኮኖሚ መስኮች | 5 044 347.56 |
| 2 | ለሆሣዕና ሆስፒታል ሕንፃ ማሰሪያ | 2 933 777.90 |
| 3 | በትምህርት መስኮች ከመደበኛው እስከ መሠረተ ትምህርት | 2 775 204.10 |
| 4 | በጤና መስኮች — ለወረዳ ክሊኒኮች መስፋፋት | 134 158.75 |
| 5 | በስፖርት መስኮች — ለስታዲየም ፣ ለስፖርት ሆቴል ለወረዳ ስፖርት ሜዳዎች | 715 115.00 |
| 6 | ለመኖሪያና ለጽሕፈት ቤቶች ለሕዝባዊ አዳራሾች ሥራ ፣ ለጽሕፈት ቤቶችና ለሕክምና ባለሙያዎች መኖሪያ ፣ ለቁጠባ ቤቶች ወዘተ... | 763 108.00 |
| 7 | ለውኃና ለመብራት ማስገቢያ ሥራዎች (ለወረዳ) | 282 536.00 |
| 8 | ለማከፋፈያ ለመጋዘን ሥራዎች | 436 975.50 |
| 9 | የገበሬ አገልግሎት ሕብረት ሥራ ማህበራት የመነሻ ካፒታል | 1 393 234.16 |
| 10 | የገበሬ የአምራቾች ሕብረት ሥራ ማህበራት የመነሻ ካፒታል | 2 775.00 |
| 11 | ለእናት አገር ጥሪ | 1 201 527.53 |
| 12 | ለመልሶ ማቋቋም | 75 337.00 |
| 13 | የተፈጥሮ ሰው ሠራሽ ችግር ለደረሰባቸው ወገኖች እርዳታ | 42 500.00 |
| | ጠ ቅ ላ ላ ድ ም ር | 15 805 596.51* |

የተገኘበት ፤ ከከምባታና ሀዲያ አውራጃ አስተዳደር ጽ/ቤት ፤ ከከምባታና ሀዲያ አውራጃ ፤ ኢክስፖ 1972 ፤ የከምባታና ሀዲያ አውራጃ መኢገማ ጽ/ቤት ፤ የሆሣዕና ሆስፒታል የሥራ ተቋራጮች ያከሬና ጉልየልሞና ልጆቹ(ሆሣዕና መጋቢት 1975) ፤ ከሆሣዕና ሁለገብ አዳራሽ (መጋቢት 1975) ። በትንተና ።

* በተጨማሪም የከምባታና ሀዲያ አውራጃ ሕዝብ 19.807 ሚሊሺያዎች አሰልጥና ከእነዚሁ 11.687 ወደ ጦር ሜዳ አዝምተዋል ። ከዚህም ሌላ 3981 የአብዮት ጥበቃ ጓዶች አሰልጥኖ በግዳጅ ላይ አሰማርቶዋል ።



ናቸው ። አንደኛ ፤ በ1971 የኢኮኖሚና የባህል ዘመቻ ከተጀመረበት ወዲህ በሆሣዕና ከተማ በማስተር ፕላን መሠረት ብዙ አዳዲስ ሠፈሮችና ቤቶች ተሠርተዋል ። ብሎም የከተማው ነዋሪዎች ቁጥር በአጭር ጊዜ ውስጥ በጣም አድጎዋል ። በዚህ አኳያ ለምሳሌ በግንቦት 1973 የከተማ ነዋሪዎች ብዛት 18 049 ነበር ። ሁለት ዓመታት ባልሞላ ጊዜ በመጋቢት 1975 ይህ ቁጥር ወደ 25 215 ደረሰ ። በሌላ አባባል ከግንቦት 1973 እስከ መጋቢት 1975 በሁለት ዓመታት ውስጥ የሆሣዕና ሕዝብ በ7 166 ሰዎች ወይም በ39 በመቶ አድጎዋል ።

### ሠንጠረዥ 29

የሆሣዕና ከተማ ሕዝ ብ ብዛት በ1955 ፤ በ1978 ፤ በ1973 ፤ በ1975

| ተራ ቁ. | ዓመት | የከተማው ሕዝብ ብዛት | የከተማው ሕዝብ ዕድገት መጠን ከ1973 እስከ 1975 | |
|---|---|---|---|---|
| | | | ዕድገት በቁጥር | ዕድገት በፐርሰንት |
| 1 | 1955 | 8 477 | | |
| 2 | 1958 | 10 000 | | |
| 3 | 1973 | 18 049 | | |
| 4 | 1975 | 25 215 | 7 166 | 39 በመቶ |

የተገኘበት ፤ Ministry of Interior, Master Plan for Hosaena p. 15; ከሆሣዕና ማዘጋጃ ቤት ለደራሲው በግንቦት 1973 እና በመጋቢት 1975 በጽሑፍ የተሰጠ ማስረጃ ።

ሁለተኛ ፣ የማስተር ፕላን አገልግሎትና የከተማ ልማት ሥራዎች ፣ ከቅድመ አብዮት ጊዜ ሲመዛዘን ፣ የሆሣዕና ማዘጋጃ ቤቱን ዓመታዊ ገቢ በከፍተኛ ደረጃ አሳድጎዋል ። በዚህ አኳያ ፣ ከአብዮቱ ፍንዳታ አንድ ዓመት በፊት በ1965 የሆሣዕና ማዘጋጃ ቤት ዓመታዊ ገቢ 32,870 ብር ነበር ። አብዮቱ ከፈነዳ ከስምንት ዓመታት በኋላ በ1974 ፣ የሚከተለው ሠንጠረዥ እንደሚያሳየን ፣ ይህ የሆሣዕና ማዘጋጃ ቤት ዓመታዊ ገቢ ወደ 152,865 ብር ደረሰ ።

ሦስተኛ ፤ ከ1971 ወዲህ በከምባታና ሀዲያ አውራጃ በከፍተኛ ደረጃ በመካሄድ ላይ ያለው የኢኮኖሚና የባህል ዕድገት ዘመቻ እንቅስቃሴና ሥምሪት ለአውራጃው ጥሩ የትራንስፖርት አገልግሎትና የንግድ እንቅስቃሴ አስገኝቶለታል። በዚህ አኳያ ፤ በሰኔ 1972 በየቀኑ የሆሣዕና ከተማን ከከምባታና ሀዲያ አውራጃ ወረዳዎች ፤ ከአዲስ አበባና ከአካባቢው አውራጃዎች የሚያገናኙ 65 የሕዝብ ማመላለሻ ድርጅት ፤ የመንግሥትና የግል መኪናዎች ነበሩ ። ከሦስት ዓመታት በኋላ መነሻና መድረሻ የሆሣዕና ከተማ ሆኖ በየቀኑ በከምባታና ሀዲያ አውራጃ ወረዳዎችና መንገዶች ላይ ሰውና ዕቃ ይዘው የሚንቀሳቀሱ በመጠንና በአገልግሎት ልዩ ልዩ የሆኑ የድርጅት ፤ የመንግሥትና የግል መኪናዎች ብዛት ወደ

### ሠንጠረዥ 30

**የሆሣዕና ማዘጋጃ ቤት የዓመት ገቢ መጠን ከ1965 እስከ 1974 በብር**

| ተራ ቁ. | የበጀት ዓመት | የዓመት ገቢ መጠን በ ብ ር | የማዘጋጃ ቤቱ የገቢ መጠን ዕድገት ከ1965 እስከ 1 9 7 4 | |
|---|---|---|---|---|
| | | | የዕድገት መጠን በቁጥር | የዕድገት መጠን ከመቶ |
| 1 | 1965 | 32 870.43 | | |
| 2 | 1966 | 36 699.74 | | |
| 3 | 1967 | 44 260.55 | | |
| 4 | 1968 | 30 712.04 | | |
| 5 | 1969 | 39 331.24 | | |
| 6 | 1970 | 49 551.64 | | |
| 7 | 1971 | 70 978.40 | | |
| 8 | 1972 | 1 35 102.53 | | |
| 9 | 1973 | 1 42 018.88 | | |
| 10 | 1974 | 1 52 865.99 | 119 995.56 | 363%ዕድገት |

የተገኘበት ፤ ከሆሣዕና ማዘጋጃ ቤት (በጥቅምት 1975) ።

አንድ መቶ ደረሰ ። በዚህ ነገር ዛሬ በኢትዮጵያ በቀን አምስት የከፍለ ሀገር አውቶቡሶች ከአዲስ አበባ ሰውና ዕቃ ጭነው የሚሄዱበት ከተማ ሆሣዕና ብቻ ነው ።

ዛሬ በብሔራዊ ኢኮኖሚና ባህል ዘመቻ ወቅት የከምባታና ሀዲያ አውራጃን በመኪና ትራንስፖርት ከአዲስ አበባና ከሌላ አካባቢ ክፍለ ሀገራትና ከተሞች ጋር በማገናኘት ተግባር እንደዚህ ከፍተኛ ሚና በመጫወት ላይ የሚገኘው ብሔራዊ የሕዝብ ማመላለሻ ድርጅት በታህሣሥ 1971 ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቱን በሆሣዕና ከተማ ከፈተ ። ከአራት ዓመታት በኋላ በ1975 የድርጅቱ 28 አነስተኛ መኪናዎች በየቀኑ በሆሣዕናና በአውራጃ ወረዳ ከተሞችመካከል ሰዎች ጭነው ሲመላለሱ ፤ ስምንት ከፍተኛና አራት መለስተኛ ማለትም 12 አውቶቡሶች ደግሞ ሆሣዕናን በየቀኑ ሰውና ዕቃ ጭነው ከአዲስ አበባ ፤ ከቡታጅራ ፤ ከናዝሬት ፤ ከሻሸመኔና ከወላይታ ሶዶ ከተሞች ጋር ያገናኛሉ ። የድርጅቱ የሆሣዕና ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ለዚህ ደራሲ በመጋቢት 1975 ጨምሮ እንደገለፀው ፤ ብሔራዊ የሕዝብ ማመላለሻ ድርጅት በቅርብ ጊዜ ውስጥ በወልቅጤ ፤ በድሬ ዳዋ ፤ በአዋሳና በጐፋ (በሰወለ) ከተሞችና በሆሣዕና መካከል ስድስት ሌላ ከፍተኛ የሕዝብ ማመላለሻ አውቶቡሶች ለማሰማራት የተወሰነ እቅድ አለው ።

ከዚህ በላይ ከተጠቀሱ መኪናዎች ሌላ ብዛታቸው በወል የማይታወቅ ብዙ የጭነት መኪናዎች በየቀኑ ከከምባታና ሀዲያ አውራጃ ከተሞች ፤ ወረዳዎችና ገበያዎች ቀጮና ቡላ ጭምር የአውራጃውን የእርሻ ምርት ወደ አዲስ አበባና



### ሠንጠረዥ 31

**በ1975 በከምባታና ሀዲያ አውራጃ ወረዳዎችና መንገዶች ላይ በየቀኑ ሰውና ዕቃ ጭነው የሚንቀሳቀሱ የድርጅት ፤ የመንግሥትና የግል መኪናዎች ብዛት**

| ተራ ቁ. | የ መ ኪ ና ባ ለ ቤ ቶ ች | የመኪና ብዛት |
|---|---|---|
| 1 | ብሔራዊ የሕዝብ ማመላለሻ ድርጅት | 40 |
| 2 | መንግሥት | 20 |
| 3 | የሲኖዶስና የካቶሊክ ድርጅቶች | 16 |
| 4 | የገበሬ ማህበራት | 11 |
| 5 | ግለሰብ ነጋዴዎች | 10 |
| | ድ ም ር | 96 |

የተገኘበት ፤ ብሔራዊ የሕዝብ ማመላለሻ ድርጅት የሆሣዕና ቅርንጫፍ ት/ቤት ሆሣዕና (መጋቢት 1975) ፤ እንዲሁም ጉዳዩ ከሚመለከተው ድርጅቶችና መሥሪያ ቤቶች በሆሣዕና (መጋቢት 1975) ።

ሌላም አካባቢዎች ጭነው ሲሄዱ ይውላሉ ። በዚህ አኳያ ፤ ከዚህ በታች እግባብ በአለው ሥፍራና ጊዜ እንደሚታየው ፤ በ1974 የእርሻ ሰብል ገበያ ኮርፖሬሽን ብቻ ከከምባታና ሀዲያ አውራጃ ከ100,000 ኩንታል በላይ እህል ገዝቶ ወደ አዲስ አበባ ወስዶዋል ።

## 3. ለ. የኢኮኖሚና የባህል ዘመቻ በትምህርት ዘርፍ

### 3. ለ. 1. የመሠረተ ትምህርት ዘመቻ ሥምሪትና ውጤት

አንድ ታላቅ ፈላስፋ በትክክል እንደአስቀመጠው ፤ እውቀት ኃይል ነው ። በአንፃሩ የእውቀት ምንጭ የተፈጥሮ አካባቢና ልምድ ሲሆን የእውቀት መንገድና መሣሪያ ደግሞ ትምህርት ነው ። በዚህ አኳያ ፤ የወዛደር ምሁርና ፈላስፋ ሌኒን እንደአለው ያልተማረ መሃይም ሰው ከፖለቲካ ጉዳይ ውጭ ነው ። የትምህርትና የፖለቲካ ነገር ከተነሳ ፤ አብዮት ማለት በመደቦች መካከል በከፍተኛ ደረጃ የሚካሄድ የርዕዮተ ዓለም ፤ የፖለቲካና የመሣሪያ ትግል ወይም ጦርነት ነው ። በዚህ ረገድ ዛሬ አገራችን በምሥራቅ አፍሪካ የአብዮት መድረክና ደሴት ነው ።

በመሆኑም የኢትዮጵያ ሕዝብ በውስጥና በውጭ ፀረ አብዮት ኃይላትና አድሃሪያን ላይ በሁሉ ማለትም በርዕዮተ ዓለም ፣ በፖለቲካ ፤ በኢኮኖሚና በወታደራዊ መስኮች ወሳኝና ዘላቂ ድሎች በመጐናጸፍ ታላቅና ኃያል አገር እንዲ

ሠንጠረዥ 32

ከአንደኛው እስከ ስምንተኛው ዙር የመሠረተ ትምህርት ዘመቻ ከ1971—1975

| የዘመቻ ዙር | የጀማሪ ጉልማሶች ብዛት | በማጠናከሪያ ክፍል የሚማሩ | በተከታታይ ክፍል የሚማሩ | የመምራን ብዛት | የጣቢያ ብዛት | መደበኛ ት/ቤት የገቡ ጉልማሶች | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | የክፍሉ ደረጃ | የተማሪ ብዛት |
| 1ኛ ዙር | 471 053 | | | 10 502 | 2 600 | በ3ኛ. ክ. | 9732 |
| 2ኛ ዙር | 28 547 | 65 286 | 36 282 | 4 509 | 1 169 | በ4ኛ. ክ. | 3198 |
| 3ኛ ዙር | 142 450 | 223 418 | 82 387 | 16 831 | 2 440 | በ5ኛ. ክ. | 1656 |
| 4ኛ ዙር | 19 754 | 100 856 | 1 48 858 | 9 110 | 2 346 | በ6ኛ. ክ. | 340 |
| 5ኛ ዙር | 3 078 | 241 018 | 94 265 | 13 544 | 2 315 | | |
| 6ኛ ዙር | 2 242 | 114 266 | 1 09 225 | 6 543 | 1 888 | | |
| 7ኛ ዙር | 17 752 | 137 942 | 1 18 395 | 16 709 | 2 338 | | |
| 8ኛ ዙር | 8 908 | 98 063 | 97 832 | 6 851 | 2 051 | | |
| ድምር | 693 784 | 980 849 | 6 97 244 | 84 599 | 17 147 | | 14926 |

የተገኘበት ፤ የከምባታና ሀዲያ አውራጃ ከ1ኛው እስከ 8ኛው ዙር የመሠረተ ትምህርት ዘመቻ (ከዘመቻው መምሪያ ጽ/ቤት በሆሳዕና ፤ መጋቢት 1975) ።



ሆን ራሱን ሙሉ በሙሉ ከታላቁ ጠላት ከመሃይምነት ጨለማ ነፃ ማውጣት ግዴታ ነው ። ስለሆነም የኢትዮጵያ አብዮታዊ መንግሥት የኢኮኖሚና የባህል ዘመቻ አካል የሆነውን የመሠረተ ትምህርት ዘመቻን በሐምሌ 1971 በሃይምምነት ላይ ማስጀመሩን በዚህ ጥናት ከዚህ በላይ አይተናል ።

በከምባታና ሀዲያ አውራጃ በብሔራዊ መሠረተ ትምህርት ዘመቻ ፕሮግራም መሠረት ፤ በመጀመሪያው ስምንት ዙሮች በአውራጃ አቀፍ ደረጃ በብዙ መቶ ሺህ የሚቆጠሩ ጉልማሶች በ85 000 በሚቆጠሩ መምህራን አማካይነት በመሠረተ ትምህርት ዘመቻ ከመሃይምነት ጨለማ ነፃ ወጥተዋል ። ከእነዚህም ከ14 000 የሚበልጠው ጉልማሶች በመደበኛ ትምህርት ቤት ገብተው ከሦስተኛው እስከ ስድስተኛው ክፍል መድረሳቸው ታውቋል ። በተጨማሪም በከምባታና ሀዲያ አውራጃ በአራት ብሔረሰቦች ቋንቋዎች ማለትም በአማርኛ ፤ በሀዲይኛ ፤ በከምባትኛና በአዘርነት በረበርኛ (ስልጢኛ) መሠረተ ትምህርት ተዘጋጅቶዋል ።

በዚህ አኳያ በከምባታና ሀዲያ አውራጃ የመንደር ወይም መሠረተ ትምህርት የተጀመረው በአውራጃው ወንጌል አስተማሪዎች በእነአቶ ሽጉጤ ዳዳ ፤ በእነ አቶ ሱብሮ ዎሰናና በእነ አቶ አባጉሌ ኑነሞ መሪነት በኢጣሊያኖች ወረራ ጊዜ ማለትም በ1920ዎቹ ዓመታት መጨረሻ እንደነበር በዚህ ጥናት ከዚህ በላይ ተጠቅሶዋል ። በዚህ ምክንያት በ1971 ብሔራዊ የመሠረተ ትምህርት ዘመቻ በተጀመረበት ጊዜ በከምባታና ሀዲያ አውራጃ ገጠር ከመሃይምነት ጨለማ ነፃ የወጡ ጉልማሶች ቁጥር በጣም ከፍተኛ ነበር ። በዚህ ምክንያት ብሔራዊ የመሠረተ ትምህርት ዘመቻ ከተጀመረ በኋላ በአጭር ጊዜ ውስጥ በአውራጃው በሚገኙ በ406 ገበሬ ቀበሌ ማህበራት ውስጥ ሙሉ በሙሉ ዘመቻው ሊካሄድ ተችሎዋል ። በዚህ አኳያ ፤ በሀዳር 1974 የአውራጃው መኢገማ ለሸዋ መኢገማ በቀረበው ሪፖርት እንደሚለው ፤ ከከምባታና ሀዲያ አውራጃው ገበሬዎች 75 በመቶ ከመሃይምነት ነፃ ወጥተዋል ። በተጨማሪም ፤ በመጋቢት 1975 ይህ ደራሲ በሆሳዕና ከተማ እንደሰማው ፤ በዕድሜ ወይም በሌላ ምክንያት ካልሆነ በስተቀር በመሠረተ ትምህርት ዘጠነኛው ዘመቻ ዙር ማለትም በ1975 በከምባታና ሀዲያ መሠረተ ትምህርት ያልጀመረ ጉልማሳ የለም ።

## 3. ለ. 2. የመደበኛ ትምህርት ዕድገት

በከምባታና ሀዲያ አውራጃ የሚገኙ ትምህርት ቤቶች በዓይነት አራት ሲሆኑ እነርሱም የመንግሥት ፤ የሕዝብ ፤ የሚሲዮንና የቤተ ክህነት ናቸው ። በአብዮቱ መባቻ ማለትም በ1965 በእነዚህ ትምህርት ቤቶች በድምሩ 23 664 ተማሪዎችና 530 አስተማሪዎች ነበሩ ። ከአሥር ዓመታት በኋላ በ1975 በእነዚህ ትምህርት ቤቶች የሚገኙ የተማሪዎችና የአስተማሪዎች ብዛት በእምርታ በማደግ በቅደም ተከተል ወደ 151,095 እና 2050 መድረሱን በሚከተለው ሠንጠረዥ ውስጥ ማየት ይቻላል ።

በከምባታና ሀዲያ አውራጃ የትምህርት ጉዳይ ለመንግሥትና ለሕዝብ የጋራ ተግባርና ኃላፊነት ነው ። ይህንን በትክክል በማወቅ የአውራጃው ሕዝብ በተለይም የአርሶ አደሩ ክፍል ከአብዮታዊ መንግሥት ጎን ተሰልፎ በራሱ ጉልበትና ገንዘብ በተወሰኑ ቀበሌዎች ክልል ውስጥ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች

እየሠራ የአስተማሪዎቹንም ደሞዝ እርሱ ራሱ እየከፈለ ልጆቹን ያስተምራል ። በዚህ አንፃርና ተግባር ለምሳሌ ከዚህ በታች በሠንጠረዥ 33 እንደሚታየው ፣ በ1975 በከምባታና ሀዲያ አውራጃ ከሚገኙ 277 ትምህርት ቤቶች 103 ፣ ከ151095 ተማሪዎች 47,603 ፣ ከ2050 አስተማሪዎችና ደግሞ 1071 የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ፣ ተማሪዎችና አስተማሪዎች መሆናቸው ለዚህ አባባል በቂ ማስረጃ ነው ። በአውራጃው ውስጥ በትምህርት መስክ ይህንን የመሰለ ሕዝባዊ ተሳትፎ በሚመለከት ፣ በህዳር 1974 የከምባታና ሀዲያ አውራጃ መኢገማ ለሸዋ መኢገማ ያቀረበው ሪፖርት እንዲህ ይላል ። በአውራጃው ገበሬ ሪፖርት አባባል ፣[2]

"አብዮታዊ ምሁር ቭላድሚር ኢሊይች ሌኒን እንዳለ ሁሉ ያልተማረ ሕዝብ ከፖለቲካ ውጭ ነው ። ስለዚህ ኅብረተሰቡ የቴክኖሎጂን ጥበብ እንቢቦና ተረድቶ ራሱን ለማሻሻል የማይምነትን ጨለማ በመሠረተ ትምህርት ዘመቻ መቀጠል ጀምሮአል ። በአለፉት ሦስት ዓመታት ውስጥ በተካሄዱ አምስት የመሠረተ ትምህርት ዘመቻ ዙሮች የተማረው በማስተማር ያልተማረውም በመማር ፣ የመኖሪያ ቤቱን ትምህርት ቤት በማድረግ የዘመቻው ግብ እንዲፋጠን ከፍተኛ ጥረት አድርጓል ። በዚህ አኳያ በ1973 ዓ.ም. ማይምነትን ጨርሶ ከአውራጃችን ለማውደም የገባነውን ቃልኪዳን ተግባራዊ በማድረግ ላይ እንገኛለን ። በዚህም አንፃር ከ1ኛው እስከ 4ኛው ዙር ብቻ ለትምህርት ከተመዘገቡት 1 321 409 ማይማን ጉልማሶች መካከል 520 842 በፈተና አልፈዋል ። በ5ኛው ዙር የመሠረተ ትምህርት ዘመቻ በሬት በፈተና ያላለፉት ሙሉ ትምህርታቸውን በመከታተል ከማይምነት ለመላቀቅ ችለዋል ። አሁን በአውራጃችን ከሚገኙ እርሶ አደሮች ሁለት ሦስተኛ ወይም 75 በመቶ በመደበኛ ትምህርት ቤት ገብተው በመማር ላይ ይገኛሉ ።

"በአውራጃው ከሚገኙት ትምህርት ቤቶች ውስጥ ደግሞ 116ቱ በሕዝብ የተሠሩ ሲሆኑ ፣ በእነዚህ ትምህርት ቤቶች ከሕዝብ ደመወዝ የሚከፈላቸው መምህራን ብዛት 885 ነው ። የሚከፈላቸውም ደመወዝ በወር ብር 53100 (አምሳ ሦስት ሺህ አንድ መቶ ብር) ፣ በዓመት ብር 538000 (አምስት መቶ ሠላሳ አንድ ሺህ ብር) ነው ።

"እስከ አሁን በአውራጃው አራት ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ቢኖሩም በአውራጃው በሚደረገው መንጓጓ ተማሪዎች በማደሪያ ቤት ወላጆችም ስንቅ በማቀበል በኩል ችግር ስለደረሰባቸው አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እንዲሠራላቸው ተፈላጊውን ገንዘብ አዋጥተው በባንክ ገቢ ከአደረጉ በኋላ ፈቃድ አግኝተው ሥራውን ለመጀመር ትግል እያደረጉ ናቸው ።

"ከላይ ስለመሠረተ ትምህርት ሲጠቀስ የቀረ ነገር ቢኖር ከማይምነት የተላቀቁ ትምህርታቸውን ተመልሰው እንዳይረሱ ለማድረግ እስከሁን ድረስ 338 ንባብ ቤቶች ተቋቁመዋል ። በእነዚህም ንባብ ቤቶች የመርቶ አደር ጋዜጣን ፣ የመስከረምና የየካቲት መጽሔቶችንና ሌላም ልዩ ልዩ

2 ከምባታና ሀዲያ አውራጃ መኢገማ ለሸዋ ክፍለ ሀገር መኢገማ በህዳር 8 ቀን 1974 ካቀረበው ሪፖርት የተወሰደ ምንባብ ።



ሠንጠረዥ 33

የትምህርት ቤቶች ፣ የተማሪዎችና የአስተማሪዎች ዕድገት ከ1965 እስከ 1975

| ዓመት | የትምህርት ቤቶች ዓይነትና ብዛት* | | | | | የተማሪዎች ዓይነትና ብዛት | | | | | የአስተማሪዎች ዓይነትና ብዛት | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | መንግሥት | ሕዝብ | ሚሲዮን | ቤተ ክህነት | ድምር | መንግሥት | ሕዝብ | ሚሲዮን | ቤተ ክህነት | ድምር | መንግሥት | ሕዝብ | ሚሲዮን | ቤተ ክህነት | ድምር |
| 1965 | 29 | 40 | 15 | 1 | 85 | 8991 | 10262 | 4035 | 376 | 23664 | 165 | 247 | 112 | 6 | 530 |
| 1966 | 28 | 60 | 19 | 1 | 108 | 12410 | 13886 | 4471 | 393 | 31160 | 210 | 338 | 119 | 6 | 673 |
| 1967 | 44 | 43 | 19 | 1 | 107 | 13097 | 12688 | 3592 | 350 | 29727 | 191 | 321 | 80 | 4 | 596 |
| 1968 | 57 | 161 | 23 | 1 | 198 | 21482 | 48939 | 3817 | 206 | 74588 | 215 | 445 | 70 | 7 | 737 |
| 1969 | 96 | 188 | 35 | 1 | 293 | 29255 | 42823 | 5637 | 255 | 77923 | 501 | 846 | 141 | 5 | 1493 |
| 1970 | 98 | 168 | 20 | 1 | 307 | 39637 | 48860 | 4414 | 409 | 93166 | 709 | 868 | 109 | 9 | 1695 |
| 1971 | 99 | 116 | 21 | 1 | 289 | 40804 | 29071 | 4706 | 324 | 74991 | 687 | 522 | 101 | 10 | 1320 |
| 1972 | 111 | 116 | 19 | 1 | 247 | 52715 | 30511 | 4450 | 350 | 88010 | 645 | 857 | 95 | 7 | 1604 |
| 1973 | 123 | 116 | 19 | 1 | 259 | 74142 | 40544 | 4680 | 283 | 121449 | 639 | 885 | 96 | 6 | 1625 |
| 1974 | 139 | 106 | 19 | 1 | 265 | 90724 | 46635 | 6110 | 236 | 145746 | 727 | 1184 | 135 | 5 | 2055 |
| 1975 | 154 | 103 | 19 | 1 | 277 | 97007 | 47603 | 6003 | 238 | 151095 | 862 | 1071 | 102 | 7 | 2050 |

የዕድገት ደረጃ ፣ 1. የትምህርት ቤቶች ዕድገት ከ1965 እስከ 1975 ፣ በቁጥር 277—85 = 192 ት/ቤቶች ፣ ከመቶ 226 %
2. የተማሪዎች ዕድገት ከ1965 እስከ 1975 በቁጥር 15095—23664 127,431 ፣ ከመቶ 539 %
3. የአስተማሪዎች ዕድገት ከ1965 እስከ 1975 በቁጥር 2050—530 = 1,520 ፣ ከመቶ 287 %

የተገኘበት ፣ ከከምባታና ሀዲያ አውራጃ ትምህርት ቤቶች ጽሕፈት ቤት (በመጋቢት 1975) በትንተና ።

* ከምባታና ሀዲያ አውራጃ በተጨማሪም ከ240 በላይ ሕጻናት የሚገኙባቸው ሁለት አጸደ ሕጻናት ይገኛሉ ።

ተራማጅ መጽሔቶች በማናር እያነበቡ አእምሮአቸውን እንዲያድሱ አብዮታዊ ትምህርት ተሰጥቶአቸዋል ።

በከምባታና ሀዲያ አውራጃ በብሔራዊ ኢኮኖሚና ባህል ዕድገት ዘመቻ መሠረትና መርሆ የሚካሄደው የትምህርት እንቅስቃሴ ምንም ደህና የዕድገት ፈር የያዘ ሆኖ ለተመልካች ቢታይ ቀረብ ብሎ ከጥናትና ምርምር አንፃር ለሚመለከተው ሰው ሁለት የጥራትና የአስተዳደር ችግሮች አሉት ። ከዚህ በላይ ሠንጠረዥ 33 እንደተገለፀው ፤ በከምባታና ሀዲያ አውራጃ በ1975 ፤ ከ277 ትምህርት ቤቶች 103 ፤ ከ151095 ተማሪዎች 47 602 ፤ ከ2050 አስተማሪዎች ደግሞ 8078 የሕዝብ ናቸው ። እነዚህ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ከድርጅት ፤ ከመማሪያና ከትምህርት አንፃር ከፍተኛ የሆነ የጥራት ጉድለት እንደአለ ፤ ይህ ደራሲ በአውራጃው ወረዳዎች እየተዘዋወረ ይህንን ጥናት በሚያካሂድበት ጊዜ ብዙ የሕዝብ ትምህርት ቤቶችን በማየት ለማወቅ ችሎዋል ። ስለዚህ ለእነዚህ ትምህርት ቤቶች ከሕዝቡ የሚሰጣቸው ሁለገብ እርዳታ የተጠበቀ ሆኖ ትምህርት ቤቶቹ በመንግሥት ቁጥጥር ሥር እንዲሆኑ ማድረግ የትምህርት ቤቶቹን የጥራት ችግር ለማቃለል ይረዳል ።

ሠንጠረዥ 34

በ1975 በሸዋ አውራጃዎች የ6ኛና የ8ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና የሚፈተኑ ተማሪዎች ብዛት

| አውራጃ | የ6ኛ ክፍል ፈተና የሚፈተኑ ተማሪዎች ብዛት | የ8ኛ ክፍል ፈተና የሚፈተኑ ተማሪዎች ብዛት |
|---|---|---|
| ከምባታና ሀዲያ | 13 655 | 9766 |
| የረርና ከረዩ | 7 897 | 6896 |
| ጨቦና ጉራጌ | 6 528 | 4590 |
| ሐይቆችና ቡታጅራ | 5 821 | 4387 |
| ጅባትና ሜጫ | 5 703 | 3976 |
| መናገሻ | 4 339 | 3478 |
| ሰላሌ | 2 256 | 1688 |
| ተጉለት | 1 733 | 1698 |
| መንዝና ግሼ | 1 336 | 768 |
| ይፋትና ጥሙጋ | 1 070 | 985 |
| መረሐቤቴ | 718 | 626 |
| ድምር | 51 056 | 38858 |

የተገኘበት ፤ ከሸዋ ትምህርት ቤቶች ጽሕፈት ቤት በጥር 30 ቀን 1975 በቁጥር ሸዋ 4/3 145534/404/16 ለከምባታና ሀዲያ አውራጃ ትምህርት ቤቶች ጽሕፈት ቤት ከሸኚ ደብዳቤ ጋር የተላከው ደብዳቤ ።



በአንድ ወይም በሌላ መንገድ ይህ በከምባታና ሀዲያ አውራጃ በግልጽ የሚታየው የትምህርት ጥራት ችግር በአገር ደረጃ ባይሆን እንኳ በሸዋ ክፍለ ሀገር ደረጃ በትምህርት ይዘትና ሂደት ላይ ተጽዕኖ ሊያደርስ ይችላል ። ምክንያቱም ከዚህ በላይ የክፍለ ሀገሩ የአንደኛውና የመለስተኛ ሁለተኛው ደረጃ ተማሪዎች ዘገባ ሠንጠረዥ እንደሚያሳየን ፤ በሸዋ አውራጃዎች መካከል በተማሪዎች ብዛት የመጀመሪያውን ደረጃ የያዘው የከምባታና ሀዲያ አውራጃ ነው ።

ትምህርትን በሚመለከት በከምባታና ሀዲያ አውራጃ ሁለተኛው ወቅታዊ ችግር በአውራጃው ወረዳዎች የትምህርት ቤቶች መብዛትና የአስተዳደር ክፍል ሠራተኞች ማነስ ያስከተለው ሁኔታ ነው ። ይህንን ችግር ለማቃለል የአውራጃው የትምህርት ቤቶች አስተዳደር የወረዳ ትምህርት ቤቶችን ከዚህ እንደሚከተለው በስምንት ቀጠናዎችና በ28 ዞኖች በመከፋፈል ሁኔታውን በቁጥጥር ሥር ለማዋል የሚያስመሰግን ጥረት አድርጐዋል ። ነገር ግን ለችግሩ ዘላቂ መፍትሔ የአውራጃውን አጠቃላይ የትምህርት ይዘትና ሂደት በድርጅትና በሰው ኃይል ማጠናከር ይሆናል ። ይህንን ሊያደርግ የሚችለው ደግሞ የአውራጃ ትምህርት ቤቶች አስተዳደር ሳይሆን ከላይ አግባብና አላፊነት ያለው የመንግሥት አካል ነው ።

ሠንጠረዥ 35

በ1975 የከምባታና ሀዲያ አውራጃ ወረዳዎች የትምህርት ቤት ቀጠናዎች ዞኖች

| ተራ ቁ. | ወረዳ | የትምህርት ቀጠና ብዛት | የትምህርት ዞኖች ብዛት | የትምህርት ቤቶች ብዛት | የተማሪዎች ብዛት |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ኮንተብ | 1 | 6 | 59 | 28 047 |
| 2 | ሊሙ | 1 | 7 | 39 | 26 756 |
| 3 | ጥምባሮ | 1 | 3 | 35 | 23 926 |
| 4. | አንጋጫ | 1 | 3 | 33 | 18 336 |
| 5 | ቀዲዳ ጋሚላ | 1 | 3 | 33 | 16 778 |
| 6 | ሲቄ | 1 | 3 | 26 | 15 193 |
| 7 | ቃጫ ቢራ | 1 | 1 | 13 | 12 891 |
| 8 | አም ሸለቆ | 1 | 1 | 22 | 9 171 |
| | ድምር 8ወረዳዎች | 8 ቀጠናዎች | 28 ዞኖች | 268 ት/ ቤቶችና 2 አፀደ ሕፃናት=270 | 151 095 ተማሪዎች |

የተገኘበት ፤ ከከምባታና ሀዲያ አውራጃ ትምህርት ቤቶች ጽሕፈት ቤት (መጋቢት 1975)

## 3፡ ሐ. የምርትና የመንግሥት ገንዘብ ገቢ ዕድገት

### 3. ሐ. 1. የእርሻ ምርት ዕድገትና ስርጭት

የከምባታና ሀዲያ አውራጃ እስከ ዛሬ የኢንዱስትሪ ድርጅት ለጓይንትም የማይገኝበት የኢትዮጵያ አንድ ኋላ ቀር ገጠር ስለሆነ ፤ በዚህ ጥናት የምርት ዕድገትና ስርጭት ሲባል ስለ እርሻ ማለትም ስለገበሬ ምርት ነው ። ይህም የምርት ሁኔታ በተጨባጭ የታየው በገበያ ሚዛን ላይ በተለይም ከ1972 ወዲህ የእርሻ ሀሰብል ገበያ ኮርፖሬሽን በሆሣዕና ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቱ አማካይነት ከከምባታና ሀዲያ አውራጃ በየዓመቱ በሚገዛው በከፍተኛ እህል መጠንና እንዲሁም ከአውራጃው በየዓመቱ ለማዕከላዊ መንግሥት በግብር በሚሰበሰበው ከፍተኛ ገንዘብ መጠን ነው ።

በድህረ ጦርነት ማለትም ከኢጣሊያኖች ወረራ በኋላ የወደቀው አድኃሪ የጕልተኛው መንግሥትና ባለሥልጣኖች በአስከተሉት በመሬት ችግር ምክንያት ብዙ የከምባታና ሀዲያ አውራጃ ሰዎች በስደት በብዙ ከተሞችና ከፍለ ሀገራት እንደተበታተኑ በዚህ ጥናት ከዚህ በላይ በአጭሩ አይተናል ። በቅድመ አብዮት ይህ የመሬት ችግር ፤ ባአንድ በኩል አምራቹን ገበሬ ከአውራጃው በማባረር ፤ በሌላ በኩል ደግሞ የአውራጃውን ለም መሬት በማያመርተው ጕልተኛ እጅና ሥር በማስገባት በአብዮቱ ዋዜማ በከምባታና ሀዲያ አውራጃ የምርት ውድቀት ብሎም በ1964—1966 አካባቢ መጠነኛ የሆነ የረሀብ ችግር አስከትሎ ነበር ። ይህ ሁኔታ በኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮትና በታላቁ በየካቲት 25 ቀን 1967 በገጠር መሬት አዋጅ በመለወጡ ፤ በ1966—1971 በተካሄደው በወሳኝ መደብ ፍልሚያ ከአውራጃው ቀንደኛ የሆኑ ፀረ አብዮት ድርጅቶችና ኃይላት በመደምሰሳቸውና የብሔራዊው የኢኮኖሚና የባህል ዘመቻ በመታወጁ በከምባታና ሀዲያ አውራጃ ለአርሶ አደሩ ምርት ዕድገት አዲስ ሁኔታና ምዕራፍ ተከፈተ ። በመሆኑም ከ1971 ወዲህ የአውራጃው ዋና አምራች ኃይል የሆነው ገበሬ በብርቱ ጥረት በጠባብ መሬቱ ላይ በአውራጃው ለሚገኙ በ2 500 000 ለሚቆጠሩ ነዋሪዎችና ከ2 300 000 በላይ ለሚገመቱ ለቤት እንስሳት ለመኖር ከሚያስፈልጋቸው በላይ በማምረት ፤ ከዚህ የሚከተሉ ሠንጠረዦች እንደሚያስዩ ፤ በቀላል የማይገመት የእህልና የቡር ምርት ለአገር ገበያ ለማቅረብ ችሎዋል ።

### 3. ሐ. 2. የመንግሥት ገንዘብ ገቢ ዕድገት

በአለፈው አድኃሪ ዘመንና ሥርዓት የመሬትና የገበሬ ምርት ወደ ግለሰብ ጕልተኞችና ባለሥልጣኖች እጅ በመግባቱ ፤ የወደቀው የጕልተኛ መንግሥት ከአገሩ ሰፊ መሬትና ገበሬ በልዩ ልዩ ግብር ስም በአንድ በተወሰነ ግብር ዓመት ለመንግሥት ግምጃ ቤት በድምር ከ42 590 000 ብር ገቢ በላይ ለመሰብሰብ አለመቻሉን በዚህ ጥናት ከዚህ በላይ አይተናል ። በዚህ አኳኋ ለምሳሌ በ1965 ከከምባታና ሀዲያ አውራጃ ከመሬት ግብር በቀጥታ ለአድኃሪው መንግሥት የተሰበሰበው የዓመቱ ገቢ መጠን 768 832.74 ብር ሲሆን በልዩ ልዩ ግብር ከአውራጃው ለመንግሥት የገባው የጠቅላላ ገንዘብ መጠን ደግሞ ከ1,130,000 ብር ያነሰ ነበር ። ከአብዮቱ ፍንዳታ ወዲህ የአውራጃው ምርት በመጠን በማ



ሠንጠረዥ 36

ከከምባታና ሀዲያ አውራጃ የእርሻ ሰብል ገበያ ኮርፖሬሽን ከ1972 እስከ 1975 መጀመሪያ የገዛው የእህል መጠን በኩንታል ።

| ተራ ቁ. | የገበያ ዓመት | የተገዛ እህል መጠን ኩንታል | ለእህሉ የተከፈለ ዋጋ በብር | የምርት ዕድገት ከ1972 እስከ 1974 በኩንታልና ከመቶ | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | | በኩንታል | ከመቶ |
| 1 | 1972 | 55 885.56 | ? | 52 888.44 | 95 |
| 2 | 1973 | 71 233.28 | 2 316 661 77 | | |
| 3 | 1974 | 108 774.16 | (በክፊል) | | |
| 4 | 1975—የተማሸ ዓመት | 60 104.63 እስከ መጋቢት ብቻ | 3 598 309.20 ? | | |
| | ድ ር ም | 295 997.57 ኩ ን ታ ል | 5 598 309.20 በ ክ ፊ ል | 52 888.44 ኩ ን ታ ል | 95 % |

የተገኘበት ፤ ከእርሻ ገበያ ኮርፖሬሽን ፣ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት (መጋቢት 1975)።

ሠንጠረዥ 37

ከከምባታና ሀዲያ አውራጃ ከ1968 እስከ 1975 መጀመሪያ ለማዕከላዊ ቡና ገበና የቀረበ ቡና በቶንና በኩንታል

| ተራ ቁ. | የገበያ ዓመት | ለገበያ የቀረበ ቡና በቶንና በኩንታል | | የምርት ዕድገት ከ1968 እስከ 1975 | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በ ቶ ን | በኩንታል | በቶን | በኩንታል | ከመቶ |
| 1 | 1968 | 1 559 | 15 590 | | | |
| 2 | 1969 | 2 756 | 27 560 | | | |
| 3 | 1970 | 3 019 | 30 190 | | | |
| 4 | 1971 | 2 176 | 21 760 | | | |
| 5 | 1972 | 3 682 | 36 820 | | | |
| 6 | 1973 | 2 161 | 21 610 | | | |
| 7 | 1974 | 2 096 | 20 960 | | | |
| 8 | 1974 | እስከ መጋቢት 16 ቀን | | | | |
| 9 | 1975 | 2 935 | 29 350 | 1376 | 13760 | 88 |
| | ድምር | እስከ መጋቢት 16 ቀን 20 384 ቶ ን | 203 840 ኩንታል | 1376 ቶን | 13760 ኩንታል | 88 % |

የተገኘበት ፤ በከምባታና ሀዲያ አውራጃ ቡናና ሻይ ልማት ሚኒስቴር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ሆሳዕና (መጋቢት 1975) ።



ሠንጠረዥ 38

በከምባታና ሀዲያ አውራጃ የመሬት ግብር ገቢ ሁኔታ በ1965 እና በ1974 በብር

| ተራ ቁ. | የግብር ዓመት | የተለያዩ የግብር ዓይነቶች | | | | ድ ም ር | የዕድገት መጠን ከ1965 እስከ 1974 በቁጥርና ከመቶ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የመሬትና የእርሻ ግ. | የገቢ. ግ. | የሥራ. ግ. | ሌ ሎ ች | | በገንዘብ | ከመቶ |
| 1 | 1965 | 768832.74 | 8892.04 | 48719.51 | 302778.12 | 1129222.41 | 1. የመሬት ግብር ገቢ፣ | |
| 2 | 1966 | 602621.66 | 2979.01 | 64840.82 | 251744.45 | 922186.03 | | |
| 3 | 1967 | 239664.66 | 15892.42 | 78963.84 | 151918.43 | 486439.35 | 3283866.26 | 426/% |
| 4 | 1968 | 754399.91 | 22656.17 | 88296.99 | 186686.90 | 1052039.97 | 2. ጠቅላላ የከምባታ የግብር ገቢ | |
| 5 | 1969 | 867226.00 | 43143.15 | 124073.95 | 157242.66 | 1191685.76 | | |
| 6 | 1970 | 1456041.00 | 44309.08 | 152435.75 | 300377.91 | 1953163.74 | | |
| 7 | 1971 | 4945095.00 | 125332.41 | 232444.28 | 336339.31 | 5639211.00 | 4061424.21 | 360/% |
| 8 | 1972 | 4314590.53 | 279800.08 | 222386.06 | 411062.83 | 5227839.50 | | |
| 9 | 1973 | 4052699.00 | 351413.70 | 281257.04 | 490351.71 | 5175721.45 | | |
| 10 | 1974 | 4044286.00 | 259921.35 | 319701.09 | 566738.18 | 5190646.62 | | |
| | ድምር | 22045456.50 | 1154339.41 | 1613119.33 | 3155240.50 | 27968155.83 | | |

1. ከመሬትና ከእርሻ ሥራ ግብር ገቢ በ1965 768,832.74 ብር ።
ከመሬትና ከእርሻ ሥራ ግብር ገቢ በ1974 4,052,6799.00 ብር ።
የመሬትና የእርሻ ሥራ ገቢ ዕድገት በ1974 በገንዘብ 3,283,866.26 ፤
ከመቶ 426

2. የከምባታና ሀዲያ አውራጃ ጠቅላላ የግብር ገቢ በ1965 1,129,222.41 ብር።
የከምባታና ሀዲያ አውራጃ ጠቅላላ የግብር ገቢ በ1974 5,190,646.62 ብር
የከምባታና ሀዲያ አውራጃ ጠቅላላ የግብር ገቢ በ1974 በገንዘብ
4,061,424.21 ከመቶ 360

የተገኘበት ፤ በከምባታና ሀዲያ አውራጃ የገንዘብ ሚኒስቴር ተወካይ ጽሕፈት ቤት በሆሳዕና (መጋቢት 1975) ።

ደት ብሎም አዲስና ትክክለኛ የሆነ የግብር ሥርዓትና አሠራር በመቀየሱ በከምባታና ሀዲያ አውራጃ በዓመት ለመንግሥት የሚገባው የገንዘብ መጠን በከፍተኛ ደረጃ ማደግ ጀምሮዋል ። በዚህ አንፃር ለምሳሌ በ1974 በአውራጃ ከመሬትና ከእርሻ ሥራ ግብር ለመንግሥት የተሰበሰበው የገንዘብ ገቢ መጠን ከ4 000 000 ብር በላይ ሲሆን ከአውራጃው በአጠቃላይ የተሰበሰበው የግብር ገንዘብ ገቢ መጠን ደግሞ ከ5 000 000 ብር በላይ ሆኖዋል ። ከዚህ በላይ ሠንጠረዥ 38 በዝርዝር እንደሚያሳየው ፤ አሁን ከከምባታና ሀዲያ አውራጃው ፤ ከ1965 ገቢ መጠን ጋር ሲመዛዘን ፤ ለመንግሥት ከመሬት የሚገኘው የገንዘብ ገቢ በ426 ፐርሰንት ሲያድግ ከአውራጃው ከልዩ ልዩ ግብር ምንጮች የሚገኘው አጠቃላይ ገቢ ደግሞ በ360 ፐርሰንት በማደግ አውራጃው በምርትና በአገልግሎት በድህረ አብዮት ከቅድመ አብዮት በበለጠ ምርታማ መሆኑን አሳይቶዋል ።

## 4. የሆሣዕና ሆስፒታል ፤ የሕዝብና የአብዮታዊ መንግሥት ትብብር ውጤትና ምሳሌ

### 4. ሀ. የሕዝብ እቅድና ጅምር

የአንድ ግለሰብ ወይም ሕብረተሰብ የጤና ጥያቄ ከትምህርትና ከኢኮኖሚ ጥያቄዎች ተለይቶ አይታይም ። በዚህ አኳያ ለምሳሌ በአለፈው ጨለማ ዘመን በከምባታና ሀዲያ አውራጃ ለሕብረተሰቡ የሀልውናው ፤ የሕሊናና የሀብት መሠረትና ምንጭ የሆነው መሬት በጉልተኛው መንግሥትና መደብ በመያዙ ትምህርት ለምርትና ለባህል ዕድገት ተግባራዊ ማለትም የሳይንስና የቴክኖሎጂ መሣሪያ ሊሆን አልቻለም ። እንዲያውም ከሁሉ በፊት ራሱ በሽታና በሽተኛ የነበረው የጉልተኛ ሥርዓትና መንግሥት መላውን የኢትዮጵያ ሕብረተሰብ እንደአደረገው ሁሉ የከምባታና ሀዲያ አውራጃ ሕዝብንም ለበሽታና ለሞት አደጋ አጋልጦት እንደኖረ በአገሩ የነበረው ዝቅተኛ የሕክምና ባለሙያዎችና የጤና ተቋሞች ቁጥር እንደሚከተለው በተጨባጭ ያሳያሉ ።

ከዚህ በታች በሠንጠረዥ 39 ውስጥ በተጨባጭ እንደሚታየው ፤ ዛሬም በድህረ አብዮት እንኳን በ2 500 000 የሚቆጠር ሕዝብ በሚኖርበት በከምባታና ሀዲያ አውራጃ ያለው አንድ ዋና የሕክምና ድርጅት ከአንድ ሚሲዮናዊ ድርጅት የተወረሰና ሦስት ሐኪሞች የሚገኙበት አንድ ባለ 35 አልጋ ሆስፒታል ነው ። እንደዚሁ ለበሽታ አደጋ የተጋለጠው የከምባታና ሀዲያ አውራጃው ሕዝብ በአብዮታዊ መንግሥት በጥቅምት 1971 የታወጀው የኢኮኖሚና የባህል ዘመቻ የፈጠረለትን አመቺ ሁኔታና ዕድል እንደሚገ ው በመጠቀም ፤ በአውራጃው ርዕሰ ከተማ በሆሣዕና ለራሱ ብቻ ሳይሆን ለብዙ አካባቢው ሕዝቦች ፤ ማለትም ለደቡብ ሸዋ ፤ ለአርሲ ፤ ለባሌ ፤ ለሲዳሞ ፤ ለጋሞጎፋና ለከፋ ክፍለ ሀገራት ጭምር የትምህርትና የሕክምና አገልግሎት ሊሰጥ የሚችል አንድ ዘመናዊ ባለ 250 አልጋ ሆስፒታል በ2 000 000 ብር ወጭ ለመሥራት በጥር 1971 በአውራጃ ኢኮኖሚና ባህል ዘመቻ ኮሚቴ ደረጃ ወሰነ ።



ሠንጠረዥ 39

በ1970 በኢትዮጵያና ክፍለ ሀገራትና በከምባታና ሀዲያ አውራጃ የሕዝብ ብዛት ፤ የጤና ተቋሞችና አገልግሎት

| ተራ ቁ. | ክፍለ ሀገራት | የሕዝብ ብዛት በ1972 | የሆስፒታል ብዛት | የአልጋ ብዛት | ክሊኒክ ብዛት | የጤና ጣቢያ ብዛት | የሐኪም ብዛት | ጤና መኮንን ብዛት | የነርስ ብዛት | የጤና ረዳት ብዛት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1. | ሸዋ | 6000000 | 10 | 590 | 150 | 16 | 16 | 28 | 184 | 680 |
| 2. | ወሎ | 4000000 | 5 | 189 | 90 | 13 | 13 | 16 | 44 | 346 |
| 3. | ሲዳሞ | 4000000 | 5 | 419 | 131 | 8 | 16 | 12 | 31 | 422 |
| 4. | ሐረርጌ | 3102100 | 12 | 828 | 102 | 13 | 47 | 20 | 119 | 303 |
| 5. | ጎንደር | 3000000 | 2 | 330 | 74 | 12 | 17 | 28 | 75 | 229 |
| 6. | ከምባታና ሀዲያ | 2540600 | 1 | 35 | 10 | 2 | 3 | 2 | 12 | 24 |
| 7. | ትግራይ | 2192628 | 4 | 410 | 72 | 9 | 19 | 15 | 57 | 172 |
| 8. | ጎጃም | 2023100 | 3 | 242 | 76 | 7 | 16 | 20 | 55 | 215 |
| 9. | ወለጋ | 2004700 | 4 | 297 | 98 | 7 | 14 | 13 | 52 | 339 |
| 10. | ኤርትራ | 2080000 | 17 | 2324 | 112 | 3 | 43 | 14 | 178 | 526 |
| 11. | አርሲ | 1300000 | 2 | 121 | 48 | 4 | 5 | 13 | 30 | 192 |
| 12. | አዲስ አበባ | 1200000 | 14 | 2499 | 28 | — | 283 | 105 | 820 | — |
| 13. | ከፋ | 1064249 | 3 | 230 | 94 | 7 | 16 | 14 | 37 | 227 |
| 14. | ጋሞ ጎፋ | 993200 | 3 | 137 | 64 | 4 | 4 | 7 | 16 | 129 |
| 15. | ባሌ | 870200 | 11 | 97 | 36 | 4 | 9 | 6 | 14 | 102 |
| 16. | ኢሉባቦር | 814439 | 2 | 163 | 62 | 5 | 12 | 8 | 35 | 203 |
| | ድምር | 34644816 | 87 | 8874 | 1237 | 112 | 530 | 316 | 1667 | 4055 |

የተገኘበት ፤ 1. "በየክፍለ ሀገሩ የሚገኙ የሕክምናና የጤና አገልግሎት ድርጅቶች የፖሊስና የጦር ሠራዊቶችን አይጨምርም" (1970) ፤ ዓመታዊ የስታቲስቲክስ መጽሔት (1970/1972) ገጽ 222 ።

2. የልደ ጥበባት ኤክስፖ 1973 (አዲስ አበባ መስከረም 1973) ።

3. ከከምባታና ሀዲያ አውራጃ ጥናት በፆፊሲው (በበጋ 1972) ።

4. በሠንጠረዡ ውስጥ የመለየልባቸው የጤና ተቋሞችና አገልግሎት አልተጨመሩም ።

ማስገንዘቢያ ፤ በሠንጠረዡ ውስጥ የሕዝብ ብዛትንና የሕክምና ተቋሞችን ሚዛን በንጽጽር ለማሳየት በስድስተኛው ተራ ቁጥር ስለከምባታና ሀዲያ አውራጃ ሕዝብ የተረው ግለረጃዎች በአንደኛው ተራ ቁጥር በሸዋ ክፍለ ሀገር ግለረጃዎች ውስጥ የቀረው ስለሆነ በመጨረሻው በሕዝብ አጠቃላይ ድምር ውስጥ አልተጨመሩም ።

በዚህ አብዮታዊ ውሳኔ መሠረት ፤ በሚከተለው ሠንጠረዥ እንደሚታየው ከጥር 28 ቀን 1971 እስከ መጋቢት 30 ቀን 1971 ድረስ በሁለት ወራት ውስጥ የሆሣዕና ከተማን ጭምር የአውራጃው ዘጠኝ ወረዳዎች ለሆስፒታል ሕንፃ ማሠሪያ የሚያስፈልገውን 2 000 000 ብር በፍጥነት አዋጥተው ወደ ሆሣዕና ንግድ ባንክ አስገቡ ። ሕዝብ ራሱን በራሱ ለመርዳት ትልቅ ውስጣዊ ኃይልና ግፊት ስለአለው ከአውራጃው ለሆስፒታሉ ሕንፃ ማሠሪያ የተዋጣው ገንዘብ በትንሽ ጊዜ ውስጥ ከታሰበው በላይ በመሄድ ወደ 2 500 000 ብር ደረሰ ።

ሠንጠረዥ 40

በ1971 ለሆሣዕና ሆስፒታል ሕንፃ ማሠሪያ ገንዘብ ለማዋጣት የከምባታና ሀዲያ አውራጃ ሕዝብ ያካሄደው ዘመቻ

| ተራ ቁ. | ወረዳ | የቀበሌ ብዛት በወረዳ | የእያንዳንዱ ወረዳ መዋጮ ገንዘብ በ ብ ር | ጠቅላላ ድምር በብር |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ኮንተብ | 93 | 4600 93 | 427 800 |
| 2 | ሊሙ | 74 | 4600 74 | 340 400 |
| 3 | ጥምባሮ | 65 | 4600 65 | 299 000 |
| 4 | ሲቄ | 45 | 4600 45 | 207 600 |
| 5 | አንጋጫ | 39 | 4600 39 | 179 400 |
| 6 | ቀዲዳ ጋሜላ | 38 | 4600 38 | 174 000 |
| 7 | ቃጫ ቢራ | 31 | 4600 31 | 142 600 |
| 8 | አሞ ሸለቆ | 25 | 4600 25 | 115 000 |
| 9 | ሆሣዕና | 25 | 4600 25 | 115 000 |
| | ድ ም ር | | | 2 001 000 |

የተገኘበት ፤ ከከምባታና ሀዲያ አውራጃ አስተዳደር ጽሕፈት ቤት ፤ ሆሣዕና (ሰኔ 1972) ።

በተጨማሪም በከምባታና ሀዲያ አውራጃ ለብዙ ጊዜ በትምህርትና በሕክምና መስኮች ማህበራዊ አገልግሎት ሲያበረክቱ የኖሩ ሁለት የግል ድርጅቶች ማለትም የማዕከላዊ ደቡብ ሲኖዶስና የካቶሊክ ሚሽን አሁን የአውራጃው ሕዝብ ራሱን በራሱ በመርዳት ፖሊሲና ፕሮግራም ዘመናዊ ባለፎቅ ሕንፃ ሆስፒታል በሆሣዕና ከተማ ሊሠራ ተደራጅቶ ሲነሳ እነርሱም በየበኩላቸው ለሆስፒታሉ ሕንፃ ሥራና ለሕክምና አገልግሎት የመሣሪያ እርዳታ ለመስጠት ያላቸውን መልካም ፈቃድና ትብብር ለአውራጃው ኢኮኖሚና ባህል ዘመቻ ኮሚቴ በአግባብ ገለጹ ። በዚህ አንፃርና ተግባር ማዕከላዊ ደቡብ ሲኖዶስ የሆስፒታሉ የሕንፃ ሥራ እንደአለቀ ለሆስፒታሉ አገልግሎት የሚያስፈልገውን የውስጥ ሙሉ መሣሪያ ለመስጠት ፈቃደኛና ዝግጁ መሆኑን ሲገልጽ ፤ የካቶሊክ ሚሽን ደግሞ ለባለ ሦስት ፎቅ ሆስፒታል የጀኔሬተርና የሊፍት እርዳታ እንደሚያደርግ አስታወቀ ።



ይህ ሁሉ ሲሆንና ሲባል ፤ የሆሣዕና ሆስፒታል ለሕዝቡ ጥቅምና አገልግሎት በኢኮኖሚና ባህል ዘመቻ መንፈስና መርሆ በከምባታና ሀዲያ አውራጃ ሕዝብና በአብዮታዊ መንግሥት ሕብረት የሚሠራ ታላቅ ድርጅት ነው ። በዚህ ረገድ ፤ የሆስፒታሉ የሕንፃ ሥራ በሕዝቡ ጥረት ከተሠራ በኋላ የሆስፒታሉን ድርጅት ከሕዝቡ ተረክቦ ለሕዝብ ጥቅምና አገልግሎት እንዲሆን በራስ ሠራተኞችና በጀት ሙሉ በሙሉ የሚያስተዳድረው ልዩ መንግሥታዊ አካልና አላፊ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ነው ።

ይህም በመሆኑ የሆስፒታሉ ሕንፃ ጥናት በስቱዲዮ ሚካኤል ቴዎድሮስ አማካይነት ተጠንቶ ከቀረበ በኋላ በመስከረም 1 ቀን 1972 የጤና ጥተቃ ሚኒስቴር ከፍተኛ ባለሥልጣኖችና የሕክምና ባለሙያዎች በሚኒስቴሩ ቋሚ ተጠሪ ሰብሳቢነት በመሥሪያ ቤቱ ስብሰባ አዳራሽ ከከምባታና ሀዲያ ገበሬ ማህበርና ከሆስፒታሉ ገንዘብ ሰብሳቢ ኮሚቴ ተወካዮች ጋር ተሰብስበው የሆስፒታሉን አጠቃላይ ፕላን ፤ አሠራር ፤ ይዘትና አገልግሎት በሚመለከት ሰፊና ዝርዝር የኤክስፐርቶች ጥናትና ምርምር ከአደረጉ በኋላ ተገቢ አስተያየትና ውሳኔ ሰጥተውበታል ። በዚህ አኳያ በዕለቱ ለሰበሰበው በአጥኚው መሐንዲስ በአቶ ገብረ መስቀል ተአረ አማካይነት በቀረበው በሆስፒታሉ ዝርዝር ፕላንና አሠራር ጥናት ላይ ፤

1. የቦታው ይዘት ፤
2. የቤቶች አቀማመጥ ፤
3. የውጪውና የውስጡ መንገዶች አወጣጥ ፤
4. የውጭ ተመላላሽ መታከሚያና አስተዳደር ጽሕፈት ቤት ፤
5. የድንገተኞች መታከሚያና አስተዳደር ጽሕፈት ቤት ፤
6. በምድር ቤት የሕፃናትና የበሽተኞች መኝታ ከነ ኦፒራሲዮን ክፍል ጋር፤
7. በአንደኛ ፎቅ የሕፃናትና የማዋለጃ መኝታ ከነኦፒራሲዮን ክፍል ጋር፤
8. በሁለተኛ ፎቅ የውስጥ ሕመምተኞች መኝታ ክፍል ፤
9. በሦስተኛ ፎቅ ፤ የውስጥ ሕመምተኞች መንታ ክፍል ፤
10. ወጥቤት ፤ ልብስ ማጠቢያና መተኮሻ ፤ የምግብ ዕቃ ማኖሪያ ፤ የምግብ አዳራሽ ፤ የሬሳ ክፍል ፤ የጀኔሬተር ክፍል ፤ የአንቡላንስ ማቆሚያና ለመሳሰሉት የዕቃ መጠገኛ ክፍል ይገኝበታል ።

የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ከፍተኛ ባለሥልጣኖችና ባለሙያዎች በአጥኚው መሐንዲስ አማካይነት በቀረበው በሆስፒታሉ ፕላን የሕክምና ለውጥና መሻሻል ከአደረጉ በኋላ የሆስፒታሉ ባለ ፎቅ ሕንፃ ከከምባታና ሀዲያ አውራጃ ሕዝብ በተዋጣው ገንዘብ በ1972 ሥራ ዓመት ጀምሮ እንዲሠራ መስማማታቸው በቃለ ጉባኤው ሰፍሮዋል ።[2]

የሆስፒታሉን ሕዝባዊ ዓላማና አገልግሎት በሚመለከት መሠረታዊ ነገር ላይ ደግሞ በጉዳዩ የቅርብ ሃላፊነትና አግባብ ካላቸው ክፍሎችና ግለሰቦች ጋር ማለትም ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ሹማምንቶችና ከሕክምና ባለሙያዎች ፤ ከከምባታና ሀዲያ አውራጃ አስተዳደርና ከሕዝባዊ ድርጅቶች ተወካዮች ጋር ይህ ደራሲ ሰፊ

2 ስለሆሣዕና ሆስፒታል ሥራ መስከረም 1 ቀን 1972 በጤና ሚኒስቴር ስብሰባ አዳራሽ በተካሄደው ስብሰባ (ከምባታና ሀዲያ አውራጃ አስተዳደር ጽ/ቤት በሆስፒታሉ ፋይል ሆሣዕና) ።

ሳምንታዊ ውይይትና ትችት አድርጓል ። በዚህ ጥናት አማካይነት ለማወቅ እንደ ተቻለው ፤

1. በሆስፒታሉ ውስጥና አካባቢ ለነፍሰ ጡሮች ለሕፃናትና ለእናቶች ልዩ የጤና ትምህርትና የሕክምና ፕሮግራም በመጀመሪያ ደረጃ ይሰጣል ።
2. ለአካባቢው ሕዝብና ሕብረተሰብ በጤና ኮሚቴዎችና ተጠሪዎች አማካይነት አጠቃላይ የጤና ትምህርትና ምክር ይሰጣል ።
3. በሆስፒታሉ የቀበሌና የአካባቢ የጤና ተጠሪዎች በውሃ ልማትና በንጹህ ውሃ አጠቃቀም ትምህርት ይማራሉ ።
4. ሆስፒታሉ ሕብረተሰቡን የሚያገለግሉ ነርሶችን ፤ጤና ረዳቶችንና የላብ ቴክኒሺያኖችን ያሰለጥናል ።
5. ሕብረተሰቡ በሚኖርበት አካባቢ በኑሮው ደረጃ የተመጣጠነ ምግብ የሚበላበትን ዘዴና አገባብ ያስተምራል ።
6. በተጨማሪም የሆሳዕና ሆስፒታል ከከምባታና ሀዲያ አውራጃ ውጭ ለደቡብ ሸዋ ፤ ለአርሲ ፤ ለባሌ ፤ ለሲዳሞ ፤ ለጋሞ ጐፋና ለከፋ ክፍለ ሀገራት የጤና ትምህርትና የሕክምና አገልግሎት ይሰጣል ።

ስለሆነም የሆሳዕና ሆስፒታል የአንድ አውራጃ ብቻ ሳይሆን ብሔራዊ ድርጅት ነው ።

በሌላ በኩል በጥር 1971 በገንዘብ መዋጮ ዘመቻ የከምባታና ሀዲያ አውራጃ ሕዝብ 2 000 000 ብር በአዋጣው ጊዜ ይህ ገንዘብ ለሆስፒታሉ ሕንፃ ማሠሪያ እንደሚበቃ በመገመት ነበር ። በተጨማሪም በመስከረም 1 ቀን 1972 ስቱዲዮ ሚካኤል ቴዎድሮስ 200 አልጋ የሚይዝ ባለፎቅ ሆስፒታል ሕንፃ ፕላን ለጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ባለሥልጣኖችና ሕክምና ባለሙያዎች ስብሰባ በአቀረበው ፕላን የሕንፃው ሥራ ተመን የተተመነው 2 200 000 ብር (ሁለት ሚሊዮን ሁለት መቶ ሺህ ብር) ብቻ እንደሚሆን ነበር ።

ሠንጠረዥ 41


በግንቦት 1972 ሦስት የሕንፃ ተቋራጮች በጨረታ ያቀረቡት የሆሳዕና ሆስፒታል ሕንፃ ዋጋ

| ተራ ቁ. | የሕንፃ ተቋራጮች | ጨረታው ከመከፈቱ በፊት የተሰጠ ዋጋ | ጨረታው ከተከፈተ በኋላ የተሰጠ ዋጋ |
|---|---|---|---|
| 1 | Wold G. Yohannes | 4 331 858.30 | 6 394 415.53 |
| 2 | Luigi Varnero | 5 283 264.18 | 5 283 999.34 |
| 3 | Jaccarino G. and Sons | 4 827 600.96 | 4 832 817.49 |


የተገኘበት ፤ በሚያዝያ 20 ቀን 1980 በማለትም በግንቦት 12 ቀን 1972 ከስቱዲዮ ሚካኤል ቴዎድሮስ ለከተማ ልማትና ቤት ሚኒስቴር የተጻፈ የጨረታ ሰነድ (ከምባታና ሀዲያ አውራጃ አስተዳደር ጽ/ቤት ሆሣዕና) ።




የሆሣዕና ሆስፒታል መሠረት በታህሣሥ ወር 1973



የሆሣዕና ሆስፒታል በመሠራት ላይ በየካቲት 1973




ጓድ ጴጥሮስ ገብሬ ከሥራ ኃላፊው ጋር
የሆስፒታሉን ሥራ ሲጐበኙ



የሆስፒታሉን ሥራ ጐብኚዎች







ጓድ አዲስ ተድላ
የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ የቋሚ ኮሚቴ አባል ፥
የብሔራዊ አብዮታዊ የምርት ዘመቻና የማዕከላዊ ፕላን ጠቅላይ መምሪያ
ምክትል ሊቀመንበርና የኢሠፓአኮ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባል
በታህሣሥ 1974 የምርት ዘመቻና የማዕከላዊ ፕላን ጠቅላይ መምሪያና የመንግሥት
ከፍተኛ ባለሥልጣኖች እስከትለው የከምባታና ሀድያ አውራጃ የልማት በዓልና የሆሣዕና
ሆስፒታል ሥራ በጐበኙበት ወቅት ።
የተገኘበት ፥ የፕሬስ መምሪያ ፎቶግራፍ ክፍል (አዲስ አበባ 1975)

ነገር ግን ከዚህ ወዲህ በገበያ የሕንፃ ዕቃዎችና መሣሪያዎች ዋጋ ከእጥፍ በላይ በመጨመሩ ከዘጠኝ ወራት በኋላ በግንቦት 1972 የሕንፃው ሥራ ለተቋራጮች በጨረታ በቀረበው ጊዜ ፣ ከዚህ በላይ በንጠረዥ 41 እንደሚያሳየው ፣ የሕንፃው ዋጋ 2 200 000 ብር መሆኑ ቀርቶ ከ4 832 817.49 እስከ 6 394 415.53 ብር ደረሰ ።

በሰኔ 25 ቀን 1972 በ4 832 817.49 ማለትም በአራት ሚሊዮን ስምንት መቶ ሠላሳ ሁለት ሺህ ስምንት መቶ አሥራ ሰባት ብር ከአርባ ዘጠኝ ሳንቲም ሂሳብ የሆስፒታሉን ሕንፃ ለመሥራት ከተስማማው ከሦስተኛው ተጫራች ድርጅት ማለትም ከያካሪና ጉል የልዋና ልጆቹ ከከምባታና ሀዲያ አውራጃ የኢኮኖሚና የባህል ዘመቻ ኮሚቴ መካከል ሕጋዊ የሥራ ውልና ስምምነት ተፈርሞ የሕንፃው ሥራ በዘመቻ መልክ ተጀመረ ።

በዚህ ውል መሠረት ለሆሳዕና ሆስፒታል ሕንፃ ማሠሪያ ከሚያስፈልገው ከ4 832 817.49 ብር የከምባታና ሀዲያ አውራጃ ሕዝብ ከገማሽ የሚበልጠውን ገንዘብ ማለትም 2 500 000 ብር አዋጥቶ ገና በመጋቢት 1971 በሆሳዕና ንግድ ባንክ እንዳስቀመጠው ከዚህ በላይ አይተናል ። ስለዚህ የወቅቱ መሠረታዊ ጥያቄ የሕንፃውን ሥራ ለመጨረስ የሚያስፈልገው ማለትም ቀሪው 2 332 817.49 ብር ከየት ይመጣል? የሚለው ነገር ሆነ ።

## 4. ለ. የአብዮታዊ መንግሥትና ሚና

በሌላ በኩል የአውራጃው ሕዝብ ራሱን በራሱ ለመርዳት ያደረገውን ታላቅ ጥረት በማየትና በማድነቅ በማዕከላዊ ዶቡብ ሲኖዶስ ማለትም በኢትዮጵያ መካነ ኢየሱስ ወንጌላዊ ቤተ ክርስቲያን በኩል የሆስፒታሉን የውስጥ መሣሪያ ለመስጠት ቃል የገባው የሉተራውያን ዓለም አቀፍ ድርጅት በ1973 በጉዳዩ ላይ ከኢትዮጵያ አብዮታዊ መንግሥት ጋር በዝርዝር ተነጋግሮበት ለባለ 250 አልጋ ሆስፒታል እስከ 3 400 000 ብር ወጭ የሚወስድ አዲስና ሙሉ መሣሪያ እንደሚሰጥ በይፋ ሲያረጋግጥ ፣ የካቶሊክ ሚሽንም እንዲሁ ለሆስፒታሉ በድምር እስከ 430 000 ብር ወጭ የሚወስዱ ሁለት ሊፍቶችና ሁለት ጀኔሬተሮች እንደሚሰጥ ገለፀ ። በአንፃሩ ደግሞ የሆስፒታሉ የሕንፃ ዋጋ እየጨመረ በመሄድ በግንቦት 1972 ጠቅላላ 4 832 817 ብር ነው የተባለው ዋጋው ወደ 5 146 505.24 ብር እንደሚደርስ ታወቀ ። በሕዝቡም በኩል በልዩ ልዩ መንገድ የተዋጣው የሆስፒታሉ ሕንፃ ማሠሪያ ገንዘብ ደግሞ ወደ 2 933 777.90 ብር ደረሰ ።

ነገሩን በአጭር ለማስቀመጥ ፣ በሕዝቡ መዋጮና በሆስፒታሉ ሕንፃ ዋጋ መካከል ያለው ልዩነት በየጊዜው እንደዚህ እየራቀ በመሄዱ የአውራጃውን ሕዝብ ጥረት ከመጀመሪያው ጀምሮ በቅርብ ይከታተል የነበረው የኢትዮጵያ አብዮታዊ መንግሥት የጎደለውን ዋጋ አሟልቶ የሆስፒታሉን የሕንፃ ሥራ ለማስጨረስ ወቅታዊና ትክክለኛ የሆነ ውሳኔ በመውሰድ የአውራጃውን ሕዝብ በቀጥታ መርዳት ጀመረ ።

በዚህ አንፃርና ተግባር ፣ ጓድ አዲስ ተድላ የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ የቋሚ ኮሚቴ አባል ፣ የብሔራዊ አብዮታዊ የምርት ዘመቻና የማዕከላዊ



ፕላን ጠቅላይ መምሪያ ምክትል ሊቀ መንበርና የኢሠፓአኮ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባል በታህሣሥ 1974 በከምባታና ሀዲያ አውራጃ በኢኮኖሚና በባህል ዘመቻ መሠረት ከ1971 ጀምሮ የተካሄደውን አጠቃላይ የልማት እንቅስቃሴ የሆስፒታሉን ሕንፃ ሥራ ጭምር ለሦስት ቀናት በዝርዝርና በጥልቀት ጐበኙ ።

ጓድ አዲስ ተድላ በዚሁ ጉብኝታቸው ወቅት በሆሳዕና ከተማ በልማት በዓል ለተሰበሰበው ለከምባታና ሀዲያ ሕዝብ በአውራጃው ውስጥ በኢኮኖሚና በባህል ዘመቻ መሠረት በመካሄድ ላይ ያለውን ከፍተኛ የልማት እንቅስቃሴና ተግባር በማየት የተሰማቸውን ልዩ ደስታ ከመግለጽ ባሻገር ፣ የአውራጃው ሕዝብ ለወደፊትም በሚያካሂደው በልማት ሥራ የአገሩ አብዮታዊ መንግሥት ከጐኑ መቆሙን በራሳቸውና በአብዮታዊ መንግሥት ስም በይፋ አረጋግጠውለት ወደ አዲስ አበባ ተመለሱ ።

በአጭሩ ከጓድ አዲስ ተድላ ጉብኝትና ቃል በኋላ የኢትዮጵያ አብዮታዊ መንግሥት የሆሳዕና ሆስፒታል ሕንፃ ሥራ ለመጨረስ የሚያስፈልገውን የገንዘብ ወጭ ለመሸፈንና ሆስፒታሉንም ከህዝቡ ወስዶ በተቻለው ፍጥነት በአጭር ጊዜ ውስጥ በአገልግሎት ላይ ለማዋል ተግባራዊ እቅድና እርምጃ መውሰድ ጀመረ ። በዚህ በከምባታና ሀዲያ አውራጃ ሕዝብና በኢትዮጵያ አብዮታዊ መንግሥት መካከል በተፈጸመው በዓላማና በተግባር አንድነት ጉዳይ ፣ የከምባታና ሀዲያ አውራጃ የኢኮኖሚና የባህል ዘመቻ ኮሚቴ በጓድ ጴጥሮስ ገብሬ ሰብሳቢነት በየካቲት 6 ቀን 1974 በሆሳዕና ከተማ ተሰብስቦ በሆሳዕና ሆስፒታል ነገር ከዚህ የሚከተለውን ታሪካዊ ውሳኔ አሳለፈ ። የውሳኔው ሙሉ ቃል እንደሚለው ፣

"የከምባታና ሀዲያ አውራጃ የምርት ዘመቻና ፕላን ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ጓድ ጴጥሮስ ገብሬ የከምባታና ሀዲያ አውራጃ አስተዳደሪና የኮሚቴው ሊቀ መንበር ፣

ጓድ ኃይሉ ጉተማ የከምባታና ሀዲያ አውራጃ የገንዘብ ሚ/ር ተጠሪና የኮሚቴው አባል ፣

ጓድ ሙሉጌታ ወርቁ የከምባታና ሀዲያ አውራጃ የግብርና ሚ/ር የኮሚቴው አባል ፣

ጓድ ደሳለኝ ለዕመንጉ የከምባታና ሀዲያ ት/ቤቶች ጽ/ቤት የኮሚቴው አባል ፣

ጓድ ደሳለኝ መኮንን የከምባታና ሀዲያ የሀገር ውስጥ ን/ሥ/ዋ(ቱ የኮሚቴው አባል ፣

ጓድ ማሞ ካሣ የከምባታና ሀዲያ ፍ/ቤት ፕሬዝዳንትና የኮሚቴው አባል

ጓድ ወልደሰንበት ጅራሞ የከምባታና ሀዲያ ገበሬዎች ማ ሊ/መ/ርና የኮሚቴው አባል ፣

ጓድ አገኘሁ ወርቅ አከሊሉ የከምባታና ሀዲያ ሴቶች ማ/ሊ/መ/ርና የኮሚቴው አባል

ጓድ ገርማ ጉበና የከምባታና ሀዲያ አኢወማ ኮሚቴ ሊ/መ/ርና የኮ/ሚቴው አባል

ጓድ በርቶሎሚ ማቴዎስ የሆሳዕና ልዩ ከፍተኛ/ከነማ ሊቀ መንበር ፣

ቃለ ጉባኤ ፀሐፊ አልማዝ ተምትሜ አንድነት ባለንበት ስብሰባ ተደርጓል ።

የስብሰባው ዓላማ በሰፊው ሕዝብ አስተዋጽኦ አዲስ በመሠራት ላይ ስለሚገኘው ሆስፒታል የሥራ ደረጃና በቀሪነት ስለሚፈለገብን ገንዘብ ከድርጅት ሥራ አስኪያጅ በ27/5/74 በቁጥር 7/34/82 የተጻፈውን ደብ ዳቤ መሠረት በማድረግ አስቸኳይና ወቅታዊ መፍትሔ ለመስጠት ሲሉ ሰብሳቢው ለቤቱ አባላት ከአስረዱ በኋላ ከላይ ቁጥሩ የተጠቀሰው ደብ ዳቤ ለቤቱ በንባብ ሲሰማ እስካሁን ለሆስፒታሉ ሕንፃ ሥራ ለሥራ ተቋራጭ የተከፈለው 15ኛ ክፍያ የደረሰ ሲሆን ወጪ የሆነው ገንዘብም የኢት ብር 2 426 903.04 (ሁለት ሚሊዮን አራት መቶ ሃያ ስድስት ሺህ ዘጠኝ መቶ ሦስት ብር ከአራት ሳንቲም) ይደርሳል ። ወደፊት የሆስፒታ ሉን ሕንፃ ሥራ ለማጠናቀቅ የኢት.ብር 2 560 000 (ሁለት ሚሊዮን አምስት መቶ ስልሳ ሺህ ብር) ቢያዝ ወጭውን ሊሸፍን ይችላል ።

## ወደፊት ሊሠራ ስለታቀደው

1. የነርሶች ትምህርት ቤት
2. የሐኪሞች መኖሪያ

## ሀ. የነርስ ትምህርት ቤትና መኖሪያ ቤት

1. የነርስ የትምህርት ክፍሎች
2. የምግብና የሳይንስ ላቦራቶሪ
3. ቤተ መጻሕፍት
4. የምግብ አዳራሽ
5. የመኝታ ክፍሎችን ለማሠራት ሕንፃው 3 759 ካሬ ሜትር ስፋት የሚያስፈልግ ሲሆን የሚፈጀው ዋጋ ግምት የኢት.ብር 3 000 000 (ሦስት ሚሊዮን ብር) አካባቢ ይሆናል ።

## ለ. የሐኪሞች መኖሪያ ቤት

የሐኪሞች መኖሪያ ቤቶች ብዛታቸው ባይታወቅም በግምት ለስድ ስት ሐኪሞች መኖሪያ የኢት. ብር 600 000 (ስድስት መቶ ሺህ) ሊፈጅ ይችላል የሚል ነው ። የአውራጃው የምርት ዘመቻና የፕላን ሥራ አስፈ ጻሚ ኮሚቴ በጉዳዩ ሰፋ አድርጐ ከተነጋገረ በኋላ ከዚህ የሚከተለውን ውሳኔ አሳልፋል ።

## ው ሳ ኔ

በመሠረቱ አስከፊው የፊውዶ ካፒታሊስት ሥርዓት ጥሎት ካለፈው ጥቁር ነጥብ አንዱ የሕብረተሰቡ ማህበራዊ ኑሮ ጠንቅ የሆነውን በሽታ ለማጥፋት በከምባታና ሃዲያ አውራጃ በብር 5 000 000 ወጭ የተጀመረው ሆስፒታል የማሠራት ስር ነቀል ርምጃ በመላ ኢትዮጵያ ውስጥ እንደ ሞዴልነት ሊጠቀስ የሚችል እንደሆነ ተደጋግሞ ተገልጾአል ። ይህ ኮሚኒ ስት መሪያችን ሊቀ መንበር መንግሥቱ ኃይለማርያም አድሃሪያንን ብቻ ሳይሆን ተፈጥሮን በቁጥጥራችን ሥር እናደርጋለን እንዳሉት ሁሉ ይህንን በከፊል ፊውዳልና በከፊል ካፒታሊስት ሥርዓት ሲጨቆንና ሲረገጥ የነበረ ሕዝብ



ከበሽታ ዓለም ነፃ ለማውጣት አሁን የተጀመረው ሆስፒታል ፍጻሜ ሲያገ አገልግሎቱ በጠቅላላው የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ሕግና ደንብን የተከተለ ማድረግ ለውጤቱ ግብ መምታትና አስተማማኝነት የበለጠ ዋስትና እንዳ ለው አያጠያይቅም ።

በተለይም የከምባታና ሃዲያ አውራጃ ሰፊ ሕዝብ በልማት እቅጣጫ ያሳየውን እምርታ በማድነቅ ጓድ አዲስ ተድላ የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ የቋሚ ኮሚቴ አባል ፤ የብሔራዊ አብዮታዊ የምርት ዘመቻና የግዐ ከላዊ ፕላን ጠቅላይ መምሪያ ምክትል ሊቀ መንበርና የኢሠፓአኮ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባል ሰላምን ፤ እኩልነትን ፤ ፍትህን ፤ ብልጽግናንና እንድነትን ለማግኘት ሠርቶ አደሮች የዓለም ልዩነት እንደሌላቸው ሁሉ ሀገርንም በመገንባት ላይ የሚገጥሙንን የሕይወትና የዕድገት መሰናክሎችን በጋራ ለማስወገድ ደግሞ ወደ ኋላ እንደማይሉ አረጋግጠውልናል ። በመሆኑም በግንባታችን ወቅት ሰፊው ሕዝብ ከራሱ አስተዋጽኦ ባሻገር ኢኮኖሚያችንን ለማድቀቅ እስፍስፍ ያለውን የዓለም አቀፍ ሞኖፖሊዎች ብዝበዛ በሠርቶ አደራዊ አንድነት ለመወጣት እንዲችል ለብዙኀኑ ጥሪ ከማስተጋባት ተቆጥቦ አያውቅም ። ይህም ዛሬ በአውራጃችን በመሠራት ላይ ባለው ሆስፒታል ላይ የተከሰተውን ኢኮኖሚያዊ የኢምፔሪያሊስቶች ጭቆና መጥቀሱ ይበቃል ።

ይህ ሆስፒታል ቀደም ሲል በብር 2 500 000 ለማሠራት ዕቅድ ከወጣ በኋላ ፕላኑ ሳይለወጥ የዕቃዎች ዋጋ መናር ብቻ ወደ ብር 5 000 000 ከፍ ያደረገው በመሆኑ ሰፊው ሕዝብ አቅሙ በፈቀደለት መጠን እስካሁን የብር 2 426 903 04 (የሁለት ሚሊዮን አራት መቶ ሃያ ስድስት ሺ ዘጠኝ መቶ ሦስት ብር ከዜሮ አራት ሳንቲም) ክፍያ እስኪያከናውን ድረስ ታግሏል ።

ከአሁን ወዲህ ግን የአስከተለውን የዕቃ ዋጋ መናር ሰፊው ሕዝብ ከዚች ከእጅ ወደ አፍ ከሆነ ኑሮው ነጥሎ መቋቋም ባለመቻሉ የኅብረተ ሰብአዊት ኢትዮጵያ ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት የጤና ጥበቃ ሚኒስ ቴር ለወገኖች ባለው ተቆርቋሪነት መሠረት ፤ 1ኛ ቀሪውን ብር 2 560 000 (ሁለት ሚሊዮን አምስት መቶ ስልሣ ሺህ) ብር ከፍሎ ሆስፒታሉን ከፍፃሜ እንዲያደርስ ፥ 2ኛ በሚኒስቴሩ ሕግ መሠረት የሐኪሞች መኖሪያ ቤቶችና የነርስ ትምህርት ቤት ከላይ በተገለጠው መሠረት እንዲያሠራ ቢደረግ በጤንነት እጦት በሕይወትና በሞት መካከል የሚገኘውን ሰፊ የደቡብን ሕዝብ ብሎም የመላ ኢትዮጵያን ሕብረተሰብ በትግል አጋርነት ፤ በዓላማ አንድነት በሰብአዊ ርኅራኄ ግዳን መሆኑን እንዲገነዘቡት ወስነናል ።[3]

ትእዛዝ ፤

የዚህ ውሣኔ ቢርሻል ፤

1. ለሀ.ሰ.ኢ.ጊ.ወ.መ. የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ፤
2. ለብሔራዊ አብዮታዊ የምርት ዘመቻ የማ.ፕ.ጠ. መምሪያ ፤

3 የከምባታና ሀዲያ አውራጃ የኢኮኖሚና የባህል ዘመቻ ኮሚቴ በየካቲት 6 ቀን 1974 የሆሣዕና ሆስፒታል ሥራ ወደ መንግሥት እጅ እንዲተላለፍ ያሳለፈው ውሳኔ ቃል።

3. ለሀ.ሰ.ኢ.ጊ.ወ.መ. የአገር አስተዳደር ሚኒስቴር ፤
4. ለሸዋ ክፍለ ሀገር የምርት ዘመቻና ፕላን መምሪያ ፤
5. ለሸዋ ክፍለ ሀገር የጤና ጥበቃ ሚ/ር ተጠሪ ጽ ቤት ፤
6. ለስቱዲዮ ሚካኤል ቴዎድሮስ በሸኚ ደብዳቤ ይድረስው ብለናል ።"

በዚህ በከምባታን ሀዲያ አውራጃ ሕዝብ ውሳኔ መሠረት ፤ በሆሳዕና ሆስፒታል ጉዳይ ከብሔራዊ አብዮታዊ የምርት ዘመቻና የማዕከላዊ ፕላን ጠቅላይ መምሪያ ለኮንስትራክሽን ሚኒስቴር በነሐሴ 18 ቀን 1974 በተጻፈው ደብዳቤ ፤ የኢትዮጵያ አብዮታዊ መንግሥት ከዚህ የሚከተለውን የመጨረሻ እርምጃ

ሠንጠረዥ 42

የነርስ ት/ቤትና የሐኪሞች መኖሪያ ቤት ዋጋ ጭምር የሆሳዕና ሆስፒታል የጠቅላላ ወጭ ግምት በብር

| | የሆስፒታሉ ሥራ ድርጅት | የዋጋ ግምት | ከልዩ ልዩ ምንጮች እስከ 1975 ድረስ የተገኘው ገንዘብ | ገና የሚያስፈልግ ገንዘብ መጠን |
|---|---|---|---|---|
| 1. | የሆስፒታሉ ሕንፃ ሥራ | 5146505.24 | | |
| 2. | ሊፍትና ጀኔሬተር | 430000.00 | | |
| 3. | የሆስፒታሉ የውስጥ መገ. | 3500000.00 | | |
| 4. | የነርስ ት/ቤት | 3000000.00 | | |
| 5. | ሐኪሞች መኖሪያ ቤት | 600000.00 | | |
| | የወጭ ድምር | 12676505.24 | | |
| 6. | ከአውራጃው ሕዝብ የተዋጣ | | 2933777.90 | |
| 7. | ከመንግሥት የተሰጠ | | 2779000.00 | |
| 8. | ከሲኖዶስ የተገኘ የመገልገያ እርዳታ | | 3500000.00 | |
| 9. | ከካቶሊክ ሚሽን የተገኘ የመገልገያ እርዳታ | | 430000.00 | |
| 10. | እስከ 1975 የተገኘ የገንዘብ ድምር | | 9,642,777.90 | |
| 11. | ሥራውን ለመጨረስ ገና የሚያስፈልግ ገንዘብ መጠን | | | 3,023,727.34 |
| | ጠቅላላ ድምር | 12676505.24 | 9,642,777.90 | 3,023,727.34 |

የተገኘበት ፤ በዚህ ጥናት ከዚህ በላይ በልዩ ልዩ ሥፍራና ጊዜ የተገለፀ ።



ወሰደ ። በደብዳቤው ቃል ፤

"በሸዋ ክፍለ ሀገር በከምባታና ሃዲያ አውራጃ በሆሳዕና ከተማ በሕዝብ መዋጮ በመሠራት ላይ ያለው የሆስፒታሉ ሕንፃ ኮንስትራክሽን ሥራ በሕዝብ መዋጮ ሙሉ በሙሉ ሊሸፈንና ሥራው ሊጠናቀቅ ባለመቻሉ እስካሁን የተሠራው ሥራና የኮንስትራክሽን ሥራ ለማስጨረስ 2 779 000 (ሁለት ሚሊዮን ሰባት መቶ ሰባ ዘጠኝ ሺህ ብር) በጤና ሚኒስቴር ስም ከመንግሥት በጀት የተፈቀደ ስለሆነ ፤ ይህ የተፈቀደው ገንዘብ በአግባቡ በሥራ ላይ መዋሉን ለማረጋገጥ የኮንስትራክሽን ሥራ በኢትዮጵያ ሕንፃ ኮንስትራክሽን ባለሥልጣን ተቆጣጣሪነት መከናወን ስለአለበት ይኸው በሥራ እንዲውል አስፈላጊው ሁሉ እንዲደረግ እናሳስባለን ።"

በገንዘብ እጥረት ምክንያት በ1974 የሆስፒታሉን ሥራ ለአጭር ጊዜ አቁሞት የነበረው የሥራው ተቋራጭ ድርጅት የኢትዮጵያ አብዮታዊ መንግሥት ለሆስፒታሉ ሕንፃ ሥራ ማስጨረሻ ገንዘብ ከአገሩ በጀት ከፈቀደ በኋላ በ1975 ሥራውን እንደገና ጀመረ ። ከዚያ በኋላ ከአብዮታዊ መንግሥት በተፈቀደው ገንዘብ ሥራው አልቆለት ሆስፒታሉ በ1976 ለአገልግሎት ደረሰ ። ከሆስፒታሉ ጋር አብረው የሚሄዱና ከዚህ በላይ የተጠቀሱ የነርስ ትምህርትና የጤና ባለሙያዎች መኖሪያ ቤቶች በአብዮታዊ መንግሥት ወጭና አላፊነት ሲሠሩ የሆሳዕና ሆስፒታል ጠቅላላ ወጭ ማለትም የሕንፃ ሥራ ፤ የውስጥ መገልገያ ፤ የሊፍትና የጄኔሬተር ፤ የነርስ ትምህርት ቤትና የጤና ባለሙያዎች መኖሪያ ቤቶች ዋጋ በአንድነት ሲደመር ፤ ከዚህ በላይ በሠንጠረዥ 42 እንደሚታየው ፤ ወደ 13 000 000 ብር ይጠጋል ።

## 5. የሆሳዕና ሆስፒታል አቀማመጥና ክፍሎች

የሆሳዕና ሆስፒታል የተሠራበት በሆሳዕና ከተማ በሰሜናዊ ምዕራብ ክፍል በጥቾም ተራራ እናት ላይ ሲሆን ከሆስፒታሉ ሕንፃ ላይ ቆመው ሲያዩት በተፈጥሮው በእንስት ፤ በባህር ዛፍና በተለያዩ ዛፎች የተሸፈነ የከምባታና ሀዲያ አውራጃ አረንጓዴ ሜካ መስሎ ከሞላው ጉደል ከዳር እስከ ዳር ይታያል ። ከሆስፒታሉ በስተምዕራባዊ ደቡብና በስተደቡባዊ ምሥራቅ የአውራጃው ሁለቱ ታላላቅ ተራሮች ማለትም በቅደም ተከተል የሾንቆላና የአምበርቾ ተራሮች ከሩቅ በጥቁር ደመና ተሸፍነው ይታያሉ ። በአረንጓዴው ከምባታና ሀዲያ አውራጃ የሆሳዕና ሆስፒታል ከሾንቆላና ከአምበርቾ ቀጥሎ ሦስተኛው ታላቅ "ተራራ" ነው ማለት ይቻላል ። የሆሳዕና ሆስፒታል በአውራጃው ከሾንቆላና ከአምበርቾ ተራሮች ጋር የመወዳደር ጉዳይ አንፃራዊ አባባል ነው ቢባል እንኳ ሆስፒታሉ በከምባታና ሀዲያ አውራጃው የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮት የድል መታሰቢያ ፤ ምልክት ፤ አርማ ፤ ሐውልት አምባና ተራራ መሆኑ የማያጠያይቅ ታሪካዊ ነገር ነው ። ያም ሆነ ይህ የሆሳዕና ሆስፒታል የኢትዮጵያ አብዮታዊ ሕዝብና መንግሥት ሕብረት ውጤትና ምልክት ነው ። ሆስፒታሉ የኢትዮጵያ የብሔረሰቦች አንድነት ውጤትና ምልክት ነው ። የኢትዮጵያ የብሔራዊ አብዮታዊ የምርት ዘመቻና የማዕከላዊ ፕላን ጠቅላይ መምሪያ ተግባራዊ ውጤትና መገለጫ ነው ።

እንደዚህ ሁለገብ ዋጋና ግምት ያለው የሆሳዕና ሆስፒታል የግቢው ስፋት ፤ ከዚህ በላይ በሠንጠረዥ 27 ውስጥ እንደታየው ፤ 70 000 ካሬ ሜትር ነው ።

በዚህ ረገድ ከደቡብ ምዕራብና ከሰሜን ምሥራቅ ወደ ሆስፒታሉ ግቢ የሚያስገቡ ሁለት መግቢያ በሮች ሲኖሩ የሆስፒታሉ ግቢ ዙሪያ በባለመንፈት ሽቦ ታጥሮዋል ። በግቢው በሁለቱ መግቢያ በሮች መካከል በአስፋልት የተሠራ የመኪና መንገድ ጠቅላላ ርቀቱ 314 ሜትር ሲሆን ጠቅላላ ስፋቱ ደግሞ 1947 ካሬ ሜትር ነው ። ከግቢው የመኪና መንገድ በስተሰሜናዊ ምዕራብ ክፍል በሚገኘው ቦታ የሆስፒታሉ የተለያዩ ቤቶችና ክፍሎች ተሠርተዋል ። የግቢው የመኪና መንገድ ከምዕራብ ደቡብ በኩል በአስተዳደርና በድንገተኛ ሕንፃዎች መካከል በኮኖፓይ ማለትም (Conopy) ድልድይ ወይም መጋናኛ ሥር ያልፋል ። የግቢው የመኪና ማቆሚያ ሥፍራ የሚገኝበት ከደቡብ ምዕራብ መግቢያ በርና በተመላላሽ በሽተኞች መታከሚያ ክፍል መካከል ሲሆን የቦታውም ስፋት 727.81 ካሬ ሜትር ሆኖ በአስፋልት ተሠርቶዋል ። በተጨማሪም ከሆስፒታሉ ውጭና ዙሪያ በድምር ስፋቱ 624.96 ካሬ ሜትር የሆነና በሲሚንቶ የተሠራ የእግር መንገድ አለ ።

ከሰሜናዊ ምሥራቅ መግቢያ በር ወደ ሆስፒታሉ ግቢ ሲገባ በመጀመሪያው የሚታየው የሆስፒታሉ በ192.64 ካሬ ሜትር ስፋት ቦታ ላይ የተሠራ ሞርግ (morgue) ማለትም የሬሳ ፣ የጀኔሬተርና የመኪና ጋራዥ ቤት ወይም ክፍል ነው ። ከሞርጉ በአሥራ ስምንት ሜትር ርቀት ላይ በ1069.08 ካሬ ሜትር መሬት ላይ የተሠራ የሆስፒታሉ የከችንና የላውንዳሪ ማለትም የወጥቤትና የልብስ ማጠቢያ ቤት ወይም ክፍል ነው ። ከከችንና ከላውንደሪ ክፍል ቀጥሎ በ20 ሜትር ርቀት ላይ በ149.04 ካሬ ሜትር ላይ የተሠራ የሆስፒታሉ የኦፕሬሽን ክፍል ሲሆን እርሱም አንድ ምድር ቤትና አንድ ፎቅ ቤት ብቻ አለው ።

ከኦፕሬሽኑ ክፍልና አንድ ምድር ቤትና ሦስት የፎቅ ክፍሎች በአለው በሆስፒታሉ ዎርድ ማለትም በበሽተኞች መኝታ ቤት ወይም ክፍል መካከል ያለው ርቀት ስምንት ሜትር ሲሆን ሁለቱም ሕንፃዎች ማለትም የኦፕሬሽንና የዎርድ ክፍሎች በሦስት ሥፍራዎች ከድንጋይ ከሲሚንቶና ከብረት እንደድልድይ በተሠሩ መገናኛዎች ተገጥመዋል ። የኦፕሬሽንና የዎርድ ሕንፃዎች በምሥራቃዊ ሰሜን ከከችንና ከላውንድሪ ክፍል በደቡብ ደግሞ ከአስተዳደር ክፍል *ሀያ ሀያ* ሜትር ወጣ ብለው በሆስፒታሉ ግቢ እናት ላይ ከምሥራቅ ወደ ምዕራብ ተሠርተዋል ።

በሁለቱም ሕንፃዎች በየደረጃዎቹ በምዕራብ በኩል የሚገኙ ክፍሎች የባለሙያዎችና የአገልግሎት ክፍሎች ሲሆኑ በምሥራቅ በኩል የሚገኙ ክፍሎች ደግሞ የበሽተኛ አልጋዎች የሚገኙባቸው ክፍሎች ናቸው ። በመካከል የሚገኘው ባለሁለት ክፍል ሊፍት የዎርዱን ሕንፃ ከምድር ቤት እስከ ሦስተኛ ፎቅ ድረስ በሁለት እኩል ክፍሎች ማለት በምሥራቅና በምዕራብ ከፍሎታል ። የሊፍቱ እናት ከዎርዱ ሦስተኛ ፎቅ ወጣ ብሎ የሆስፒታሉ ቁንጮ መስሎ ከሩቅ ይታያል። ከሊፍቱ ቁንጮ በታችና በሰሜናዊ ምሥራቅ በኩል ከኦፕሬሽኑ ፎቅ በላይ የዎርዱ ሁለተኛውና ሦስተኛው ፎቆች ከሩቅ ለሚመለከታቸው የሆስፒታሉ ልዩ መቀነቶች መስለው ይታያሉ ።

ከዎርዱ ሕንፃ ፊት ለፊት በደቡብ በኩል ከዎርዱ ሕንፃ 20 ሜትር ላይ በሚገኘው በ2715 ካሬ ሜትር መሬት ላይ የሆስፒታሉ የኦፒድ ማለትም የአስተዳደርና የተመላላሽ በሽተኛ መታከሚያ ክፍል ተሠርቶዋል ። በኦፒድ መሀል ከላይ ክፍት የሆነ መናፈሻ ሥፍራ ሲኖር በመናፈሻው ዙሪያ ደግሞ ክብ የሆነ የመተ



ላለፊያ መንገድና በ16 ድንጋይ ዓምዶች ላይ የተሠራ በረንዳ አለ ። በዎርዱና በመናፈሻው መካከል የሚገኘው የኦፒዱ ሰሜናዊ ክንፍ የሆስፒታሉ የአስተዳደርና የቤተ መጻሕፍት ክፍል ፣ የምዕራቡ ክንፍ የተመላላሽ በሽተኞች መታከሚያ ክፍል ፣ የምሥራቁ ክንፍ የመድኃኒትና የኤክስሬይ ክፍል ፣ የደቡብ ክንፍ የልዩ ልዩ የሕክምና ባለሙያዎች ማለትም የአይንና የጥርስና የቀዶ ጥገና ሐኪሞች ክፍል ነው ።


በደቡብ በኩል በኦፒድና በድንገተኛ ክፍል መካከል ያለው ርቀት 18 ሜትር ሲሆን ሁለቱም ሕንፃዎች በስምንት ዓምዶች ላይ በተሠራና ቁመቱ ከመሬት ወደ ላይ 2.70 ሜትር በሆነ በከኖፓይ ድልድይ ተገጥመዋል ። በከኖፓይ ድልድይ ሥር በኦፒድና በድንገተኛ መካከል የግቢው የመኪና አስፋልት መንገድ እንደሚያልፍ ከዚህ በላይ ተገልጿል ።

ነገሩን ለማሳጠር ፣ ከዚህ በላይ በአጭሩ የተገለፁ የሞርግ ፣ የከችንና የላውንደሪ ፣ የኦፕሬሽን ፣ የዎርድ ፣ የኦፒድና የድንገተኛ ሕንፃዎች የሆማዕና ሆስፒታል ዋና ዋና ክፍሎች ሲሆኑ ዝርዝር ይዞታቸውንና ገጽታቸውን ከዚህ እንደሚከተለው በሠንጠረዥ ማስቀመጥ ይቻላል ።

ሠንጠረዥ 43

የሆሳዕና ሆስፒታል መጠንና ይዘት

| ተራ ቁ. | የሆስፒታሉ አበይት ክፍሎች | ስፋት በካሬ ሜትር | የክፍል ብዛት | የመዝጊያ ብዛት | መስኮት ብዛት | የዓምድ ብዛት | የሆስፒታሉ የአልጋ ብዛት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ሞርግ—የሬሳ ፣ የጀኔሬተርና የጋራዥ ክፍል | 192.64 | 8 | 8 | 36 | 28 | 250 |
| 2 | ኪችንና ላውንድሪ ፣ ወጥቤትና የልብስ ማጠቢያ | 1096.08 | 20 | 26 | 384 | | |
| 3 | የኦፕሬሽን ክፍል/ሕንፃ | 149.04 | 31 | 27 | 054 | | |
| 4 | የዋርድ ማለትም የበሽተኞች መኝታ ክፍል | 916.15 | 189 | 187 | 239 | | |
| 5 | ኦፒድ ፣ የተመላላሽ በሽተኛና የአስተዳደር ክፍል | 2715.30 | 119 | 112 | 171 | 43 | |
| 6 | የድንገተኛ ክፍል | 170.30 | 15 | 14 | 26 | 8 | |
| 7 | የሆስፒታሉ ጠቅላላ ውስጣዊ ስፋት | 5239.51 | | | | | |
| 8 | የመኪና መንገድና ማቆሚያ<br>የውጭ የእግር መንገድ | 3050.39<br>624.40 | | | | | |
| | ጠቅላላ ድምር | 8914.30 | 382 | 374 | 630 | 79 | 250 |




የሆሳዕና ሆስፒታል ፕላን



የሆሣዕና ሆስፒታል የሕንጻው ሥራ ካለቀ በኋላ

# የጥናቱ ጽሑፋዊ ምንጮች


"Adulis Inscription' in Cosmas, *The Christian Topography of Cosmas,* tr. and ed. by J. McCrindle (1897).

Arab-Faqih, *Histoire de la Conquete de L'Abyssinie,* tr. and ed. by R. Basset (1897).

Bahrey, *History of the Galla* in C. F. Beckingham and G.W.B. Huntingford; and eds; *Some Records of Ethiopia* 1593-1646 (1954).

Basset, R. *Etudes Sur L'Histoire d'Ethiopie* (1881).

Bender, M. L., *The Ethiopian Nilo-Saharans* (1975).

———, ed., *Non-Semitic Languages of Ethiopia* (1976).

Blundell, H. W., tr. and ed., *The Royal Chronicle of Abyssinia* (1922).

Borelli, J. *Ethiopie Meriodionale* (1890).

Braukämper, U. *Geschichte der Hadiya Sud-Athiopiens* (1980).

Bruce, J. *Travels to Discover The* Sourceof the Nile, 5 Vols. (1790).

Cerulli, E., *Folk-Literature of the Galla of Southern Abyssinia* (1922).

Cotterell, F. P., *Born At Midnight* (1973).

Crawford, O. G. S., ed.; *Ethiopian Itineraries Ca.* 1400-1524 (1958U.

Drewes, A. J., *Inscriptions de L,Ethiopie* (1962).

Ethiopia, "Land Taxes Proclamation", Numbers 70, 94, 117, 18-14 of 1942, 1947, 1951, 1959.

———. *Annual External Trade Statistics,* (19678).

———. ; *Statistical Abstract* (1978).

———. ; (Ministry of Interior); *General Analysis and Report On the Master Plan for Hosaena* (1968).

———. ; *Les Revendications de L'Ethiopie Concerant Les Ancienne Colonees Ilatiennes; Docum'entation Presentees par la Delegation de L'Ethiopie* (A.-C. 1-W8), October 20, 1949).

Fleming, H.C., "West Cushitic Within H1mitio-Semitic" in D.F. McCall, *East African History* (1969).

Guebre Selassie, *Chronique de Menelik II*, 2 Vols (1930).

Huntingford, G. W. B., "Arabic Inscriptions in Southern Ethiopia", *Antiquity*, Vol. 29 (1955), pp. 230-233.

; tr. and ed; *The Glorious Victorious of Amda Seyon King of Ethiopia* (1965).

Ibn Fadl Allah Al Omari, *Masalik Absar Fi Mamalik el Masar*, tr. and ed., tr. and ed; G. Demombynes (1927).

Lawerence, J.C.D. and Mann, H.S., *Land Policy Project* (1965).

Lewis, H.S., "Origins of the Galla and Somali", *Journal of African History*, Vol. 7, No. 1 (1966), pp. 27-346.

Leslau, W. "Is There a Promto-Gurage", *Projceddings of the Interna. tional Conference On Semitie Studies* (Jerusalem, 1964).

Littmann, E., tr. and ed., *Sabaische, Grechische Und Altabessinische Inschriften in Deutsche Aksum Expendition*, Band IV (1913). Inscriptions Numbers 4, 6, 7, 8, 9, 10, 11, pp. 4-35.

Mann, H. S., *Land Tenure of Chore* (1965).

Maqrizi, *The Book of the Ttrue Knowledge of the Moslem Kings in. Abyssinia* tr. by G. W. B. Huntingford (Typescript, 1955).

Muller, D., "On the Inscriptions from Yeha and Aksum" in J. T. Bent, *The Sacred City of the Ethiopians* (1896), pp. 231-281.

Murdock. G. P., *Africa; Its Peoples and Culture History* (1959).

Perruchon, J. tr. and ed., *Les Chroniques de Zara Yaeqob et de Baeda Maryam* (1893).

Rosenfeld, C. P., *A Chronology of Menelik II of Ethiopia* (1976).

Schneider, R., "Les Debuts de L'Histoire Ethipienne", *Documents Histoire Civilisation Ethiopienne*, RCP. 230, CNRS, FASC. (1976) pp. 47-54. à

Schneider, M., "Steles Funeraires Muslmanes de la Probince du Choa", *Annales d'Ethiopie*, Vol. 8 (1970), pp. 73-78.

Trimingham, J. S., *Islam in Ethiopia* (1952).



ላጵሶ ጌ. ድሌቦ ፤ "የቀይ ባህርና የአባልይ ሸለቆ ሚና በኢትዮጵያ ታሪክ ከጥንት እስከ ዛሬ ፤" በምፅዋ ሲምፖዚየም ጥር (1974)

ማህተመ ሥላሴ ፤ ዝክረ ነገር (1942)

ታሪክ ንጉሥ ሠርፀ ድንግል ፤ Historia Regis Sarsa Dengel (Malak Sagad, 1563—1597) tr.and ed. by Conti Rossini (1907).

ተክለ ሥላሴ (ጸሐፌ ትእዛዝ) ፤ የአጼ ሱስንዮስ ታሪክ 1605—8632 (ያልታተመ ዜና መዋዕል) ።

አጥሜ ጊዮርጊስ ፤ የጋላ ታሪክ ፤ 2 ቅጽ (ያልታተመ ጽሑፍ 1907) ።

ኢትዮጵያ (መንግሥት) ፤ በኢትዮጵያ ከጥንታውያን የፍርድ መዛግብት የተገኘና የተዘጋጀ የፍትሐብሔር ሕጋዊ ድርጅት ፤ በ4 ቅጽ (1945 ዓ.ም.) ።

—. የዕደ ጥበባት ኤክስፖ 1973 (መስከረም 1973 አዲስ አበባ) ።

—. የትግል ምዕራፍ (መስከረም 1967 ፤ 1969 ፤ 1970) ።

—. የአብዮታዊት እናት አገር ጥሪ ልዩ እትም (1969) ።

—. ከየካቲት እስከ የካቲት (1969) ።

—. ፀረ ምዝበራና ፀረ ብኩንነት ኤግዚቢሽን (አዲስ አበባ) 1973 ።

—. ኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ ሁለተኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች (1973) ።

—. ኢሠፓአኮ በፓርቲ ምስረታ ሂደት ፤ ከአንደኛው እስከ ሁለተኛው ጉባኤ (1975) ።

—. ወዛደራዊ ዓለም አቀፋዊነትና የኢትዮጵያ አብዮት (1975) ።

—. የብሔራዊ አብዮታዊ የመሠረተ ትምህርት ዘመቻ 1ኛ ፤ 2ኛና 3ኛ ዙር (1972) ።

—. የብሔራዊ አብዮታዊ የኢኮኖሚና የባህል ዘመቻ አዋጅ መግለጫ (1978) ። የዓለምገና — ወላሞ መንገድ ድርጅት (ያልታተመ ዶኩሜንት 1970) ፤

ገብረ ሥላሴ (ጸሐፌ ትእዛዝ) ፤ ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ (1959) ።

የጉራጌ መንገዶች ሥራ ድርጅት (ያልታተመ ዶኩሜንት 1973) ።

ስለሆማዕና ሆስፒታል በመስከረም 1 ቀን 1972 በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ስብሰባ አዳራሽ አዲስ አበባ የተደረገ ስብሰባ ቃለ ጉባኤ (ከምባታና ሀዲያ አውራጃ አስተዳደር ጽ(ቤትና ሆማዕና) ።

“የቤተ መንግሥት መርጃ ስለሚሸጡ ቁርጥራጭ መሬቶች” ፋይል ቁጥር ከ1801—8850 (የከምባታ አውራጃ መዝገብ ቤት ሆሳዕና)።

የከምባታ አውራጃ ልዩ ፀጥታ ጉባኤ ከጥቅምት 15—19 ቀን 1965 በተማሪዎች አመጽ ጉዳይ ፤ ቁጥር 1012/11 ፤ ቀን 1/3/65 ፤ ከምባታ አውራጃ ግ/ጽ/ቤት ሆሳዕና ።



## ማረሚያ

| ገጽ | መስመር | ስህተት | እርምት |
|---|---|---|---|
| 27 | 5 | ቤጅና | ቤጅኛ |
| 27 | 8 | ቱርካኝ | ቱርካኝኛ |
| 33 | 2 | መንግሥት | መንግሥት ሥር |
| 33 | 31 | ማስታወቂ | ማስታወሻ |
| 39 | 2 | *Èthiope* | *Ethiopie* |
| 39 | 2 | 1980 | 1890 |
| 46 | 42—43 | ያአ—አገሩ | የአገሩ |
| 46 | 43 | የኢኮኖሚው | የኢኮኖሚ |
| 47 | 30 | 1,380,344 | 380,344 |
| 65 | 29 | ግፍና | ግፍና በደል |
| 78 | 14 | የማስታወቂያ | የማስታወቂያና |
| 82 | 7 | አ. አ. ዮ. | አ. አ. ዩ. |
| 82 | 7 | አሥመራ ዮ | አሥመራ ዩ |
| 83 | 5 | ዕድገት ከ1966 እስከ 1972 በ ፐርሰንት እስከ 1972 በቍጥር | ዕድገት ከ1966 እስከ 1972 በቍጥር |
| 93 | 14 | የብምረሰብ | የብሔረሰብ |
| 94 | 2 | *Èthiope* | *Ethiopie* |
| 103 | 14 | ትንሽ | ትንኝ |



በከምባታና ሀዲያ ስፖርት ሆቴል ግቢ ባሕላዊ ጎጆዎች



ምባታና ሀዲያ አውራጃ የኢሠፓአኮ የመንግሥታዊና የሕዝባዊ ድርጅቶች
የምርትና የባሕል ዘመቻ ኮሚቴዎች የአመራር አባላት በአንድነት በ1975